# ከመጋቢት እስከ መጋቢት



የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር
ክቡር **ዐቢይ አሕመድ**
**ከመጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም.**
እስከ **መጋቢት 24 ቀን 2011 ዓ.ም.**
ያደረጓቸው ንግግሮችና ያስተላለፏቸው
መልእክቶች


መጋቢት
፳፻፲፩
ዓ.ም. ታተመ

ኢትዮጵያ፡ አዲሲቷ የተስፋ አድማስ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

# ከመጋቢት እስከ መጋቢት

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ ከመጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 24 ቀን 2011 ዓ.ም. ያደረጓቸው ንግግሮችና ያስተላለፏቸው መልእክቶች


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

መጋቢት
፳፻፲፩
ዓ.ም. ታተመ

ቅንብር፣ አርትዖትና ዝግጅት
የኢፌዴሪ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት

**የዚህ መጽሐፍ ገቢ ለበጐ**
**አድራጐት የሚውል ነው።**

ISBN 978-999-44-74-88-2
Copyright © 2019 FDRE Office of the Prime Minister
*መጋቢት ፳፻፲፩ ዓ.ም. ታተመ*

# ማውጫ

**ቀዳሚ ቃል** i

**ንግግሮች: አማርኛ**

1. የበዓለ ሢመት ንግግር 1
2. የጅግጅጋ ንግግር 17
3. የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይት ንግግር 23
4. የሚሊኒየም አዳራሽ ንግግር 30
5. የጎንደር ሕዝባዊ ጉባኤ ንግግር 42
6. የባሕር ዳር ሕዝባዊ ጉባኤ ንግግር 53
7. የሐዋሳ ሕዝባዊ ጉባኤ ንግግር 60
8. የአሶሳ ንግግር 65
9. ”እኔ ነኝ አዲሲቷ ኢትዮጵያ” ንግግር 72
10. የጋምቤላ ሕዝባዊ ጉባኤ ንግግር 84
11. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ንግግር 89
12. የመደመር ቀን በአዲስ አበባ ንግግር 97
13. የሰመራ ንግግር 101
14. የኤርትራ ንግግር 106
15. የአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ንግግር 110

16. የአሜሪካ ሎስ አንጀለስ ንግግር 117

17. የአሜሪካ ሚኒሶታ ንግግር 127

18. የመካላከያ ምርቃት ንግግር 136

19. ምስጋና 144

20. የሐዋሳ ኢሕአዴግ ጉባኤ ንግግር 148

21. የጀርመን ፍራንክፈርት ንግግር 157

22. የፕሬዚዳንት ሙላቱ ተሾመ መሸኛ ንግግር 169

23. የኢትዮጵያ የፖለቲካ ለውጥ ጉባኤ ንግግር 175

24. የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ንግግር 181

25. የጅማ ዩኒቨርስቲ ምርቃት ንግግር 184

26. የግብር አከፋፈል ንቅናቄ ማስጀመሪያ ጉባኤ ንግግር 189

27. የመከላከያ ቀን ንግግር 195

28. የደብረ ብርሃን ንግግር 200

29. የአንድ ዓመት የለውጥ ሂደት መዘከሪያ ፕሮግራም ንግግር 206

## ንግግሮች: እንግሊዘኛ

30. 60th Anniversary of ECA Speech 216

31. FOCAC Address 224

32. 33rd IGAD Opening Summit 230
33. World Economic Forum Speech 237
34. 32nd AU Summit Dinner Speech 248
35. Africa Health Summit Speech 255

## ንግግሮች: ኦሮምኛ

36. Haasawa Amboo 260
37. Haasawa Mineesootaa 260
38. Haasawa Baalee Magaalaa Roobee 273

## ንግግሮች: ትግርኛ

39. የመቐሌ ንግግር 284

## መግለጫዎችና መልእክቶች: አማርኛ

40. ለግንቦት 20 ያስተላለፉት መልእክት 288
41. በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የተሰጠ መግለጫ 293
42. ለአሸንዳ/ ሻደይ/ አሸንድዬ ያስተላለፉት መልእክት 297
43. የአዲስ ዓመት የመልካም ምኞት መግለጫ 301

44. ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የተላለፈ መልዕክት 307

45. ካንሰርን በጋራ እንከላከል 312

46. ለመውሊድ የተላለፈ መልእክት 318

47. ‹ቤት ለእንግዳ›ን በተግባር 320

48. የብሔር ብሔረሰቦች (የኢትጵያዊነት) ቀን መልእክት 323

49. በሰብአዊ መብት አያያዝ ዙሪያ የተላለፈ መልእክት 328

50. ለክርስትና እምነት ተከታዮች የገና መልእክት 333

51. ለክርስትና እምነት ተከታዮች የጥምቀት መልእክት 338

52. ለከተሞች ቀን ክብረ በዓል የተላለፈ መልእክት 343

53. ለ123ኛው የዐድዋ ድል መታሰቢያ በዓል የተላለፈ መልእክት 346

# ቀዳሚ ቃል

የመሪዎች ታሪክ የሀገሮች ታሪክ ነው፡፡ የሥልጣን ማሽኑ የሚዘወረው በእነርሱ ስለሆነ፡፡ በሌላው ዓለም የፕሬዚዳንቶችን ታሪክ ተከታትለው የሚጽፉ አሉ፡፡ ይህን ታሪክ ለመጻፍ የሚሰለፉ፡፡ የቀደምት ነገሥታትን ንግግሮች እምብዛም አናገኝም፡፡ ዐፄ ናዖድ ሐሳባቸው በቅኔ ይገልጡ ስለነበር ቅኔዎቻቸው ተመዝግበው ደርሰውናል፡፡ ቅኔዎቹ በተለያዩ ቦታዎች የተቀ፝ቋቸው ናቸው፡፡ ከዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በኋላ ያሉ ነገሥታት ደብዳቤዎቻቸውን ለማግኘት ተችሏል፡፡ በተለይም ከዐፄ ገላውዴዎስ እስከ ዐፄ ምኒልክ ያሉት ነገሥታት ደብዳቤዎቻቸው በሀገር ውስጥና በውጭ አብያተ መዛግብት ይገኛሉ፡፡

ንግግሮችን በተመለከተ በሀገራችን በነ ዝክረ ነገርና ፍሬ ከናፍር(የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንግግሮች) መጻሕፍት የመሪዎችን ንግግሮች ለትውልድ ለማስተላለፍ ተሞክሯል፡፡ ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በጳጉሜ 1976 ያደረጉት ረዥም ንግግር ታትሞ ለሕዝብ ቀርቦ ነበር፡፡ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ንግግሮችም ታትመው ነበር፡፡

በለውጥ መንገድ ላይ ያለቺው ኢትዮጵያ ከመጋቢት 2010 እስከ መጋቢት 2011 ያለፈቺበት ጎዳን አስደናቂ ነው፡፡ ያልታሰቡ ሀገራዊ ትሩፋቶች ተገኝተዋል፡፡ ያልተጠበቁ አሳዛኝ ክሥተቶችም ተከሥተዋል፡፡ እያንዳንዷ ቀን፣ ሳምንትና ወር በኢትዮጵያ ጉዞ ውስጥ ወሳኝ ነበረች፡፡

ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሐሳባቸውን ለሕዝብ መግለጥ የሚወዱ ሰው ናቸው፡፡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሐሳባቸውን ለሕዝብ ያስረዳሉ፡፡ ኦፊሴላዊ በሆነ መንገድ ሁለት ስልቶችን መርጠዋል፡፡ ንግግሮችንና መልእክቶችን፡፡ ንግግሮቻቸው ለአድማጭ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ አባባሎች፣ ተረቶች፣ ምሳሌዎች፣ ታሪክ ጠቀስ ትርክቶች በስፋት ይገኛሉ፡፡ ከተለመደው የፖለቲካ ደረቅ ዲስኩር ወጣ ያለ ነው፡፡ በየአካባቢው ሲሄዱም አካባቢዎቹን ሰዎች ባሕሎች፣ አባባሎች፣ የሰላምታ ቃሎችን ይጠቀማሉ፡፡

አንዳንዶቹ ንግግሮች ባልተለመደ መልኩ ‹ይደገም› የሚል ሕዝባዊ ምላሽ አምጥተው ነበር፡፡ መልእክቶቹ በብሔራዊና ሃይማኖታዊ በዓላት እንዲሁም በሀገሪቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

የንግግሮቹን ዋና ዋና አንኳዎች ካየን በዋናነት በኢትዮጵያዊነት፣ በኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ በይቅርታ፣ በፍቅርና በሰላም ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በቀደመው የከበረ ታሪካችን እንድንኮራ፣ መታረም ያለበትን እንድናርም ያሳስባሉ፡፡ አንድ ሆነን ከመኖርና አንድ ሆነን ከመታገል የተሻለ አማራጭ እንደሌለንም አበክረው ይገልጣሉ፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ 53 ጽሑፎች ተካትተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል 39ኙ ንግግሮች 14ቱ ደግሞ መልእክቶች (መግለጫዎች) ናቸው፡፡ ንግግሮቹ በመድረክ የቀረቡ ሲሆኑ መልእክቶቹ በሚዲያዎች የተለቀቁ ናቸው፡፡ ከንግግሮቹ 29ኙ በአማርኛ፣ 6ቱ በእንግሊዝኛ፣ 3ቱ በኦሮምኛ፣ አንዱ ደግሞ በትግርኛ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከንግግሮቹ ስድስቱ በውጭ ሀገሮች የተደረጉ ሲሆኑ ቀሪዎቹ በሀገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች የተደረጉ ናቸው፡፡ በሀገር ውስጥ በመቀሌ፣ ጎንደር፣ ባሕርዳር፣ አዲስ አበባ፣ አምቦ፣ደብረ ብርሃን፣ ሐዋሳ፣ጅማ፣ ጅግጅጋ፣ ባሌ፣ ጋምቤላና አሶሳ ከተሞች ተደርገዋል፡፡

ንግግሮቹና መልእክቶቹ ሀገሪቱ የነበረችበትን ሁኔታ፣ የመሪውን ሐሳብና የመሪውን የአመራር ዘይቤ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ከሃምሳ ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያን የዚህ ዘመን ታሪክ ያለነዚህ ሰነዶች ለማሟላት ያስቸግራል፡፡ የታተሙበትም አንዱ ምክንያት ይሄው ነው፡፡ ታሪክን ሰብስቦና ሰንዶ ለትውልድ ለማቆየት፡፡

**መልካም ንባብ**


፳፻፲፩
መጋቢት
ከመጋቢት
እስከ መጋቢት

# ከመጋቢት እስከ መጋቢት

## ንግግሮች፡ አማርኛ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

መጋቢት
፳፻፲፩
ዓ.ም. ታተመ

# የበዓለ ሢመት ንግግር

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያደረጉት ንግግር

**መጋቢት 24/2010 ዓ.ም.**

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣**
**የተከበራችኹ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት፣**
**የተከበራችኹ የአገራችን ሕዝቦች፣**
**ጥሪ የተደረገላችኹ እንግዶች፣**
**ክቡራት እና ክቡራን፤**

አገራችን ኢትዮጵያ በመንግሥት አስተዳደር ሥርዓቷ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር በምታከናውንበት በዚህ ታሪካዊ ቀን በተከበረው ምክር ቤት ፊት ቀርቤ ይህን ንግግር ለማድረግ ስለ በቃሁ የተሰማኝን ልዩ ክብር ለመግለጽ እወዳለሁ። ከሁሉ አስቀድሜ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአገራችን ለተከሠተው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት የመፍትሔ አካል ለመኾን፤ የሀገር ክብር እና ብሔራዊ ጥቅም በተሻለ ኹኔታ በአዲስ አመራር ሊጠበቅ ይችላል ብለው በማሰብ፣ ለአህጉራችን ምሳሌ በኾነ መልኩ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለአሸጋገሩት ለክቡር አቶ ኀይለ ማርያም ደሳለኝ ከፍ ያለ አክብሮቴን እገልጻለሁ። በተመሳሳይ የመንግሥታዊ ሥልጣን ሽግግሩ ያለ እንከን እንዲከናወን ልዩ ሚና ሲጫወቱ ለቆዩት ሁሉ በመላው ሕዝባችን ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

## ዕለቱ ለአገራችን ታሪካዊ ቀን ነው!

በታሪካችን በተለያዩ አጋጣሚዎች አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ የመጀመር ዕድሎችን አግኝተን ብዙዎቹን በወጉ ሳንጠቀምባቸው አምልጠውናል። አሁንም፣ ይህ የሥልጣን ሽግግር አዲስ ምዕራፍ የምንጀምርበት ሌላ ታሪካዊ ዕድል ነው፤ በመኾኑም በከፍተኛ የሓላፊነት ስሜት ልንጠቀምበት ይገባል።

ኢትዮጵያ ማሕፀነ ለምለም ናት። ከፍ ባለ የአገር ፍቅር መንፈስ ሠርክ የሚተጉ ልጆችን አፍርታለች፤ ልጆቿም ወደ ቀድሞ ክብሯ እንድትመለስ፣ የሕዝቧ ሰላምና ፍትሕ እንዲጠበቅ፣ ብልጽግና ያለ አድልዎ ለመላው ዜጎች ይደርስ ዘንድ አጥብቀው ይመኛሉ፤ ይደክማሉ። በሀገር ውስጥና በውጪ ኾነው ስለ ሀገር አንድነትና ሰላም፣ ስለ ፍትሕና እኩልነት እንዲሁም ስለ ብልጽግና ይጮኻሉ፤ ይሞግታሉ፤ ይሞታሉ።

ይህ የሥልጣን ሽግግር ኹለት ዐበይት እውነታዎችን የሚያመለክት ነው። ክሥተቱ፣ በአንድ በኩል በሀገራችን፥ ዘላቂ፣ የተረጋጋና ሁሉን አቀፍ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት መሠረት ስለ መጣላችን ማሳያ ሲኾን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከጊዜው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማኅበራዊ ኹኔታዎች ጋራ እኩል የሚዳዝና በሕዝብ ፍላጎት ሕዝብን አለቃው አድርጎ የሚያገለግል ሥርዓት እየገነባን መኾኑን ያመለክታል። ወቅቱ ከስሕተታችን ተምረን አገራችንን የምንክስበት ነው!

መሪ ድርጅታችን ኢሕአዴግ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመሩን አጥብቆ በመያዝ ሀገራችንን ከኹለት ዐሥርት ዓመታት በላይ በአስተዳደረበት ወቅት በሁሉም መስክ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣ ሕገ መንግሥታዊ እና ፌዴራላዊ ሥርዓት ገንብቷል። ዓለም በአንድ በኩል በጥሞና፣ በአግራሞትና በጉጉት በሌላ በኩል ደግሞ በስጋት እየተመለከተው ያለ ሀገራዊ ለውጥ ላይ እንገኛለን። ያሳካናቸው በርካታ ድሎች እንዳሉ ሁሉ በፍጥነት መቀረፍ የሚገባቸው በርካታ ጉድለቶች እንዳሉም እናምናለን። ልናተኩርበት የሚገባው ጉዳይ፣ ከስሕተቶቻችን ተምረን ወደፊት በመራመድ የተሻለች ሀገር ለሁላችንም በመገንባቱ ላይ ነው። ዋናው ቁም ነገር፣ ሀገራችንን ከፍ ወዳለ ምዕራፍ

ማሸጋገሩና አንድነቷን ጠብቃ የምትቆይበትን ኹኔታ በቀጣይነት እያረጋገጡ መሔዱ ነው። ኢትዮጵያዊነት ያስተማረን እውነታ፣ በጊዜያዊ ችግሮች ተሸንፎ መውደቅን ሳይኾን ፈተናዎችን ወደ ዕድልና መልካም አጋጣሚ ቀይሮ ድል መቀዳጀትን ነው። ትላንት አባቶቻችን በመተማ፣ በዐድዋ፣ በማይጨውና በካራማራ አጥንታቸውን ከስክሰው የከበረ ደማቸውን አፍስሰው በክብር እና በአንድነት ያቆይዋት አገር አለችን። እኛ ዕድለኞች ነን። ውብ አገር፣ አኩሪ ታሪክ አለን። እኛ መነሻችንን እናውቃለን። በርካታ ዘመናትን የሚሻገር ታሪክ ያለው ታላቅ ሕዝብ ነን። ኅብረታችን ለዓለም ምሳሌ መኾን ይችላል - ጠላቶቻችንን አንበርክኳል፤ ሉዓላዊነታችንን ጠብቆ ዛሬ ላይ ከማድረሱም በላይ ለሌሎች ሕዝቦችም የነፃነት ትግል አርኣያ ኾኗልና።

**ማንነታችን፥ እንዳይለያይ ኾኖ የተሰናሰለ፣ እንዳይነጣጠል ኾኖ የተገመደ፣ የተዋደደ እና የተዋሐደ ነው!**

አማራው በካራማራ ለሀገሩ ሉዓላዊነት ተሠውቶ የካራማራ አፈር ኾኖ ቀርቷል። ትግራዋይ በመተማ ከሀገሬ በፊት አንገቴን ውሰዱ ብሎ የመተማ አፈር ኾኗል። ኦሮሞው በዐድዋ ተራሮች ላይ ስለ ሀገሩ ደረቱን ሰጥቶ የሀገሩን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ከዐድዋ አፈር ተቀላቅሏል። ሶማሌው፣ ሲዳማው፣ ቤንሻንጉሉ፣ ወላይታው፣ ጋምቤላው፣ ጉራጌው፣ አፋሩ፣ ስልጤው፣ ከምባታው፣ ሐዲያው እና ሌሎቹም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ በባድመ ከሀገሬ በፊት እኔን ብለው እንደ ወደቁ ከባድመ አፈር ጋራ ተዋሕደዋል። አንድ ኢትዮጵያዊ አባት እንዳሉት፥ እኛ ስንኖር ሰዎች - ስናልፍ አፈር - ስናልፍ ሀገር እንኾናለን። የየትኛውንም ኢትዮጵያዊ ክቡር ሥጋ እና ደም በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ አፈር ኾኖ ታገኙታላችሁ። ኢትዮጵያውያን፥ ስንኖር ኢትዮጵያ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያ እንኾናለን።

## ኢትዮጵያ የሁላችን ሀገር፤ የሁላችን ቤት ናት!

በአንድ ሀገር ውስጥ የሐሳብ ልዩነቶች ይኖራሉ። የሐሳብ ልዩነት እርግማን አይደለም። ልዩነቱ እንዳለ ኾኖ መደማመጥና በመርሕ ላይ ተመሥርተን መግባባት ስንችል የሐሳብ ልዩነት በረከት ይዞልን ይመጣል። በሐሳብ ፍጭት

ውስጥ መፍትሔ ይገኛል። በመተባበር ውስጥ ኀይል አለ። ስንደመር እንጠነክራለን። አንድነት የማይፈታው ችግር አይኖርም፤ አገር ይገነባል። የእኔ ሐሳብ ካላሸነፈ ሞቼ እገኛለሁ ማለት ግን፣ እንኳን አገርን ሊያቆም ቤተሰብን ያፈርሳል። ያለችን ኢትዮጵያ ነች፤ ከየትኛውም የፖለቲካ አመለካከት በላይ ሀገራዊ አንድነት ይበልጣል። አንድነት ማለት ግን አንድ ዓይነትነት ማለት እንዳልኾነ ሊሰመርበት ይገባል። አንድነታችን፥ ልዩነቶቻችንን ያቀፈ ብዝኀነታችንን በኅብረ ብሔራዊነት ያደመቀ መኾን አለበት።

## እኛ ኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲ እና ነጻነት ያስፈልገናል፤ ይገባናልም!

ዴሞክራሲ ለእኛ ባዕድ ሐሳብ አይደለም። በዓለም ውስጥ በብዙ ማኅበረሰቦች እና አገሮች ዴሞክራሲ በማይታወቅበት ዘመን በገዳ ሥርዓታችን ተዳድረን ለዓለም ተምሳሌት ኾነን ኖረናል። አሁንም ዴሞክራሲን ማስፈን፣ ከየትኛውም ሀገር በላይ ለእኛ የህልውና ጉዳይ እንደ ኾነ እናምናለን። ዴሞክራሲ ያለ ነጻነት አይታሰብም። ነጻነት ከመንግሥት ለሕዝብ የሚበረከት ስጦታ አይደለም፤ ከሰብአዊ ክብር የሚመነጭ የእያንዳንዱ ሰው የተፈጥሮ ጸጋ እንጂ።

ነጻነትን በዚህ መልኩ ተረድቶ እውቅና የሰጠውን ሕገ መንግሥታችንን በአግባቡ መተግበር፣ የሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተለይም ሐሳብን የመግለጽ፣ የመሰባሰብ እና የመደራጀት መብቶች በሕገ መንግሥታችን መሠረት ሊከበር ይገባል። ዜጎች በሀገራቸው የአስተዳደር መዋቅር በዴሞክራሲያዊ አግባብ በየደረጃው የመሳተፍ መብትም ሙሉ በሙሉ እውን መኾን አለበት።

ሁላችንም መገንዘብ ያለብን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መደማመጥን ይጠይቃል። ሕዝብ አገልጋዩን የመተቸት፣ የመምረጥ፣ የመጠየቅ ሙሉ መብት አለው። መንግሥት የሕዝብ አገልጋይ ነው፤ ምክንያቱም፣ ገዥ መርሓችን የሕዝብ ሉዓላዊነት ነውና።

በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ውስጥ፣ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም መርሕ፣ በመደማመጥ የሐሳብ ልዩነትን ማስተናገድ መኾን አለበት። ኢትዮጵያ፥ የጋራችን፣ የእኛ የሁላችን መኾኗን ተገንዝበን የሁሉም ድምፅ የሚሰማበት፣ ሁላችንንም የሚያሳትፍ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመገንባቱን ትግል አጠናክረን እንቀጥላለን።

ዴሞክራሲ ሲገነባ መንግሥት ዜጐች ሐሳባቸውን በነጻነት ለመግለጽ ያላቸውን መብት ማክበር አለበት። ዴሞክራሲን ከዜጐች ሰላማዊ እንቅስቃሴ እና ከመንግሥት መሪነት፣ ደጋፊነት እና ሆደ ሰፊነት ውጭ ማዳበር አይቻልም። በመኾኑም፣ መንግሥት የዜጐች ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንዳይስተጓጎል በጽናት ይሠራል።

በተመሳሳይ መልኩ፣ ዜጐች ሐሳባቸውን ሲገልጹ ሰላማዊ በኾነ መንገድ መኾን ይገባዋል። የራስን ዴሞክራሲያዊ መብት እየጠየቁ የሌላውን መብት መጋፋት እርስ በርሱ ይጣረሳል፤ ዴሞክራሲንም ያቀጭጫል። መንግሥት ሕግን ማክበር አለበት፤ ማስከበርም ግዴታው ነው፤ ታጋሽነትም ሓላፊነቱ ነው። የመንግሥት ታጋሽነት ሲጓደልም ዴሞክራሲ ይጎዳል። በኹለቱም አካሔድ የምንናፍቀው ዴሞክራሲ ሊመጣ አይችልም።

በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ውስጥ የሕግ የበላይነት መስፈን ይገባዋል። የሕግ የበላይነትን ለማስፈን በምናደርገው ትግል ውስጥ መርሳት የሌለብን ቁም ነገር፣ ሕዝባችን የሚፈልገው የሕግ መኖርን ብቻ ሳይኾን የፍትሕ መረጋገጥንም ጭምር መኾኑን ነው። የሕዝብ ፍላጎት፥ ከፍትሕ የተፋታ ደረቅ ሕግ ሳይኾን፣ በፍትሕ የተቃኘ፣ ለፍትሕ የቆመ የሕግ ሥርዓትን ነው። የሕዝብ ፍላጎት፥ የሕግ አስከባሪ ተቋማት ገለልተኛ፣ ለፍትሕ ታማኝ እና ለዜጎች መብት ቀናዒ እንዲኾኑ ነው። ሕግ፣ ሁላችንንም እኩል የሚዳኝ መኾን አለበት። እንዲህ ሲኾን፣ ሕግ በተፈጥሮ ያለን ሰብአዊ ክብራችንን ያስጠብቅልናል። ይህን እውነታ በመረዳት በሀገራችን ዴሞክራሲ እንዲያብብ፣ ነጻነትና ፍትሕ እንዲሰፍን፣ የሕግ የበላይነት እውን እንዲኾን አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ በዘርፉ ያለውን ክፍተት እንሞላለን።

ለሰላም፥ መሠረቱ ፍትሕ ነው፤ ሰላም፥ የግጭት አለመኖር ብቻ አይደለም፤ ሰላም፥ በመግባባት ላይ የተመሠረተ ጽኑ አንድነታችን ነው፤ ሰላም፥ መተማመናችን ነው። ሰላም፥ በሁላችንም ፈቃድ ዛሬም የቀጠለ የአብሮነት ጉዞችን ነው። ሰላም፥ አለመግባባት እና ተቃርኖዎችን በሠለጠነ መንገድ መፍታት የሚያስችል መንገድ እና ግባችን ነው።

## የተከበሩ አፈ ጉባዔ፣ ክቡራትና ክቡራን፤

ያለንበት ጊዜ፣ የአፍሪካ ቀንድ በቀውስ ውስጥ የሚገኝበት፣ የየራሳቸው ፍላጎትና ዓላማ ያላቸው ብዙ ኀይሎች የሚራኮቱበት፣ ውስብስብ መጠላለፍ በቀጣናው የሚስተዋልበት ወቅት ነው። በዚያው ልክ ደግሞ፣ በደም፣ በባህል፣ በቋንቋ እና በረጅም ጊዜ የጋራ ታሪክ የተሳሰርን ሕዝቦች ያለንበት አካባቢ ነው፡፡
የውጭ ግንኙነታችንን በተመለከተ፣ ሀገራችን፥ የፓን አፍሪካኒዝም መሠረት፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (የአፍሪካ ኅብረት) መሥራችና መቀመጫ፣ የቀደምት ዓለም አቀፍ ተቋማት መሥራች እና በዓለም አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እንዲሁም ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ ጉልሕ እና ገንቢ ሚና የምትጫወት ሀገር ናት። ይህንኑ በጋራ ተጠቃሚነት እና እኩልነት ላይ የተመሠረተውን ፖሊሲያችንን አጠናክረን እንቀጥላለን።

ከአፍሪካውያን ወንድሞቻችን ጋራ በአጠቃላይ እና ከጎረቤቶቻችን ጋራ በተለይ፣ በችግርም በተድላም አብረን እንቆማለን። ከኤርትራ መንግሥት ጋራ ለዓመታት ሰፍኖ የቆየው አለመግባባት እንዲያበቃም ከልብ እንፈልጋለን። የበኩላችንንም እንወጣለን። በጥቅም ብቻ ሳይኾን በደም ለተሳሰሩት የኹለት ሀገር ሕዝቦች የጋራ ጥቅም ሲባል ልዩነቶቻችንን በውይይት ለመፍታት ያለን ዝግጁነት እየገለጽኹ የኤርትራ መንግሥትም ተመሳሳይ አቋም እንዲወስድ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

## የተከበሩ አፈ ጉባዔ፣
## የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት፣
## ክቡራት እና ክቡራን፤

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሕዝባችንን ብሶት ካጋጋሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ ሙስና አንዱ ነው። ሙስናን ፀረ ሙስና ተቋም በመመሥረት ብቻ መከላከል እንደማይቻል ተረድተን ሁላችንም፣ ኢትዮጵያችን፣ አንዱ ሠርቶ ሌላው ቀምቶ የሚኖርባት አገር እንዳትኾን ለመጠበቅ የምንችለውን ሁሉ እንድናደርግ በትሕትና እጠይቃችኋለሁ።

ትላንት የተፈጠረን ሀብት ከሌላው በመቀማት ሒሳብ ለማወራረድ የሚተጋ አገር እና ሕዝብ ወደፊት ለመራመድ አይችልም። ገበታው ሰፊ በኾነበት፣ ሁሉም ሠርቶ መበልጸግ በሚችልበት ኢትዮጵያችን፣ አንዱ የሌላውን ለመንጠቅ የሚያስገድድ ይቅርና የሚያሳስብ ምንም ዓይነት ምክንያት የለም። ይልቁንም፣ወቅቱ የፈጠረልንን ልዩ አጋጣሚና አገራዊ አቅማችንን አቀናጅተን የእጥረት እና ዕጦት አስተሳሰብን በማስቀረት ለጋራ ብልጽግና እንትጋ። ታዋቂው የሕንድ የነጻነት ንቅናቄ መሪ ማሕተመ ጋንዲ በአንድ ወቅት እንደተናገረው፣ አገር ለሁሉም የሚኾን በቂ ሀብት አላት፤ ሁሉም እንደ ልቡ የሚዘርፈው ሀብት ግን ሊኖራት አይችልም። አሁን በጀመርነው አዲስ ምዕራፍ፥ ዘረፋን፣ የሀብት ብክነትንና የተደራጀ ሙስናን፣ መላው ሕዝባችንን በሚያሳትፍ ርምጃ ለመመከት ሌት ተቀን እንተጋለን።

### ክቡራት እና ክቡራን

ሀገራችን ባለፉት ዓመታት በአስመዘገበችው ፈጣን ዕድገት የተነሣ በድህነት ቅነሳ፣ በመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በሰው ኃይል ልማት እና በመሳሰሉት ያገኘናቸው ስኬቶች ለሁሉም የሚታዩ ናቸው። ከዚህ አኳያ መንግሥት የዋጋ ንረትንና የውጭ ምንዛሬ ዋጋን ለማረጋጋት፣ የፋይናንስ ዘርፉን ጤናማነት ለመጠበቅ፣ ለኢኮኖሚ የሚቀርበውን የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነትንና

አካታችነትን ለማስፋት፣ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን እንዲሁም ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የሕዝቡን የነፍስ ወከፍ ገቢ ለማሳደግ እንዲሁም አስከፊ ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ የፖሊሲ እና የትግበራ ርምጃዎችን ወስዷል።

በአንጻሩ፣ ባለፉት ዓመታት በተለያዩ ጊዜያት የኢኮኖሚ ዕድገቱንና የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋቱን የሚፈታተኑ ተግዳሮቶች ተከሥተዋል። ከእነዚህም ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ፥ የውጭ ንግድ በምንፈልገው መጠን አለማደጉ፣ ይህን ተከትሎ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እና ፍላጎት አለመመጣጠን፣ የዋጋ ንረት እና የኑሮ ውድነት፣ የውጭ ዕዳ ጫና እና የሀገር ውስጥ ቁጠባ እና ኢንቨስትመንት መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መምጣቱ ናቸው። በግብርናው ዘርፍ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አበረታች ቢኾኑም፣ ዘርፉን በተገቢው ኹኔታ በቴክኖሎጂ መደገፍ ባለመቻሉ እንደ ሀገር ማግኘት የሚገባንን የኢኮኖሚ ትሩፋት ሳናገኝ ቆይተናል።

እንደ ትልቅ አገር እና ሕዝብ፣ ከምናስበው የስኬት ጫፍ ላይ መድረስ የምንችለውና ችግሮቻችንን የምንፈታበትን ዋና ቁልፍ የምናገኘው በትምህርት እና በትምህርት ብቻ እንደ ኾነ በማመን መንግሥት ለትምህርት ዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ቢኾንም፣ በተለይ የትምህርትን ጥራት ከማስጠበቅ አንጻር እጅግ ብዙ የቤት ሥራዎች ከፊታችን እንዳሉ በውል በመገንዘብ በርካታ ሥራዎች ይሠራሉ። የትምህርት መስፋፋት ይበል የሚያሰኝ የመንግሥታችን ስኬት ቢኾንም፣ ይህ የትምህርት ሽፋን ዕድገት በጥራት እስካልተደገፈ ድረስ ልፋታችንና ጥረታችን ሁሉ የምንተጋለትን ውጤት ሊያመጣልን አይችልም። በመኾኑም፣ ከመጀመርያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉትን የዕውቀት ተቋሞቻችን በጥራት ላይ አተኩረው እንዲሠሩ መንግሥት በፍጹም ቁርጠኝነት ይረባረባል። በተለይም፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችንና ከቴክኒክ እና ሞያ ኮሌጆች የሚወጡት ተማሪዎቻችን ከሚገበዩት ዕውቀት ጋራ የሚነጻጸር ክህሎት እንዲኖራቸው ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል።

እነዚህንና ሌሎቹንም ችግሮቻችንን ለመቅረፍ፣ የኹለተኛውን የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የኹለት ዓመት ተኩል አፈጻጸም ገምግመን አስፈላጊ የኾኑ የፖሊሲ ርምጃዎችን በመውሰድ፣ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስቀጠል እንተጋለን።

## ውድ የአገራችን ወጣቶች፤

ኢትዮጵያ የእናንተ ነች፤ መጪውም ዘመን ከሁሉ በላይ የእናንተ ነው፤ አሁንም አገሪቷን በመገንባት ግንባር ቀደም ኾናችሁ መሳተፍ ይኖርባችኋል። የወጣቱ ጥያቄ፥ የኢኮኖሚ እኩል ተጠቃሚነት ብቻ ሳይኾን፣ የዴሞክራሲ እና የፍትሕ ነው ብለን እናምናለን። የሁሉም ዜጐችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት፣ ማኅበራዊ ፍትሕ እና ፖሊቲካዊ ተሳትፎ ከማሳደግ አንጻር ክፍተቶች ነበሩ።

አገራችን፣ ጥሩ የሚባል ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን እያስመዘገበች እንደ ኾነ ቢታወቅም፣ ዕድገቱ በቅርፅ እና በይዘት ተለዋዋጭ የኾነውን የወጣቱን ትውልድ ፍላጎት በሚፈለገው ደረጃ የሚያረካ አልነበረም። ይህም፣ ሕዝባችንን ለብሶት እንደዳረገው እንገነዘባለን። ያለ ወጣቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት አገር የትም ልትደርስ እንደማትችልም እንረዳለን። ኢትዮጵያ ለወጣቶቿ ተስፋ የምትሰጥ እንጂ፣ ተስፋ የምታስቆርጥ አገር እንዳትኾን የምንችለውን ሁሉ እንደምናደርግ ቃል እገባለሁ።

በሚቀጥሉት ጊዜያት፣ ለወጣቱ የሥራ ዕድል መፍጠር ብቻ ሳይኾን፣ ወጣት ባለሀብቶች በብዛት እንዲፈጠሩ እንሠራለን። ለዚህም፣ ዕንቅፋትና መሰናክል የሚኾኑ አመላካከቶች እና የተንዛዙ አድሏዊ አሠራሮች ተወግደው ፍትሐዊ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት እንዲኖረን መንግሥት ምቹ ኹኔታን ይፈጥራል። መርሳት የሌለብን ሐቅ ግን፣ ለራሱም ኾነ ለአገሩ በሥራው እና በጥራቱ ሀብት የሚፈጥረው ወጣቱ ራሱ እንደ ኾነ ነው።

## ውድ የኢትዮጵያ ሴቶች፤

በብዙ አስቸጋሪና ፈታኝ ኹኔታ ውስጥ ኢትዮጵያን ገንብታችሁ፣ ታሪክ ሠርታችሁ፣ ትውልድ ቀርፃችሁ ዛሬ ላይ ደርሰናል፤ በትግላችሁም የተሻለች አገር እንድትኖረን ብዙ መሥዋዕት ከፍላችኋል። ትግላችሁ፥ የፍትሕ ትግል ነው፤ ትግላችሁ፥ ክቡር ትግል ነው፤ ትግላችሁ፥ ትግላችን ነው። መንግሥት የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና በአገራችን ኹለንተናዊ የዕድገት ግሥጋሴ ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ላይ የሚገኝ ቢኾንም፣ አሁንም ከሠራነው ይልቅ ያልሠራናቸው ሥራዎች እጅግ እንደሚበዙ እናምናለን። በመኾኑም በቀጣይ፣ የአገራችን ሴቶች፣ ተፈጥሮ እና ኑሮ የሰጧችሁን በረከቶች ተጠቅማችሁ ለአገራችን ዕድገት እና ብልጽግና፣ ለፖለቲካችንም ስምረት አዎንታዊ ሚና እንደምትጫወቱ ተስፋዬ የላቀ ነው።

አገራዊ ማንነታችን ያለ እናንተ ያለ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ምንም ነው። አገሪቷን የገነቡ፣ ያገለገሉ፣ ያቆሙ ሴቶችን ዕውቅና በመንፈግ ሀገራዊ ትንሣኤን ማረጋገጥ አይቻልም። መንግሥታችን ለሴቶች መብት እና እኩልነት የሚቆመው፣ ለሴቶቻችን ውለታ ለመዋል ሳይኾን ለሁላችንም ብለን ነው። ግማሽ አካሉን የረሳ አገር ሙሉ የሀገር ሥዕል ይኖረው ዘንድ ከቶ እንደማይችልና ወደፊትም እንደማይራመድ መንግሥት በውል ይገነዘባል። በመኾኑም መንግሥታችን፣ ከዚህ ቀደም ከነበረው ፍጥነት እና የትግበራ ስኬት በላቀ መልኩ ለሴቶች ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት በቁርጠኝነት ይሠራል።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣**
**የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት፣**
**የተከበራችሁ የአገራችን ሕዝቦች፣**
**ጥሪ የተደረገላቸሁ እንግዶች፣**
**ክቡራትና ክቡራን፤**

**ችግሮቻችን በርካታ እና ፋታ የማይሰጡ ናቸው።**

የዳበረ የዴሞክራሲ ባህል አለመኖር፣ ሥር የሰደደ ድህነት፣ የተደራጀ የሙስና እና ብልሹ አሠራር መስፋፋት፣ የመልካም አስተዳደር ዕጦት ተደማምረው ሰፊ እና ውስብስብ ፈተና ደቅነውብናል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ፣ በርካታ ወገኖቻችን ከመኖሪያ ቀዬአቸው ተፈናቅለው ለሕይወት እና ንብረት መጥፋት ተዳርገው እንደ ነበር ይታወሳል።

ዜጎች በአገራቸው ውስጥ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር እና ሀብት የማፍራት መብታቸው መከበር አለበት። በመኾኑም፣ እንዲህ ዓይነት ተገቢ ያልኾነ ድርጊት እንዲያበቃና ዳግም እንዳይፈጠር መሥራት ይኖርብናል።

ችግሮቻችንን፣ ተለያይተን ቀርቶ ተባብረንና ተዋድደንም ለመፍታት ዓመታት ያስፈልጉናል። በመኾኑም፣ የባከነውን ጊዜ በማካካስ ወደ ፊት መጓዝ እንችል ዘንድ በአዲስ መንፈስ መረባረብ ይጠበቅብናል።

ሁሉም ችግሮቻችን በአንዲት ጀንበር ሊፈቱ አይችሉም፤ ነገር ግን፣ የጀመርነውን የተሻለች ሀገር የመገንባት ሒደት ማፋጠን እንችላለን። የተሻለች አገር መገንባት የሚያስችል ጠንካራ ተነሣሽነት አለ። ጠንካራ አገር ለመገንባት ሁላችንም ሓላፊነት አለብን። እንደ ተለያየ አገር ዜጋ በባዕድነት እና በባይተዋርነት ሳይኾን፣ ሁላችንም እንደ ባለቤቶች እጅ ለእጅ ተያይዘን መጓዝ ይጠበቅብናል። ይህ ሲኾን ስንወድቅም፣ ስንነሣም በጋራ ይኾናል።

በቀሪው የኹለተኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት፣ ቀሪ የልማት መርሐ ግብሮቻችንን በፈጠነ ጊዜ ለማሳካት ጥረት ይደረጋል።

ከመደበኛው የሥራ ሰዓታችን በሚሻገር ጊዜ፣ ከፍ ባለ ፍጥነት እና ተነሣሽነት በመሥራት በቅርብ ዓመታት ውስጥ በተከሠተው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት የደረሰብንን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጉዳት ለማካካስ አገራዊ ንቅናቄ እንድናደርግ ከአደራ ጭምር መልእክቴን አስተላልፋለሁ።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣**
**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት፣**

## ክቡራትና ክቡራን፣
## በውጭ አገሮች የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖች፤

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለሥራም ኾነ ለትምህርት በሔደበት ሁሉ ኢትዮጵያን ተሸክሟት ይዞራል። ኢትዮጵያዊውን ከኢትዮጵያ ታወጡት እንደ ኾነ ነው እንጂ ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያዊው ልብ ውስጥ አታወጧትም፤ የሚባለውም ለዚህ ነው። ሁላችኹም በታታሪነታችሁ፣ በልቀታችሁ እና የትም በሚከተላችሁ የአገራችሁ የጨዋነት ጠባይዕ የኢትዮጵያ እና የዕሴቶቿ እንደራሴዎች ናችሁ።

አንዳንድ ጊዜ፣ ከኢትዮጵያ ያነሰ የተፈጥሮም ኾነ የታሪክ ሀብት ባላቸው ነገር ግን እጅግ በበለጸጉ አገሮች ውስጥ ራሳችሁን ስታገኙት፣ ስለ አገራችሁ ቁጭት ሳይሰማችኹ አይቀርም። ሁላችንም ውስጥ ያ ቁጭት አለ። እንደ አገር ያለን ሀብት አሟጠን ለመጠቀም የምናደርገው ጥረት በቂ ሳይኾን ሲቀር መቆጨታችሁ አይቀርም፤ መቆጨትም አለባችሁ። ይህንም ኹኔታ ለመለወጥ ለሁላችንም የምትበቃ በዚያው ልክ ግን የሁላችንንም ተሳትፎ የምትፈልግ አገር አለችንና ዕውቀታችሁንና ልምዳችሁን ይዛችሁ ወደ አገራችሁ ለመመለስና አገራችሁን አልምታችሁ መልማት ለምትሹ ሁሉ እጃችንን ዘርግተን እንቀበላችኋለን። በውጭ አገሮች ኑሯችሁን ላደረጋችኹትም ቢኾን፣ በማንኛውም መልኩ በአገራችሁ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንድትኾኑና አገራችንን በሙሉም መልክ ለመቀየር ለምታደርጉት አስተዋፅኦ መንግሥት ያልተቆጠበ ድጋፍ ማድረጉን ይቀጥላል።

### ውድ የልማት አጋሮቻችን፤

እስካ ዛሬ በአደረግነው የሰላም እና የልማት እንቅስቃሴ ከጎናችን የቆማችሁ የልማት አጋሮቻችን የአገራችን ጥብቅ ወዳጆች እንደ ኾናችሁ እንገነዘባለን። የአገራችንን ልማት እና ሰላም ለማረጋገጥ በምናደርገው ጥረት እንደ ወትሮው ሁሉ ከጎናችን እንደምትቆሙ ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ።

**መጪው ጊዜ በኢትዮጵያችን የፍቅር እና የይቅርታ ጊዜ ነው!**

አገራችን፥ ፍትሕ፣ ነጻነት እና ሰላም የሰፈኑባት፣ ዜጎችዋ በሰብአዊነት የሚተሳሰቡባት፣ በእኅትማማችነት እና በወንድማማችነት የተሳሰሩባት እንድትኾን እንፈልጋለን፡፡ ይህ ሕልማችን እውን የሚኾነው ከዕንቅልፋችን ነቅተን ስንሠራ ነው፡፡ መመኘታችን መልካም ነው፤ ነገር ግን ምኞታችን ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ መሥራት፣ መትጋት፣ መታገል ይጠበቅብናል፡፡ በመጀመሪያ ሥራችን ልናደርገው የሚገባንና ትግላችን ማተኮር ያለበት ራሳችን ላይ ነው፡፡ አመለካከታችንን ከጥላቻ፣ ከቂም በቀል ስሜት እና ከዘረኝነት ማጽዳት ይገባናል፡፡ በብሔር፣ በፆታ፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በሃይማኖት… ወዘተ ያሉን ልዩነቶች እንደ በረከትነታቸው በፍቅር በማስተናገድ ከልዩነቶቹ የሚነሣ አለመግባባት ቢኖር እንኳ ከፍትሕ እንጂ ከበደል ጋራ ባለ መተባበር ሞራላዊ እይታዎቻችንን ልናስተካክል ይገባል፡፡ ፍትሕ ዋናው መርሓችን፣ ለሰው ልጆች ሁሉ ፍቅር እና ክብር የሞራል መልሕቃችን ሊኾን ይገባል፡፡ ይህ ሠርተን የማናገባድደው፣ ሁሌም ልፋት፣ ትግል የሚጠይቅ የዕድሜ ዘመን ሁሉ የቤት ሥራ ነው፡፡

አገራችን በአሁኑ ወቅት ለደረሰችበት ምዕራፍ በርካታ ትውልዶች መሥዋዕት ኾነዋል፡፡ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችን እውን እንዲኾንም አእላፋት ተሠውተዋል፡፡ አዳጊውን ዴሞክራሲያችንን ለማዳበር ግን ተጨማሪ የሕይወትም ኾነ የአካል መሥዋዕት አያስፈልገንም፡፡
ከዴሞክራሲ ባህላችን አለመዳበር ጋራ ተያይዞ ባለፉት ዓመታት እንደ መንግሥትም እንደ ዜጎችም በታዩብን እጥረቶች፣ በዜጎቻችን ሕይወት፣ በግል እና በጋራ ንብረቶቻችን ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት ደርሷል፡፡ ይህን ሁላችንም ማስቀረት እንችልና ይገባንም ነበር፡፡

በተለያየ ጊዜ መሥዋዕት ለከፈሉ የመብት ተከራካሪዎች እና ፖለቲከኞች፣ በቅጡ ሳይቦርቁ ሕይወታቸው ለተቀጠፈ ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች፣ ለሥነ ልቡናዊ እና ለአካላዊ ቀውስ ለተዳረጉ ቤተሰቦች እና ግለሰቦች ከልብ የመነጨ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡

እንዲሁም ሰላም ለማስከበር እና ሕገ መንግሥታዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ሲንቀሳቀሱ ሕይወታቸውን ያጡ የፀጥታ ኀይሎች አባላት ለከፈሉት መሥዋዕት ያለኝን አድናቆት እና አክብሮት ለመግለጽ እፈልጋለሁ፡፡ ለተፈጠሩ ችግሮች እልባት በማበጀት ሕዝባችንን እንደምንክስም ጭምር በዚሁ አጋጣሚ ቃል እገባለሁ፡፡

በአገር ውስጥም ኾነ በስደት ከአገር ውጭ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከልባችን ይቅር ተባብለን፣ የትላንትናውን ምዕራፍ ዘግተን፣ በብሔራዊ መግባባት ወደ ቀጣይ ብሩህ አገራዊ ምዕራፍ እንሻገር ዘንድ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

## ክቡራን የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፤

ከኢሕአዴግ ውጭ ያሉ ፓርቲዎችን የምናይበት መነጽር እንደ ተቃዋሚ ሳይኾን እንደ ተፎካካሪ፣ እንደ ጠላት ሳይኾን እንደ ወንድም፣ አማራጭ ሐሳብ አለኝ ብሎ እንደ መጣ አገሩን እንደሚወድ የዜጋ ስብስብ ነው፡፡ ስለዚህ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ የተመቻቸ እና ፍትሐዊ የመወዳደሪያ ሜዳ እንዲኖር በመንግሥት በኩል ጽኑ ፍላጎት ያለ በመኾኑ ስለ ሰላም እና ፍትሕ በልዩ ልዩ መንገድ የምትታገሉ የተፎካካሪ ፓርቲ መሪዎች፣ አብሮነታችንንና ሰላማችንን አደጋ ላይ የሚጥሉ፣ ብሔራዊ ጥቅሞቻችንንም አሳልፈው የሚሰጡ የአስተሳሰብ መስመሮችን በአርቆ አስተዋይነት፣ በአገራዊ ፍቅር እና በሰጥቶ መቀበል መርሕ የተሻለ የፖለቲካ ባህል ለመፍጠር የምናደርገውን ጥረት እንድታግዙ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡
የአገራችን አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች፣ በሁሉም ደረጃ የምትገኙ የሀገራችን የፀጥታ ኀይሎች፣ ምሁራን፣ ባለሀብቶች፣ በገጠርም ኾነ በከተማ የምትገኙ የተለያየ ሞያ ባለቤቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖች፣ ዋቄፈታዎች እንዲሁም ሌሎች ሃይማኖቶችን የምትከተሉ ወገኖች፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የምትገኙ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ ሁላችንም የዳበረ ዴሞክራሲ ለመገንባት እንረባረብ! አገራችንን ከድህነት አዘቅት ውስጥ ለማውጣት እንትጋ! ዘረኝነትንና መከፋፈልን ከአገራችን እናጥፋ! የተማረ እና በምክንያት የሚከራከር ዜጋ እንፍጠር! የዛሬው

ዕለት፣ በአኩሪ ኢትዮጵያዊ ወኔ የተጀመረው ታላቁ የሕዳሴ ግድባችን ሰባተኛ ዓመት ነው፡፡ በዚህ ግድብ ግንባታ የታየው አንድነት እና መሰባሰብ፣ የአገራችንን ችግሮች በሙሉ መቅረፍ እና መሻገር እንደምንችል ያረጋገጠልን በመኾኑ ይህንኑ መንፈስ ይዘን ከግድቡ መጠናቀቅ ባሻገር የአገራችንን ብልጽግና እስከምናረጋግጥበት ከፍታ ድረስ እንድንዘልቅ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡ በመጨረሻም በዚህ ወቅት ሀገሬንና ሕዝቤን ለማገልገል ይህን ከባድ ሓላፊነት ስቀበል አመሰግናቸው ዘንድ የሚገቡኝን አካሎች እንዳመሰግን ትፈቅዱልኝ ዘንድ በትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

***በመጀመሪያ፥*** ለዚህ ሓላፊነት የመረጡኝንና እምነት የጣሉብኝን ድርጅቴን ኢሕአዴግንና የአገሬን ሕዝብ በተለየ አክብሮት እና ፍቅር አመሰግናለሁ፡፡

***ኹለተኛ፥*** የሰባት ዓመት ልጅ እያለሁ እንዲህ ከፊታችሁ እንደምቆም የምታውቅ፣ ይህን ሩቅ ጥልቅ እና ረቂቅ ራእይ በውስጤ የተከለች፣ ያሳደገች እና ለፍሬ ያበቃች አንዲት ኢትዮጵያዊት እናት እንዳመሰግን በትሕትና እጠይቃለሁ... ይህች ሴት እምዬ ናት፡፡

እናቴ፥ ከሌሎቹ ቅን፣ የዋህ እና ኅበዝ ኢትዮጵያውያን እንደ አንዶቹ የምትቆጠር ናትና ቁሳዊ ሀብት ብቻ ሳይኾን ዓለማዊ ዕውቀትም የላትም፡፡ በእናቶች ውስጥ ሁሉንም የኢትዮጵያ እናቶች ዋጋ እና ምስጋና እንደ መስጠት በመቁጠር፣ ዛሬ በሕይወት ከአጠገቤ ባትኖርም ውዷ እናቴ ምስጋናዬ በዐጸደ ነፍስ ይደርሳት ዘንድ በብዙ ክብር ላመሰግናት እወዳለሁ፡፡

ሌሎች ኢትዮጵያውያን እናቶቼ፣ በልጆቻቸው የነገ ራእይ ላይ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው በመገንዘብ ነገ ለሚያጭዱት መልካም ፍሬ፣ ዛሬ ላይ የሚዘሩት ዘር ዋና ጉዳይ መኾኑን በመገንዘብ ለሚከፍሉት መሥዋዕት ያለኝን በምንም የማይተካ አድናቆት፣ ምስጋና እና ክብር በብዙ ልባዊ ፍቅር ሳቀርብ በቀጣይም ልጆቻችን የዚህች አገር ሕዳሴ እንዲረጋገጥ ዋና ተዋንያን መኾን እንዲችሉ እናታዊ - አይተኬ - ሚናችሁን እንድትወጡ አደራ በማለትም ጭምር ነው፡፡

***ሦስተኛ፣*** የሚስቶች ስኬት ኹለት-ሦስት ነው፡፡ ኹለት ሲኾን፣ አንዱ የራሳቸው ሌላው የባላቸው፡፡ ሦስት ሲኾን ደግሞ፣ የልጆቻቸውም ይጨመርበታል፡፡

አንዳንዴ ድል ስኬታቸው ከዚህም ይሻገራል፡፡ የእናቴን ራእይ ተረክባ በብዙው የደገፈችኝና የእናቴ ምትክ የኾነችልኝ ውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸው ከእነዚህ ሚስቶች ተርታ ትመደባለችና እጅግ አድርጌ ላመሰግናት እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም፣ ከትግል ጓዶቼ እና በዝለት ብርታት፤ በድካም ጊዜ ኀይል ከኾኑኝ የቅርብ-የሩቅ ወዳጆቼ ውጭ፣ ዛሬ እኔ ከፊታችሁ መቆም ባልቻልኩ ነበር፤ ለሁላችሁም ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፣**
**ተከብራ እና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ**

## አመሰግናለሁ !

# የጅግጅጋ ንግግር

**መጋቢት 29/2010 ዓ.ም.**

**ሃምበልዮ ኢዮ ሰላን**
**ደማን ሸዓብ ወይነሃ ሶማሊዳ ኢትዮጵያ!**

**የተከበራችኹ የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥራ ሓላፊዎች፣**
**የተከበራችኹ ገራዶች እና ኡጋዞች፣**
**የተከበራችኹ ሡልጣኖች እና የአገር ሽማግሌዎች፣**
**የተከበራችኹ ሴቶች እና ወጣቶች፣**
**የተከበራችኹ ምሁራንና የዳያስጶራ አባላት፣**

**መርዋይን ኢዮ ሙደነያል!**

ከሁሉ በማስቀደም በፈጣን የልማት እና የለውጥ ግሥጋሴ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሶማሌ ብሔራዊ ክልል፣ ርእሰ ከተማ በኾነችው ጅግጅጋ፣ የመጀመሪያውን የሥራ ጉብኝት ለማድረግ ዕድል በማግኘቴ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በራሴ ስም ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

የኢትዮጵያ ሱማሌ ሕዝብ፣ ለምሥራቅ ኢትዮጵያ ሰላም እና ደኅንነት ቃፊር ኾኖ ለኖረበትና ዛሬም በዚሁ አገራዊ ፈለግ እና ጽናት ለቆመበት ጀግንነት ያለኝን አድናቆት በላቀ አክብሮት ስገልጽ ኩራት ይሰማኛል። በትላንቱም ኾነ በዛሬው

የኢትዮጵያ ሶማሌ ትውልድ ውስጥ ጀግንነት ሞልቶ የተረፈ መኾኑን የማይመሰክር አይኖርም። ስለኾነም፣ በጀግኖች መካከል መገኘት የላቀ ክብር በመኾኑ፣ ዛሬ የሚሰማኝ ደስታ ወሰን የለውም።

የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝብ በውጭ ኀይሎች ወረራ እና ትንኮሳ፣ እንዲሁም በተፈጥሮ በትር እና ከባድ ተግዳሮት የተነሣ የክልሉን እምቅ ጸጋ የማልማት እና የመጠቀም ፋታ እና ዕድል ባለማግኘቱ ትውልድ በተቀባበለው የጊዜ ርዝመት ውስጥ የድህነትን ገፈት ሲቀምስ መኖሩ በቁጭት ይታሰባል። የቱንም ያህል ድህነት ቢጫነውና ኑሮ ቢከብደውም ቅሉ ኢትዮጵያዊነትን በልቡ ይዞ በየጎራው በመሰለፍ ወራሪዎችን የተፋለመበት ገድል፣ አገር እስከ ወዲያኛው ሲኮራበት የሚኖር ነው።

ለዚህ ደግሞ በአብነት የሚጠቀሰው የጀግንነት ውሎ እጅጉን የበዛ ነው። ከዘመን ግሥጋሴ ጋራ ቢዞርም ወልወል አይረሳም። በርግጥም እነ ዑመር ሠመተር፣ ሰይድ መሐመድ፣ አብዱላሂ ሐሰን አገር ላይ ቆሞ መናገር ከኩራት በላይ ነው። ክልሉ፣ መላው የኢትዮጵያ ሶማሌ ልጆች ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወንድሞቻቸው ጋራ በኅብረት ለአገር ሉዓላዊነት የተሰለፉበት የፍልሚያ እና የድል ምድር ነው። ወረራን ለመመከት ቀድመው የተገኙበት የግንባር ረድፍ ነው። ዛሬም በምሥራቅ ኢትዮጵያ፣ አገራችንን ሊጎዱት የሚያስቡ ኀይሎች መግቢያ ቀዳዳ እንዳያገኙ የሰላም ዘብ ኾኖ ይገኛል።

የባድመን ወረራ ለማምከን የኢትዮጵያ ሶማሌ ወጣቶች ከየማዕዘኑ በቁጣ ከተመሙ ወንድሞቻቸው ጋራ ገሥግሰው የደረሱበት ፍጥነት፣ ወራሪዎችን ከማስደንገጡም በላይ ኢትዮጵያዊነት እና አንድነት የማይበገር ኀይል መኾኑን ዳግም አረጋግጧል። ድርጊቱ፣ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ምንጊዜም የማይሹት የጦርነት ክሥተት ቢኾንም ኅብረ ብሔራዊነትን አድምቆ አልፏል። በብዝሐነት ውስጥ አንድነት፣ በአንድነት ውስጥ ብዝሐነት የመኖሩ ወርቃማ ጸጋ ከመቼውም በላይ ታይቶበታል።

የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝብ ለኢትዮጵያዊ ማንነት የዳር፣ የጠረፍ፣ የሩቅ ተደርጎ ሊታይ አይችልም። በኅብረ ብሔራዊ አስተሳሰባችን፣ በፌዴራላዊ ሥርዓታችን፣ ለኢትዮጵያዊ ማንነት ዳር እና መሀል ሳይኖር፣ ሁላችንም እኩል ዜጎች፣

ሁላችንም የኢትዮጵያ አስኳል ነን። የኢፌዴሪ መንግሥትም ይህን እሳቤ ከመቼውም ጊዜ በላቀ መልኩ እውን ለማድረግ ጸንቶ እንደሚሠራ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝብ፣ ሁሉን አቀፍ በኾነ ሰብአዊ ልማት በየዘርፉ ከዛሬ ይልቅ ነገ የተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ፣ ደኅንነቱ እና ሰላሙ እንዲረጋገጥ፣ የሁሉም ዜጋ ነጻነቱ እና መብቱ እንዲከበር የኢፌዴሪ መንግሥት ተገቢውን አትኩሮት ሰጥቶ ይሠራል።

## መርዎይን ኢዮ ሙደነያል!

አገራችን ዛሬ የምትራመድበት የሰላም፣ የልማት እና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉዞ፣ ስንት እና ስንት መሥዋዕት ተከፍሎ የተገኘ መኾኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው። አገራችንን ለብዙ አደጋ እና ስጋት ኢጋልጦ የቆየ የጭቆና ሥርዓት ከተገረሰሰበት ማግሥት አንስቶ በነበሩት ወርቃማ ጊዜያት፣ ፈጣን ልማት መመዝገቡንና የዜጎችን የዘመናት ችግር እያቃለለ መቀጠሉን ዓለም ተመልክቷል። በሰላም እና በመረጋጋት ድባብ ውስጥ ሕዝብ ተግባብቶ የልማት ክንዱን ከአነሣ ድህነት አቅም እንደሌለው አገራችን ማሳያ ለመኾን የበቃችበት ስኬት ተመዝግቧል። በዚህ የልማት ጉዞ ውስጥ፣ አፍሪካም ኾነ ቀሪው ዓለም ብሩህ ተስፋችንን አሻግሮ እየተመለከተ አብሮን የተሰለፈበት ዘርፍ ብዙ ነው።

ይኹንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ አካባቢዎች፣ ሰላማችንን አደጋ ላይ የሚጥል እክል እንደ ገጠመን አይተናል። ከዚህ ችግር መካከል ከወራት በፊት በኢትዮጵያ ሶማሌ ብሔራዊ ክልል እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል አዋሳኝ ቀበሌዎች ላይ የተፈጠረው የእርስ በርስ ግጭት ያልተለመደና ፈጽሞ ሊከሠት የማይገባው በመኾኑ በሁሉም ዘንድ ተወግዟል። ያ ክሥተት ልባችንን ያደማ፣ በመላው አገራችን ከባድ ሐዘንን ያስከተለ ፈጽሞ ሊደገም የማይገባው ነው። ሐዘኑም ችግሩ የማያዳግም እልባት እስከሚያገኝበት ዳርቻ ድረስ የሚዘልቅ ስለኾነ፣ ጠባሳው ፈጥኖ እንዲሽር በርትተን በጋራ መሥራት ግድ ይለናል። የተጎዳዱት ወንድማማቾች በመኾናቸው፣ ወደ ነባሩ የወንድማማችነት ሥፍራና ደረጃ የመመለሱ ሥራ ከአቅማችን በላይ ይኾናል ተብሎ አይታሰብም። ከባህላችን፣ ከወጋችንና ከልማዳችን ሁሉ ያፈነገጠውን ያን ግጭት፣ ነባር በኾነው፣ ከዘመን ዘመን በተሻገረውና በደረጀው የአብሮነት ትውፊታችን እንደ

ምንውጣው አምናለሁ። አብሮነታችንና ወንድማማችነታችን፣ ዛሬ ወይም ትላንት ያልጀመረ፣ ዛሬም ያልተቋረጠ፣ የሚዘልቅ፣ ይበልጥ የሚያብብ ታላቅ እና ሕያው ቅርስ ነው።

ርግጥ ነው፣ ከልዩነታቸው ይልቅ አንድ አካልነታቸው እጅጉን በዝቶ እያለ በመካከላቸው የገባ የጥፋት ነፋስ ጊዜያዊ በመኾኑ ብንጽናናም አብረው የኖሩ፣ ክፉውንና ደጉን ያሳለፉ፣ በወዳጅነት፣ በፍቅር፣ በጉርብትና የተሳሰሩ የአንድ አገር ሰዎችን ወዲያና ወዲህ አድርጓቸዋል። ይህ በኢትዮጵያዊነት ልማድም ኾነ በሰብአዊነት እይታ፣ በሕግም ኾነ በኅሊና ሚዛን ፍጹም ተቀባይነት የለውም። በማንኛውም መለኪያ ቢፈተሽ፣ አሸናፊ የሌለበት ተሸናፊነት ብቻ ነው። የደረሰው መፈናቀል፣ ሞትና ጉዳት የሁላችን ሕመም፣ የሁላችን ሐዘን፣ የሁላችን ኪሳራ ነው።

የኢትዮጵያ ሶማሌ እና የኦሮሞ ሕዝቦች በተፈጠሩበት ምድር ላይ፣ በአንድነት የኖሩበትን የዘመን ርቀት ማስላት ያዳግታል። ደስታን በአብሮነት የተካፈሉበትና መከራን በጋራ የገፉበት ማኅበራዊ አኗኗር ብዙ ትውልድ እየተቀባበለው ዛሬ ላይ የደረሰ ሲኾን፣ ወደፊትም ሕዝባዊ ወዘናውን እንደ ተላበሰ ይቀጥላል። የኹለቱ ሕዝቦች አብሮነት ጥልቅ መሠረት፣ ጠንካራ ምሶሶ ያለው ነው። በፖለቲካ እና በአስተዳደር ወሰን የማይከለል፣ በድንበር የማይገደብ ነው።

እነዚህ ወንድማማች ሕዝቦች፥ በደም፣ በባህል እና በቋንቋ፣ በእምነት እና በሥነ ልቡና፣ በኢኮኖሚ እና በማኅበራዊ የተሳሰሩበት ገመድ ሊላላም ኾነ ሊበጠስ የማይችል ነው። ግንኙነቱ ኀልፈት እና ውልደት የሚስተናገድበት የጸና መስተጋብር ነው። ሰው፣ በተፈጥሮ ኀልፈት ከኖረበት ዓምባ ሲለይ፣ ኹለቱም ሕዝቦች እኩል እንባ እያፈሰሱ የሸኙበትና ሕፃን ሲወለድ የሁሉም እልልታ ሕብር ድምፅ ኾኖ ሲሰማበት የኖረ ነው። ዛሬ ደግሞ፣ ኹለቱን ሕዝቦች የበለጠ አንድ የሚያደርጋቸው፣ ድህነትንና ዕጦትን ለማሸነፍ ከመቼውም በላይ እየታተሩ መኾናቸው ነው። እዚህ ላይ አንድ የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝብ ድንቅ አባባል ብጠቅስ ገላጭ ይኾናል፡- “ውሂ ኡሙሻ ኡሮን አያ ኢልመሀና ኡሮን” - ለአራስ እናት የሚጠቅመው ለሕፃኑም ይበጃል! እንደ ማለት ነው።

ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝብ የሚሠራው የልማት ሥራ ለኦሮሞ ሕዝብ፣ ለኦሮሞ ሕዝብ የሚከናወነው የልማት ተግባር ለኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝብ እና ለመላው አገራችን ሕዝቦች አብነት መኾኑ ግልጽ ነው። የዚህ ዓይነቱ በማኅበራዊ ድምቀት እና በልማት ትስስር የታጀበ ቀዬ፣ ዛሬ እክል ገጥሞት ሲታይ ቁጭቱ ያንገበግባል፤ ለመፍትሔም ያሰልፋል። እነዚህ ፍጹም ወንድማማች ሕዝቦች ለኢትዮጵያ አንድነት የከፈሉት ዋጋ እና ዛሬም በአዲሲቷ ኢትዮጵያ በሰላም፣ በልማት እና በዴሞክራሲ ጐዳና የሚተሙበት ጉዞ አንድ ነው። ግባቸው፥ በዕድገት የተራመደች፣ በሁሉም ዘርፍ ከትላንት ዛሬ የተሻለች አገር ለትውልድ አውርሶ ማለፍ ነው።

የኢትዮጵያ የከፍታ ጅማሬ፣ ለዓለም መታየት በጀመረበት በዚህ የሕዳሴ ዘመን ላይ በወንድማማቾች መካከል ጥፋት ያስከተለ ግጭት መከሠቱ፣ አገራዊ ተስፋችንን የሚያጨልም ነው። ፍልሚያችን ከድህነት እንጂ እርስ በርሳችን አይደለም። ምንስ ጠፍቶ እንጋጫለን? ጸጋ በረከትን በበቂ ታድለናል። የገጸ ምድሩን ሲሳይ ብዙም ሳንነካው፣ የከርሰ ምድሩ ሀብት አለሁላችኁ በሚልበት አገር ላይ የልማትን ሰልፍ ከማሣመር ውጭ ወደ ግጭት የሚወስድ ጤነኛ እና ምክንያታዊ መንገድ የለም። የብልጽግና መንገድም ኾነ የሰላም ዋስትና አብሮነት ነው፤ ውበትም ኾነ ጥንካሬያችን የሚመነጨው ከኢትዮጵያዊ አንድነታችን ነው።

እነዚህ ወንድማማች ሕዝቦች ከጥንት እስከ ዛሬ ተሳስረው የኖሩበትን የአንድነት ገመድ ለመበጠስ፣ ካራ ይዞ የሚገዘግዘውን በማያዳግም ኹኔታ መመከት አማራጭ የለውም። የዜጎችን መሠረታዊ መብቶች፣ የአገርን ሰላም፣ የሁላችንንም ደኅንነት በእጅጉ አደጋ ላይ የሚጥል እኵይ አካሔድን ልንታገሥ አይገባም። ሁሉም ነገር ወደ ነበረበት ፈጥኖ እንዲመለስ፣ ሁሉም ወገን የመፍትሔው አካል ኾኖ መሰለፍ ያለበት ዛሬ ነው። የሕዝቦች አንድነት እንደ ወትሮው ሞቆና ደምቆ እንዲቀጥል እዚህ የተገኛችሁትን ሁሉ ከልብ እለምናለሁ። ከአያያዝ ጉድለት የተሸነፍንበትን ችግር መልሰን የማሸነፍ ሕዝባዊ አቅም በእጃችን አለ። ከወዲያም ሆነ ከወዲህ የተፈናቀሉ ሕዝቦች፣ ወደ ነበሩበት ተመልሰው የሚቋቋሙበትን ቅርብ ጊዜ ሁላችንም መናፈቅ አለብን።

ፍቅርን የሚያኽል ኀያል ነገር ስለማይኖር ፍቅር ያሸንፋል። ሽምግልና ችግር የሚፈታበት ጌጠኛ ባህል ኾኖ በኖረበት ሀገር ላይ፣ ወንድማማቾች ተኮራርፈው ሲያድሩ ኢትዮጵያችን ትተክዛለች። የከበደ ወቀሳም ኀሊናችንን ክፉኛ ይሸነቍጣል። ስለኾነም የተፈጠረው ችግር ከዚህ በኋላ ውሎ ሳያድር በማያዳግም ዕርቀ ሰላም እንዲቋጭ አሁንም በአክብሮት እለምናለሁ።

**ነበድ ኢዮ ኣኖ**

**መሃድ ሰንዲን/አመሰግናለሁ**

# የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይት ንግግር

**ሚያዚያ 04/2010 ዓ.ም.**

**የተከበራችኹ የአገራችን የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፣**
**ጥሪ የተደረገላችኹ እንግዶች፣**
**ክቡራት እና ክቡራን፤**

በአገራችን ሰላምን፣ ዴሞክራሲንና ልማትን ለማምጣት እና ለማረጋገጥ በሚደረገው ሁሉን አቀፍ ርብርብ ውስጥ፣ የዳር ተመልካች ከመኾን ይልቅ የምናበረክተው የበኩላችን አስተዋፅኦ አለ፤ በሚል እምነት ተነሣስታችኹ፣ ተደራጅታችኹ እና ፓርቲ መሥርታችሁ እስከ ዛሬዋ ዕለት ለአደረጋችሁት ያላሰለሰ ትግልና ጥረት ልባዊ የኾነ ከበሬታዬንና ምስጋናዬን አቀርባለኹ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሕዝቡን አመለካከት እና ፍላጎት ማንጸባረቂያ መስተዋቶች ናቸው። የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የአንድ አገር ሕዝብ በተደራጀ መልኩ ቀጥተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ ለማድረግ የሚሰባሰብባቸው፣ ፖለቲካዊ ሐሳቡን፣ የፖሊሲ እና የርእዮተ ዓለም ምርጫውን የሚገልጥባቸው፣ ሕዝብንና

መንግሥታዊ ሥልጣንን የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸው። ዘመናዊ ዴሞክራሲ፣ በተለይም ፓርላመንታዊ ዴሞክራሲ ያለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ቀጥተኛ እና ሙሉ ተሳትፎ ሊሳካ አይችልም።

የዴሞክራሲ ሥርዓት ምሰሶ፥ የሕግ የበላይነት፣ ዋልታ እና ማገሮቹ ደግሞ በነጻ የመደራጀት እና አስተሳሰብን በነጻነት የመግለጽ መብቶች ናቸው፤ መሠረቱም የሕዝብ ሉዓላዊነት መርሕ ነው። ዴሞክራሲ፣ ዜጎች የሀገራቸው ጉዳይ ያገባቸዋል፣ እንደ ሀገር ባለቤትም ይመለከታቸዋል፤ስለዚህም በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሲሰጥ በቀጥታም ኾነ በተወካዮቻቸው በኩል ድምፅ ሊኖራቸው ይገባል ተብሎ የሚታመንበት መንግሥታዊ አሠራር እንደ መኾኑ መጠን በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ፣ “የእውነት፣ የዕውቀት እና የቀናነት ብቸኛ ባለቤት እኔ ነኝ፤ ሀገር ወዳድ እና ለሀገር አሳቢም እኔ ብቻ” የሚል አካሔድ ተቀባይነት አይኖረውም። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሁሉም ዜጋ በግሉም ኾነ ከመሰሎቹ ጋራ ተሰባስቦና ተደራጅቶ ለአገር ይበጃል የሚለውን ሐሳብ፣ የአመራር ክህሎቱንና አቅሙን በዐደባባይ አቅርቦ ይፎካከራል፤ ይወያያል፤ ይከራከራል፤ ሕዝብ የፈቀደውን መርጦ ይሾማል፤ በዚህ ሒደት የፖለቲካ ድርጅቶች ሊተካ የማይችል እና ጉልሕ ሚና አላቸው።

ኾኖም፣ እስከ ዛሬ ድረስ በምንፈልገው ደረጃ ዴሞክራሲያዊ ባህል በአገራችን አልዳበረም፡፡ ልዩ ልዩ የፖለቲካ አመለካከቶች የሚስተናገዱበት፣ በሕግ ፊት እኩልነት የሚረጋገጥበት፣ ፍትሕ ቢጓደል በዳይ የሚጠየቅበት፣ ሰብአዊ መብት የሚጠበቅበት፣ እንደ መደራጀት እና መሰብሰብን የመሳሰሉት የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች የሚከበሩበት ሕገ መንግሥታዊ እና ዴሞክራሲያዊ ባህል በበቂ ኹኔታ እንዲዳብር መንግሥት በቁርጠኝነት ይሠራል፡፡

በተጨማሪም፣ የሲቪል ማኅበራት እና ምሁራን በሀገራቸው ጉዳይ አመለካከታቸውንና ያገባናል ባይነታቸውን ማንጸባረቅ የሚያስችላቸውን ነጻነት የሚጎናጸፉበትን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ ተግተን እንሠራለን፡፡ ይህም፣ ሕዝብ እና ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን፣ በአገራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮቻችን ላይ የእኔነት ስሜት ኖሯቸው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ዕድል ይከፍታል፡፡

የዴሞክራሲ መድረኩን ማስፋት፣ በዜጎች ዘንድ የመገለል ስሜትን አክሽፎ የባለቤትነት ስሜትን ያጎለብታል፡፡ በተጨማሪም፣ ፈርጀ ብዙ ችግሮችን ተሸክሞ ከመሔድ ይልቅ ለዘላቂ መፍትሔው በጋራ የመረባረብ ልምምዳችንን ከፍ ያደርጋል ፡፡

## ክቡራት እና ክቡራን፤

መድበለ ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓትን ከዴሞክራሲያዊ እና ከተደራጀ የሕዝብ ተሳትፎ ውጭ ማረጋገጥ ከቶውንም የሚታሰብ አይደለም፡፡ በተለይም በኢትዮጵያ ነባራዊ ኹኔታ ያልተቀናጀ፣ ያልተደራጀ፣ ያልተባበረ፣ ያልተሳሰበ ሕዝብ፤ የውስጥ ችግሮቹንም ኾነ የውጭ ጥቃቱን  በብቃት እና በንቃት መመከት ፈጽሞ እንደማይችል የቀደሙ ታሪኮቻችን ጥሩ ማሳያ ናቸው፡፡

ስንቀናጅ ጉልበት እንፈጥራለን፤ ስንደራጅ እንጠነክራለን፤ ስንተባበር የተሻለ ሐሳብ እናመነጫለን፡፡ ኢትዮጵያ፥ ታላቅ መሥዕዋት የተከፈለበት የጋራ ዕሴት ድምር ውጤት በመኾኗ አስጎምጂው ጅማሮ በጨለማ እንዳይዋጥ ሆደ ሰፊነት፣ ፍቅር እና ከስሜታዊነት ይልቅ ምክንያታዊነት የሰፈነበት፣ ሕዝብንና አገርን መሠረት ያደረገ፣ የተሻለ የመደማመጥ ፖለቲካ ባህልን በአገሪቱ ሕዝቦች ልብ ውስጥ መዝራትንና ማለምለምን ይጠይቃል፡፡

የመድበለ ፓርቲ ሥርዓታችንን፣ የሲቪል ማኅበረሰብንና የምሁራን ተሳትፎን በማቀናጀት ወደ ሙሉ ቁመናው ማሸጋገር የሚያስችል ሰፊ የፖለቲካ ምኅዳር መፍጠሩን ማረጋገጥ ለምንፈልገው ፈጣን የልማት እና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሚናው አይተኬ ነው።

የዴሞክራሲ ትግበራ ሒደታችን ውስጥ ያሉ እንከኖችን በጋራ ለማረም እና ለማከም፣ ሁሉም የዜግነት ሓላፊነቱንና የድርሻውን ያህል በመወጣት ወቅቱ ለጋረጠብን በሽታዎች ኹለንተናዊ  ፈውስ ለማግኘት መረባረብ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራር ቀዳሚ ጉዳይ ሊኾን ይገባል፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች ጠያቂ ብቻ ሳይኾኑ መላሽም ጭምር የሚኾኑበት በቀጣይም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ

ተዋናይ ኾነው የሚሰለፉበት ኹኔታ ሊፈጠር ይገባል፡፡ ችግሩ እና በሽታው የሁላችንም በመኾኑ መፍትሔ እና ፈውሱም ያለው ከሁላችንም ዘንድ ነው።

## ክቡራት እና ክቡራን፤

የአንድ አገር ዴሞክራሲ የሚጎለብተው፣ የአገሪቱ ፖለቲካ ፓርቲዎች አቅም ሲጠናከር ብቻ ነው። ኢኮኖሚያዊ ግሥጋሴ ያለ ዴሞክራሲያዊነት እና ፖለቲካዊ ጥንካሬ ረጅም መንገድ እንደ ማያስኬድ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ጠንካራ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲኖር ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ተነሣሽነት አለ ብለን የገለጽነው እንዲያው ለመድረክ ፍጆታ ሳይኾን ካልተደመርን ሕልማችን ዕውን መኾን እንደማይችል ስለምናምን ነው፡፡

የተሻሉ ሐሳቦች በወጉ ተቀናጅተው፣ ተፈትነውና ነጥረው ወጥተው፣ የፓርቲ አማራጭ- የመወዳደሪያ ርእዮት ኾነው፣ በዙሪያቸው የሐሳብ ተከታይ አሰልፈው፣ ሰላማዊ ትግልን ማካሔድ ሲችሉ፣ የፖሊሲ እና የስትራቴጂ አማራጮች እንዲበራከቱና አገር በትክክለኛ የፖለቲካ መስመር ውስጥ እንድትጓዝ ምቹ ኹኔታን ይፈጥራል።

ድርጅታችን ኢሕአዴግ፣ መንግሥታዊ ሥልጣንን ጨብጦ ከኹለት ዐሥርት ዓመታት በላይ እንደ መቆየቱ፣ ለአገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ከሚጠበቀው አንጻር አስተዋፅኦው ምሉዕ አልነበረም። አካሔዳችን ከመርሐችንና ከንግግራችን ሳይጣጣም፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መጎልበት መጓዝ የሚገባንን ርቀት ያህል አለመሔዳችን ግልጽ ቢኾንም፣ ይህንኑ አሉታዊ ገጽታ፣ ለመንደርደር እንደ መዘጋጃ መልካም አጋጣሚ ተጠቅመን በሙሉ ኀይል እና የአብሮነት መንፈስ ልንረባረብ ይገባል። ይህን መሠረታዊ ጉዳይ እውን ለማድረግም፣ ኢሕአዴግ ራሱን ገምግሞ ችግሮቹን ከመለየት ባሻገር ከችግሩ ለመውጣት፣ በሁሉም ደረጃ በሚገኙ አደረጃጀቶቹ የሪፎርም እና የለውጥ ሥራዎችን ማካሔድ ጀምሯል፡፡

ይኸው የለውጥ ሥራ፣ ከራሱ ከድርጅቱ እና ከመንግሥታዊ መዋቅር አልፎ አገራዊ ትራንስፎርሜሽንን ማረጋገጥ እንዲችል፣ ወደ ሁሉም የኅብረተሰባችን

ክፍል መድረስ ይኖርበታል ብለን እናምናለን። ኢትዮጵያ ጠንካራ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ከመቼውም ጊዜ በላይ በምትፈልግበት ምዕራፍ ላይ ትገኛለች፡፡

በመኾኑም፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ራሳቸውን ለለውጥ ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከምሬት እና ከቁዘማ ወጥታችሁ በአዲስ መንፈስ ልትነሡ ይገባል፡፡ ኢሕአዴግ የተሻለ እና ጠንካራ ፓርቲ እንዲኾን፣የዴሞክራሲን ባህልንም ለማጎልበት የተፎካካሪ ፓርቲዎች መኖር ወሳኝ መኾኑን እንገነዘባለን። ፉክክር ያተጋል፤ ያጠነክራል፤ ሙሉ አቅም አውጥቶ ለመሥራት ያበረታታል፤ አዲስ ሐሳብና አማራጭ እንድናመጣ ያግዛል፡፡ ይህን በመረዳት ለፉክክር የሚመች ሜዳ እና ነጻነት እንዲኖር በማድረግ ለአገራችን፣ ለሕዝባችንና ለድርጅታችንም የሚበጅ ፖለቲካዊ ዐውድ ለመፍጠር እንተጋለን፡፡

## የተከበራችሁ የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፣
## ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣
## ክቡራት እና ክቡራን፤

**መልካም ሥርዓት፣ በትውልድ ቅብብሎሽ ይጠናከራል እንጂ ከመሠረቱ አይናድም፡፡**

በቅንነት፣ በመተባባር እና አርቆ አሳቢነት ከተጠቀምንበት በሚገባ ሊያገለግለን የሚችል ሕገ መንግሥታዊ ዴሞክራሲ አለን። በዚህ መሠረት ላይ ለመገንባት እንድንችልና እንዲዳብር የፖለቲካ እንቅስቃሴያችን ሁሉ ፍጹም ሰላማዊ ሊኾን ይገባዋል፡፡ በጉልበት እና በዐመፅ መንግሥት እየተለወጠ፣ ለአዲስ ሥርዓት ግንባታ መሠረት መቆፈር እና አርማታ መሙላት እጅግ የከፋ ኪሳራ ነው፤ትልቅ ብክነትም ነው፡፡ ሁል ጊዜ ከዜሮ መጀመር፣ የተገነባን እያፈረሱ እንደ አዲስ መነሣት ዋጋ ያስከፍላል። የሚያመዛዝንና አስተዋይ ሕዝብ ልማዱ የሚያደርገው፣ ካለፈው ትውልድ የተረከበውን አሻሽሎ፣ አጠናክሮና አሳድጎ ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብን ነው፡፡

እኛም አገር፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሒደት ሰላማዊ መኾኑን በቃልም በተግባርም ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ባህል እንዲገነባና ሥር እንዲሰድ ከልብ የምንሻ ከኾነ፣ አገር ከፖለቲካ አመራሮች የምትፈልገው ቀዳሚ ጉዳይ፣ ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ምኅዳር እንዲኖር ነው። ሰላማዊ የትግል ስልት፣ የፈሪዎች የትግል ስልት ሳይኾን፣ የሥልጡንነት መገለጫ መኾኑ በሁላችንም ታምኖ ደም ሳንቃባ በሐሳብ ልዕልና አሸናፊ የምንኾንበት፣ የተሸነፍንም አዲስ ሐሳቦችን በመፍጠር ለሌላ ድል የምንዘጋጅበት ልምምድ ልንፈጥር ይገባል።

የፖለቲካ ምኅዳሩን ለማስፋት፣ የዜጐችን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት መብቶችን ከማክበር እና እንዲከበሩ ከማድረግ ባለፈ፣ ማንኛውም ሰው ያመነበትን የፖለቲካ አስተሳሰብ በመያዝና ከሚመሳሰሉት ጋራ በመደራጀት፣ ለሕዝቡ በማቅረብ፣ ለፖለቲካ ሥልጣን የመወዳደር መብት እና የመገናኛ ዐውዶችንና አውታሮችን በመጠቀም የሐሳብ የበላይነትን ለማግኘት በመትጋት፣ በጉልበት ሳይኾን በሐሳብ የበላይነት ነጥሮ ለመውጣት መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

የዴሞክራሲ ተቋማት መጎልበት እና መጠንከር፣የአገራችንን የዴሞክራሲ ሥርዓት የሚያጠናክር በመኾኑና እነዚህ ተቋማትም የተቋቋሙባቸውን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችላቸውን አቅም በመፍጠር የአሠራር ሥርዓቶችን በማሻሻል የዜጐች ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ለዜጐች ወግነው መሥራት እንዲችሉ መጠናከር ይኖርባቸዋል፡፡

መንግሥታችን የፖለቲካ ምኅዳሩን ለማስፋት፣ በራሱ ውስጥ ከጀመራቸው ለውጦች ባሻገር፣ ይህንኑ የሚያግዙ ርምጃዎችን በተከታታይ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ይህ የዛሬው መድረክ፣ ተቀራርበን ለመሥራት ያለንን ዝግጁነት ያሳየንበት ነው፡፡ በመኾኑም፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች የውይይት መድረክ የወጣችኹ የተፎካካሪ ፓርቲ መሪዎች፣ ወደ መድረኩ እንድትመለሱና ያሉብንን ችግሮችም በጋራ ለመፍታት የያዝነውን ቁርጠኛ አቋም እንድትደግፉ፣ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

አገራችን በቀጣይ ለምታካሒደው ብሔራዊ ምርጫ፣ ፓርቲያችን ኢሕአዴግ እና መንግሥታችን፣ ከልብ የኾነ ፍትሐዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ነጻ ምርጫ እንዲካሔድ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ በመኾኑም፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎቻችን በግል እና በጋራ በመኾን ከኢሕአዴግ ጋራ የጀመራችሁትን ሁሉን አቀፍ ውይይት፣ ክርክር፣ ድርድር እና ምክክር አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ ከአደራ ጭምር ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

እምነት የሚጣልበት፣ እየተጠናከረ፣ እያደገና እየጎለበተ የሚሔድ ሥርዓት እንዲኖረን፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ አገር ከልዩነትም በላይ እንደ ኾነች በማስተዋል ኢትዮጵያን በጋራ ለመገንባት እንድትነሡ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፣**
**ተከብራ እና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ**

**አመሰግናለሁ !**

# የሚሊኒየም አዳራሽ ንግግር

**ሚያዝያ 07/2010 ዓ.ም.**

**የተከበራችኹ የአገራችን ሕዝቦች፣**
**ክቡራን የፌደራል እና የክልል አመራሮች፣**
**ክቡራን ጥሪ የተደረገላችኹ እንግዶች፣**
**ክቡራት እና ክቡራን፤**

ዛሬ በዚህ ታላቅ እና ታሪካዊ ቀን ከፊታችሁ ቆሜ ይህን ንግግር ለማድረግ በመታደሌ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ከተለየ አክብሮት እና ፍቅር ጋራ ለመግለጽ እወዳለሁ። የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተምሳሌት፤ በብዙ ማጣት፣ በብዙ ማግኘት፣ በብዙ ለቅሶ፣ በብዙ ሣቅ፣ በብዙ ሐዘንና በብዙ ደስታ ውስጥ መዳፍ እና ጣት ኾናችኹ አዝማናትን በመሻገር ከነፍስ የተጋባ የአብሮነት ልክ በኾናችኹት በእናንተ በውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ፊት ተገኝቼ መልእክት ማስተላለፍ እና የእናንተንም ሐሳብ መጋራት በመቻሌ ራሴን እንደ ዕድለኛ እቆጥራለሁ።

**ይህች አገር ያለ ጥርጥር ታላቅ፣ ሕዝቧም ያለ ክርክር ንዑዳንና ክቡራን ናቸው፡፡**

የተሸከማትን በግ ‘ውሻ ናት’ ብለው ደጋግመው ነግረውት አውርዶ እንደ ጣላት ምስኪን ሰው ካልኾነብን በስተቀር የእኛ እና የአገራችን ንውድነት፣ ታላቅነት እና ክቡርነት ጉዳይ ምንም የሚያጠያይቅ አይደለም። ብዙዎቻችሁ እንደ ሰማችሁት የማምነውን አንድ የአገሬን ጫዎታ እዚህ ጋራ ላንሣ። ሰውዬው እጅግ ያማረበትና በሚገባም የሰባ በግ ተሸክሞ ወደ ቤቱ ይጓዛል። በመንገዱ ላይም በጉን ሊቀሙት የፈለጉ ሰዎች በበጉ ስባት እና ዐይነ ግቡነት ተማርከው የራሳቸው ለማድረግ ይወስናሉ፤ ነገር ግን ሰውዬው እንዲህ በቀላሉ እጅ የማይሰጥ ብርቱ እንደ ኾነ ስላወቁ ሌላ ብልሃት ዘየዱ፤ ዘይደውም አልቀሩም፤ በመንገደኛው ጎዳና ላይ በየመቶ ሜትሩ ተበታትነው በመቆም ባለ በጉን መጠበቅ ጀመሩ።

በግ የተሸከመው ሰው የመጀመሪያው ሌባ ጋራ እንደ ደረሰ ሰላምታ ተሰጣጥተው ሊያልፍ ሲል፣ “ውሻ ተሸክመሃልሳ ጃል ምነው ? ” ቢለው ባለ በጉ ደንግጦ ትከሻዉ ላይ ያለውን ሸክም ፈጥኖ ተመለከተው፤ ውሻ ሳይኾን በግ እንደ ተሸከመ አረጋግጦ ጉዞውን ቀጠለ። ይህ ተመሳሳይ የኾነ የ“ውሻ ተሸክመሃል” አንድ ዐይነት ነገራ ለአራተኛ ግዜ ቢደጋገም፣ ከሚያየው የራሱ እውነት ይልቅ የሌሎች ተደጋጋሚ ሐሰት እምነቱን ሸፍኖበት በጉን ‘ውሻ ነህ’ ብሎት ባዶ እጁን ተጓዘ፤ የሚለው ወግ ለሁላችንም ማንቂያ የሚኾን ታላቅ ቁም ነገር ያዘለ መልእክት እንደ ኾነ በጽኑ አምናለሁ።

## የተከበራችኹ የአገራችን ሕዝቦች፣
## ክቡራን የፌደራል እና የክልል አመራሮች፣
## ክቡራን ጥሪ የተደረገላችኹ እንግዶች፣
## ክቡራት እና ክቡራን፤

አገራችን ኢትዮጵያ፣ የቅርቦቻችንም ኾኑ የሩቆቻችን፣ ወዳጆቻችንም ኾኑ ጠላቶቻችን እንደ ሚያረጋግጡት የብዙ አኩሪ ታሪኮች፣ አጀብ የሚያሰኙ ድንቅ ባህሎች፣ በአድናቆት የሚያፈዙ አያሌ የተፈጥሮ በረከቶች፣ በብሔር

ብሔረሰቦቻችን ማንነት ውስጥ ያለ መናወጥ የተተከሉ ሰብአዊ ዕሴቶች እና በረከቶች የታደለች ሀገር ናት።

እነዚህን በኢትዮጵያዊ ቀለሞቻችን የተሸቆጠቆጡና የእኛነታችን መገለጫ የኾኑ ውድ ሀብቶቻችንን የማክበር፣ የመጠበቅ፣ የመከባከብ እና በተረት-ወጎቻችን፣ በፈሊጥ-ምሳሌዎቻችን፣ በወግ ጫዎታችን ውስጥ ሁሉ እየሰደርን በልጅ ልጆቻችን ልብ ውስጥ የመትከል ግሩም ባህል ያለን ሕዝቦች ነን፤ ነገር ግን በአንድም ይኹን በሌላ ምክንያት እነዚህን የሚያስቀኑ ዕሴቶቻችንን የሚበታትኑና የምናየውን በግ 'ዉሻ ነው' ብለን እንድንጥል ተደጋግመው የሚባሉ-የሚጮኹ የውስጥ እና የውጭ ድምፆች እዚህም እዚያም ሲገዳደሩን ይስተዋላል።

ይኹን እንጂ በተለያዩ መድረኮችና ባገኘኋቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ደጋግሜ እንደምለው፣ ኢትዮጵያዊነት ያስተማረን፣ ለፈተናዎች ተሸንፎ ከመንገድ መቅረትን ሳይኾን ሁሉንም ዕንቅፋቶቻችንን በድል መሻገርን በመኾኑ ያን የድል አድራጊነት ወኔና ቆራጥነት በነፍሳችን ላይ እንደ ገና የምናለመልምበት ወቅት አሁን ነው።

በፍጹም ፍቅር የተዋደዱ ብቻ ሳይኾኑ፣ በፍጹም ቅይጠት የተዋሐዱ የአገራችን ሕዝቦች ደግሞ፣ አሁን ከተጋረጠብን ፈተና ብቻ ሳይኾን፣ የትኛውንም የችግር ክምር የሚሻገር፣ በወጀብ እና በአውሎ ነፋስ መሀል አጓጉዞ ካሰቡት ከፍታ ላይ በእፎይታ የማሳደር አቅም ያለው፤ ጽናት፣ ትዕግሥት፣ አስተውሎት፣ ጉልበት እና አገራዊ ስሜት እንዳላቸው አጥብቄ አምናለሁ። መንግሥትም፣ ይህን የሕዝባችንን ሁሉን አቀፍ ሙሉ ጥንካሬ መሠረት በማድረግና የተለያዩ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ አገራዊ አንድነታችንን ይበልጥ ለማጎልበት በጽናት ይሠራል፡፡

**አብሮነታችን፣ ፈተናዎቻችንን የማሸነፍ ብርቱ ኀይል ያለው ሕዝቦች ነን፡፡**

ችግሮቻችን፣ ችግሮች ብቻ ሳይኾኑ፣ እልባት እና መፍትሔዎቻችንም ጭምር ናቸው። ዕንቅፋቶቻችን፣ ዕንቅፋቶች ብቻ ሳይኾኑ፣ የጉዞ ስንቅ እና መንገዶቻችንም ናቸው።

ልቅሶአችን ልቅሶ ብቻ ሳይኾን፣ የማንባት ጊዜያችን ማብቂያ፣ የሣቅ ዘመናችንም መከሠቻ ዋዜማ ነው። ከሁሉም አስቸጋሪ ዕጣ ፈንታችን ውስጥ፣ ችግራችንን ተረት የሚያደርጉ መልካም አጋጣሚዎችን የመፍጠር፣የተፈጥሮ እና የኑሮ ልምምዶች ያሉን ብርቱ ሕዝብ ነን፤ በመኾኑም ከብረት የጠነከረ የሥነ ልቡና እና የሞራል ብርታታችንን ስንቅ አድርገን የማንወጣው አቀበት፣ የማንሻገረው ጅረት እና የማንረታው ጽልመት አይኖርም፤ በፍጹም!!

በአገራችን ኢትዮጵያ፣ እዚህም እዚያም ተከሥተው የነበሩና በአንድም ይኹን በሌላ መልኩ አሉታዊ በኾነ ገጻቸው የሁላችንንም ቤት ያንኳኩት አለመግባባቶች እና ግጭቶች በወንድማማቾች እና እኅትማማቾች መካከል የተፈጠሩ እና መፈጠር ያልነበረባቸው ቀውሶች ቢኾኑም፣ ለቀጣይ አብሮነታችን ሰላማዊነት ትምህርት ከመኾንና እንዳይደገም ከመሥራት የዘለለ ትዝታ እንዳይኖራቸው የሁላችንንም የጋራ ትብብር የሚጠቅይ የቤት ሥራ ሰጥተውን በራሳችን ጥረት ተሸኝተዋል።

ቀሪ የቤት ሥራዎቻችን ሁሉ የሚሠሩት፣ በእኛው በጉዳዩ ባለቤቶች በመኾኑ ከራስ በሚነሣና እስከ ቤተሰብ፣ አካባቢ እና አገር ድረስ በሚሰፉ የሓላፊነት ስሜት ለአገራዊ ልዕልናችን በጋራ እንድንሥራ የሚጠይቀን አስገዳጅ ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡ በቀጣይም ሁላችንም የየበኩላችንን በማድረግ ወደ ቀደመ ታላቅነታችን ለመመለስ ለምናደርገው ጉዞ የድርሻችንን ማዋጣት እንድንችል፣ መንግሥት ሁሉንም የሚሰማ ጆሮ፣ ለሁሉም የሚመልስ አንደበት፣ ሁሉንም የሚይዘ እቅፍ እና ሁሉንም የሚያይ ዐይን በመጎናጸፍ የበኩሉን ሁሉ ያደርጋል።

ተከሥተው የነበሩት እነዚያ ፈተናዎቻችን፣ በፖለቲካችን፣ በኢኮኖሚያችን፣ በማኅበራዊ መስተጋብራችን፣ በውጭ ግንኙነታችንና በሥነ ልቡናዊ ቀለማችን ላይ ጥለውት ያለፉት አሉታዊ ነጥብ ቀላል የሚባል ባይኾንም፣ ከዚህ ሁሉ የሚበልጠው ግን መለያየትን ፍጹም በመጥላት፣ ከአንድነት-ኅብረታችን ጋራ እንድንዛመድ የፈጠረልን መልካም አጋጣሚ ነው። አብሮነት-ፍቅራችን ሁሉን ያሳልፋል፤ ሁሉን ያሸንፋል።

በቀላሉ ልንረዳው፣ ልንገልጸውና ልንቆጣጠረው በማንችለውና ብዙ ጥናት በሚጠይቀው፣ ከዘወትራዊው አስተውሎታችንም በሚርቀው ሌላ ብዙ ሰበብ፣ የዚህችን አገር ሕዝቦች ብልጽግና የሚፈልጉ እልፍ ወዳጆቻችን የመኖራቸውን ያህል ተቀናቃኙም ብዙ ነው። ከአቀንቃኙም ኾነ ከተቀናቃኙ የየራስ ፍላጎትና ስሜት ጋራ የማይነጻጸረው ኀያል ጉዳይ ግን፣ የእኛ እና የአገራችን ከነፍስ የሚቀዳ ዘላለማዊ የእናት እና ልጅ አገራዊ ኪዳን ነው። ስንደመር እንበዛለን፤ እንጠነክራለን፤ እናንተ እና እኛ ሳይኾን "እኛ" ብቻ እንኾናለን፤ እኛነት ደግሞ ለአገራዊ አንድነታችንና ለብሔራዊ ስሜታችን ያለው አስተዋፅኦ በምንም የሚተካ አይደለም።

በኢሕአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ እና በኢሕአዴግ ምክር ቤት በተደረሰው ስምምነት መሠረት፣ መንግሥት እና ኢሕአዴግ የሕዝባችንን የአብሮነት ዕሴት የሚፈታተኑ መሰናክሎችን ለመበጣጠስ እና አገራዊ አንድነታችንን ለማደስና ለመመለስ ሌት ተቀን ይሠራሉ። ጥረቶቻችንና የጋራ ርብርቦቻችን እንደ ጉም የሚበተኑና የማይጨበጡ ሳይኾኑ፣ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ የሚኖሩና በመውጣት መግባታችንም ሰላማዊ አሻራቸውን የሚያኖሩ እንደሚኾኑ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። ይህ ሐሳባችን እውን እንዲኾንና የምናስባትን ታላቅ አገር መገንባት እንድንችል፣ መላው የአገራችን ሕዝቦች የሰላማቸው አምባሳደር እንዲኾኑ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

## የተከበራችኹ የአገራችን ሕዝቦች፣
## ክቡራን የፌደራል እና የክልል አመራሮች፣
## ክቡራን ጥሪ የተደረገላችኹ እንግዶች፣
## ክቡራት እና ክቡራን፤

ትግላችን፣ የዚህን ታሪካዊ ሕዝብ እና ሉዓላዊት አገር ህልውና ከሚፈታተኑ ዕንቅፋቶች ጋራ እንጂ ከሌላ ከማንም ጋራ አይደለም።

መራራ ጸብ ያለንና ኹለመናችንን ጦር አድርገን ሰብቀን የምንነሣበት ጠላት ጥሩ ከተባልን፣ ከድህነት እና የድህነት እናት ከኾነው ከተደራጀ ሙስና የሚቀድም

ምንም ጠላት የለንም። ዘረኝነት፣ ፀረ ዴሞክራሲያዊነት፣ ኢፍትሐዊነት… ወዘተ የመሳሰሉት ፈተናዎቻችንም የማንታረቃቸው ጠላቶቻችን ናቸው። ከእነዚህ የሚበልጥ ጠላት የለንም፤ በፍጹም!!

በአገራችን ለተፈጠረው ችግር ሁሉ ዘላቂ እልባት ማግኘት ይቻል ዘንድ፣ ሁሉንም የፖለቲካ ውሳኔ አማራጮች ያለምንም ቅድመ ኹኔታ እንጠቀማለን። የፖለቲካ መስመራችን፣ ከሚያጋጥሙን አገራዊ ዕንቅፋቶች ሁሉ የሚያሳርፈን በመኾኑ አስፈላጊውን ፖለቲካዊ ውሳኔ በማሳለፍና ተገቢዉን ርምጃ በመውሰድ የተፈጠረውን ኹለንተናዊ መስተጓጎል ለመሙላት በጽናት እንደምንሠራ ላረጋግጥላችኹ እወዳለኹ።

የአገራችን ኢኮኖሚ፣ እንደ ነዳጅ ባሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ሳይኾን፣ በዜጎቻችን ላብ እና የማያባራ ጥረት ላይ የተመሠረተ በመኾኑ፣ የሕዝባችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አንድ ቦታ ላይ እክል ሲገጥመው ሙሉ ኢኮኖሚያችን እክል ይገጥመዋል። የኢኮኖሚያችን ኹለንተናዊ ትርታ የሚነሣውና ማደግ መመንደጉም ርግጥ የኾነ ህልዉናውን እንደተጎናጸፈ የሚጓዘው፣ የሕዝባችን ሰላማዊ እንቅስቃሴ ርግጠኛ የኾነ ሰላማዊ ፍሰቱን መቀጠል ሲችል ብቻ ነው።

በመኾኑም፣ ባለፉት ኹለት እና ሦስት ዓመታት በአገራችን ተፈጥሮ የነበረው ግጭት እና አለመረጋጋት፣ በአጠቃላዩ ኢኮኖሚያችን ላይ ጥሎት ያለፈዉ ጠባሳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ይኹን እንጂ፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ኾነንና እጅ ለእጅ ተያይዘን በፍጹም ቁርጠኝነት በጋራ እስከ ሠራን ድረስ ያን ማካካስ የሚያስችል በቂ ዕድል ያለው በራሳችን መዳፍ ውስጥ ነው። መንግሥትም ይህን እውነት በመረዳት፣ አርሶ አደሩ እና አርብቶ አደሩ፣ የመንግስት ሠራተኛው፣ ነጋዴው፣ ተማሪው፣ አመራሩ…ወዘተ ሰላማችንን ጠብቆ ኢኮኖሚያችን ባዘገመበት ትይዩ እንዲመነደግ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል። ወደ ኋላ መመለስ ወይም ጥቂት ወደ ኋላ መራመድ ማለት ሁል ጊዜም ወደ ኋላ መመለስ ብቻ ላይኾን ይችላል። ምልሰቱ እንደ መለሰን ሲያስቀር ሽንፈት ቢኾንም፣ ወደፊት ሲያንደረድር ግን የድል መሠረት ነው። ከዚህ አኳያ፣ በኢኮኖሚያችን ላይ ታይቶ የነበረውን አንጻራዊ መቀዛቀዝ፣

ለመንደርደር እንደ መመለስ የብልህ ተግባር ቆጥረን ወደፊት ተንደርድረን ካሰብንበት የመድረሻ መልካም አጋጣሚ የምናደርግበት ዕድል በእጃችን ነው። በተለይም የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋሞቻችን፣ የሕዝብን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥና በአገልግሎት አሰጣጥም የተገልጋዩን ፍላጎት ከማርካት ረገድ የያዙትን ግብ እንዲያሳኩ ከሠራተኞቻቸው ጋራ በመወያየት የባከኑ ቀኖቻቸውን ማካካስ እንዲችሉ መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል። ከወጣቶቻችን ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ ምናልባትም ዋነኛው ፍትሕ እና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት በመኾኑ የአገራችን ወጣቶች ከአገራቸው ሀብት ተገቢውን የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ማግኘት እንዲችሉ፣ መንግሥት ሌት ተቀን እንደሚሠራ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

## የተከበራችኹ የአገራችን ሕዝቦች፣ ክቡራት እና ክቡራን፤

እኛ ኢትዮጵያውያን፣ ከብረት የጠነከረ ማኅበራዊ መስተጋብር ያለንና ሚልዮናት ስንኾን እንደ አንድ ቤተሰብ የሚቀንት በፍቅር የደረጀ ትስስር ያለን ሕዝቦች ነን። በመኾኑም፣ ይህን ማኅበራዊ ውድጅት እና መዋሐድ ወደ አገራዊ ሁሉን አቀፍ በረከትነት ለመቀየር፣ መንግሥት የተለያዩ ሥራዎችን ይሠራል። ይህ አገራዊ ስንሳሌም፣ ለሕዝባችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ሕዳሴ የማይተካ ሚና እንደሚኖረው መንግሥት በጽኑ ያምናል።

የዓለም አገሮች ሁሉ፣ የዚህች ታላቅ አገር እና ክቡር ሕዝብ ጥብቅ ወዳጆች ናቸው። የአፍሪካውያን ወንድሞቻችን ዕጣ ፈንታ የእኛም ዕጣ ፈንታ እንደ ኾነ በውል የሚረዳና በዚሁ ማዕዘናዊ ሐሳብ መሠረትነትም የሚሠራ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ያለን በመኾኑ፣ ከሁሉም የአፍሪካ አገሮች ጋራ ያለን ወንድማዊ ጉድኝት አጠናክረን እንቀጥላለን። ከአፍሪካ አገሮች ጋራ በተለይ ያለንን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ትስስር ለማጠናከር ከምን ጊዜውም በተሻለ ፍጥነት እና ትጋት እንደምንሠራ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። የአገሬ ሕዝብ፣ “ሰላም እንዳድር፣ ጎረቤቴን ሰላም አሳድርልኝ” የሚለው ኢትዮጵያዊ ብሂል ያስተማረንም፣ በሰላም ለመኖር የጎረቤቶቻችንን ሰላም የመጠበቅ

ሓላፊነት እንዳለብን በመኾኑ፣ ለጋራ ሰላማችን በጋራ የመሥራት ባህላችንን አጠናክረን እንቀጥላለን።

## ክቡራት እና ክቡራን፤

ይህች ሀገር ጀግኖች ያስፈልጓታል፡፡
ይህች አገር ዘመኑን የዋጁ እና ዘመናዊውን የጀግንነት መስፈርት ያሟሉ፣ የሰላም-የዕድገት፣ የለውጥ-የብርታት፣ የብልጽግና- የፍቅር፣ የአንድነት - የምክንያታዊነት፣ የይቅርታ እና የመከባበር ጀግኖችን ትፈልጋለች፤ ትናፍቃለች።

ሁሉም ትውልድ፣ ሁል ጊዜም የሚዘክረውና ነገውን የሚተልምበት ጀግና ያስፈልገዋል፡፡ ጀግና የሌለው ትውልድ በጠንካራ መሠረት ላይ ይተከል ዘንድ አይችልም፡፡ በጥንታዊው የሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የነበረውን እውነታ ስንፈትሸው፣ በሁሉም ባህል ውስጥ ማለት በሚያስችል መልኩ፣ ሰዎች ጀግኖቻቸውን ይፈጥራሉ፡፡ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጀግኖችን፣ አዲስ የኀይል እና የመነቃቃት መልክ በማልበስም ጭምር፣ በነበረው ማንነታቸው ላይ የሚደረብ ብቻም ያይደለ ከነፍሳቸው የሚዋሐድ አዲስ ተምሳሌታዊ ገጽ በመፍጠር ለልጆቻቸው ቀጣይ ሕይወት የሰብአ ሰገል ኮከብ ይኾኑ ዘንድ ጀግኖቻቸውን በፍቅር ይሞሽራሉ፡፡ አገራችን የጀግኖች አገር የመኾኑዋን እውነት ጠላትም ኾነ ወዳጅ በልበ ሙሉነት የሚመሰክረው እውነት በመኾኑ፣ ልጆቻችን ከወል ጀግኖቻችን ታሪክ የአገር ፍቅርንና የወገን አለኝታነትን እንዲማሩ ሁላችንም የየበኩላችንን ልንወጣ ይገባል፤ መንግሥትም የሚጠበቅበትን ሁሉ ያደርጋል፡፡

በአንድ ድንቅ መጽሐፍ ውስጥ ያገኘሁትን አንድ ሐሳብ እንዳነሣ ይፈቀድልኝ፡፡ የሰው ልጅ የዝርያውን እምነታዊ፣ ፍልስፍናዊ እና ልቡናዊ ኹኔታዎችን ቀርፆ የሚያኖርበት ሰነዱ፣ የታሪክ እና የነገም የትንቢት ኹነቱ የሚጓጓዘው በተጋዳዩ ወይም በጀግናው አማካይነት ነው፡፡

የዛሬዋ የእኛ ዓለም እና አገራችን፣ እንደ ከዚህ በፊቱ ተጋዳሊዎቻችን ያሉና በእነርሱ መልክ የተበጁ ባይኾንም ቅሉ፣ ብርቱ ተጋዳሊዎችን ወይም ጀግኖችን

ዛሬም ትናፍቃለች፡፡ ዛሬ ዘመኑ ለሚጠይቀው ጀግና ምላሽ ለመስጠትና ተጋዳሊም ኾኖ ለመውጣት ግን የትላንቶቹ ተጋዳሊዎች ታሪክ እና አትመው ያለፉት ደማቅ አሻራ መቼም ቢኾን ችላ ሊባል የማይገባው ጽኑ መሠረት ነው፡፡ ይህ ዕውቅና የምንሰጠው ጀግንነት፣ ሙሉ ቁመናውንና ያልተሸራረፈ ክበቡን የሚይዘው ተምሮ፣ ነግዶ፣ አርሶ፣ አርብቶ፣ አገልግሎ...ወዘተ ሌላዋን ቀን በሌላ ብርታት ለወገኖቹ ሊሸልም የተዘጋጀው የዘመናዊው ዓለም ጀግና ለማኅበረሰቡ የሚበጅ አንዳች በረከት ይዞ መገኘት ሲችል ብቻ ነው፡፡

**"ሁሉን ተሸክማ የምትኖር ዓለም፣**
**ከሰነፍ ሰው በቀር የሚከብዳት የለም፤"**

የሚለው የክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል ጣፋጭ ስንኝም፣ ይህንኑ ሐሳባችንን የሚያጸና ነው፡፡

ዛሬ ላይ ዘመናዊ ጀግና መፍጠር እንችል ዘንድ የትላንት ጀግኖቻችንን የማክበር ባህላችን እጅጉን መዳበር አለበት፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ለትውልድ ተምሳሌት መኾን የሚችሉ ጀግኖችን የማፍራት ንጥፈት የለባትም፡፡ ኾኖም፣ ያፈራናቸውን ጀግኖች ከማክበር፣ ከማንገሥ፣ ከመሠየም እና አሰረ ፍኖታቸውን የሚከተል ትውልድ ከመፍጠር ረገድ፣ ብዙ ያልሠራናቸው ሥራዎች ከፊታችን ይጠብቁናል፡፡ በሁሉም ሕዝቦቻችን ባህል ውስጥ በተለያየ ዘውግ የጀገኑ ዋኖቻችን በክብር የሚነሡ ቢኾኑም፣ በሁሉም ሕዝቦቻችን የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ጀግኖች እየተሞገሱ - እየተወደሱ - በዘፈኑ፣ በጌገርሳ/በፉከራው እየተነሣሱ ከዛሬ ቢደርሱም፣ አሁንም ድረስ ትውልዱ ነገውን የሚያበጅባቸውና የጋራ ራእዩን የሚቀምርባቸው ማእከለ ስበት መኾን አልቻሉም፡፡ የሕዝባቸውን ቅጥር ከመጠበቅ እና የእኔ የሚለውን ርስቱንም የእርሱ ከማድረግ አንጻር ደማቸውን ያፈሰሱ፣ አጥንታቸውን የከሰከሱ እና ሥጋቸውን የቆረሱ ጀግኖቻችንን እንጥራ ብንል ከአእምሯችን ጓዳ የሚፈልቁ ሺሕ ምንተ ሺሕ ጀግኖች በክብር አሉልን፡፡

አብዲሳ አጋን፣ ዐፄ ዮሐንስን፣ በከር ዋሬን፣ የቋራው ዐፄ ቴዎድሮስን፣ ጋኪ ሰሬቾን፣ ታደሰ ብሩን፣ የሶማውን ሳተና በላይ ዘለቀን፣ ጃገማ ኬሎን፣ የወላይታው ካኦ ጦናን፣ ትንታጉ ፈረሰኛ አቢቹን፣ አዝማቹን ፊታውራሪ ሀብተ

ጊዮርጊስ ዲነግዴን፣ የዐድዋውን ደማቅ ድል ከዋከብት ባልቻ ሳፎ-አባ ነፍሶን፣ ፊታውራሪ ገበየሁ አባ ጎራው እና ራስ አሉላ አባ ነጋን፣ የኢትዮ-ሶማሌውን ዑመር ሰመተርን… ወዘተ የቱን ጠርተን የቱን እንተዋለን፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ በዐውደ ውጊያ ብቻ ሳይኾን፣ በተሰለፉበት መስክ ሁሉ፣ ተኣምር መሰል ተኣምር አከል ድል በማስመዝገብ እንኳን የእኛ ኾኑ ያሰኙንና ከአንጀት በሚፈልቅ የእንባ ጎርፍ እና ከነፍስ በሚቀዳ የሣቅ ባሕር በሲቃ ያጥለቀለቁን- የመሰጡን/ያስደመሙን- በደስታ ያሰከሩን በብሔራዊ አንድነት ያጠመቁን ጥቋቁር ከዋክብትን ያፈራች አገር ናት፡፡ ይህን ብዬ ተወንጫፊዎቹን ቀስቶች እነአበበ ቢቂላን፣ ምሩጽ ይፍጠርንና ኀይሌ ገብረ ሥላሴን፤ የጥበብ ቀንዶቹን ጸጋዬ ገብረ መድኅን ቀዌሳንና ሐዲስ ዓለማየሁን፣ ሸራን በተኣምር አናጋሪው አፈ ወርቅ ተክሌን፣ የግብርናው ዐውድ የምርምር ፈርጡን ገቢሳ ኤጀታ ገቢሳን፣ በመረዋ ድምፁ የኹለት ትውልድ ድልድይ የኾነውን ጥላሁን ገሰሰን… አለማንሣት አይቻልም፡፡ እንደ መታደል ኾኖ ጀግኖቻችን ብዙ ናቸው፡፡ ዛሬ ላይ ልጆቿ በሁሉም ረገድ እንዲጀግኑላት የምትፈልግ አገር፣ ልጆቹ፥ ከትምህርት፣ ከሥራ፣ ከንግድ፣ ከእርሻ፣ ከአመራር፣ ከጥበብ፣ ከስፖርት እና በአጠቃላይ ከሕይወት መድረክ ላይ በጀግንነት እንዲነግሡለት የሚሻ ሕዝብ፣ እነዚህን ጀግኖች የማክበር፣ የመዘከርና በልጆቹ ልብ ውስጥ በፍቅር የመትከል አገራዊ፣ ሞራላዊ እና ሰዋዊ ግዴታ አለበት።

**እኛ፣ በጀግና በረከት የተባረክን ጀግና አክባሪ ሕዝቦች ነን፡፡**

ዛሬ ይህ ትውልድ አገራዊ ጀግና ይኾን ዘንድ ጀግና ያስፈልገዋል፡፡ የዛሬው ጀግና እንዲፈጠር ግን የትላንቱ ጀግና የግድ ያስፈልጋል፡፡ ነባሩ ጀግና የአዲሱ ጀግና ወላጅ፣ ነባሩም ታሪክ የአዲሱ ታሪክ መሠረት ነው፡፡ ሒደቱ አይቋረጥም፡፡ የነገረ ተጋዳሊ(Heroism) ጠበብት እንደሚሉትም፣ ጀግንነት የየትኛውም ትውልድ ነፍስ(soul) ነው፡፡

መነሻውን የማያውቅ ትውልድ መድረሻውን ለማወቁ እጠራጠራለኹ፡፡ ከዚህ በፊትም በአንድም ይኹን በሌላ መንገድ ደጋግሜ እንደምለው፣ መድረሻውን የማያውቅ ሁሉ፣ ሁሉም መድረሻው ነው የሚለውን ሐሳብ እዚህም ጋራ አክላለኹ፡፡ በመኾኑም፣ አገራችን በሁሉም መልክ ምሉዕ ትኾን ዘንድ፣

ልጆቻችን ጀግና ሊኾኑና የትኛውንም የአገራቸውን ሕመም አብረው የሚታመሙ መኾን ይገባቸዋል፤ ያ እንዲኾን ደግሞ፣ ያለፉትን ጀግኖቻችንን ማክበር ዋና ጉዳይ ነው፡፡

ምንም እንኳን ሁሉም ጀግኖቻችን በሁሉም ጥግ ጉድለት የሌለባቸው ፍጹማን ባይኾኑም፣ ከታሪክ ማዕዳችን ላይ ፍሬ ፍሬውን በመውሰድ እንክርዳድ ገለባውን ግን ለመማርያነት ብቻ ልናወሳው ይገባል፡፡ አንድ ፈረንሳዊ ፈላስፋ እንዳለውም፣ ከታሪክ መሠዊያ ላይ ዓመዱን ሳይኾን ፍሕሙን የመጫር ልምምዳችንም መጎልበት አለበት፡፡

በመኮራረፍ እና በመጠላለፍ የሚመጣ ድልም ኾነ የሚመዘገብ መልካም ውጤት የለም፡፡ አገራችን ላይ እንዲኾን የምንፈልገውን መልካም ነገር ሁሉ፣ ወደ መሬት ለማውረድና በተጨባጭም ሕልም-ምኞታችንን እውን ለማድረግ፣ የአገራችን ብዙኀን መገናኛ ሚና እጅጉን ከፍ ያለ ነው፡፡ ፍትሕ፣ ዴሞክራሲ እና ሰላም በአገራችን እንዲሰፍን በምናደርገው እልክ አስጨራሽ ትግል ውስጥ፣ የሚዲያዎቻችን ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ይኹን እንጂ ከዘርፉ ተጽዕኖ ፈጣሪነት አንጻር በቂ ነው ማለት ግን አይቻልም፡፡ የማኅበራዊ ሚዲያውም ኾነ የብሮድካስት እና የኅትመት ብዙኀን መገናኛዎቻችን፣ ለአገራችን ኹለንተናዊ ዕድገት እስከ አሁን ከሠሩት ይልቅ ወደፊት የሚሠሩት እንደሚበዛ መንግሥት ይረዳል፡፡ ይህም ኾኖ ለእስከ አሁኑ ጥረታቸው እና ውጤታቸው የአገራችንን ሁሉንም የሚዲያ ተቋማት፣ ጋዜጠኞች፣ ሌሎች የሚዲያ ባለሞያዎች፣ የሚዲያ ተቋማት አመራሮች፣ ባለቤቶች እና ገና በማደግ ላይ ያለውን ይህን ኢንዱስትሪ ለመደገፍ የሚታትሩ አካላትን በሙሉ በይፋ እንዳመሰግናቸው ይፈቀድልኝ፡፡

ሕዝባችን፣ ከመንግሥትም ኾነ ከተፎካካሪ ወንድሞቻችንና ፓርቲዎች የሚነሡ ሐሳቦችን በመደገፍም ኾነ በመቃወም ኹለት ጽንፎችን በማጸነፍ የሚዘግብ-የሚያትትለት ሳይኾን፣ የሞያ እና የሰውነት ሞራላዊ ግዴታዎቹን ተጠቅሞ ማእከላዊ ነጥብ ላይ ኾኖ መረጃ የሚያቀብለው ባለሞያ ይፈልጋል፡፡ በተለይ በመንግሥት በኩል፣ የግሉም ኾነ የመንግሥት ሚዲያ ተቋሞቻችን፣ ክፍተቶቻችንን የሚያሳዩንና ቀጣይ ነገሮችንም የሚጠቁሙን እንዲኾኑ ብርቱ ፍላጎት አለ፡፡

በመኮራረፍ እና በመጠላለፍ የሚመጣ ድልም ኾነ የሚመዘገብ መልካም ውጤት አለመኖሩን በመገንዘብ ከመሞጋገስም ኾነ ከመወቃቀስ ቋሚ ተሰላፊነት ወጥተን ፍትሐዊ መረጃን ለሕዝባችን የማድረስ ተቋማዊ እና ሞያዊ ተልእኳችንን መወጣት አለብን፡፡ መንግሥትም፣ ሁሉም የሚዲያ ዘርፎች ለአገራችንና ለሕዝባችን ያላቸውን የማይተካ ሚና በሚገባ ይረዳል፡፡ በመኾኑም ለሕዝባችን ለሚመጥን የሚዲያ ሽፋን፣ ጥራት እና ተደራሽነት አበክሮ ይሠራል፡፡ ያሉን የኅትመት እና የብሮድካስት ሚዲያዎችም፣ ጨፍኖ ከማመስገንና ጨፍኖ ከማሞካሸት አሠራር ተላቅቀው የሕዝብን ተገቢ መረጃ የማግኘት መብት እንዲያከብሩ መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

**የተከበራችኹ የአገራችን ሕዝቦች፣**
**ክቡራን የፌደራል እና የክልል አመራሮች፣**
**ክቡራን ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣**
**ክቡራት እና ክቡራን፤**

በርግጠኝነት በኢትየጵያ ሰማይ ሥር፣ ነገ ከዛሬ የተሻለች ትኾናለች፡፡ ይህን መሻል የምንፈጥረው ደግሞ እኛው ነን፤ እኛ እና እኛ ብቻ፡፡ ሁላችንም ያለ ሁላችን ምንም ነን፤ እናም እኛ ውስጥ እነርሱ የሚባል ሐሳብ ዘበት የሚኾንበትን ቀን በጥረታችን መፍጠር አለብን፡፡ ያን ስናደርግ፣ ወደ ታላቅነታችን የሚወስደው መንገድ ትግል የሚጠይቅ ቢኾንም፣ ቅርብ ነው፡፡

**“ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!”**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ**

# የጎንደር ሕዝባዊ ጉባኤ ንግግር

**ሚያዝያ 12/2010 ዓ.ም.**

**የተከበራችሁ የፌዴራል መንግሥትና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አመራሮች፣**
**የተከበራችኹ የሃይማኖት አባቶች፣**
**የተከበራችኹ የጎንደር እና አካባቢዋ ወጣቶች፣**
**የተከበራችኹ የጎንደር እና አካባቢዋ ነዋሪዎች፣**
**ክቡራት እና ክቡራን፤**

ከሁሉ አስቀድሜ፣ የኢትዮጵያችን የታሪክ ወጭት እና የኩሩ ሕዝብ ምድር በኾነችው ጎንደር ከተማ ተገኝቼ መልእክቴን ለማስተላለፍ እና ለሀገር - ለወገን የሚበጅ ሐሳብም ለመለዋወጥ በመቻሌ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ እገልጻለሁ፡፡

ጎንደር፣ የአንድነት እና የሉዓላዊነት ልክ እንደ ኾነች መላው ኢትዮጵያዊ በኩራት ይመሰክራል፡፡ በዚህች የዛሬያችን መሠረት ትላንት በተጣለባት ድንቅ ከተማ መገኘት ማንንም ቢኾን በሐሰት ማጥለቅለቁ፣ መንፈስን በደስታ መሙላቱ እና አንገትን በኩራት ማቅናቱ አይቀሬ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጎንደር፥ የአብሮነትና የዘመናዊነት ተምሳሌት፣ የቀደምት ሥልጣኔዎቻችን መሠረት እና የሕዝባችን የከፍታ መሰላል፤ የባህል እና ውብ ዕሴቶቻችን ማኅተም፤ የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ጌጥ እና የትጉሃን ልጆች እናት የኾነች ድንቅ ከተማ ናት፡፡ ጠቢባን ልጆቿዋ በኪነ ሕንፃ የላቀ ርምጃቸው ዛሬም ድረስ የምንደመምበትን የፋሲል ቤተ መንግሥት አንፀው እንዳቆዩን ሁሉ አብሮነትን ባካተተ ዝማኔ የመንግሥት መቀመጫና የዋና ከተማ ቀደምት አሻራን አስተዋውቀውናል፡፡ ሊቃውንቷ፣ አማርኛን ከንግግር ወደ ጽሑፍ ቋንቋነት ያሸጋገሩ ብቻም ሳይኾኑ፣ ደማቅ ፍልስፍናዊ አሻራቸው፣ ዘመንና ትውልድን በተሻገሩ የአለቃ ዘነብ ሥራዎች ውስጥ ተከብክበው ሕያው ኾነው ይኖራሉ፡፡

ጎንደር፥ ከጃን ተከል ጥላዋ ሥር በዘመን ሐዲድ ላይ እያኖረች የመጣችው የመነጋገር፣ የመከራከር፣ የመወያየት፣ የመደማመጥ፣ የመቀራረብ፣ የመተሳሰብ እና ያለ መናወጥ የተተከለ የአብሮነት ካብ የመካብ ጥልቅ-ድንቅ እና ረቂቅ ባህል፣ ለዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ያለው አንድምታ ከመገለጥም በላይ ነው፡፡ የጎንደር እና የአካባቢው ሕዝብ፥ በባህል፣ በኪነ ጥበብ፣ በኪነ ሕንፃ፣ በነጻነት ተጋድሎ፣ በዛሬዋ ኢትዮጵያ እልክ አስጨራሽ ምሥረታ እና ለተፈጥሮ በረከቶቻችን ለዋለው በምንም የማይተካ ውለታ መላ ኢትዮጵያውያን ባለ ዕዳ ነን፡፡

## የተከበራችሁ የጎንደር ከተማ እና የአካባቢዋ ወጣቶች፤

ለአገራችሁ እና ለሕዝባችሁ ያላችሁን ፍቅር፣ ለፈጣሪያችሁ እና ለቃላችሁ ያላችሁን ክብር እና በባህላችሁ መነሻነት ለማንነታችሁ ያላችሁን የማትደራደሩበት ድንበር፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በውል ይረዳዋል፤ በፍቅርም ያከብረዋል፤ ለዚህም ምስክሮቻችሁ እልፍ ናቸው፡፡ እኔም በዚህ አጋጣሚ፥ ትግል፣ ታሪክ፣ እምነት እና እውነት ለአጎናጸፏችሁ ለእነዚህ መገለጫዎቻችሁ ያለኝን አድናቆት እና ከበሬታ ከተለየ አክብሮት እና ፍቅር ጋራ እንድገልጽላችሁ ይፈቀድልኝ፡፡

የጎንደር ልጅ፥ ከጋይንት እስከ ዳባት፣ ከፎገራ እስከ ቋራ፣ ከስማዳ እስከ በየዳ፣ ከደራ እስከ ወገራ፣ ከደባርቅ እስከ ጃናሞራ፣ ከአርማጭሆ እስከ ጩጩሆ፣ ከእስቴ እስከ ጠገዴ፣ ከፋርጣ እስከ መተማ፣ ከሊቦ፣ ከእብናት እና ከበለሳ እስከ ጭልጋ፣ ደምቢያ እና መተማ ድረስ ከሰው ልጆች ሁሉ ፍቅር የያዘውና ራሱም ፍቅር የኾነ ኩሩ ኢትዮጵያዊ እንደ ኾነ ማንም ሳይነግረን በኢትዮጵያዊነት ነፍስ ተሳስረን-ተከባብረን አብረን ኖረን እናውቀዋለን፡፡

እንኳንስ ጎንደር ከምድሯ - ከጥቁር አፈሯ ላይ ኾናችሁ ይቅርና፣ የሕይወት ዕጣ ፈንታ ከአየር አየራት አንሳፎ ሰው አገር አድርሷችሁ እንኳን፥ ወገናችሁን፣ አገራችሁን፣ ትላንታችሁንና ኪዳናችሁን የማትረሱ ባለ ማዕተብ እንደ ኾናችሁ እናውቃለን-ታውቃላችሁ፡፡ በባሕርይና በኹኔታ ቢለያዩም ቅሉ በየዘመናቱ እና በየመንግሥታቱ የሚገጥሟችኹን ፈተናዎች የምትሻገሩበት ትዕግሥት፣ ወኔ፣ ጥንካሬ እና ስክነት እንዲሁም ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችሁ ጋራ ያላችሁ የማትደራደሩበት ዘላለማዊ የአብሮነት ድንቅ ዕሴት ሁል ጊዜም ሁሉንም እንዳስደመሙ ዛሬም አሉ፡፡

መንግሥት ለእነዚህ በጎንደር እና አካባቢዋ ላሉ ግን ደግሞ እስከ ሩቅ የኢትዮጵያ ጥግ ድረስ ለሚሰመሩ ሰዋዊ ዕሴቶች እና የኢትዮጵያዊነት ውብ ቀለሞች፣ ልዩ ክብር እና አድናቆት እንዳለውና እንዲጠበቁ፣ እንዲለሙና ወደ ታላቅ አገራዊ ጥብቅ የወል ሀብትነትም እንዲለወጡ እንደሚሠራ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

እንደ ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን መሰል ወጣቶች ሁሉ፣ የጎንደር እና የአካባቢዋ ወጣቶችም፣ ዘመን የተሻገሩ ግን ደግሞ ከጥያቄነት አልፈው በቂ መልስ ያላፈሩ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት፣ የፍትሕ፣ የመልካም አስተዳደር እና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች እንዳሏችሁ በውል እንገነዘባለን፡፡ በመኾኑም ለእነዚህ መሻቶቻችሁ ብቻ ሳይኾን፣ መብቶቻችሁም ጭምር ለኾኑት የረጅም ጊዜ ጥያቄዎቻችሁ መልስ ለማግኘት የሔዳችሁትን ርቀት እና የጥበቃችኹንም ትዕግሥት እያደነቅኩኝ ለዚህ ዘመን ለተሻገረ ጥያቄያችሁ መንግሥት በየደረጃው ምላሽ ለመስጠት እንደሚሠራ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

ከሁላችንም በፊት ትላንት ላይ ኾኖ ዛሬን ያየውና በአምና ሽራ ላይ ዘንድሮን የሣለው ታሪካዊው ሰው የመይሳው ልጆች ናችሁና፣ በተለመደው ትዕግሥታችሁና አርቆ አሳቢነታችሁ ከጎናችን እስካላችሁ ድረስ፣ በምንችለው ፍጥነት እና መጠን ተረባርበን በመሥራት የማንፈታው ምስቅልቅል፣ የማንሻገረው ገደል እና በጥበብ የማናቋርጠው የሕይወት እክል በፍጹም ሊኖር እንደማይችል አጥብቄ አምናለሁ፡፡

የጎንደር እና የአካባቢዋን ወጣቶች ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አስቸኳይ የመፍትሔ ርምጃዎች የመሚወሰዱ ሲኾን፣ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥም ትጉሃን የጎንደር ልጆች ብርቱ እና ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ከመንግሥት ጎን እንድትሰለፉ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡ እንደ አገር ያሉብንና ደረጃ በደረጃ የምንፈታቸው በርካታ ችግሮች ቢኖሩብንም፣ አፋጣኝ እልባት ለሚያስፈልጋቸው ክፍተቶቻችን ሁሉ አፋጣኝ እልባት በማበጀት ሕዝባችንን ለመካስ ከልብ መዘጋጀታችንን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

በዘላቂነትም የጎንደር እና አካባቢዋ ወጣቶች፣ ተፈጥሮ ከቸረቻቸው በረከት ተጠቅመው ራሳቸውንና አካባቢያቸውን መቀየር እና ማሳደግ እንዲችሉም፣ የደቡብ ጎንደርን ደጋማ ቦታዎች የገብስ እና የስንዴ ማምረቻ፤ የፎገራ እና የመተማን፣ የደንቢያንና የአርማጭሆን ሜዳማ ቦታዎች ደግሞ የጤፍ፣ የሩዝ፣ የሰሊጥና የጥጥ ማምረቻ የዕድገት ኮሪደር ኾነው እንዲለሙ፣ ለአገራችን የውጭ ንግድ እንቅስቃሴ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ በማበርከት የወጣቱንና የነዋሪውን ገቢ በአስተማማኝ መሠረት ላይ የሚያንጹበትን ኹኔታ ለማመቻቸት በተገቢው መንገድ ዐቅደን እንደምንሠራ ቃል እገባላችኋላሁ፡፡

ልማታችን እውን ኾኖ፣ ለወጣቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሮ፣ የዜጎች ሕይወት ተሻሽሎና ጎንደር በአጠቃላይ አምራና ደምቃ በምትታይበት የልማት ጎዳና እንድትገሠግስ በማድረግ ለብዙ ጊዜ ስትጠይቁት ለቆያችሁት የልማት እና የፍትሐዊ ኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ጥያቄ ለጊዜው የሚመጥን መልስ ለመስጠት ተግተን እንሠራለን፡፡

## የተከበራችኹ የጎንደር እና የአካባቢዋ ሴቶች፤

እንደ ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ሁሉ ይህችን አገር በመሥራት እና ሉዓላዊነቷን ጠብቃ ዛሬ የደረሰችበት እንድትደርስ ከማድረግ አንጻር የእናንተ ሚና ከምንም የሚወዳደር እና ከማንም የሚነጻጸር አይደለም፡፡ ጎንደር፥ የድንቅ ታሪክ ባለቤት፣ የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ጽኑ መሠረት፣ የጥበብ እና ውበትም ቤት፣ የእምነት እና የድል ተምሳሌት የመኾኗን ነገር አንሥተን በዚህ ሁሉ ድንቅ ሕብራዊ ማንነት ውስጥ የእናንተን አይተኬ እና አይለኬ ሚና አለማንሣት በፍጹም አንችልም፤ እናንተ ለጎንደር፣ እናንተ ለኢትዮጵያ አገር የመኾን መሠረቶች፤ ማማራችን የተከተበባችሁ ውድ ጌጦች፣ ጀግንነታችን የሚሠራባችኹ የወኔ -ኩራታችን የክብር ቤቶች፤ አገር በጨነቃት ጊዜ ከአሳር ማምለጫ መንገዷን አመላካች የሰብአ ሰገል ኮከቦች ናችሁ፡፡

ልጆቻችሁን ለወግ ለማዕርግ አብቅታችሁ፣ በፍሬዎቻችሁ ውስጥም ሰላማዊዋን፣ የበለጸገችዋን፣ ውቧንና የታፈረች-የተከበረችዋን ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የምትጥሩትን ጥረት፣ የምታደርሱትንም ጸሎት፣ መላው የአገራችን ሕዝብ ያውቃል፤ ክብር እና ዕውቅናም ይሰጣል፡፡ ለዚህች ታሪካዊት እና ታላቅ አገርም የበኩላችሁን ሁሉ ያደረጋችኹ ቢኾንም፣ ስለ አገር በጎበጠው ወገባችኹ፥ ባሎቻችኹን፣ ልጆቻችኹን፣ ወገናችኹን በውክልናውም ውድ አገራችኹን በመሸከም በባተለ ትከሻችኹ እና ስንቱ ለስንቱ ባለቀሱ ዐይኖቻችሁ ድምር መባዘን ልክ ሐሳብ ጥያቄዎቻችሁ ሁሉ በበቂ ኹኔታ መልስ እንዳላገኙ መንግሥት ይረዳል፡፡

በመኾኑም መንግሥታችን፣ ጥያቄዎቻችሁ መልስ እንዳላገኙ አውቃለኹ በሚልና ልብንም ጆሮንም በማይገዛ የውኃ ቅዳ ውኃ መልስ አዙሪት ሳይታጠር በተደጋጋሚ ለምታነሧቸው የልማት፣ የሰላም፣ የፍትሕ፣ የዴሞክራሲ፣ የኢኮኖሚ እና የወሰን ጥያቄዎች፣ ተገቢውን መልስ በመስጠት በተገቢው መንገድ ሊከሳችሁ ከምን ጊዜውም የበለጠ በቁርጠኝነት እንደሚሠራ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

ሴት፥ የቤት፣ የአካባቢ፣ የማኅበረሰብ፣ የአገር እና የሕይወት መሠረት ናት፡፡ የሴቶችን ጥያቄ መመለስ ማለት፣ የአብዛኛውን ማኅበረሰብ ብዙ ጥያቄ መመለስ ማለት እንደ ኾነ በሚገባ ስለ ምንረዳ የእናንተን ጥያቄ ከመልሱ ለማገናኘት እና ችግሮቻችንንም በጋራ ለመፍታት እስከ ዛሬ ድረስ ከሔድነው ርቀት፣ ከተጓዝንበት ፍጥነት በሚሻል መልኩ ተግተን በርግጠኝነት ነገ ከዛሬ የተሻለች እንድትኾን ሴት ተቀን እንሠራለን፡፡

## የተከበራችኹ የፌዴራል መንግሥት እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አመራሮች፣ የተከበራችኹ የሃይማኖት አባቶች፣ የተከበራችኹ የጎንደር እና የአካባቢዋ ወጣቶች፣ የተከበራችኹ የጎንደር እና የአካባቢዋ ነዋሪዎች፣ ክቡራት እና ክቡራን፤

የኢትዮጵያ የቅርብ ዘመን የታሪክ ድርሳን ሲገለጥ፣ ጎንደር እና አካባቢዋ የተስፋ ጎሕ ብሥራት መፍለቂያ፤ የአንዲት ኢትዮጵያ የአንድነት ፀሐይ መፈንጠቂያ ሰማይ ተደርገው ይታያሉ፤ ተገቢም ነው፡፡ በዘመነ መሳፍንት አካባቢ፣ በጦር አበጋዞቿ እኔ እገዛ እኔ እገዛ ፉክክር በተጫረ የእርስ በርስ ጦርነት፣ አገራዊ ንድፏ የመከፋፈል አደጋ በተጋረጠበት በዚያ የጨለማ ዘመን እናት ዓለም ጎንደር የአንድነት እና የተስፋ ብርሃን፣ ከቋራው መይሳው ካሳ ዘመን ተሻጋሪ ድንቅ ምናብ አመንጭታ ከትውልድ ወደ ትውልድ አሸጋግራለች፡፡ በጋፋት፥ አፈር አቅልጠው፣ ብረት ቀጥቅጠው መድፍ የሠሩት የአገራችን ልጆች ወኔ፣ ታሪክ የማይረሳው እና ትውልድ የሚቀባበለው ጀግንነት ከመኾኑም ባሻገር፣ ቴክኖሎጂን በማሸጋገር በራስ አቅም ነጻነትን አስጠብቆ ለመቆም ያደረግነው ጥረት መታሰቢያ በመኾኑ፣ ያለፈው ብቻ ሳይኾን የዛሬውም ትውልድ በክብር ያስታውሰዋል፡፡ ይህ ሕዝብ እና ይህ ምድር፣ በደርግ ፋሺስታዊ በትር ይሳደዱ የነበሩ በርካታ ኢትዮጵያውያንን አቅፎና ደግፎ ወደ ሱዳን በማሻገር ሕይወታቸውን ከማትረፍም በላይ ዛሬ በአውሮፓ እና በሰሜን አሜሪካ፣ አገር

የምትጠራባቸው፣ አገር የምትመካባቸው ታዋቂ ምሁራን፣ ተመራማሪዎች፣ ሠርቶ አዳሪ ዜጎች እንዲኖሯት አድርጓል፡፡

በደርግ የጭካኔ በትር፣ የከተማ መዋቅሩ ሙሉ በሙሉ ከተበጣጠሰው የኢሕአፓ አባላት ውስጥ ጥቂቶች ግን ያልተንበረከኩ ቆራጥ ታጋዮች የዛሬውን ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ በዚያን ጊዜ መጠሪያው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ በሚል ስያሜ የፈጠሩት፣ ጎንደር በለሳ ምድር ላይ እንደ ኾነ፣ በታሪክ ደማቅ ብዕር የተመዘገበ የጽናት መገለጫ ኾኖ ይኸው ዛሬም በክብር ይነሣል፡፡

የኢሕአዴግ የመሀል አገር ግሥጋሴ ብሥራት፣ በዘመቻ ቴዎድሮስ ስያሜ በጎንደር ዙሪያ ወታደራዊ ጥቃት መጀመሩ፣ በድርጅቱ ታጋዮች ብቻ ሳይኾን በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም ድረስ ትውስታው ያልደበዘዘ የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ነው፡፡ በአገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ፣ ጎንደርና አካባቢዋ የአብሮነት ብቻ ሳይኾን የተስፋ ጎሕ ብሥራት ምድርም ነች የሚባለው በዚህ የተነሣ ነው፡፡

ይህች የጥበብ፣ የዝመና እና የተስፋ ብሥራት አገር፣ በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ፍትሕ፣ ዴሞክራሲ እና እኩልነት እንዲረጋገጥ እንደ ሁሉም የአገራችን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ሁሉ የአማራ አርሶ አደሮች፣ ምሁራንና ወጣቶች በጎንደር፣ በአዲስ ዘመን፣ በጋይንት፣ በእስቴ፣በደብረ ታቦር፣ በጉና፣ በበለሳ በሁሉም የአማራ ክልል ገጠር እና ከተሞች የከፈሉት ውድ የሕይወት እና የአካል መሥዋዕት በክብር የምንዘክረው ብቻ ሳይኾን፣ ዘብ የምንቆምለት ሕያው አደራም ጭምር ነው፡፡

በዓምባገነን ገዢዎች የተጫነባቸውን የጭቆና ቀንበር እምቢኝ በማለት ባካሔዱት መራር ትግል በርካታ የአማራ ወጣቶች በዐደባባይ ተረሽነው ሬሳቸው ሜዳ ተጥሏል፤ ታስረው ተገርፈዋል፤ አካላቸው ጎድሏል፡፡ ከቁጥር በላይ የኾኑ ዜጎችም ከተወለዱበትና ካደጉበት ቀዬ ቤተሰባቸውን ጥለው ሀብት ንብረታቸውን በትነው ስደት ገብተዋል፡፡

የሰላምን ዋጋ፣ የዴሞክራሲን አብነት እና የአብሮነትን ጥቅም ለጎንደር ሕዝብ መንገር ለቀባሪው እንደ ማርዳት ዓይነት ከንቱ ድካም ከመኾኑም ባሻገር ከቴዎድሮስ ሩቅ ርእይን፣ ከፋሲል ጥበበ ንግሥናንና ኪን፣ ከአለቃ ዘነብ ቅኔንና ፍልስፍናን፣ ከገብርዬ ጀግንነትንና የአገር ፍቅርን… ከእልፍ ተምሳሌቶቹ እልፍ የበረከት ዕሴቶችን ለተማረ፣ ለተቀበለ እና በሕይወቱ ውስጥም ላጸደለ ሕዝብ፥ አገር ማለት አገር እንደ ኾነች በውል ይረዳልና ይህን ለማብራራት መነሣት በፀሐይ ላይ ባትሪ ለማብራት ከመሞከር ከንቱ ድካም የዘለለ ትርጉም አይኖረውም፡፡

በመኾኑም፣ ይህችን የጋራ ኪዳናችን መነሻ እና መድረሻችን፣ ብዙ ስንኾን አንድ የመኾኛ ምስጢራችን፣ ኖረን በስሟ መጠሪያችን፣ ሞተን ስሟን መኾናችን፣ አብረናትም ኾነን እንኳን ናፍቆታችን፣ ተሰደንም ስስታችን ለኾነች ውብ ቅኔ አገር ኹለንተናዊ ዕድገት እና ብልጽግና ሁላችንም የአንድ አካል ክፍሎች ኾነን በጋራ እንድንሠራ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

## የተከበራችሁ የጎንደር እና አካካቢዋ ሕዝቦች፣ ክቡራት እና ክቡራን፤

ጎንደር እና ጎንደሬ፣ አብረዋቸው ከሚኖሩ ሌሎች ሕዝቦች እና ወገኖቻቻው ጋር በጋራ ያሏቸው ድንቅ መገለጫዎች እንዘርዝር ብንል ሌላውን የማይጋፋ እና ምቾት የማይነሳ ኩራት እና በራስ መተማመን (confidence) አንዱ ነው፡፡ ይህ በራስ ከመተማመን ድንቅ ሰብእና ወስጥ የሚቀዳ ድንቅ ባሕርይ ለራስ፣ ለወገንና ለአገር እስከ መታመን የሚዘልቅ ግሩም ሰው የመኾን ጸጋም የሚታይበት ድንቅ መገለጫ ነው፡፡

አሁን አሁን ግን፣ ሥር የሰደደ ድህነት፣ የመገፋት/የመተው/ እና የመላሸ የለኝም ቀቢጸ ተስፋ ስሜት፣ ያን ኩራት እና በራስ የመተማመን ልክ እየተፈታተነው የመጣ ይመስላል፡፡

በመኾኑም፣ ከድህነት ጋራ የምናደርገው ትግል፣ ድኻ ላለመኾን የሚደረግ ትግል ብቻ ሳይኾን፣ ለዘመናት አብረውን የዘለቁ ነገር ግን በብዙ ፈተናዎቻችን ምክንያት ቀለማቸውን እየለቀቁ ያሉ መገለጫ ዕሴቶቻችንን የምናስመልስበት እና የምናድስበትም የህልውና ጥያቄ የኾነ እልክ አስጨራሽ ትንቅንቅ ነው፡፡

ጎንደር፣ የጥንታዊ ሥልጣኔያችን አሻራ፣ የመንፈሳዊ ገጽታችን ዕፁብ ስፍራ፣ አስደናቂ ባህሎች፣ ዕሴቶች እና ከፍ ያለ ጨዋነት የከተሙባት ውብ ጋራ እና የአስጨናቂ አርበኞች የነጻነት ጎራ የመኾኑዋን ያህል ጥንታዊውን መልኳን ከዘመናዊው መልክ አጣምራ በመያዝ የበለጠ እንድትዘምን የማድረግ ሓላፊነት በሁላችንም ላይ ወድቋል፡፡ መኾኑም፣ መንግሥት ለዚህ ተግባር ልዩ ትኩረት በመስጠት ጎንደር ከተማችን እንደ ጥንቱ ሁሉ ዛሬም የዘመናዊነት፣ ዕድገት፣ውበት እና ምቹነት ማሳያ እንድትኾን ከክልሉ መንግሥት ጋራ በመተባበር በትጋት ይሠራል፤

## ክቡራት እና ክቡራን፤

ጎንደር፣ ጎንደርን ብቻ ሳይኾን አገርን የሚሸከም ሰፊ ትከሻ ያለው ሕዝብ እና ምድር እንደ ኾነ የቅርቦችም የሩቆችም በጋራ የሚመሰክሩት እውነት ነው፡፡ ይህችን ዛሬ የምናያትን ኢትዮጵያ እኛ ሳናያት ያዩ፤ እኛ ዛሬ እንኳን ያላልነውን እነርሱ ግን ያኔ ከፈረንጅ ሥልጣኔ ምን እንደሚያስፈልጋቸው በጥበብ የለዩ፤ ሴባስቶፖልን በጋፋት አቁመው ለዓለም ያሳዩ የኢትዮጵያችን የቁርጥ ቀን ልጆች ናቸው፤ የጎንደር እና ዙርያዋ ኢትዮጵያውያን፡፡ መንግሥት፣ ይህ ሕዝብ ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር በጋራ በመኾን ያፈሰሰውን-ያዋሐደውን ደም፣ የከሰከሰውን-የማገረውን አጥንት፣ የፈተተውን-የቆረሰውን ሥጋውንና የከፈለውን ወደር የለሽ መሥዋዕት የሚመጥን ዴሞክራሲ - ልማት - ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት - ፍትሕ እና ሰላም እንዲያገኝ ለማድረግ በቁርጠኝነት ይረባረባል፡፡

በምዕራብ ከሱዳን እና በሰሜን በኩል ከትግራይ ጋራ አሉ የሚባሉ የድንበር፣ የማንነት፣ የአስተዳደራዊ ወሰን... ወዘተ ጥያቄዎችን፣ ሕግንና ሕግን ብቻ መሠረት በማድረግ፣ እንዲሁም አስፈላጊውን ፖለቲካዊ ውሳኔ በመወሰን ለማስተካከል እንደምንሠራ በዚህ አጋጣሚ ቃል እገባለኹ፡፡ የወልቃይት ሕዝብ

ያሉበትን የመልማት እና የእኩል ተጠቃሚነት ጥያቄ በምንመልስበት ትኩረት፣ ፍጥነት እና ፍትሐዊነት ልክ፣ ሌሎች ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ተቀብለን ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት ከሚመለከታቸው ሁሉ ጋራ በመኾን በጽናት እንደ ምንረባረብ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

የትኛውም ትክክለኛ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ አለው፤ የትኛውም ሕጋዊ ሒደት ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል፤ የትኛውም የሰከነ እና የበሰለ ሐሳብ እና የአመለካከት ቅብብል፣ የሰከነ እና የበሰለ ፍሬ ማስገኘቱ አይቀርም፡፡ በመኾኑም መንግሥታችን፣ እነዚህን የጎንደር እና የጎንደሬዎችን፣ በተራዘሚውም የመላ ኢትዮጵያውያን የሕጋዊነት፣ የስክነት፣ የብስለት እና የትክክለኛነት ዕሴቶች ተከትሎ ላሉብን ችግሮች ሁሉ መፍትሔ ለማበጀት በቁርጠኝነት እንደሚሠራ ላረጋግጥላቸሁ እወዳለሁ፡፡

ባለፉት ኹለት እና ሦስት ዓመታት፣ በአገራችን ተከሥቶ በነበረው ግጭት ሳቢያ በተፈጠረው የሰው ሕይወት መጥፋት - የአካል ጉድለት - የሥነ ልቡና ስብራት እና የንብረት ውድመት... ወዘተ በመንግሥታችን ስም የተሰማኝን ልባዊ ሐዘን ለመግለጽ ይህ መድረክ ትክክለኛ ቦታ ይመስለኛል፡፡ በመኾኑም፣ በተለይ ጎንደር ከተማ ውስጥ እና በዙርያዋ ለተፈጠረው ቀውስ ሁሉ ከልብ የመነጨ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ ከይቅርታም በላይ ልባችንን የሚሞላውና ስብራታችንን የሚጠግነው ከይቅር በሉኝ - ይቅር ብለንሃል አዙሪት የሚሻገር ተግባራዊ ውጤት በመኾኑ መንግሥት፣ በመላው ሕዝባችን ውስጥ ፍትሕ እና ዴሞክራሲ በተጨባጭ እንዲረጋገጥ በማድረግ የሕዝባችንን ሰላም በማረጋገጥ፤ የሕዝብን እኩል ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ትርጉም ባለው መልኩ በሕይወቱ ውስጥ በማሳየት፤ ለጥያቄዎቹ ሁሉ ፈጣን ምላሽ በማበጀት እና የሥልጣን ባለቤት አንተ ነህ የሚለውን መርሕ ከጀሮው ነጥቆ ለዐይኑ በመስጠት ማረጋገጥ ሲቻል በመኾኑ፣ መንግሥት ለዚሁ ተግባር ስኬታማነት አጥብቆ ይሠራል፤ ይታገላል፡፡

ጎንደር፣ የኢትጵያውያን፥ የክብር - የኩራት - የአብሮነት እና በራስ የመተማመን ምልክት ናት፡፡ ጎንደር፣ የቤተኛው ጎንደሬ እና ቅማንት ብቻ ሳትኾን የእንግዳው ቱሪስትም ቤት እንደ ኾነች ለመመስከር፣ የተመቸው ጥምቀትን፣ ያልኾነለት

ሰንበትን አልያም ደግሞ አንድ ዕድለኛ ምሽትን ከጎንደር ሰማይ ሥር ማደር በቂ ምስክርነት ያሰጣል፡፡ ይህ ፍቅር እና ከነፍስ የሚነሣ ኢትዮጵያዊ ክብር ከምንጊዜውም በላይ ዛሬ ያስፈልገናል፤ ምክንያቱም ፍቅራችንና የኢትዮጵያዊነት ሞራላዊ፣ መንፈሳዊ እና ሰዋዊ መገለጫዎቻችን፣ የትኛውንም ፈተና ያለ መናወጥ ያሻግሩናል፡፡ ትላንት የነበሩን፥ መልካም ስም፣ ዝና፣ ታሪክ እና የጀግንነት ገድሎችን የበለጠ ጉልበት እና የመንደርደርያ ኀይል እንዲኾኑን በሚገባ ልንጠቀምባቸው ይገባል፡፡ የቴዎድሮስ ራእይ፣ የፋሲል ሥልጣኔ፣ የገብርዬ ጀግንነት፣ የአለቃ ዘነብ ጥበብ፣ የአበቅየለሽ ሞያ፣ የይርጋ ዱባለ ባህል ቃና እና፡-

**ጎንደር እንኳን ሰዉ ያቅራራል አሞራው፣**
**ግርግር ሲነሣ ይላል ቋራው ቋራው፤**

የተባለለት የጀግንነት ዝና፣ የትላንት ኹነት፣ የዛሬም እውነት ከመኾን ባለፈ ነጋችንንም የምንሥራበትና ዛሬያችንን ዘመኑ ከሚጠይቀው መሰጠት አንጻር የምናበጅበት የዘመናዊ ጀግንነት ምንጭ እንዲኾነን ጠንክረን ልንሠራ ይገባል፡፡

በመጨረሻም፣ መላው የጎንደር እና የአካባቢዋ ሕዝብ፣ መንግሥት የሕዝብ ጥቅም የበለጠ ይጠበቃል ብሎ በአመነበት አቅጣጫ በአደረገው እንቅስቃሴ እና በቅርቡ በተካሔደው ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር መነሻነት ከጎናችን በመቆም ላሳያችሁን ድጋፍ እና ወደፊትም ይህችን አገር ወደ ከፍታዋ ለመመለስ በምናደርገው እልክ አስጨራሽ ትግል ውስጥ ከጎናችን ስለምትኾኑ በከፍተኛ አክብሮት እና ፍቅር ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡

**"ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!"**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**አመሰግናለሁ**

# የባሕር ዳር ሕዝባዊ ጉባኤ ንግግር

**ሚያዝያ 13/2010 ዓ.ም.**

**የተከበራችኹ የአማራ ብሔራዊ**
**ክልላዊ መንግሥት አመራሮች፣**
**የተከበራችኹ የሃይማኖት መሪዎች፣**
**የተከበራችኹ የባሕር ዳር ከተማ እና አካባቢዋ ነዋሪዎች፣**
**የተከበራችኹ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣**
**ክቡራን እና ክቡራት፤**

ከሁሉ አስቀድሜ፣ በደሙ እና በላቡ አገር ባቆመው እና ራሱም አገር በኾነው በዚህ ታላቅ ሕዝብ ፊት ቆሜ ንግግር ለማድረግ በመታደሜ እና የታሪክ፣ የባህል፣ የተፈጥሮ፣ የውበት እና የእምነት ሙዳይ በኾነች ውብ ከተማ ውስጥ ተገኝቼ ከእናንተ ጋራ ሐሳብ መለዋወጥ፣ ፊት ለፊትም መገናኘት በመቻሌ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ በታላቅ አክብሮት እና ፍቅር ላቀርብ እወዳለሁ፡፡

ይህ ሕዝብ፣ ለዚህች አገር ህልውና እና ለሕዝቦቿም ልዕልና አይተኬ መሥዋዕት የከፈለ ሕዝብ ነው፡፡ ይህ ሕዝብ የጋራ ቤታችን የኾነችውን ኢትዮጵያን ከሌሎች ወንድም እኅቶቹ ጋራ በነፍስ ተሳስሮ በብዙ አስቸጋሪ ኹኔታዎች ውስጥ አሳልፎ ለዛሬ ያደረሰ ብርቱ ሕዝብ ነው፡፡ ይህ ሕዝብ በተለያዩ ዘመናት የተነሡበትን

ዓምባገነኖች በጽናት በመፋለም እምቢኝ ለሀገሬ - እምቢኝ ለነጻነቴ ብሎ በየጋራው፣ በየፈፋው፣ በዱር በገደሉ በጀግንነት ተፋልሞ በመሥዋዕት የወደቀ ጀግና ሕዝብ ነው፡፡ መላው የአገራችን ሕዝቦችም፣ የዚህን ታላቅ ሕዝብ የዘመናት ተጋድሎ እና በዛሬው ድላችን ውስጥ ያለውን ጉልሕ ድርሻ በተለየ ክብር ያደንቃሉ፤ያከብራሉ፡፡

በውጭ ወራሪዎች በየዘመኑ የተቃጡብንን ወረራዎች በመመከትና በድል አድራጊነትም ወራሪዎችን አሳፍሮ በመመለስ የሸዋ፣ የወሎ፣ የጎጃም፣ የጎንደር እና በአጠቃላይም የአማራ ሕዝቦች የአርበኝነት ተጋድሎና የቁርጥ ቀን ልጅነት በነፃነት ወዳዶቹ ሁሉም የአገራችን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ዘንድ ዛሬም ድረስ በክብር የሚዘከር ሕያው የታሪክ አሻራ ነው። ሕዝባዊ ጀግንነትንና የፋኖነት ዋጋን ከበላይ ዘለቀ እና

**ታናሽ ነው ይሉታል እጅጉ ዘለቀን፣**
**ከበላይ እኩል ነው እሱም የከፋው ቀን፤**

ከተባለለት አርበኛ ከእጅጉ ዘለቀ፣ ስለ ሀገሩ ክብር እና ስለ ወገኑ ፍቅር ሶማ ከወደቀው ከሺፈራው፣ ከገብርዬ እና ከመይሳው አብነታዊ ተምሳሌት የወረስነው አገራዊ ፍቅር እና ወገንን ከራስ የማስቀደም ብርታት፣ ለትውልዳችን ሁል ጊዜም ኀይል የሚኾን ዘመን ተሻጋሪ ስንቅ ኾኖ እስከ ዛሬ ዘልቋል፡፡

ዛሬ እንደ አገር በደረስንበት የጉዞ መስመር ውስጥ፣ ሁሉም ኢትዮጵያውያን የየራሳቸውን ጡብ አኑረዋል፡፡ ቀደምት የሶማሌ፣ የጉራጌ፣ የትግራይ፣ የአፋር፣ የኦሮሞ፣ የሲዳማ፣ የወላይታ፣ የጋምቤላ፣ የከምባታ፣... ሕዝቦች በአገራችን ገዢ መደቦች የተጫነባቸውን ቀንበር አንቀበልም በማለት በአንድ በኩል ከፈታኟ ሕይወት፣ በሌላ በኩል ከተፈጥሮ ንጥፈት እና ከዓምባገነን መንግሥት ጋራ እየታገሉ ይህችን አገር ከዛሬ አድርሰዋታል፡፡ የአማራ አርሶ አደሮችም፣ እንደ ሌሎች ወገኖቻቸው ሁሉ የዚህ መራራ ትግል ገፈት ቀማሾች የነበሩ ሲኾን፣ በዚህ አሁን ባለንበት አካባቢ የነበረውን የጀግንነት ትንቅንቅ በማሳያነት መመልከቱ ነገሩን ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል፡፡

የጎጃም አርሶ አደሮች የተሠውበትንና በብቸና፣ በሞጣ፣ በዳሞት እና በአካባቢዎቻቸው ያካሔዱትን የገበሬ ዐመፅ በዚህ መድረክ ላይ አለማንሣት አይቻልም፡፡ በዚያ የጎጃምን ሰማይ የሞት ሲላ ይዞረው በነበረበት አስቸጋሪ ጊዜ፣ ደረታቸውን ለጦር እና ለጥይት ሰጥተው ለልጆቻቸው ሰላም እና ነጻነት ለማቆየት የቆረጡትን ትንታግ አርበኞች ለማቆም የዐፄው መንግሥት ጦር በማዝመት የፊት ለፊት ውጊያ ከማድረጉም ባሻገር የበልግ-የክረምት ጠል ይዘንብበት እና በዝናም በረከትም ይረሰርስ የነበረ የጎጃም ምድር ከአየር በሚርከፈከፉ ቦምቦች እንዲደበደብ ኾኗል፡፡ በዚህ ሁሉ አስቸጋሪ ኹኔታ ውስጥ በጽናት ያለፈው ይህ ሕዝብ የዛሬዋን ኢትዮጵያ እውን በማድረግ ፈታኝ መስመር ላይ ያተመው አሻራ እጅጉን ደማቅ ነው፡፡

**የተከበራችሁ የአማራ ብሔራዊ**
**ክልላዊ መንግሥት አመራሮች፣**
**የተከበራችሁ የሃይማኖት መሪዎች፣**
**የተከበራችሁ የባሕር ዳር ከተማ እና አካባቢዋ ነዋሪዎች፣**
**የተከበራችሁ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣**
**ክቡራን እና ክቡራት፤**

በሕዝቦቿ ፈቃድ እና እኩልነት በመገንባት ላይ ያለችው የዛሬዋ ሕብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያ፣ አሁናዊ ቀለም እና አገራዊ አንድነት እንዲረጋገጥ የአማራ ሕዝብ ያበረከተው ታላቅ ድርሻ በጦርነት ዐውደ ግንባር ብቻ ታጥሮ የሚያበቃ አይደለም፡፡ በአገራችን መንፈሳዊ እና ዓለማዊ የዕውቀት ዓለም ውስጥ፣ የኢትዮጵያ ነፍስ እና ሥጋ በሯሷ አገራዊ የዕውቀት ሸማ እንዲታነፅ ጥንታዊ እና ታላላቆቹ ጣና ቂርቆስ፣ ደብረ ወርቅ፣ ደብረ ኤሊያስ፣ ዲማ ጊዮርጊስ፣ ዋሸራ፣ የጋይንት ቤተ ልሔም አድባራት፣ ገዳማት እና አብያተ ክርስቲያን የነበራቸው አስተዋፅኦ አገር ትረሳው ዘንድ ከቶ የማይቻላት ዘመን አይሽሬ ታሪክ ነው፡፡ የአብያተ መስጂዶቻችን የትምህርት መድረኮች፣ የመድረሳዎቻችን አይተኬ አስተምህሮዎች፣ ከየመስጊዶቹ ከለዋዎች የመነጩ እና በዚህች አገር የረጅም ዘመን ታሪክ ውስጥ መሠረታቸውን ያኖሩ ባለውለታዎቻችን ብዙ ናቸው - በጣም ብዙ፡፡

ማኅበራዊ ችግር በተለይም በሽምግልና አልረታ ያለን ሰው እና ለእርቅ አሻፈረኝ ያሏቸውን ጉዳዮች ሁሉ በመፍታትና ሰዎችን በመምከር የሚታወቁት አራት አይና ጎሹንና አካለ ወልድን፣ መርሳ አባጌትዬንና ሐጂ መሐመድ ሳኒ ሀቢብን፣ በነገሥታቱ ዘመን አድያም ሰገድ ኢያሱን ምርጥ መሪ ማድረግ የቻሉት መምህርና ሊቅ አባ ስብሐት ለአብን፣

**ዓባይ በጣና ላይ መሔዱ ለምን ነው?**
**ትንሹ ሲያጠፉ ትልቁ ሊችል ነው፤**
**ቢያጠፉም ቢያበጅም ዓባይ ማለፉ ነው፣**
**ሰውን በግዴታ የሚገዛው ማነው?**
**ከምክር በስተቀር የቀረው ከንቱ ነው፤**

በሚለውና በሌሎች እልፍ ፍልስፍናዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ትንቢታዊ እና ቅኔያዊ ግጥሞቻቸው የሚታወቁት ሼህ ሑሴን ጂብሪል....፣ ማንን ጠርቶ ማንን መተው ይቻላል? ይህ ሕዝብ ለዚህች አገር የዋላቸው ውለታዎች እና ያበረከታቸው ሊቃውንት - የቀለም ቀንዶች እጅጉን ብዙ ናቸው፡፡

በአገራችን ታሪክ ዘመናዊ ትምህርት ባልተጀመረበት በዚያ ወቅት የአገሪቱ የአስተዳደር መዋቅርም ጭምር ይሸፈን የነበረው ከአብነት ት/ቤቶች ተመርቀው በሚወጡ ምሁራን ስለነበር እኒያ አገር በቀል ሊቃውንት ከኹለት እስከ ሦስት ዐሥርት ዓመታት ተምረውና ተመርቀው የሚወጡት አኮፋዳ ይዘው፣ ቁራሽ እንጀራ ከእያንዳንዱ አርሶ አደር ቤት ለምነው እየበሉ እንደ ነበር ይታወቃል፡፡

አርሶ አደሩ ከዕለት ጉርሱ ቀንሶ፣ በቀን አንድ እንጀራ ለተማሬ ወይም የቆሎ ተማሪ መድቦ ያለ ማንም አስገዳጅነት ነገ ይጦሩኛል የሚላቸውን ሳይኾን፣ ነገ አገሬን ያገለግሉልኛል የሚላቸውን የሕዝብ እና የአገር ልጆች አስተምሮ ያስመርቃል፡፡ ተማሪዎች የሚመጡት ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሲኾን፣ ተመርቀው ሲወጡም አገልግሎት የሚሰጡት በየትኛውም የአገሪቱ ክፍሎች እነርሱ ወደ ፈቀዱት ሔደው ነበር፡፡ የቅኔው ሊቅ፣ ድንቁ ሠዓሊ እና ጥበበኛው ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ፣ ትውልዳቸው ወለጋ የነበረ ቢኾንም፣ ጎጃም ደብረ ኤልያስ ተምረው የጎጃም ሊቅ ተብለው ወንበር ዘርግተው ማስተማራቸውን ለአማራ ሕዝብ

በአጠቃላይ ለጎጃም ሕዝብ ደግሞ በተለይ የሁሉን አቃፊነት፣ ለሁሉ ወዳጅነት እና ለፍቅር ተምሳሌትነት ጥግ በማሳየነት ማንሣት ይቻላል፡፡

በጎጃም እንደ ዲማ እና ዋሸራ ያሉ ስመ ጥር የአብነት ትምህርት ቤቶችም፣ በዘመናቸው፣ ከሃይማኖታዊ አስተምህሯቸው በተጨማሪ ለአገራችን የመንግሥት አስተዳደር የሚመጥኑ ሹማምንት እና ሠራተኞቻቸውን አስተምረው እና አስመርቀው በማውጣት ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡

በመኾኑም ጎጃም በተለይ የአማራ ሕዝብ በአጠቃላይ፣ ለዘመናዊ ትምህርት መነሻ የኾኑን የአብነት ትምህርት ቤቶች በስፋት የሚገኙበት፣ ሕዝቡም ከዕለት ጉርሱ ቀንሶ ከየትኛውም የአገራችን ክፍሎች የሚመጡ ተማሪዎችን ቀለብ በመስፈር፣ የመምህራኑን ደሞዝ አዋጥቶ በመክፈል፣ የተማሪዎችንና የሊቃውንቱን የመኖሪያ እና የመማሪያ ቦታዎች በማዘጋጀት እና በመከባከብ ለዛሬው ዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት እና ለሥልጣኔያችን ፈር መቅደድ በብዙው የደከመ እና ውጤታማም የኾነ ሕዝብ በመኾኑ መመስገን ይገባዋል፡፡

"በፍርድ ከሔደች በቅሎዬ፣ ያለፍርድ የተነጠቀችብኝ ጭብጦዬ ትቆረቁረኛለች" በሚል ብሂሉ የሚታወቀውና በፍትሐዊ ፍርድ የሚያምነው የጎጃም ሕዝብ፣ በአገራችን ውስጥ የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ በጽናት የሚታገለውም ከዚሁ ማኅበረ ባህላዊ ዕሴቱ በወረሰው እምነቱ ነው፡፡ በጉልበት ለሚመጣበት ሁሉ ጎራዴውን መዝዞ፣ ጋሻ እና ጦሩን ሰብቆ፣ ጠመንጃውን ወልውሎ፣ሰንጋ ፈረሱን ቀስቅሶ፣ አመሉን በጉያው፣ ስንቁን በአህያው ጭኖ ለጦርነት ይዘምታል፤ ይፋለማል፤ይሠዋል፤ ድልም ያደርጋል፡፡ የጣሊያንን ወራሪ ኀይል አይቀጡ ቅጣት የቀጡ እንደነ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ያሉ በርካታ አርበኞች መፍለቂያ መኾኑን ማንሣት ለዚህ ሐሳቤ በማስረጃነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ጎጃሜ ፍትሕ ይወዳል፤ ለሕግም ይገዛል፤ ኹለት ሰዎች ሲጣሉ ያገኛቸው መንገደኛ እንኳን የጠበኞችን ነጠላ ቋጥሮ፣ "ዳኛ ይፍታችሁ" ብሎ ካቆራኛቸው ከዳኛ ሳይደርሱ ራሳቸው ቋጠሮውን አይፈቱትም፡፡ መንግሥት፥ ይህን ለፍትሕ

የመቆም፣ ለእውነተኛ ዳኝነት የመስጠት እና ለሕግ የመገዛት የቆየ ድንቅ ባህል፣ በዘመናዊ የፍትሕ ሥርዓታችን ውስጥም እንዲረጋገጥ ለማድረግ ቀን ከሌት እንደምንሠራ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

ጎጃም፥ አየሩ ለኑሮ፣ አፈሩ ለምርት ተስማሚ እና ለም ከመኾኑም ባሻገር የዓባይ ወንዝ መነሻም ነው፡፡ ያለውን የማምረት ጸጋና በአግባቡ የሚጠቀም፣ ለሥራ ደከመኝ ሰለቸኝ የማይል ሕዝብ ነው፡፡ የጎጃም አርሶ አደር፣ ጠዋት በሬዎችን ከጠመደ የሚፈታው ማታ ጨለማ ሲገላግለው ብቻ ነው፡፡ በሌሎች የአጨዳ፣ አረም እና ሌሎች ሥራዎችም፣ ማልዶ ሥራ ጀምሮ ጨለማው ሲገባ ብቻ ሥራ ማጠናቀቅ የተለመደ የጎጃም ሕዝብ የሥራ ባህል ነው፡፡ ይህን የማያደርግና የማይፈጽም ሲታይ፣ “እገሌ ቆቻ አይውልም” በሚል ምፀት ይሣለቅበታል፡፡ በመኾኑም፣ በጎጃም አርሶ አደር ዘንድ የዕረፍት ጊዜ የሚባል የለም፡፡ ጤፍን ጨምሮ ትርፍ አምራች የኾነውም ያለ ዕረፍት በመሥራቱ ነው፡፡

በዚህ ሁሉ ልፋቱ ውስጥ ግን፣ ከላቡ በረከት ማግኘት የሚገባውን ጠቀሜታ ከማግኘት አንጻር በልፋቱ እና በውጤቱ መካከል ያለው ርቀት እጅጉን ሰፊ ነው፡፡ በመኾኑም፣ ገበሬው የድካሙን ያህል ራሱ ተጠቅሞ አገሩን መጥቀም ይችል ዘንድ፣ የአገር ዋልታ አርሶ አደሩ በቴክኖሎጂ መደገፍ የሚችልበትን ኹኔታ መንግሥት ያመቻቻል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ለግብርና ሥራው ዕንቅፋት የሚኾኑትን፥ የግብአት እጥረት፣ የመልካም አስተዳደር ጉድለት፣ የሞያዊ ድጋፍ ክፍተት፣ የገበያ ትስስር መላላትና ለመሳሰሉት ተግዳሮቶች ሁሉ፣ የፌዴራል መንግሥት ከክልሉ መንግሥት ጋራ በመኾን ኹነኛ መፍትሔ ለማበጀት በቁርጠኝነት ይሠራል፡፡

ከቱሪዝም ዘርፍ አኳያም ካየነው፣ አካባቢው እንዳለው የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ የቱሪስት መስሕቦች ብዛት እና ሳቢነት ልክ በተገቢው መልኩ ተጠቃሚ ኾኗል ማለት አይቻልም፡፡ ጎጃም የበርካታ ገዳማት እና አድባራት፣ አስደናቂ ቅርሶች እና ባህሎች፣ የዓባይ መነሻ ነጥብ፣ የጢስ ዓባይ ፏፏቴ እናት፣ የአገራችን ብሎም የምሥራቅ አፍሪካ የውኃ ማማ እና ኩራት፣ ከ200 በላይ ወንዞች መፍለቂያ የኾኑት የጮቄ እና አዳማ ተራራ ዕንብርት፣ 3600 ስኩዌር ኪሎ

ሜትር የቆዳ ስፋት ያለው፣ በውስጡ 36 ደሴቶች እና ዘጠኝ ገዳማትን ያቀፈው የጣና ሐይቅም መገኛ እና የአገራችን የውበት፣ የታሪክ እና የባህል ሰገነት ብትኾንም፣ ከእነዚህ ሁሉ በረከቶቿ ማግኘት የሚገባትን ትሩፋት አላገኘችም፡፡ በመኾኑም መንግሥት፣ እነዚህ መስሕቦቻችን ተጠብቀው፣ ለምተው እና ለቱሪስቶችም ምቹ ኾነው፣ ለአካባቢው ሕዝብ፣ ለክልሉ እና ለመላው የአገራችን ሕዝብ፥ የገቢ፣ የተዝናኖት እና የታሪክ ማእከል እንዲኾኑ አስፈላጊው ሥራ ሁሉ ይሠራል፡፡

በመጨረሻም፣ ያሉብንን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመፍታት፣ መንግሥት እየወሰደ ካለው ርምጃ ጎን ስለ ቆማችሁ እና የመፍትሔውም አካል ለመኾን አብራችሁን መኾናችኁ ስላሳያችኹን ልባዊ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

**“ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!”**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ**

# የሐዋሳ ሕዝባዊ ጉባኤ ንግግር

**ሚያዝያ 18/2010 ዓ.ም.**

**የተከበራችኹ የመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች፣**
**የተከበራችኹ የሃይማኖት አባቶች**
**እና የአገር ሽማግሌዎች፣**
**የተከበራችኹ የሐዋሳ እና አካባቢዋ ነዋሪዎች፣**
**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣**
**ክቡራት እና ክቡራን፤**

በራስጌዋ የታቦር ተራራን ዘብ አቁማ፣ በስተግርጌ የስምጥ ሸለቆውን ሐይቅ ዘርግታ፣ ከዕድሜዋ በላይ በፈጣን የዕድገት ግሥጋሴ ምሕዋር ላይ በምትገኘው የክልሉ መዲና በኾነችው በውቢቷ ሐዋሳ ከተማ እና በእንግዳ ተቀባይ ሕዝቦቿ መካከል በመገኘቴ የተሰማኝን ከፍተኛ ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ኢትዮጵያዊነት፣ በሕብረ ብሔራዊ ቀለማት ያጌጠበት የአንድነት እና የአብሮነት ረቂቅ ሸማ፣ ድር እና ማግ ነው፡፡ የዚህ ክልል ሕዝብ፣ እንደ ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ፣ የረጅም ዘመን ታሪክ እና የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት ነው፡፡

ከአራት ሺሕ ዓመታት በላይ የዘለቀው እንስትን ጨምሮ የሰብል ልማት እርሻ ሥራ፣ የሥነ ጥበብ እና ጥበበ እድ ሥራዎች፣ የራሳቸው የዘመን አቆጣጠር ያላቸው፣ ጥንታዊ የተደራጀ የአስተዳደር እና ፖለቲካ ሥርዓት ባለቤትነታቸው ሲታይ ክልሉ የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት መኾኑን ያረጋግጣል፡፡

## ክቡራት እና ክቡራን፤

የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፥ ኢትዮጵያ ጥንት፣ ኢትዮጵያ ትላንት፣ ኢትዮጵያ ዛሬ፣ ኢትዮጵያ ኾና በነጻነት እና በአንድነት እንድትኖር፣ ከተቀሩት የአገራችን ሕዝቦች ጋራ በአብሮነት በመሰለፍ፣ በዐድዋ፣ በማይጨው፣ በካራማራ እና በባድመ፣ በታላቅ ጀግንነት አገራችንን ጠብቀው አቆይተዋል፡፡

ይህ ሕዝብ፣ በሰላም ለመጡበት ሁሉ እጁን ዘርግቶ፣ ያለውን አካፍሎ፣ መኻታውን ለቅቆ በአብሮነት ለመኖር ከፊት ተርታ የሚሰለፍ ነው፡፡ በአገር ባለቤት እና በማንነታቸው ኮርተው ከሌሎች የአገራችን ሕዝቦች ጋራ በወንድማማችነትና በጋራ ለመኖር ለዘመናት ያካሔዱትን የአርበኝነት ተጋድሎ እና የተከፈለውን መሥዋዕት የምንዘክረው ብቻ ሳይኾን፣ ዘብ የምንቆምለት ዓላማ ነው፡፡ ዝክራችን፥ የሲዳማ፣ ወላይታ፣ ጉራጌ፣ ቀቤና፣ ሐዲያ፣ ማረቆ፣ ስልጤ፣ ጌዴኦ፣ ዳውሮ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ የም፣ አይዳ፣ ባስኬቶ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጠምባሮ፣ ዶንጋ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ ደራሼ እና ኮሬ ሕዝቦች ያደረጉትን የሞት ሽረት ትግል በማስታወስ የሚያበቃ ሳይኾን፤ የካፋ፣ ቤንች፣ ሸካ፣ መኢኔት እና የደቡብ ኦሞ ሕዝቦች፣ እስከ ዐድዋ ጦርነት መባቻ ድረስ፣ ገባርነትን መከላከል ችለው እንደ ነበር ከሚያረጋግጥ እውነታ ጋራ የሚዘከር ነው፡፡

## ክቡራት እና ክቡራን፤

ይህ ክልል፣ በልዩነት ውስጥ አብሮ መኖር እንደሚቻል ያስመሰከረና አርኣያ መኾን የሚችል ነው፡፡ በልዩነት በምንም መልኩ ሊበጣጠስ የማይችል መዋሐድ እና የጋራ ዕሴቶች ባለቤት የኾኑ ሕዝቦች መኖሪያ ክልል ነው፡፡ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፥ የራሳቸው ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ ያላቸው መኾኑ

እንደተጠበቀ ኾኖ በባህላዊ የቤት አሠራር፣ የእንስት አመራረት እና ዝግጅት፤ በሕዝባዊ በዓላት አከባበር እንዲሁም፣ በአገር በቀል ዕውቀቶች አጠቃቀም እና በመሳሰሉት ለበርካታ ዘመናት የፈጠሩት ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ግንኙነቶች የሚያስተሳስራቸውን የጋራ ዕሴቶች ፈጥረዋል፡፡

የክልሉ ሕዝቦች ለረጅም ዘመናት ሲተዳደሩበት የነበረ፣ የየራሳቸው የተደራጀ ጥንታዊ የአስተዳደር እና የፖለቲካ ሥርዓት ያላቸው ብቻ ሳይኾኑ፣ ሕዝቡም የራሱን መሪ የሚሠይምበት እና የሥልጣን ርክክብ የሚያከናወንበት፣ የሐሳብ ልዩነቶችን የሚያስተናግድበት፣ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበት፣ በቋንቋው የሚዳኝበት፣ ማንነቱን የሚገልጽበት፣ የጀግንነት ተግባር የፈጸሙትን የሚያበረታታበት እና የሚሸልምበት የዳበረ ጥንታዊ ባህላዊ የአስተዳዳር ሥርዓት ባለቤት መኾኑ ታሪክ ብቻ ሳይኾን፣ ዛሬም በሕይወት ያሉ የአገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት አባቶች የሚመሰክሩት ሐቅ ነው፡፡

በመኾኑም፣ ሩቅ ሳይሔድ ይህ ሕዝብ፣ በራሱም ኾነ ከአጎራባች ወንድሞቹ ጋራ አልፎ አልፎ የሚከሠቱ፣ ለሕይወት እና ለንብረት ውድመት ምክንያት የኾኑ ግጭቶችን ለማስወገድ እና የነበረውን የቆየ ጠንካራ መስተጋብር እና ትስስር ወደ ነበረበት ለመመለስ፣ ጥንታዊ ባህላዊ ሥርዓቱን ተተግኖ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን መሠረት እና ለቀጣይ ርእያችንም ዋስትና፣ መፍትሔ ማመንጨት ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም መረጋገጥ፣ የፌዴራል መንግሥት ከክልሉ መንግሥት ጋራ በመኾን አበክሮ የሚሠራ መኾኑን በዚሁ አጋጣሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

## ክቡራንና ክቡራት፤

ክልሉ በአመዛኙ፣ የመሬት ጥበት እና ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር መጨመር ከሚስተዋልባቸው የአገራችን ክፍሎች መካከል አንዱ በመኾኑ፣ በክልሉ የተመዘገበው ፈጣን ዕድገት የሁሉንም የክልሉን ነዋሪዎች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንዳላስቻለ፣ ከሕዝቡ የዕለት ተለት ኑሮ የምንረዳው ሐቅ ነው፡፡ በጤና፣ በትምህርት፣ በመንገድ፣ በመብራት፣ በውኃ እና ሌሎች መሠረተ ልማቶች ለማዳረስ የተደረገው እንቅስቃሴ፣ ረጅም ርቀት መጓዙ የሚካድ

ባይኾንም፣ ከሕዝቡ ፍላጎት አንጻር ግን፣ ገና ብዙ መሥራትን የሚጠይቅ ሰፊ ክፍተቶች ያሉበት እንደ ኾነ ሐቅ ነው፡፡ ይህን እውነታ ለመለወጥ፣ የፌዴራል መንግሥት ከክልሉ መንግሥት ጋራ በመኾን፣ ከ20 ሚሊዮን በላይ ቁጥር ያላቸውንና በየትኛውም ደረጃ ሥራ ሳይንቁ ሠርተው ለመለወጥ ደፋ ቀና የሚሉ የክልሉን ሕዝቦች በአጠቃላይ ከጎናችን በማሰለፍ ኑሯቸውን ለመለወጥ፣ በተለይም የወጣቱን ሕይወት የተሻለ ለማድረግ በትጋት እንሠራለን፡፡

ኾኖም ግን፣ ባሕር ላይ ቆማ የምትጠጣውን ውኃ ከሰማይ እስኪዘንም እንደምትጠብቅ ወፍ፣ እግር እና እጃችንን አሳስረን መቀመጥ አይኖርብንም፡፡ የደቡብ ክልል ሕዝቦች፣ ታታሪ ሠራተኛነት እና ድንቅ የመቆጠብ እና የመሻሻል መንፈስ፣ ከራሳቸው አልፎ ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ተምሳሌት ናቸው፡፡ ይህ ሕዝብ፣ ጠንክሮ የመሥራትን ብቻ ሳይኾን፣ የመተባበርንና የመደጋገፍን ዋጋ አስቀድሞ በመረዳት፣ ባንክ ሳይፈጠር፣ አክሲዮን ሳይመጣ፣ ሴፍቲ ኔት ሳይቋቋም በፊት፣ ባህላዊ የዕቁብና የዕድር ሥርዓትን የመሠረተ፣ ለተቀረው የአገራችን ሕዝቦችም ያሸጋገረ ሕዝብ ነው፡፡ በዚሁ ባህላዊ ሥርዓት፣ ትላንት አያሌ የክልሉ እና የአገራችን ሕዝቦች ችግርን ማሸነፍ እንደቻሉት ሁሉ፣ የዛሬውም ትውልድ የአባት አያቶቹን ታታሪ ሠራተኛነት፣ ድንቅ የመቆጠብ እና የመሻሻል መንፈስ፣ ከመተባበር እና መደጋገፍ ሥርዓቱ ጋራ በማስተሳሰር፣ ለራስ፣ ለቤተሰብ፣ ለክልል እና ለአገራዊ ዕድገት፣ የልማት አርበኛ እንዲኾን በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

በውጭ አገር የተያዙ የንግድ ሥራዎችን፣ በአገር ዜጎች በመተካት አገርን ከእጅ መጠምዘዝ የታደጉ፣ በቤተሰብ የሚመራ ንግድ በኢትዮጵያ ያስተዋወቁ ቀደምት የልማት አርበኞች እንደነበሩ፣ የዛሬዎቹ የእዚህ ክልል ሕዝቦች በመረዳት፣ መታወቂያችኹ የኾነውን ታታሪ ሠራተኝነት እና አገር ወዳድነት በውስጣችሁ ሕያው መንፈስ እና የጉዞ አቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስ በማድረግ ለአገራችሁ ሰላም፣ ዴሞክራሲ እና ልማት ዘብ በመቆም ታሪክ ትሠሩ ዘንድ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

## ውድ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፤

በመንደር፣ በአካባቢ ያልታጠረ አድማስ ተሻጋሪ፣ አብሮ የመኖር እና የመሻሻል ጽኑ እምነት ባለቤት መኾኑና ከባህላዊ እምነቶች ጎን ለጎን በሰላም ተጎራብተው ብቻ ሳይኾን፣ በአንድ ቤተሰብም ውስጥ ተጣምረው የሚኖሩትን የተለያዩ ሃይማኖቶች ማሳያ አድርጎ ማቅረብ ይቻላል፡፡ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በሰው እና በአካባቢ፣ በግለሰብ እና በማኅበረሰብ መካከል ተፈጥሯዊ ሚዛን ተጠብቆ የሚኖርበትን አገር በቀል የግብርና፣ የተፈጥሮ ጥበቃ፣ የሕግ እና የአስተዳደር ሥርዓት፣ ዛሬም ድረስ ማዝለቅ የቻሉ ናቸው፡፡

በዚሁ ክልል፣ የስምጥ ሸለቆ ትሩፋት የኾኑ የተለያዩ የውኃ ሀብቶች ለአብነት ያህል አባያ፣ ጫሞ፣ ሐዋሳ፣ ሩዶልፍ ሐይቆች፣ ኦሞ ወንዝ እና ሌሎችም የሚገኙበት ከመኾኑ በተጨማሪ፣ ክልሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ፣ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች ለአብነት ያህልም የኮንሶ እርከን ሥራ፣ ጢያ ትክል ድንጋይ፣ የካፋ የጫካ ቡና፣ የሲዳማ ፍቼ ዘመን መለወጫ፣ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ መካነ ቅርስ፣ የጌዴኦ ጥምር ግብርና ተጠቃሽ ሀብቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዳ ያላቸው ሀብቶች፣ የክልሉን ሕዝቦች ተጠቃሚነት ማሳደግ ለሚችል ልማት መነሻ ከመኾን አልፈው ደቡብንም፣ የኢትዮጵያ እስትንፋስ የማድረግ አቅም የሚያጎናጽፉ ናቸው፡፡

በመጨረሻም፣ በተለመደው የእንግዳ ተቀባይነት ባህሉ፣ ዳኤ ቡሾ፣ በላለዲ ይምጣ፣ በአፈር ንተን፣አሻም... በማለት በፍጹም ፍቅር እጆቹን ዘርግቶ ለተቀበለን ሕዝብ እና ለክልሉ አመራሮች፣ እኔም ከወገቤ ዝቅ በማለት ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

**"ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!"**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ**

# የአሶሳ ንግግር

**ሚያዝያ 23/2010 ዓ.ም.**

**እንጃይሮታ**
**ኤያባቻ ግሽርማ**
**ጀኒትኔ**
**ናሹምኮዳ**
**ሱኩምናገዳ ጉያ**

**የተከበራችኹ የመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች፣**
**የተከበራችኹ የሃይማኖት**
**አባቶች እና የአገር ሽማግሌዎች፣**
**የተከበራችኹ የአሶሳ እና አካባቢዋ ነዋሪዎች፣**
**ክቡራት እና ክቡራን፤**

ከሁሉ አስቀድሜ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ሐውልት የኾነው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ መገኛ በኾነውና "ከላይ ከወደቀብህ ማንጎ፣ ከሥር ካደናቀፈህ ወርቅ ሊኾን እንደሚችል ገምት" እየተባለ በሚነገርላት የሰላም እና የመተሳሰብ፣ የመቻቻል እና የመከባበር ተምሳሌት በኾነችው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ የእንግዳ ተቀባይ ሕዝቦች መናገሻ በኾነችው የአሶሳ ከተማ ተገኝቼ ከክልሉ ሕዝቦች ጋራ ሐሳብ ለመለዋወጥ በመብቃቴ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ እና ክብር ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕዝብ፣ ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት ያልተለየው- ቸር ሕዝብ እንደ ኾነ ሁሉም የሚገነዘበው ሐቅ ነው፡፡ ይህ ሕዝብ፣ ለኢትዮጵያውያን ወንድሞቹ ብቻ ሳይኾን፣ ከጎረቤት አገር ሱዳን በስደት የሚመጡትንም ሕዝቦች እንደ ራሱ ሕዝብ አቅፎ፣ ያለውን አካፍሎ የማኖር የረጅም ጊዜ ባህል ያለው በመኾኑ ከችግራቸው ጋራ ተቸግሮ፣ ከጉዳታቸው ጋራ ተጎድቶ እንግዶቹን ያስተናግዳል፡፡ ይህ ባህሉ የሚደነቅና ለወደፊቱም ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ሲኾን፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነገ ሕዳሴው ተስፋ የጣለበት ታላቁ ግድብ እዚህ ታሪካዊ ምድር እና ፍቅር የኾነ ሕዝብ ደጅ ላይ እንዲቆም የልብ እምነት የጣሉበት ባለ አደራ ሕዝብ ነው፡፡

በክልሉ፥ ከበርታ፣ ጉሙዝ፣ ቦሮ-ሺናሻ፣ ማኦ እና ኮሞ ብሔረሰቦች በተጨማሪ አማራው፣ ኦሮሞው፣ አገዉ፣ ትግሬው፣ ጉራጌው እና ሌሎችም ሕዝቦች በአንድ የአብሮነት ማግ ተሸምነው በሰላም እና በፍቅር የሚኖሩበት፣ ኅብረ ብሔራዊ ውበት የሚታይበት ክልል እንደ መኾኑ መጠን፣ በዚህ ድንቅ ክልል እና የክልሉ ርእሰ መዲና በኾነችው በአሶሳ መገኘት በመቻሌ የተሰማኝ ውስጣዊ ደስታ በምንም ቃል ሊገለጽ የሚችል አይደለም፡፡

የዚህ ክልል ሕዝቦች እንደ ብሔር ብዝሐነታችሁ ሁሉ የራሳችሁ የኾነ ዐይነተ ብዙ የአስተዳደር እና የፍትሕ ሥርዓት ያላችሁ ታላቅ ሕዝቦች ናችሁ፡፡ የቅብብል ተዋረዱ ቅርፅ የያዘ እና የተደራጀ የአስተዳደር መልክ እንዳላችሁ ማስታወስ ብቻ ሳይኾን፣ በማንነታችሁ ኮርታችሁ፣ መልካም ባህሎቻችሁን አዳብራችሁ፣ አገር በቀል ሁሉን አቀፍ ዕሴቶቻችሁ ለአገራዊ ዴሞክራሲ ግንባታችን ሒደት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ እንደምታደርጉ እተማመናለሁ፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፣ ያለንን በውል ያልተጠቀምን እንጂ፣ ምንም የሌለን ሕዝቦች አይደለንም፡፡ በመኾኑም፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ሕዝቦች፣ አገር በቀል የኾኑ፥ የአብሮነት፣ የፍትሕ፣ የዕርቅ፣የፍቅር እና የመከባበር ባህሎቻችሁን ተከባክባችሁ በመያዝ ለአገራዊ ሕዳሴያችን የከፍታ ጉዞ ዋና መሣሪያ ማድረጋችኹን እንደምትቀጥሉ እምነቴ የጸና ነው፡፡

## ውድ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕዝቦች፤

መዛግብቶች እና በአርኪዮሎጂ ቁፋሮ የተገኙ ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት፣ በዚህ ክልል ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች የንግድ እንቅስቃሴያቸው፣ ከኢትዮጵያ አልፎ እስከ ግብፅ የተዘረጋ ነበር፡፡ የአኩስም እና ሜርዌ ነገሥታት፣ የግብፅ ፈርዖኖች ጭምር ወርቅ እና ልዩ ልዩ ማዕድናትን ከቀደሙት የዚህ አካባቢ ሕዝቦች ይገበዩ እንደ ነበር ታሪክ ያስረዳናል፡፡ ይህ ሕዝብ እና ይህ ክልል፣ እንደ ሌሎች ወንድም/እኅቶቹ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፣ ታላቅ እና ሕዝብ-ምድሩም የውብ ተፈጥሮ በረከቶች ማማ ነው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ፣ እንኳን ለልጆቿ፣ ለጎረቤቶቿ የሚተርፍ መሬት እና ሀብት እያላት ከዚህ በተቃራኒ በኾነ መልኩ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ፈተናዎች ውስጥ ለማለፍ የተገደደች አገር ናት፡፡ ያለፉትን ኹለት እና ሦስት ዓመታት እንኳን ብንመለከት፣ ሣቃችንን በሚሸፍኑ እንባዎች፣ ደስታችንን በሚያጨልሙ መከራዎች፣ ዕድገት/ልማታችንን በሚያጠልሹ ግጭቶች እና ተስፋችንን በሚነጥቁ መቆራቆሶች ውስጥ በሠቀቀን የተጓዝንባቸውን መሪር ቀናት ለአብነት ማንሣት እንችላለን፡፡

በእነዚህ አስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥ፣ በአስቸጋሪ ጎዳና ስንደነቃቀፍ፣ የዚህ ክልል ሕዝቦች ከሌሎች የአገራችን ወገኖቻቸው ጋራ በመኾን የኢትዮጵያችን ደግ ቀን እንዲነጋ፣ በሐሳብ፣ በምክር፣ በስክነት፣ በዱዓ/በጸሎት፣ ከመሪዎቻቸውም ጋራ በማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ሰላምን የማበጀት ስልት ለከፈሉት መሥዋዕት እና ላሳዩት አገራዊ አንድነት ያለኝን የተለየ ክብር እና አድናቆት ከተለየ አክብሮት እና ፍቅር ጋራ ለገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕዝቦች፣ እንደ ሌሎች የአገራችን ሕዝቦች ሁሉ ለኢትዮጵያ ገናናነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን ጠብቃ እንድትቆይ፣ የክልሉ ሕዝቦች በምዕራቡ የአገራችን ክፍል ዘብ ኾነው ለአሁኑ ትውልድ ነጻነቷ የተጠበቀ አገርን እንዳቆዩልን ሁሉ፣ ለወደፊቱም የኢትዮጵያ ሉአላዊነት እንዳይደፈር በከፍተኛ የአገር ፍቅር ስሜት አለኝታ እንደምትኾኑ አልጠራጠርም፡፡ ዛሬ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ማለት

የሕዳሴያችን ሰገነት፣ የነገ ተስፋችን ቤት፣ የኅብረታችን መሠረት፣ የምንናፍቀው አስተርእዮዋችን ካስማ እና የከፍታችንም ማማ ናት፡፡

## ክቡራት እና ክቡራን፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ በተፈጥሮ ሀብት ክምችት የበለጸገ ነው። ወርቅን ጨምሮ ልዩ ልዩ ማዕድናት፣ ጥቅጥቅ የተፈጥሮ ደኖች፣ የዱር ሙጫ እና ዕጣን፣ የጎማ ዛፍ፣ የጓሮ አትክልት እና ፍራፍሬ በተለይም ማንጎ፣ ከዓመት ዓመት የሚፈሱ ጅረቶች፣ እንደ በለስ - ዴዴሳ - ሆሃ - ካማሽ - ሽርቆሌ የመሳሰሉ ታላላቅ የዓባይ ገባር ወንዞች ከክልሉ የተፈጥሮ ሀብቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። የክልሉ ሕዝብ በተቸረው የተፈጥሮ ሀብቱ ተጠቅሞ ራሱንና ክልሉን እንዲጠቅም ከማድረግ ረገድ፣ አሁንም ሰፊ ሥራ እንደሚጠብቀን ብንረዳም፣ የዚህ ታላቅ ሕዝብ እና ክልል የተፈጥሮ በረከት ሀብታምነት ግን አያነጋግርም፡፡

በቀርከሃ ሀብትም ቢኾን፣ ክልሉ እንደ አገር ብቻ ሳይኾን እንደ አፍሪካ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀስ እጅግ ከፍተኛ ክምችት ያለበት ነው፡፡ ክልሉ፣ ለእርሻ እና ለእንስሳት እርባታ የተመቸ ቢኾንም፣ ይህን ሀብት በአግባቡ መጠቀም ባለመቻል ግን፣ የክልሉ ሕዝብ የሚጠበቀውን ያህል ተጠቃሚ አልኾነም፡፡ ይህን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት፣ በአግባቡ በቴክኖሎጂ ታግዞ በመጠቀም ለብዙዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር የተሠራው ሥራ እምብዛም ነው፡፡

የአሶሳ ከተማ ከተቆረቆረች፣ ዐሥርታት ዕድሜዎችን ብታስቆጥርም፣ የዕድገቷ እንቅስቃሴ የጀመረው ዘግይቶ ነው። በክልሉ የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት አቀናጅቶና ሕዝብን አስተባብሮ ቢሠራበት የአሶሳን ከተማ እና በአጠቃላይ ክልሉን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማሳደግ እንደሚቻል አልጠራጠርም፡፡ በአንድ አገር እና ሕዝብ ውስጥ ምንም ያህል የተፈጥሮ ጸጋ ቢኖርና አጀብ ቢያሰኝም ሕዝብ እስካልተጠቀመበትና በሕይወቱ ውስጥ አንዳች ትርጉም ያለው በረከት እስካላስገኘ ድረስ፣ ኹለንተናዊ ዋጋው ምንም ካለ መኖር ጋራ ብዙም የሚለያይ አይደለም፡፡

የውኃ ማማ እየተባልን ከመጠማት፣ የለም አፈር ባለቤት እየተባልን ስንዴ እና በቆሎ ለመሸመት ማዳበርያ አንጠልጥለን ካናዳ እና አውሮፓ ተሻግረን ከመሸመት፣ የ13 ወር ጸጋ ባለቤቶች ኾነን ሳለን በምግብ እጥረት ከመታወቅ እና ከመጠራት እስካልተላቀቅን ድረስ፣ የተፈጥሮ በረከቶቻችን ሁሉ ስም ከመኾን ባለፈ እምብዛም አይፈይዱም፡፡ በመኾኑም፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድም - እኅቶቹ ጋራ በመኾን በተለመደው ታታሪነቱ እና ሰላማዊ ማንነቱ ተከብክቦ ታሪክ በመቀየር እንደገና ወደ ታላቅነቷ የተመለሰች ኢትዮጵያን እንደሚፈጥር እምነቴ የጸና ነው፡፡

## ውድ የአገሬ ሕዝቦች፤

አገራችን ዛሬ የምትራመድበት የሰላም፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እና የልማት ጉዞ ግቦቻችን፣ የሁላችንንም ርብርብ የሚጠይቁና ያለ መሥዋዕትነት ሊሳኩ እንደማይችሉ ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ ችግሮቻችን ዘርፈ ብዙ ቢኾኑም፣ የችግሮቻችን መፍቻ ቁልፎችም ያንኑ ያህል ብዙ ናቸው፤ የተደቀኑብን ፈተናዎች ውስብስብ ቢኾኑም፣ እነኚህን እክሎቻችንን የሚያሻግሩን ኢትየጵያዊ ብልሃቶቻችንም ከመወሳሰብ የሚሻገሩ ብርቱ ናቸው፡፡ ከፊታችን የሚጠብቀን ሥራ ከባድ ቢኾንም፣ ኢትዮጵያዊ የአርበኝነት እና የትጋት ስንቃችን ግን ይበልጥ ኀያል ነው፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፣ በጉዳታቸው ለአገር ነጻነት እና ህልውና ዋጋ መክፈልን በተግባር ያስተማሩ ትጉሃን ልጆች ነን። ይህች አገር፣ መሥዋዕትነትን እንደ ሽልማት የሚሻሙና ለአገር ሲባል ቤዛ መኾንን እንደ ምርጫ ሳይኾን እንደ ግዴታ የሚቀበሉ አእላፍ ጀግኖች መፍለቂያ ነች።

ዛሬ አምረውና ደምቀው እንድንጎበኛቸው ጉጉትን የሚያጭሩ አገሮች የተገነቡት፣ መሥዋዕትን ለመክፈል ቆርጦ በተነሣና በተግባርም ይህንኑ በአረጋገጠ ትውልድ መቃብር ላይ ነው፡፡ እኛም ዛሬ ላይ የምንኮራባቸው ደግ ነገሮቻችን በሙሉ በአጋጣሚ የተበረከቱ ሳይኾኑ፣ ከዛሬ አሻግሮ ነገን በመመልከት፣ ከራስ ይልቅ ወገንን በማስቀደምና አገርን በማየት ድንቅ ዕሴት የተገኙ በረከቶች ናቸው፡፡ እናም፣ አገር በመሰጠት እና በመታገል እንጂ በመጠቀም እና በመከፈል ብቻ ስለማትገነባ፣ ለሠራነው ሥራ ቀዳሚው

ክፍያችንና ዋጋ ደመወዛችን፣ የዚህች አገር የስኬት ልክ እና የኀሊናችንም የእርካታ ጥግ እንዲኾን በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን ለማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡

ከዚህ ሲሻገር ግን፣ በለፋንበት ልክ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ የምንኾንባትን የበለጸገች ኢትዮጵያ በጋራ እንድንገነባ በአክብሮት እጠይቃቹሃለኹ፡፡ በመኾኑም፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያውያንን ይዘን ከኢትዮጵያውያን ጋራ እጅ ለእጅ ብቻ ሳይኾን፣ ልብ ለልብም ተያይዘን የማንሻገረው ችግር እና የማንፈታው የተግዳሮት ቁልፍ በፍጹም አይኖርም፡፡

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደሚገነዘበው፣ የአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ ጠንካራ ኅብረ ብሔራዊ ክንዳቸውን በድህነት ላይ በማንሣት በስኬት ለመራመድ አቅደው ከተንቀሳቀሱበት ፕሮጀክቶች አንዱና ዋናው የሚገኘው በዚሁ ክልል ውስጥ ነው፡፡ መላ ኢትዮጵያውያንን፣ በአንድ የልማት መንፈስ ላስተሳሰረው፣ ለአገራችን ብልጽግና እና ሕዳሴ መሠረት ለኾነው፣ገጣሚው እንዳለውም አትዮጵያውያንን ስለ ማስተሳሰር ከደም ስለ ወፈረው እና ገና ከጅምሩ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የብርሃን ዘመን መገለጫ ተደርጎ ታይቶ የአንድነታችን መከሠቻ በኾነው ወንዛችን ላይ ለሚገነባው የሕዳሴ ግድባችን፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሚናው ከፍተኛ ቢኾንም፣ የዚህ ክልል ሕዝብ፣ የሕዳሴው ግድብ ግንባታ በስኬት ይካሔድ ዘንድ፣ ከመሠረት ድንጋይ መጣል አንሥቶ አሁን እስከ ደረሰበት ደረጃ ድረስ እያበረከተ ያለው አስተዋፅኦ እና እየከፈለ ያለው መሥዋዕት፣ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ልዩ እና ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት እንደሚኖር ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

በዚህም መሠረት፣ ለለፋችሁት እና ወደፊትም ለምትለፉት ልፋት፣ የሕዳሴያችን መሠረት ለኾነው ለዚህ ፕሮጀክታችን እውን መኾን ላጋባችሁብን ወደር የለሽ ትጋት እና በሁሉም ረገድ እናንተ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን 100 ሚሊዮን ሕዝብ ወክላችሁ በረሓውን ገነት፣ ዕቅድ-የሕዳሴ ተስፋችንንም እውነት ለማድረግ እያደረጋችሁ ላለው ትግል እና በጋራ እያስመዘገባችሁት ላለው ድል ያለኝን አድናቆት በኢፌዴሪ መንግሥት፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ እና በራሴ ስም ልገለጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

## ክቡራት እና ክቡራን፤

ንግግሬን ከማጠቃለሌ በፊት፣ በዚህ ክልል የሚስተዋሉ ጎጂ ልማዶችን ላንሣ፡፡ የዚህ ክልል ሕዝቦች፣ ሕብር ያለው ውዝዋዜያችሁ እና የሚያምረው ኪነታችሁ በብዙዎች ዘንድ ይወደዳሉ፡፡ መልካም ባህል፣ መልካም ወግ እና ልማድ እንዳሏችሁ ሁሉ ጎጂ የኾኑ ልምዶችም በክልሉ ይታያሉ፡፡ ጥሩ ጥሩውን ለቀጣዩ ትውልድ ለማሸጋገር እንደምትተጉት ሁሉ፣ ጎጂ ልማዶችን ለማስወገድ ጠንክራችሁ እንድትሠሩ ከትሕትና ጋራ እጠይቃችኋለሁ፡፡ ይህን ማድረግም፣ ማንም አምጥቶ የሚጭንባችሁ እና በእኔ አውቅልህ ስሜት የሚያስጥላችሁ ሳይኾን፣ በተለመደው መልካሙን የማጽናትና ጎጂውን የማጥፋት ባህላችሁ ተጠቅማችሁ ለቀጣዩ ትውልድ የሚጠቅመውን ብቻ ቀጣይ እንድታደርጉ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም፣ አገራችን በተያያዘችው የሰላም፣ የልማት እና ዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሒደት ላይ የሚፈጠሩ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለመፍታት፣ በአንድነት ከጎናችን ኾናችኊ ጥንካሬያችንን እንደምትጨምሩት እተማመናለኹ፡፡ ምክንያቱም፣ ውበትም ኾነ ጥንካሬያችን የሚመነጨው፣ ከኢትዮጵያዊ አንድነታችን፣ አንዳችን ከሌላችን በመደመራችን ነው።

**“ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!”**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**አመሰግናለሁ !**

# "እኔ ነኝ አዲሲቷ ኢትዮጵያ" ንግግር

**ግንቦት 11/2010 ዓ.ም.**

ከ ዶክተር ምሕረት ጋር ለሀገራችን ኢትዮጵያ አዲስ ቪዥን፤ አዲስ አተያይ፤ ለአዲስ ትውልድ ያስፈልጋል የሚል ምክክር ስንመካከር፤ ዋናው ሐሳብ የነበረው ኢትዮጵያ 70 በመቶ የሚሆን በዕድሜ አዲስ የሆነ ትውልድ ያላት ሀገር ነች፡፡ በአሮጌ አስተሳሰብ ይህንን ትውልድ መምራት፣ ማሻሻል፣ ማሻገር የማይቻል ነው፡፡ አዲሱ ትውልድ አዲስ አስተሳሰብና አሮጌውን ነገር መጠገን፣ ማሻሻል፣ ማደስ፣ የሚያስችል ብቃት ስላለው፤ የአዲስ እይታን ፓርት ወይም ቪዥን እንድናገር ዕድል ሰጥተውኛል፡፡ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!!

እይታችን መቀየር አለበት። በዚህ ሁኔታ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ራእይ ለማጋራት በተለይ ወጣቶች የዚህን ራእይ ሐሳብ ሰፊ ጊዜ ወስዶ፣ መነጋገር፣ መወያየት፣ መግባባት፣ የሚጠይቅ ቢሆንም፤ ዋና ሐሳቡን በግርድፉ ዛሬ ካካፈልኳችሁ በኋላ ወደፊት በዝርዝር የምናየው ይሆናል።

አዲስ ያሰኘው ምንድነው? ያላችሁ እንደሆነ፤ ኢትዮጵያ አዲስ አይደለችም፤ ጥንታዊት ሀገር ናት፡፡ ሕዝቦቿም አዲስ አይደሉም። መንግሥትም አዲስ አይደለም። ባለው ሰው ላይ አዲስ ሐሳብ የተፈለገበት ዋናው ምክያት ያለውን አሮጌ ለማለት ሳይሆን የሚመጣውን ከነበረው እና ካለው ለማስማማት ነው። የነበረውን አሁን ካለው ደግሞም ከሚመጣው ማስማማት ካልቻልን፤ እኛነታችን ቢቀጥልም በየሄድንበት መታሰር አይቀርልንም።

የማይታሰር ዜጋ፤ የሚከበር ዜጋ ለመፍጠር አዲስ አስተሳሰብ ያስፈልጋል። አዲሱ ሐሳብ "ኢትዮጵያ እኔ ነኝ አንተ ነህ አንቺ ነሽ" የሚል ነው። አንተ ስትታመም፤ ኢትዮጵያን ያማታል። አንተ ስትታሰር ኢትዮጵያ ትታሰራለች። አንተ ስትማር አንቺ ስትማሪ፤ ኢትዮጵያ ትማራለች።

የሚነሳቆል ዜጋ፣ የሚታሰር ዜጋ፣ የሚናቅ ዜጋ ያለው ሀገር የሕዝቦቹ ውጤት ነው እና የተናቀ ከመሆን አይድንም። በነበርንበት ሀገር ጥሩ አቀባበል አድርገውልን፤ «ምን ትፈልጋላችሁ?» ሲሉ ገንዘብ ሳይሆን ዜጎቻችንን ፍቱልን ነው ያልናቸው። የሚገርመው ነገር ግን ዜጎቻችንን ማክበር ስንጀምር፣ ዜጎቻችን ሲፈቱ፣ ያልጠየቅነው ሁሉ ይሰጣል።

አዲስ ሐሳብ የሰው ልጅ በዘመኑ ሁሉ ሲፈልገው፣ ሲደክምለት የነበረ ነው። የሰው ልጅ ምድር ላይ፣ ከምድር በታች፣ ከምድር በላይ ያስሳል። አዲስ ነገር ፍለጋ፣ አዲስ ነገር ለመሞከር፣ የሁላችንም የዕለት ከዕለት ተግባር ነው። በዚያው ልክ የሰው ልጅ አዲስ ነገር ይጠላል፣ ይፈራልም።

ሕዋን ደፍሮ በመንኮራኩር መጓዝ የጀመረ የሰው ልጅ፤ ትንሽ አዲሰ ፊት ሲያይ ባለበት ለመቀጠል ካለው ፍላጎት ሲሸሽ፣ ሲደበቅ፣ ይታያል፡፡ እንደግልም፣ እንደ ማኅበረሰብ። ለዚህ ነው ሰው በባህል ውስጥ፣ በታሪክ ውስጥ፣ በትላንት ውስጥ፣ ተሸብቦ የሚኖረው፡፡ ዋናው ምክንያት አዲስ ነገር ላለመስማት፣ ላለማየት ካለ ፍላጎት ነው።

አዲስ የመፈለግና አዲስ የመቃረን ሐሳብ ያለው የሰው ልጅ፤ እንዴት ነው አስታርቆ በጋራ አሮጌውን ከአዲሱ አስማምቶ የሚሄደው? የሚለውን ሐሳብ ስናይ፤ ለውጥ አይቀሬ መሆኑን አምኖ መቀበል ነው። ለውጥን ማቆም አይቻልም። ስትገቡ የነበረውን ሰዓት እዚያው ላይ ማቆም አይቻልም። አሁን መሽቷል። ስትመጡ የነበረችው ፀሐይ አሁን የለችም፤ ጠልቃለች።

በየጊዜው በሁኔታዎች ሁሉ ለውጥ አለ። በዚያ ለውጥ ውስጥ እንዴት መማር ይቻላል?! እንዴት መቀየር ይቻላል?! ያ ለውጥ አዎንታዊ እንዲሆን ምን ማድረግ ይገባናል? የሚለው ጉዳይ ነው፤ ዋናው ለውጥን ለውጥ የሚያሰኘው። ይሄ ደግሞ ዛሬ ላይ ሆኖ ነገን ከማየት ነው። ዛሬ ላይ ቆሞ ነገን ከማየት ነው።

ዛሬ ላይ ቆሞ ነገን የማሰብ፣ ነገን የማለም ጉልበት ነው። ምክንያቱም አዲስ የከፋም ሊሆን ይችላ። አዲስ ማለት ሁሌ የተሻለ ማለት አይደለም። የከፋ ነገር ሊያመጣ ስለሚችል፤ ምን ብናደርግ ነው መልካም ነገር የምንሠራው? የሚለው ጉዳይ የሚወሰነው ዛሬ ላይ ሆነን ነገን ማየት ስንችል ነው። ያን ደግሞ ልበ ብርሃን መሆን ይጠይቃል። ማስተዋል ይፈልጋል። ስትወጡ መውረድ እንዳለ ማወቅ ያስፈልጋል።

ራእይ ያለው ሰው የሚጓዝበትን መንገድ ብቻ ሳይሆን፤ ፍጻሜውን የሚያይ መሆን አለበት። ሀብት የሚሰበስብ ሰው ለጤናው ግድ የሌለው እንደሆነ፣ ሥልጣን የሚሰበስብ ሰው ለዜጋው ግድ የሌለው እንደሆነ፣ ፍጻሜውን ማየት አይችልም ማለት ነው።

አዲሱ ቪዥን «ኢትዮጵያ አንተ ናት» ብሎ የተነሣበት ምክንያት፤ ሀብታችንን ማወቅ፣ ሀብታችንን ማክበር፣ በሀብታችን መጠቀምና መለወጥ ስለሚያስፈልግ ነው። የነበርኩባቸው ሁለት ሀገራት በጣም ሀብታሞች ናቸው። ነገር ግን ሁለቱ ሀገራት አጠቃላይ "ፖፕሌሽን" ኢትዮጵያ በትምህርት ቤት ካላት ሰው አይበልጥም። 29 ሚሊዮን ግድም ተማሪዎች አሉን፡፡ ሳኡዲ ዐረቢያ እና ዐረብ ኤምሬት እዛው አካባቢ ናቸው። በጣም የሚገርመው ነገር በነዳጅ ሀብት የበለጸጉ ስለሆኑ አሁን እየሠሩበት ያሉት ሥራ ከእነሱ ሀብት የሚቃረን ነው። ሀብታቸውን የሚያፈሱት፣ ምርምር የሚያካሂዱት፣ አዲስ ኢነርጂ ፍለጋ ነው። የሶላር ኢነርጂን ለመጠቀም፣ የዊንድ ኢነርጂን ለመጠቀም ብዙ ሀብት ያፈስሳሉ፤ ይመራመራሉ። "ለምን?" አልናቸው። "ነዳጅ አባቶቻችን ለእኛ የሰጡን ነው። በእሱ ኖረን እንደምታዩት በልጽገናል፤ ለልጆቻችን የሚመጣው ዓለም ፈተናው ከባድ ስለሆነ ለእነሱ የምናወርሳቸው እና የምናዘጋጃቸው የውድድር ዐውድ ሌላው ዓለም ከሚሮጥበት ጋር የሚስተካከል ስለሆነ ነው።" አሉን።

ያላቸውን የሚያውቁ፣ ያላቸውንም አጥብቀው የያዙ እናም የሚጠቀሙ ናቸው። እንደዚህ ያሉ ሀገራት ለረዥም ዘመናት መዝለቅ ይችላሉ። መዝለቅ የማይችሉ ሀገራት ያላቸውን የማያውቁ፣ የሌላቸውን ሲያልሙ የሚኖሩ ናቸው።

ኢትዮጵያ ያላት የሚያምር ሜዳ፣ ሸንተረር አይደለም። ወንዝ አይደለም። ወርቅ አይደለም። ነዳጅ አይደለም። የኢትዮጵያ ትልቁ ሀብት ዜጎች ናቸው።

ድንግል መሬታችን ስንል ከርመናል። መሬታችን ድንግል የሆነችው ለእኛ ነው። ተደፍራለች ። መሬታችንን ከሰማይ ላይ ሆነው፤ የት ጋ ምን እንዳለን? እነሱ ያውቃሉ፡፡ እኛ ነን የማናውቀው። ሳይንስ የዕውቀት ጥግ ያመጣው አንዱ ጸጋ፤ ከሰማይ ላይ ሆኖ በከርሰ ምድር ያለን ሀብት በተወሰነ ደረጃ ማወቅ የሚያስችል ብቃት ነው። እኛ ስለማናውቅ ድንግል እንላለን። እነሱ ሰለሚያወቁ «የት ጋ ኢንቨስት እናድርግ?» ይላሉ። አሁን ኢትዮጵያ ያልተደፈረው የሰው ልጅ ጭንቅላት ብቻ ነው። ያንን ጭንቅላት ስናምን፣ ስናከብር፣ ስንጠቀምበት፣ ኢትዮጵያ ትለወጣለች። ምክንያቱም 100 ሚሊዮን ጭንቅላት አለን። በምሥራቅ አፍሪካ ያሉ ሀገራት፣ በመካከለኛው ምሥራቅ ያሉ ሀገራት ተደምረው 100 ሚሊየን ጭንቅላት የላቸውም።

ያለንን ከአራከስነው፣ ያለንን እንዳላወቅን ከሆንን፣ ያ የምናስበው ህልም ብቻ ነው የሚሆነው። ያለንን ስናከብር፣ ስንጠቀምበት፣ ስንደመር፣ ምን ያህል ክብር እንዳለን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ማየት ችለናል።

የሳኡዲ ዐረቢያ መንግሥት በብዙ ነገር መስመር ተሻግሮ ሊያግዘን ወስኗል። ያ የሆነበት ዋና ምክንያት ኢትዮጵያውያን አንድ እየሆናችሁ ነው የሚል ነው። አንድ መሆናችን ለእኛ ኩራት፣ ለእኛ ክብር፣ ሌላ ቦታ ደግሞ አንድ ባለመሆናችን የሚጎዱ ዜጎቻችን ታላቅ ሀገር ያጣነውን ትልቁን ሞራል የሚመልስ ስለሆነ፤ አንድነታችንን መጠበቅና ሰዋችንን ማክበር የዕለት ተዕለት ሥራችን ሊሆን ይገባል።

ይህ እንዲሆን ባለራእይ መሪዎች ያስፈልጋሉ። ራእይ ያላቸው፣ የሚጓዙበትን መንገድና ፍጻሜያቸውን የሚያውቁ መሪዎች ያስፈልጉናል። መሪ ተከታዩን የሚፈጥረው በውስጡ በተፈጠረ የራእይ ብርሃን ነው። በውስጡ ያለውን ብርሃን እየገለጠ፣ ጨለማ እየገፈፈ፣ ተከታዩን ማስከተል ሲችል ነው። ራእይ የሌለው መሪ ነጂ መሆን ይችላል፤ እንጂ መሪ መሆን አይችልም።

አንድን ሕዝብ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚነዳ፣ ፍጻሜውን የማያውቅ፣ ከንቱ ተጓዥ ነው የሚሆነው። ባለራእይ መሆን የሚያስፈልገን መንገዳችንን እንድንወስን፣ ፍጻሜያችንንም እንድንወስን ጭምር ስለሆነ መሪ ራእይ ያስፈልገዋል። ግን ያ መሪ ማነው? መሪ ማነው? ለኢትዮጵያ መሪ የምንለው ማንን ነው? የሚለውን ጉዳይ ማወቅ ያስፈልጋል።

በሀገራችን መሪ የሚባለው የፖለቲካ መሪ ብቻ ነው። የፖለቲካ መሪዎች የሚመሩ የሚመሩም መሪዎች ናቸው። የፖለቲካ መሪዎች ወይም የፖሊሲ መሪዎች መምራትን እጂ መመራትን የማያውቁ ከሆነ ራእይ የላቸውም ማለት ነው። መመራት በማን? መምራት ማንን? የሚለውን ደግሞ ትንሽ ማየት ያስፈልጋል። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ድልብ ማኅበራዊ ሀብት ያለው ሀገር፤ የሞራል መሪዎች አሉት። የሞራል መሪዎቻችን የሀይማኖት አባቶችና እናቶቻችን ናቸው። በሞራል እነሱን ልንመራ ብናስብ ከንቱ ኪሳራ ነው። በሞራል እነሱ እየመሩን እነሱን ብንመራ ግን ፍጻሜያችን ያማረ ይሆናል። ስኬትም እናመጣለን።

የመረጃ መሪ የሚዲያ ማኅበረሰብ ነው። በአዳዲስ መረጃ መምራት ብናስብ፤ ሚዲያን ማሳደግና መጠቀም የማንችል ከሆነ አዲስ ሐሳብ የሌለን ነጂዎች እንጂ መሪዎች መሆን አንችልም። የዕውቀት መሪዎች መምህራን ምሁራን ተመራማሪዎች ናቸው። ምሁራን ተመራማሪዎች የዕውቀት መሪዎች እንደሆኑ ያላመነ መሪ ቅድም እንዳልኩት፤ ሕዝቡን በደመነፍስ ይዞ ይጓዝ እንደሆነ እንጂ ያለንን ለይቶ፣ የሌለንን ደግሞ መሙያ መንገድ አሳይቶ፣ ማሻገር አይችልም። የሐሳብ መሪዎች (የአይዲያ መሪዎች)፣ የዕውቀት መሪዎች እነማን እንደሆኑ ለይቶ ማወቅ እና በወጉ መጠቀም የሚችል መሪ ሲሆን፤ መመራትን ያውቃል፣ መምራትም ይሆንለታል ማለት ነው።

የጥበብና የፈጠራ መሪዎች አርቲስቶች ናቸው። የጋሽ አበራን ሚና (ሮል) ለመውሰድ ብሞክር ሙከራ ሆኖ ይቀራል አይሳካልኝም። ያ ጥበብ የእሱ ስለሆነ፤ እሱ በጥበብ በፈጠራ፣ በጥበብ በአርት ሲመራ መመራት፣ በፖሊሲ የምመራ ስሆን የተሟላ አመራር ማረጋገጥ ይቻላል ማለት ነው።

የሐሳብ መሪዎች ፈላስፋዎች ናቸው። ሊቆች ናቸው። ሐሳብን ፈላስፋዎች ሲያፈልቁ፤ ያ ስፍራ፣ ያ ድርሻ፣ የእነሱ መሆኑን አውቆ የሚመራ መሪ ነጂ ሳይሆን አሻጋሪ ይሆናል። ሐሳብ ማፍለቅ ያለብኝ፣ መፈላሰፍ ያለብኝ፣ እኔ ነኝ፤ ያለ እንደሆነ ግን ያው ነጂ ሆኖ ይቀራል። የጤና መሪዎች ሀኪሞች ናቸው። ቤተሰብ መሪዎች ወላጆች ናቸው። የሰላም መሪዎች ፖሊሶች ወታደሮች ናቸው። የፍትሕ መሪዎች ዳኞች፣ የሕግ ባለሙያዎች ናቸው።

በእነዚህ የሚመራና እነዚህን የሚመራ መሪ ያስፈልጋል። ያ የፖሊሲ መሪ ይባላል። የሕግ መሪዎች የፖሊሲ መሪውን በሕግ መምራት ካልቻሉ፣ መሪው ከሕግ በላይ ከሆነ፣ መንዳት እንጂ መምራት አይችልም። በሕግ የሚገዛ፣ በሕግ የሚዳኝ፣ በሕግ ስር መሆኑን የሚያውቅ መሪ መሆን ያስፈልጋል፤ ይገባልም። ታዲያ እነዚህ መሪዎች የፍትሕ መሪዎች ፍትሕ ካዛቡ፤ የሰላም መሪዎች ሰላምን ማስጠበቅ ካልቻሉ፤ ቤተሰብ መሪዎች ትውልድን መፍጠር ካልቻሉ፤ የቤተሰብን "ቫልዮ" ማሳየት ካልቻሉ፤ የጤና መሪዎች አሳስተው ወግተው ለዓመታት ሕጻናት ሆስፒታል ላይ እንዲተኙ ማድረግ ከቻሉና ከገደሉ፤ የፖሊሲ መሪዎች እነሱን የሚመራ መፍጠር ካልቻሉ፤ መመራት ስላልቻሉ፣ ነጂ እንጂ መሪ መሆን አይችሉም።

ኢትዮጵያ በሁሉም ረድፍ መሪዎች ያስፈልጓታል። የሚዲያ መሪዎች ሙያቸውን የሚያከብሩ፣ ሥራቸውን የሚያውቁ፣ ለምን እንደሚሠሩ የሚያውቁ፣ እንደ መአዛ ብሩ ሲሆኑ፤ መሪዎች ደግሞ ዛሬ ምን ተመራምራ አምጥታ ይሆን ብለው መአዛን መከተል ሲችሉ፤ ያኔ ተያይዘን መዝለቅ መሻገር ይሆንልናል። ያ መሆን ካልቻለ እኔ በፍጹም መአዛን መተካት አልችልም ። በፍጹም ምሕረትን መተካት አልችልም። ምሕረትም እንደዚሁ። ጥሩ ሐኪም ስለሆነ፤ ጥሩ ጸሐፊ ስለሆነ እኔን መተካት ማሰብ የለበትም።

"ኢትዮጵያ አንተ ናት አንቺ ናት!" የምንለው ብዙ መሪዎች ያሏት፣ የሚያምር ካርታ፣ ውብ ሕገ መንግሥት እና የሚደንቅ ሕገ መንግሥት ያለው ግን የማይኖርበት ሀገር ሳይሆን፤ ኢትዮጵያ የምትኀለው በእያንዳንዱ ዜጋ ልብ ውስጥ ነው። እያንዳንዱ ዜጋ ባንዲራውን፣ ድንበሩን ሀገሩን የሚያከብር ከሆነ፣ የማይሰርቅ ከሆነ፣ የሚተጋ ከሆነ፣ ኢትዮጵያ ማለት በልባችሁ ውስጥ ያለችው፣

በፍቅር የምትቀነቀነው፣ ሲዜምላት ሲዘመርላት የምታስለቅሰው፣ እንጂ ካርታ ካርታዋን የምንናገር፣ ዜጋ ዜጋዋን የማንፈልግ አይደለችም።

ኢትዮጵያ አንተ ስትሆን ትናንት ኢትዮጵያ የነበሩትን አንተዎች መዘንጋት ግን መሆን የለበትም። አንተ የተገኘኸው በትናንት ውስጥ ነው። አንቺ የተገኘሽው በትናንት ውስጥ ነው። አንተና እኔ የምንገኘው ደግሞም በልጆቻችን በነገ ውስጥ ነው። ያ የሰው ልጆች የሕይወት ቅብብሎሽ ሳይጣረስ፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያ ሲደመር፣ ሲሰናሰል፣ መቶ ሚሊዮን ትልቅ ኢትዮጵያ ትፈጠራለች ማለት ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ ታሪክ ጠገብ፣ እንዲሁም ወጣት ሀገር ነች። ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ኢትዮጵያውያን በግርድፉ ከ45 ፐርሰንት አያንሱም። የሚደንቅ አዲስ ኃይል እየተፈጠረ ያለበት ሀገር ነው። ይሁን እና ይህ ወጣት እንጀራ ፍለጋ በልቡ የያዛትን ኢትዮጵያ እየሸሸ በየበረሐው፣ በየሀገሩ የሚታሰር፣ የሚንሳቀል፣ ጠያቂ የሌለው፣ የተበተነ ሆኗል። ይህን መበተን መታደግ የሚቻለው በልባችን የሣልናት ኢትዮጵያ የምትሰጠን ብቻ ሳይሆን ከእኛ የምትፈልገውንም ማወቅ ስንችል ነው። ከእኛ የምትፈልገው ባለሥልጣኖች ቀና አገልጋይ ሲሆኑ እና ሌባ መሆንን ሲተዉ ነው።

ወጣቶች በአንድ ጊዜ፣ በአንድ የምርጫ ጣቢያ፣ አንድ መሪ አስባችሁ፣ የፖሊሲ መሪ ያ መሪ መሆኑን አምናችሁ፣ ማድመጥና መመራትን ስታውቁበት ነው። የሥራ ክፍፍላችንን ካላወቅን ቅድም እንዳነሣሁት ካልተደማመጥን፣ ካልተመራራን ፍላጎት ይኖራል፣ ሐሳብ ይኖራል፣ ግን አይከወንም። መከወን እንድንችል መደማማጥ፣ በንጹሕ ልብ በመደመር መትጋት፣ አስፈላጊ መሆኑን አምነን ከሠራን አሁን የጀመርነው ክብር፣ አሁን ጀመርነው ኢትዮጵያዊ ስሜት፣ ይበለጽጋል፡፡ ደግሞም ሊያቆመው የሚችል ኃይል የለም።

ወጣት ብቻ ሳይሆን ሰፊ ሕጻናት ያሉበት ሀገር ስለሆነ፤ እያንዳንዱ ትልቅ ሰው ከሕጻኑ ውስጥ እንደሚወጣ አምኖ፤ ሕጻናት የሚውሉበት፣ የሚጫወቱበት፣ የሚቦርቁበት ምቹ ቦታ መዘጋጀት አለበት፡፡ ለሕጻናት ተብለው የሚያደምጡት ሚዲያም በሞል ውስጥ፣ በእንደዚህ ዓይነት ስፍራ እየታሰበ የማይሠራ ከሆነ፤ ሕጻናት ሳይቦርቁ ወጣት ይሆኑና ወጣት ከሆኑ በኋላ ከትኩስ ጉልበት ጋር በዲንጋይ ይቦርቃሉ። ወጣቶቻችን መልካም ወጣት እንዲሆኑ ሕጻናት ሳሉ ማድረግ የሚገባንን ለማድረግ በሐላፊነት ስሜት ሁላችንም ልንሠራ ይገባል፤

ያስፈልጋል። ያ ካልሆነ የዛሬው ሕጻን ነገ ጎረምሳ ይሆንና ዛሬ የረሳነውን ፓርት በጉልበት ይሞላዋል። ቢሞላውም ግን የተሠራውን እያፈረሰ ማለት ነው። ያ እንዳይሆን ሕጻን ተኮር ሥራ በሚዲያዎቻችን፣ በመዋያ ቦታዎቻችን፣ በእንደዚህ ቦታ ጭምር ለሕጻናትም የሚገባቸውን ክብርና ቦታ መስጠት ያስፈልጋል።

በትምህርት በኩል እየተሠራ ያለው ሥራ ለሌሎች ሀገራት ስንናገር ይደነቃሉ። በጣም ሰፊ ኢንቨስትመንት አለ። ነገር ግን ብዛት (ኳንቲቲ) በምንም መመዘኛ ጥራትን (ኳሊቲን) መተካት አይችልም። ሁለቱን አስታርቆ መሄድ የሚችል የትምህርት ሥርዓት ዜጎች የመፍጠሪያ መንገድ ከምንጊዜውም በላይ ለእኛ ያስፈልገናል። የሚመረቁ ግን የማይመርቁ ሳይሆኑ፤ የሚመረቁ ደግሞም አስተምረው የሚያስመርቁ ዜጎች መፍጠር ከሁሉም ትምህርት ቤቶች መምህራን የሚጠበቅ ትልቅ ተልእኮ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

መምህራን በወጣቶች ላይ ደግሞም በሕጻናት ላይ የምትሠሩት ሥራ ነገን የሚፈጥር ታላቅ ሙያ፣ የተከበረ ሙያ፣ መምህርነት መሆኑን አውቃችሁ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የተሳካለት ሙያ መምህርነት መሆኑን አውቃችሁ፤ እንዲሆን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። እስከአሁን በኢትዮጵያ ውስጥ፣ በክልሎችም፣ በፌደራል መንግሥትም ትላልቅ ሐላፊነት ቦታ መያዝ የቻሉ ሰዎች መምህራን ናቸው። መጀመሪያ መምህርነትን ሲመርጥ ሰው፤ ሐኪም መሆን ከመምህርነት የሚሻል አድርጎ ያስባል። ሐኪም መሆን መሻቱ ካለ ጥሪው ከሆነ አላስፈላጊ ነው። ከመምህርነት ግን አይሻልም። መምህር ነውና ሐኪም የሚፈጥረው። መምህር የተከበረ መሆኑን፣ ጋዋኑን የሚያከብር መሆኑን ማሳየት እንዲችል ሁሉም በተለያየ ሐላፊነት ላይ የፖሊሲ አመራር፣ የሚዲያ አመራር፣ ቅድም ያነሣኋቸው የመምራት ዘርፎች በሙሉ አልፎ አልፎ፤ ፐብሊክ ሌክቸር መስጠት እና የመንግሥት ትምህርት ቤቶች መጎብኘት መልመድ ያስፈልገናል።

ያንን ማድረግ ስንችል ሕጻናት መሆን የሚፈልጉትን እያወቁ እንዲያድጉ ስለሚያስችል፤ ሚኒስትሮች፣ የከተማ ከንቲባዎች፣ የክልል አመራሮች በዓመት ሁለት ቀን፣ በጣም ካልቻላችሁ አንድ ቀን በአካባቢያችሁ በሚገኝ ሙዓለ ሕጻናት፣ አንደኛ ደረጃ፣ ሆለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሄድ ሌላው ቢቀር የሕይወት ጉዞአችሁን ብትናገሩ የሚቀርላቸው ነገር ይኖራል።

በዚህ ዓመት በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ጎልድ ተመራቂዎች በሙሉ የአንድ ሳምንት ቆይታ ይኖራቸዋል፤ ከእኛ ጋራ። ይሄ አዲስ ፕሮጀክት ነው። ጎልድ ተመራቂዎች ከተመረቁ በኋላ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቢሮ፣ የፕሬዚዳንቱን ቢሮ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቢሮ፣ የፓርላማን መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ አፍሪካ ኅብረትን፣ በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (ኢሲኤ)ን እንዲሁም አንዳንድ የልማት ቦታዎችን፤ እንደ ኢንደስትሪያል ፓርክ ጨምሮ እንዲጎበኙና እንዲወያዩ ይደረጋል፡፡

ዘንድሮ አዲስ ስለሆነ ምን ያህል እንደሚሳካልን ባላውቅም፤ አንድ ሳምንት መቆየት ብቻ ሳይሆን በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ በሚዘጋጅ ስኮላርሺፕ ቀጣይ ትምህርት በምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲማሩ ይደረጋል።

የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች፣ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በጣም ዕድለኞች ናችሁ። ዘንድሮ በወርቅ የሚመረቁ ይሄ ዕድል አልነበራቸውም። አሁን በርትታችሁ ከሠራችሁ እና በሚቀጥለው ዓመት ከሁለት ዓመት በኋላ የወርቅ ምሩቅ ሆናችሁ መጨረስ ከቻላችሁ፤ በዓለም ላይ በምትመኟቸው ዩኒቨርሲቲዎች ድኅረ ምረቃ እንደምትማሩ አስባችሁ፣ ለመመረቅ ጋዋን ለብሶ ፎቶ ለመነሣት ሳይሆን ለሚቀጥለው ትምህርትና ምርቃት ራሳችሁን እንድታዘጋጁ በዚሁ አጋጣሚ መልእክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

ሁለተኛው ሐሳብ የወርቅ ተመራቂዎች በወርቅ መመረቅ ያልቻሉ የኔ ቢጤዎች እንዴት ብለው ቤተ መንግሥት እንደገቡ፣ ቤተ መንግሥት የማንም ህልመኛ ግለሰብ መግቢያ እንጂ የተለዩ ሰዎች ብቻ ቦታ እንዳልሆነ እንዲያውቁና እንዲመኙም ጭምር ነው። ስትመጡ በሚኖረን የውይይት ቆይታ እንድታጫውቱን የምንፈልገው ሀይ ስኩል የገጠማችሁን የልጅነት ጊዜ፣ የነበራችሁን ህልም፣ ነገ ምን መሆን እንደምታስቡ፣ አንዱ ለአንዱ እየነገረ የምንማማርበት ጊዜ እንዲሆን ነው። እንኳን ደስ አላችሁ ! ቀጣዩ ደግሞ ከፍተኛ ፉክክር ያለበት እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

ስለመምህርነትም በዚህ መልኩ ካነሣሁ በኋላ በመምህርነት ውስጥ፣ በወጣትነት ውስጥ፣ በአመራር ውስጥ፣ በቤተሰብ ውስጥ፣ ያለ አንድ ግዙፍ ማኅበረሰብ አካል ሳልገልጽ ማለፍ አልችልም።

ሴቶች፤ የኢትዮጵያ ሴት ያልተሸከመችው ጉድ የለም። የኢትዮጵያ ሴቶች በሆድ ፅንስ ይሸከማሉ፤ በጀርባቸው ሕጻን ያዝላሉ፤ በትከሻቸው የኔ ብጤ ሰነፍ ባሎቻቸውን ይሸከማሉ። ቤተሰብ ተሸክመው የሚያሻግሩ ሴቶች የሚገባቸውን ክብር ሰጥተን መያዝ ካልቻልን ቅድም እንዳልኩት ኢትዮጵያ አልገባችንም ማለት ነው።

"ኢትዮጵያ አንተ ነህ! አንቺ ነሽ !" ካልን በኋላ ኢትዮጵያን ተሸክሞ የሚሄደውን እያናናቅን እና ሳናከብር ኢትዮጵያ የምትባለው በድንበር ብቻ ከሆነ፣ በመሬት ብቻ ከሆነ፣ ክብር የለም ማለት ነው። የኢትዮጵያ ሴቶች በሀገራቸው፣ በሰፈራቸው፣ በቤተሰባቸውና በሥራቸው የሚያገኙት ክብርና እኩልነት የሀገሪቱ ዋነኛ የሥልጣኔ መገለጫ መሆን አለበት። ሴትን የሚንቅና የሚያንገላታ ሕዝብ ያልሠለጠነ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም የማይሠለጥን ሕዝብ ነው። ሥልጣኔ የተሸከመህን ማክበር ነውና ወንዶች ከዛሬ ጀምሮ በምትሄዱበት ስፍራ ሁሉ ታክሲም ሰልፍ ቢሆን ሴቶች ማስቀደም ልማድ ይሁን።

እንዲሁ ዲያስፖራን በዚህ አጋጣሚ ትንሽ ነገር ሳልል ማለፍ አልፈልግም። አንዳንድ ዕድለኛ ሀገር ዲያስፖራዎች የፈረሰ ሀገራቸውን መገንባት ችለዋል። የዛሬ 70 ዓመት እስራኤል አልነበረችም። እስራኤልን የገነባው ዲያስፖራ ነው። እስራኤል ብቻ ሳትሆን ህንድ፣ ፓኪስታንና በሩቅ ምሥራቅ ያሉ ሀገራት ዲያስፖራው በእውቀት፣ በመረጃ፣ በገንዘብ ከፍተኛ ድጋፍ አድርጎ ቀይሯቸዋል። ወደኛ ስንመለስ ዲያስፖራዎች የወጡበት መንገድ አንድም ችግር፣ አልያም መገፋት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከኢትዮጵያውያን ዲያስፖራ በላይ ኢትዮጵያ ማለት አንቺ ወይም አንተ መሆኑን የሚገነዘብ ሰው የለም። ምክንያቱም በዋሽንግተን መንገድ ላይ ሆነው መርካቶና ሜክሲኮ ሳይሉ ስለማይውሉ። ዲያስፖራዎችን ቤት ገንብተን፣ መኪና ገዝተን፣ አስፋልት አንጥፈን ለመቀበል ዛሬ ኢትዮጵያ አትችልም። ነገር ግን ደረታችሁን ነፍታችሁ የምትሄዱበት፣ የምትወደዱበት፣ እንደ ዜጋ የምትታዩበትና የምትከበሩበት ሀገር አላችሁ፡፡ ፍቅር የሚያውቁትና እንግዳ ተቀባይ የሆኑ ሕዝቦቿ ባላቸው ሁሉ እጃቸውን ዘርግተው ቀበሏችኋል።

በውጭ ሀገር ያሉ ዲያስፖራዎች ወደ ሀገራችን ገብተው በኢንዱስትሪያል ፓርክ፣ በሰርቪስ ሴክተር፣ በልምድ፣ በዕውቀት፣ በአነስተኛ ደሞዝ ግን በፍቅር

ቢያገለግሉ፤ አዳዲስ ወጣቶች ደግሞ አሠልጥነን በስፋት ብንልክ፤ የሄደው የተማረ፣ የሚያውቅ፣ ህልም ያለው፣ እንደወጣ የሚቀር ሳይሆን ሲፈልግ የሚመጣ ቢሆን፣ ወጥቶ የቀረውም ቢመለስ፣ በጣም ህልመኛ ነህ አትበሉኝ እና በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ኢትዮጵያን አሁን ካለችበት ሁኔታ መቶ ፐርሰንት መቀየር ይቻላል።

በቆየንባቸው ሁለት ቀን ቆይታ ውስጥ አንድ ስንሆን እና ስንሠራ ለእኛ ችግር የሆኑትን ነገሮች መልቀቅ እንደሚቻል፣ ማምጣት እንደሚቻል አይተናል። ዝርዝሩን ለዲስፕሊን መናገር ቢያስቸግረኝም ስኬታማ የሚባል የዲፕሎማሲ ቆይታ ነበረን። በቆይታችን የጠየቅነው ጥያቄ በሙሉ ከአንድ ጥያቄ በስተቀር ሙሉ ምላሽ አግኝቷል። አንደኛው ጥያቄ ሼህ መሐመድ አላሙዲንን ማምጣት ነበረ። እሳቸውን በሚመለከት ከክራውን ፕሪንሱ ጋር መቶ በመቶ ተግባብተናል። አንድ ሺሕ እስረኞች ሳኡዲ ፈታለች። መፍታት ብቻ ሳይሆን ዛሬ ምሽት ከፊሉ መግባት ይጀምራል።

ሼህ መሐመድ አላሙዲንን በተመለከተ እንደ ሀገር ያለንን ጽኑ አቋም አመላክተናል። እኛ ሀብታምም ደሃም ዜጋ ነው። ሼህ መሐመድ አላሙዲን የማንፈልጋቸው ሰዎች ያለን እንደሆነ ሲመጡ እንነግራቸዋለን እንጂ በባይተዋር ሰዎች ሲታሰሩ የሚጨክን ልብ ኢትዮጵያውያን የላቸውም። ይሄን ጠንካራ አቋማችንን ያወቁት ክራውን ፕሪንሱ አሳዛኝ ቢሆንም ማታ ከሌሊቱ 10 ላይ ተግባብተን ጠዋት ሊሰጡን ከተስማሙ በኋላ ቤተሰቦቻቸው ባደረሱባቸው ከፍተኛ ጫና አሁን ከኛ ጋር ሊመጡ አልቻሉም። ከሳቸው በስተቀር 10 ጥያቄዎች ነበሩን ዘጠኙን መልሰውልን ለአሥረኛው ጥቂት ጊዜ ስጡን ብለዋል። የሼህ አላሙዲን መታሰር በዓለም ላይ ያሉ ዲስፖራዎች ሁሉ አጀንዳ መሆን አለበት። ምክንያቱም ኢትዮጵያ አንተ አንቺ ከሆንሽ አንድ ኢትዮጵያ ታስራለችና ኢትዮጵያ ስትታሰር ዝም ማለት የሚያስችለው ሌላ ኢትዮጵያ መኖር የለበትም። የጀመርነውን ዲፕሎማቲክ ጫና በመቀጠል ጊዜውን መናገር ብቸገርም በቅርብ ጊዜ ወደ ሀገራቸው እንደሚመለሱ እርግጠኛ ሆኜ እናገራለሁ።

በመጨረሻም የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሀገርን መውደድ፣ ለሀገር በጎ ማሰብ፣ ለዚያም መታገል ከሁሉም ዜጎች የሚገባና የሚያስፈልግ ቢሆንም፤

ከእናንተ የሚጠበቀው ሐሳብ በማፍለቅ ኢትዮጵያን በሐሳብ መግዛት ነው። ኢትዮጵያን በሐሳብ መግዛት ማለት እኔን፣ እሷና እሱን ማሸነፍ ማለት ነው። እነሱን ስታሸንፉ በሠለጠነ መንገድ ምርጫ ስናካሂድ፤ ቢሮ የምንቀያየር፣ ሐሳብ የምንቀያየር ግን ደግሞ የማንጠላለፍ እንሆናለን። ቢሮ ለመቀያየር፣ ሐሳብ ለመቀያየር፣ የተሻለ መንገድ ለማመላከት አንዱ አንዱን የሚጠልፍ ከሆነ የምንመኛትን ሳይሆን አሁን ያለችውን ኢትዮጵያን እናስቀጥላለን። ምክንያቱም ቀላሉ ነገር ማሰር ነው። ቀላሉ ነገር መግደል ነው። ቀላሉ ነገር መሳደብ ነው። ከባዱ ነገር የታሰረ መፍታት ነው። ቀላል ነገር ላይ ምርጫው የሚያደርግ ሕዝብ አይሻገርም።

ጠብ፣ ጥላቻና ቂም አያስፈልገንም። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኤምባሲ ውስጥም ይኑር፣ በውጭ ሀገር ላጠፋው ጥፋት ከልብ ይቅር ብሎ መመለስ ያስፈልጋል። ዋነኛው የማሸነፊያው መንገድ ይቅርታና ፍቅር መሆኑን በጽኑ ልናምን ይገባል። የማያምን ሰው ካለ ኢንተርኔት ለቀቅ ሲል ዩ ቲዩብ ላይ ገብቶ አንዲት ጥቁር አሜሪካዊ ልጇን የገደለባት ወጣትና ቤተሰቦች ፍርድ ቤት ሄዳ «መታገዝ አለብህ፤ እንዲታሰርብኝ አልፈልግም ላግዘው እፈልጋለሁ፤ ልጄን የገደለው ቢያመው ነው እንጂ ልጄ የሚታቀፍ እንጂ የሚገደል አይደለም» ብላ ፍርድ ቤቱን በለቅሶ ገዳይን በለቅሶ እንዴት እንዳሸነፈች ማየት ትችላላችሁ። ማሸነፍ ከፈለጋችሁ በፍቅር እናሸንፍ፤ በይቅርታ እናሸንፍ። ይቅርታና ፍቅር ደግሞ ድንበር የለውም። ዘር የለውም። ሀይማኖት የለውም። ፖለቲካ የለውም።

ለየትኛውም ዘር፣ ለየትኛውም የፖለቲካ ግሩፕ፣ አጥፊ ለሆነ ሰው ሁሉ በፍቅር፣ በይቅርታ ካሸነፍን፤ አሁን በጀመርነው አንድነት ከሄድን፤ አትጠራጠሩ ኢትዮጵያ ትልቅና የተከበረች ሀገር ትሆናለች።

**አመሰግናለሁ!**

# የጋምቤላ ሕዝባዊ ጉባኤ ንግግር

**ግንቦት 13/2010 ዓ.ም.**

***ዲርጀት ማለ ዲጎይ ዲጋ ዲጋሞ***

**የተከበራችኹ የጋምቤላ ከተማ እና አካባቢዋ ነዋሪዎች፣**
**የተከበራችኹ የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ**
**ክልላዊ መንግሥት አመራሮች፣**
**የተከበራችኹ የሃይማኖት አባቶች እና የአገር ሽማግሌዎች፣**
**የተከበራችኹ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣**
**ክቡራን እና ክቡራት፤**

ከሁሉ አስቀድሜ የበረሓዋ ገነት በሚለው ቅኔያዊ ቅጽል ስሟ በምትታወቀው እና በረሓነትንና ልምላሜን አስማምታ በያዘችው የደቡብ ምዕራብ ኮከቧ ጋምቤላ ከተማ ተገኝቼ ከእናንተ ጋራ ፊት ለፊት ለመገናኘት እና ሐሳብ ለመለዋወጥ በመቻሌ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ከተለየ አክብሮት እና ፍቅር ጋራ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ ነጻነቷንና ክብሯን ጠብቃ ዘመናትን እንድትጓዝና ዛሬ ከደረሰችበት የሉዓላዊነት ካብ ላይ እንድትገኝ ካስቻሉ የአገራችን ሕዝቦች ውስጥ የበረሓዎቹ ትጉሃን የጋምቤላ ሕዝቦችም ከእነዚያ እንደ አንዶቹ ይቆጠራሉ፡፡

አገራችንን ከወራሪዎች ለመጠበቅ በአደረግናቸው እልክ አስጨራሽ ትግሎች ውስጥ፥ የአኙዋውን፣ የኑዌሩን፣ የማጃንጉን፣ የኮሞውን፣ የኦፖውንና የሌሎች ወንድሞቻቸውን አይተኬ ሚና ሳናነሣ የዚህች አገር ታሪክ ነገራ በፍጹም ሙሉ ሊኾን አይችልም፡፡ በመኾኑም እናንተ የጋምቤላ ሕዝቦች ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችሁ እና እኅቶቻችሁ ጋራ በመኾን የጋራ ቤታችን የኾነችውን ኢትዮጵያን ለመገንባት የከፈላችኹትን መሥዋዕት፤ በደስታ ጊዜ ሕይወት፣ በመከራ ጊዜም የተቋደሳችኹትን ሞት መላ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችኹ በልዩ ፍቅር ይመለከቱታል፡፡ እኔም ከአገራችን የጎን አጥንት ላይ በፍቅር እየኖራችኹ ለድንበራችን መከበር እና ለሉዓላዊነታችን መጠንከር ለምታደርጉት ክቡር ተግባር ያለኝን አድናቆት እና ክብር በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

## የተከበራችሁ የጋምቤላ ከተማ እና አካባቢዋ ነዋሪዎች፣ ክቡራን እና ክቡራት፤

ይህ ኩሩ እና ጀግና ሕዝብ፥ በጥረቱ፣ በደሙ እና በሕይወቱ ባቆማት በዚህች አገር ውስጥ መጠቀም በሚገባው ልክ እና መጠን እንዲጠቀም፤ ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቱ እንዲከበር፤ አስተማማኝ እና ፍትሐዊ ዳኝነት እንዲያገኝ፤ በመሠረተ ልማት ረገድም አስፈላጊውን የመሠረተ ልማት አቅርቦት ማግኘት እንዲችል እና ከብልሹ አስተዳደራዊ ዕንቅፋቶች ነጻ የኾነ ፖለቲካዊ ቁመና ኖሮ በቂ ግልጋሎት እንዲያገኝ ለማስቻል የተሠሩ በርካታ ሥራዎች ቢኖሩም ውጤቱ አመርቂ አልኾነም፡፡ በመኾኑም ዛሬ፣ በዚህች ተወዳጅ ከተማችሁ ስንገናኝና ስለ ቀጣዩ ጊዜያችንም ለመወያየት ስንተያይ፣ ከሠራናቸው ይልቅ ያልሠራናቸውን እልፍ ሥራዎች ከፊታችን አስቀምጠን እንደ ኾነ እንረዳለን፡፡

ወፎች በተጥለግለግ ሰማይዋን የሚዞሯት እና ዓመቱን ሙሉ እየፈሰሱ በፍቅር የሚያለመልሟት በርካታ ወንዞች ያሏት ክልል በብዙ መልካም ነገሮች ትታወቅ ዘንድ የሁላችንም ርብርብ የግድ ያስፈልጋል፡፡ አንድን ክልል በተራዛሚውም አንድን አገር ለማልማት እና የሕዝብንም ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በቂ መሬት፣ የሚሠራ የሰው ሀብት፣ የተፈጥሮ በረከት እና የአመራር ቁርጠኝነት እጅግ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይህም ብቻ ሳይኾን፣ እነዚህን የማቀናጀትና ለአንድ አገራዊ ግብ ብዙውን እንደ አንድ የመቀነት ብቃትም የግድ ያስፈልጋል፡፡

የጋምቤላ ክልል ለመልማት የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ጉዳዮችን በተፈጥሮ በረከት እና በሕዝቦችዋ ጥረት የታደለች ብትኾንም፣ ከሕዝቡ የመልማት ፍላጎት ጋራ የማይመጣጠን ስኬት ላይ ለመገኘታችን ምንም አያነጋግርም፡፡ በመኾኑም፣ የፌዴራሉ መንግሥት ከክልሉ መንግሥት ጋራ በመኾን የሕዝቡን ጥያቄዎች ለመመለስና ጋምቤላ የፈጣን ዕድገት ተምሳሌት ለመኾን የምታደርገውን ጥረት ለማገዝ በቁርጠኝነት እንደሚሠራ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

በኢትዮጵያ ለባሕር ትራንስፖርት የሚውል ብቸኛው ወንዝ ባለቤት ከመኾኗ እና ድንበር ላይም ከመገኘቷ ጋራ ተያይዞ፣ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ አካባቢ፣ የምዕራብ ኢትዮጵያ ዋነኛ የውጭ ንግድ(International trade) ማእከልና ወደብ ኾና የቆየችው ጋምቤላ አሁንም ይህን ታሪኳንና የሀገር ባለውለታነቷን የሚመጥን ልማት ያስፈልጋታል፤ ይገባታልም፡፡ ይህን እውን ለማድረግ ግን የሕዝባችን-የክልሉ አመራሮች-የመንግሥት ሠራተኞች-የባለሀብቶች እና የፌዴራል መንግሥትም ያልተቆጠበ ርብርብ የግድ ያስፈልጋል፡፡ በመኾኑም ሁላችንም እጅ እና እጅ ኾነን ጋምቤላን ለማልማት እና ለሕዝቦችዋም የዘመናት ጥያቄ ኹነኛ መልስ ለማበጀት እንድንተጋ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

## ክቡራን እና ክቡራት፤

ጋምቤላ፣ የዚህች አገር ታሪክ ሲነሣ ስማቸው አብሮ የሚነሣ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆችን ያፈራች ምድር ናት፡፡ ስለ ራሳችን ብቻ ሳይኾን ስለ ሌሎች ክብር እና ልዕልና ዘብ ልንቆም፣ ውቅያኖስ አቋርጠን ኮርያ ልሳነ ምድር ላይ በተገኘንበት በዚያ ታሪካዊ ወቅት ላይ የቃኘው ሻለቃ ድምቀት ከነበሩት ጀግኖች አባቶቻችን ዝርዝር ውስጥ ኡጃንግ ጊሎ የሚል ትልቅ ስም በደማቁ ተጽፏል፡፡ የጋምቤላ ሕዝብ በተለያዩ ጊዜያት ከጨካኞች በትር አምልጦ ሱዳን ለመግባት ይሰደድ የነበረን ብዙ ኢትዮጵያዊ፣ ልቡንና በሩን ከፍቶ በመቀበል የሚበላው ጉርሱን-የሚለብሰው ልብሱን አጋርቶ ክፉውን ቀን ያሻገረ ደግ ሕዝብ ነው፡፡
ይህ ሕዝብ፣ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቹ የሰማይ መስኮቶች ተዘግተውባቸው፣ ምድር በረከትዋን አንጥፋባቸው ችግር በጸናባቸው ጊዜ፣ ያለውን ተካፍሎ በመብላት ድንቅ ባህሉ ታግዞ፣ ብዙዎችን ቤተኛ ያደረገ

ከባህል-ማንነቱም ያዋደደ/ያዋሐደ ጀግና ሕዝብ ነው፡፡ በመኾኑም፣ የዚህ ሕዝብ ልጆች የሥራ ባህላቸው፣ ዘመኑ በሚጠይቀው ቅኝት ተመንድጎ እና ለመለወጥ በሚደረግ ትግል ውስጥ የሚጋረጥ ዕንቅፋት ተጠራርጎ ክልሉ የመልካም አስተዳደር-የልማት-የፍትህ-የሰላም እና የአብሮነት ማሳያ እንዲኾን ለማስቻል መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

በጋምቤላ ክልል ማጃንግ ዞን የሚገኘውና በዩኔስኮ የብዝሐ ሕይወት የዓለም ቅርስነት የተመዘገበው ጥብቅ ደን፣ የአገራችን ብቻ ሳይኾን የምሥራቅ አፍሪካም ሳምባ ከሚባሉ ጥቂት የተፈጥሮ በረከቶች ውስጥ አንዱ እንደ ኾነ መንግሥት በውል ይገነዘባል፡፡ በመኾኑም፣ ይህን ሀብት ጠብቆ የቱሪዝም ምንጭ ከማድረግ ባሻገር ለወጣቶቻችን የገቢ ማግኛ አንድ አማራጭ የሚኾንበትን መንገድ በጥንቃቄ ማየትም ያስፈልጋል፡፡ በዚህ የተፈጥሮ ሀብታችን አንጻር የሚደረግን የትኛውንም የልማት ሥራ፣ ከጋምቤላ እና ከደቡብ ክልል መንግሥታት ጋራ በመኾን በውል የማጤንና ችግሮች ካሉም በአፋጣኝ የማረም ሥራ በአስቸኳይ እንደሚሠራ ላስገነዝባችሁ እወዳለሁ፡፡

እንደ ታታ እና ቢሻን ዋቃ ወይም ካቦ ሐይቅን የመሳሰሉ ውብ እና ታላላቅ የውኃ ገነቶችን የያዘች ክልል ይህን ሀብት ወደ ልማት ለመለወጥ ያላት ዕድል ብዙ ነው፤ በጣም ብዙ፡፡ በመኾኑም፣ የፌዴራሉ መንግሥት ከክልሉ መንግሥት እና ከሌሎች አካላት ጋራ በመተባበር የተሻለች ጋምቤላን ለመፍጠር አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ያደርጋል፡፡

ጋምቤላ፣ የዛሬዋ ብቻ ሳይኾን የነገዋም ኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ የታተመባት ውብ ክልል እንደ መኾኗ መጠን በጋራ እስከ ሠራንና "በአጭር ጊዜ ውስጥ ትልቅ ለውጥ እናመጣለን" ብለን በቁርጠኝነት እስከ ተረባረብን ድረስ በርግጠኝነት፣ ከበረሓው ሰማይ ሥር፣ ነገ ከዛሬ የተሻለች ትኾናለች፡፡ የባሮ እና የጊሎ፤ የአኮቦ እና የጎደሬ እንዲሁም የሌሎች ወንዞች እናት የኾነችው ጋምቤላ ነገን ከዛሬ የተሻለች ለማድረግ እልፍ መንገዶችን መዳፏ ውስጥ ተሸልማለች፡፡ በመኾኑም፣ ያሉንን የመልማት አማራጮች በሙሉ ተጠቅመን የሚታይ ስኬት ማስመዝገብ እንድንችል መንግሥት ከክልሉ ሕዝብ እና አመራር ጋራ በቁርጠኝነት ይሠራል፡፡

ይህ ክልል፣ ከባድመ ምሽጎች በታች ጠላትን ያደባዩ እና ስለ አገር ፍቅር ተግባራዊ ምሳሌ መኾን የቻሉ እንደ ቢል ጀክ ያሉ ጀግኖችን ያፈራ ክልል ነው፡፡ በመኾኑም፣ የተከበራችሁ የጋምቤላ ሕዝቦች ይህን ከባህላችሁ፣ ከታሪካችሁ እና ከማንነታችሁ ጋራ በጥብቅ የተቆራኘ የአይበገሬነት መንፈሳችሁን በልማት፣ በዕድገት እና ድህነትን በመውጋት ላይም እንድትደግሙት በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡ መንግሥትም፣ የጋምቤላ ሕዝብ እና አመራሩ፣ የዚህን ክልል ታላቅነት፣ ሁሉን አቀፍ በኾነ የለውጥ ትሩፋት ለማረጋገጥ በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ አስፈላጊውን ሁሉ እንደሚያደርግ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

ጋምቤላ በጥረታቸው እና በትጋታቸው ራሳቸውንና አገራቸውን በበጎ ያስጠሩ እና ስማቸውንም ከታሪክ መዘገብ ላይ ያለ መናወጥ የተከሉ ብርቅዬ ልጆችን አፍርታለች፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ለታሪኳ እና ለክብሯ በማይመጥን መልኩ ከአፍሪካ ዋንጫ በራቀችበትና እኛም በቁጭት ከተምሰለሰልንበት 31 እልክ አስጨራሽ ዓመታት በኋላ፣ ዋልያዎቹ ከድላችን ሲያስታርቁንና አስተቃቅፈው ሲያስቦርቁን- የጋምቤላውን ፈጣን አጥቂ እና የባሮ ማዶውን ኮከብ ዑመድ ኡኩሪን በክብር አለመጥቀስ በፍጹም አንችልም፡፡ እግር ኳስን አንሥተንም፣ የዓለም ታዋቂ ክለቦች ዓይናቸውን የጣሉበትንና የሜዳ ላይ ውበት የኾነውን ግዙፉን እግር ኳሰኛ ጋትዊች ፓኖምንም መቼም አንረሳውም፡፡

ሌሎች የጋምቤላ ወጣቶችም፣ በስፖርት መድረክ ብቻ ሳይኾን፣ በሌሎች ዘርፎችም ጭምር ስኬታማ ኾነው ክልላቸውን፣ አገራቸውንና ራሳቸውን መጥቀም እንዲችሉ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**"ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!"**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**አመሰግናለሁ**

# የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ንግግር

**ሰኔ 11/2010 ዓ.ም.**

## የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣
## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፤

በቅድሚያ በ2010 ዓ.ም. የበጀት ዓመት የመንግሥት አፈጻጸም አጠቃላይ ሪፖርት አጠር አድርጌ ለማቅረብና ከተከበሩ የምክር ቤት አባላት ለሚቀርቡልኝ ጥያቄዎች ማብራሪያ እንድሰጥ ዕድል ስለተሰጠኝ ለማመስገን እወዳለሁ፡፡

በዚህ አጭር ሪፖርት በጥቅሉ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ አገልግሎት፣ የዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎችን፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና፣ ከሀገራዊ የጸጥታና ሰላም ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የተሠሩ ሥራዎችና አሁን ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ እንደሚከተለው በአጭሩ አቀርባለሁ፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣
## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣

አትዮጵያ ባለፉት ሁለት እና ሦስት ዓመታት፣ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ቀውሶችን ስታስተናግድ ቆይታለች። ቀውሶች በያዝነው በጀት ዓመት የከፋ መልክ እየያዙ መጥተው በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ተደጋጋሚ

አለመረጋጋት ተስተውሏል። በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የነበሩ ግጭቶች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠራቸዉ ኣልቀረም፡፡ በዚሁ ምክንያት የኢኮኖሚ ዕድገቱ ወደ አንድ አሐዝ የወረደ ሲሆን፣ ፈጣን ዕድገቱ ግን አሁንም ቀጥሏል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የሀገራችን የነፍስ ወከፍ ገቢ 863 የአሜሪካን ዶላር ደርሷል፡፡ በ2009 ዓ.ም. መጨረሻ አንድ አሐዝ የነበረው የዋጋ ግሽበት በ2010 ዓ.ም. የበጀት ዓመት የየካቲት ወር አጠቃላይ የዋጋ ንረት ወደ ሁለት አሐዝ ከፍ ብሏል።

ከአጠቃላይ የኢኮኖሚ ሁኔታ በተጨማሪ ወሳኝ ዘርፎች ያሉበትን ሁኔታ እንደሚከተለው ባጭሩ አቀርባለሁ።

1.ግብርና፡- በ 2008 ዓ.ም. የተከሠተውን ኢሊኖን ተከትሎ ያጋጠመው የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተለው የምርት መቀነስ በ2009 እና 2010 ዓ.ም. ማገገም ቢችልም በግብርና ሴክተር የስልተ ምርት ሥርዓቱ ሥር ነቀል የለውጥ ሂደት ውስጥ ባለመግባቱ የዕድገት ምጣኔው ከአየር ሁኔታው ጋር ተዳምሮ እንዲዋዥቅ አድርጎታል፡፡

ሴክተሩ ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ መስኖን መሠረት ወደ አደረገ የአመራረት ሥርዓት ትርጉም ባለው ሁኔታ መድረስ ይኖርበታል፡፡ በሀገራችን የእርሻ ዘርፉን በሰፊው ማስተሣሠር ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የአዝርዕት ልማትና የእንስሳት ርባታን አስተሳስረው የሚያሳድጉ መርሐ ግብሮችን በመቅረጽ ተግባራዊ ለማድረግ መረባረብ ይኖርብናል፡፡

2.ኢንዱስትሪ፡- በኢንዱስትሪ ዘርፍ በተለይም የውጭ ንግድን መሠረት ያደረገ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን ለማሳደግ በርካታ ሥራዎች ቢሠሩም በተፈለገው ርቀት ተሂዶ ዘርፉ ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምጣኔ ያለው አስተዋጽዖ ቀዳሚ እንዲሆን ማድረግ ፈታኝ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህንን ተግዳሮት ለመመከት በኢንዱስትሪና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል ያለውን ደካማ ትሥሥር ለማሻሻል እንዲሁም የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቶ

ውይይት እየተደረገበት ሲሆን፣ ክፍተቱ ሥር ነቀል በሆነ መልኩ የዘርፉን ችግር ለመፍታት በዕውቀት ይሠራል፡፡

ኤክስፖርት ንግድ የውጭ ምንዛሪ ክምችት እና እዳን በሚመለከት በ2010 ዓ.ም. በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ጠቅላላ የሸቀጦች ገቢ ንግድ ወጪ አፈጻጸም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ 0.02 በመቶ የጨመረ ሲሆን የንግድ ሚዛን ጉድለቱ ግን ካለፈዉ በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ2.2 በመቶ ሰፍቷል።

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የካፒታል መጠን 7.7 ቢልዮን ዝቅ ብሏል፡፤ በመሆኑም በዚህ ዘርፍ በርትተን በመሥራት ሥር ነቀል ለውጥ ማምጣት እንዳለብን ሊሰመርበት ይገባል። የውጭ ምንዛሪ ችግር ዋነኛው ምንጭ የኤክስፖርት ንግድ አፈጻጸማችን ያለብን ድክመት ሲሆን፣ ዋነኛ መፍትሔውም ከግብአት እስከ ምርት ባለው ሰንሰለት በሃገር ውስጥ አምርተው ኤክስፖርት የሚያደርጉትን ለይቶ ማበረታታት ይሆናል። በአንድ በኩል ጠንካራና የተስፋፋ የጥቁር ገበያንና የኮንትሮባንድ ንግድ ባግባቡ መቆጣጠር አለመቻል በሌላ በኩል አብዛኛዎቹ ላኪ ኢንደስትሪዎች ወደ ውጭ የሚልኳቸውን ሸቀጦች ከታች ጀምረው እስከ መጨረሻው ሙሉ በሙሉ በሃገር ውስጥ አምርተው መጨረስ አለመቻል ያለብንን መዋቅራዊ ክፍተት የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ ክፍተት ከመሠረቱ መስተካከል ያለበት መሆኑ ታምኖ ከሚመለከታቸው ዘርፎች ጋር በቅንጅት እየተሠራ ይገኛል።

በ2010 ዓ.ም. በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት 688.6 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እዳ ክፍያ ተፈጽሟል። በተመሳሳይ ለተለያዩ የልማት ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል በድምሩ 1.6 ቢልዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ብድር ፈሷል፡፡ በዚህም የሃገሪቱ ጠቅላላ የውጭ ብድር ክምችት በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት መጨረሻ 24.7 ቢልዮን የኣሜሪካን ዶላር ሆኖ ተመዝግቧል። ይህ እዳ አጠቃላይ የሃገሪቱ እዳ ሲሆን ከዚህም ውስጥ መንግሥት የ 56.1 በመቶ ድርሻ ሲይዝ፣ ቀሪው 43.9 በመቶ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በመንግሥት ዋስትናና ያለመንግሥት ዋስትና የወሰዱትን ብድር ይሸፍናል።

ሃገራችን ከአነስተኛ የውጭ እዳ ጫና ወደ ከፍተኛ የውጭ እዳ ጫና ካለባቸው ሃገሮች ተርታ ተሰልፋለች።

ከውጭ ከሚገኙ ብድሮች ተጠቃሚነትን ስንመለከት 43.9 በመቶ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በመንግሥት ዋስትናና ያለመንግሥት ዋስትና የወሰዱትን ብድር ይሸፍናል። ይህንን ገንዘብ በአግባቡ ጥቅም ላይ አውሎ ወደ ተጨማሪ ካፒታልና ትርፍ በመቀየር እዳን መክፈል አለመቻሉ የውጭ እዳ የመክፈል አቅም እንዲቀንስ ካደረጉ ምክንያቶች ውስጥ ተጠቃሹ ነው።

በዚህም አግባብ ግምገማ በማድረግ ዋናው መፍትሔ ኤክስፖርትን ማበረታታት ቢሆንም በቀጣይነት የማሻሻያ ፖሊሲዎች እና ስትራተጂዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ። ከዚህም ውስጥ ከሰሞኑ የተወሰነው የፕራይቬታይዜሽን የፖሊሲ አቅጣጫ ተጠቃሽ ይሆናል።

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣
## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፤

መንግሥት የሐሳብ ብዝኃነትን ለማጎልበት የፖለቲካ ምኅዳሩ ይበልጥ እንዲሰፋ ብዝኃነት እንዲጎለብትና የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ሥር እንዲሰድ ካለው ጽኑ እምነት እና ቁርጠኛ አቋም በመነሣት በርካታ እርምጃዎች እየወሰደ ይገኛል። ምክንያቱም መንግሥት የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ጉዳይ የህልውና ጉዳይ አድርጎ የሚመለከተው በመሆኑ ነው። በዚህ ረገድ እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች እንደ ቁልፍ ጅማሮ ሊወሰድ የሚገባ ነጥብ የፖለቲካ ምኅዳሩ ይበልጥ እንዲሰፋ መንግሥት ሁሉም ያገባኛል የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዲሳተፉ በሩን ክፍት አድርጎ ለሂደቱ ስኬታማነት እየሠራ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሠረት በርካታ ፖለቲከኞች የሕግ ታራሚዎች ከእስር ተፈተዋል፡፡ በክስ ሂደት ላይ የነበሩ የፍርድ ሂደቶች እንዲቋረጥ ተደርጓል። እንዲሁም ከሃገር ውጭ ሆነው መንግሥትን ለመጣል ሲንቀሳቀሱ ከነበሩ ኃይሎች መንግሥት ያደረገውን ጥሪ ተከትሎ በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ ለመታገል ወደ ሃገር ውስጥ መግባት ጀምረዋል።

የፖለቲካ ምኅዳሩን ይበልጥ ከማስፋት አንጻር ሊታይ የሚገባው ሌላው ጉዳይ ከሚዲያና ሐሳብን በሰላም ከመግለጽ ጋር ተያይዞ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአንድ በኩል ሥራ ላይ የነበሩ የመንግሥትና የግል የኅትመት የብሮድካስትና የሳይበር ሚዲያዎች በነጻነት እንዲዘግቡና የሕዝቡ ድምፅ እንዲሆኑ በመወሰኑ ምክንያት በጎ ጅምር መታየት ጀምሯል።

በተመሳሳይ ተዘግተው የነበሩ ድኅረ ገጾች እና የሚዲያ ማሰራጫ ተቋማት፣ መካነ ጦማሮች እንዲለቀቁ በማድረግ የኢንተርኔት ዓምደኞች ጦማርያንና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ሐሳባቸውን በነጻ እንዲያንሸራሽሩ ዕድሉ ተፈጥሮላቸዋል። ይህም ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ ይህን የሚዲያ ሙያተኞች ሊወስዱ የሚገባቸው ሐላፊነት በቀጣይ ሊሠራበት የሚገባ ይሆናል።

ሌላው ትኩረት የሚጠይቀው ጉዳይ ከፍጥነት ጋር የተያያዘው ጉዳይ ሲሆን የሕግ እና የፍትሕ ሥርዓቱ በርካታ ክፍተቶች ያሉበትና ከመሠረቱ መለወጥ ያለበት ዘርፍ መሆኑ ጽኑ አቋም ተይዟል።

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣
## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፤

በአሁኑ ወቅት የሃገራት ስኬት የሚለካው ባላቸው ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም። ስለሆነም መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ካደረገባቸው ጉዳዮች አንዱ የዲፕሎማሲያዊ ጉዳይ ነው። የመንግሥት ትኩረት ከዚህ በፊት ጥሩ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ካላቸው ሃገሮች ጋር ይበልጥ ማጠናከር፣ ክፍተት ያለባቸውን አካባቢዎች ደግሞ ማስተካከል ነው። ከዚህ በመነሣት ሦስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከዚህ በፊት ዝቅተኛ ግንኙነት ከነበረን አንዳንዴም እንደ ጠላት ከሚታሰቡ የጎረቤትና መካከለኛው ምሥራቅ ሃገራት ጋር በተደረገው የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እጅግ በጣም አመርቂ ድል ማስመዝገብ ተችሏል።

በዲፕሎማሲያዊ ስኬቶች ከተገኙ ፍሬዎች መካከል ትልቅ ትርጉም ያለው ጉዳይ በየሃገራቱ በተለያየ ምክንያት ታስረው የነበሩ የዜጎቻችን መፈታት ሲሆን በተጨማሪም አሁን እያጋጠመን ያለውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመሸፈንም ከፍተኛ ድጋፍ ያገኘንበት አኩሪ ተግባር ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

በምሥራቅ አፍሪካ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ኢትዮጵያ የምትጫወተው ሚና ከዚህ ቀደም ከነበረው ይበልጥ ለማጎልበት፣ በኢኮኖሚ ለመተሳሰር፣ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ሥራም ተሠርቷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚገባው ጉዳይ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ላለፉት አሥራ ስምንት ዓመታት ነግሦ የነበረውን ሞት አልባ ጦርነት ከመሠረቱ ለመፍታት መንግሥት የሰላም ሐሳብ ጥሪ ለኤርትራ መንግሥትና ሕዝብ የማቅረቡ ጉዳይ እንደ ትልቅ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

የኢትዮ ኤርትራን ድንበር ጉዳይ የመፍታቱ ሐሳብ በዋናነት የሕዝባችንን ይልቁንም በድንበር አካባቢ የሚኖሩትን ዜጎቻችንን ጥቅም ያስከብራል። በሁለቱ ሃገራት መካከል ያለውን ግንኙነት ከዚህም አልፎ ቀጠናውን በማረጋጋት ረገድ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል ከሚል ጽኑ እምነት በመነሣት የተወሰደ እርምጃ ነው።

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣
## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፤

ላለፉት ሦስት ዓመታት የቆየውና በበጀት ዓመቱ በከፍተኛ ሁኔታ ደርሶ የነበረው በሃገሪቱ የነበረው አለመረጋጋት፣ አገሪቱ ከአንዴም ሁለት ጊዜ በላይ አስቸኳይ ዐዋጅ ውስጥ እንድትቆይ ከማድረጉም በላይ፣ የዜጎችን መብቶች፣ ሠርቶ የመኖር፣ የዜጎችን ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ ሕገ መንግሥታዊ መብቶች አደጋ ላይ የወደቁበትና በሃገር አንደነት ላይ ግልጽ የሆነ የመበታተን ስጋት የፈጠረና የሃገርን ህልውና አደጋ ላይ የጣለ የነበረ መሆኑ የማይካድ ሐቅ ነው። የተደረገውን የአመራር ለውጥ ተከትሎ የሕዝብ ሰላምና መረጋጋት በመፍጠር

ሕዝቡን ለማወያየት፣ በሕዝብ ውስጥ የሠረጸውን የሥጋት፣ ያለመተማመንና የጥላቻ አስተሳሰቦችን ለማስወገድ የሚረዱ ሥራዎች በሰፊው ተሠርተዋል።

የሕዝቡን ፍላጎት የልብ ትርታ በማዳመጥ የችግሮቹን ብሶትና ያለውን ሁኔታ ለመረዳት ተችሏል። በዚህም ምክንያት አንጻራዊ በሆነ መልኩ ከፍተኛ ተስፋ የሚሰጥ ሃገራዊ መግባባት እና መነቃቃት ሰላም መረጋጋትና አንደነት ተፈጥሯል። ሆኖም ግን ይህን ለውጥ ወደ ኋላ ለመመለስ የሚጥሩ ግለሰቦችና ቡድኖችም እንዳሉ መዘንጋት የለበትም።

ሃገራዊ የጋራ ዕሴቶችን ለመጠበቅና ለማጎልበት ባለመሥራታችን ለዘመናት ተዋዶና ተዋልዶ የኖረ ማኅበረሰብ በወሰን፣ በግል ጥቅም እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ባላቸው አካላት ሰላማቸውና አብሮነታቸው ሲፈተን ተስተውሏል። በአጠቃላይ በአንጻራዊ መልኩ ሰላምና አንድነት የማስፈን በተሠራው ሥራ ሕዝቡን የማረጋጋትና የነበረውን ጭጋግ ገፎ ወደ ብሩህ ተስፋ እና መልካም አጋጣሚ ለመቀየር ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል።

የሕዝቡ ሥነ ልቦና ላይም ከሚያለያዩ ነገሮች በላይ አንድ የሚያደርጉን፣ ከጥላቻ ይልቅ ለኢትዮጵያዊነትና ለወንድማማችነት፣ ከመፍረስ ይልቅ ለመደመር በማሰብ የተሻለና አዋጭ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጊዜው የሚጠይቀው መሆኑንም ለማስረዳትና ለመግባባት ተችሏል።በአጠቃላይ በነበረው ሰላም እና አንድነትን የማስፈን ሥራ፣ ሕዝቡን የማረጋጋትና የነበረውን ጭጋግ ገፎ ወደ ብሩህ ተስፋ መልካም አጋጣሚ መቀየር ተችሏል።

በሃገር ደረጃ ከጥላቻ ይልቅ ስለወንድማማችነት፣ ከመፍረስ ይልቅ ስለመደመር ለማሰብ እንዲቻል የሚያስችሉ ሥራዎችም በስፋት ተሠርተዋል። ከሁሉም በላይ ሰሚ ያጣ የመሰለው ሕዝብ ተስፋ ወደ መሰነቅ መሸጋገር ጀምሯል። የዜጎችን ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስና በሃገር ሠርቶ የመበልጸግን መብት ለማስከበር ከፍተኛ ጥረቶች በመደረግ ላይ ያሉ ቢሆንም ችግሩ ሙሉ በሙሉ አልተቀረፈም፡፡

ቀጣይ ጥረትና ሥራም እንደሚጠይቅ ያመላክታል። በድምሩ ሲታይ የኢኮኖሚ ተግዳሮቶች እንዳሉ ሆነው፤ በሰላም፣ በአንድነት፣ በተስፋ መረጋጋት፣ በፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ ጉዳዮች፣ ከትላንት ይልቅ ዛሬ በተሻለ ቁመና ላይ እንገኛለን፡፡ አሁንም ተጨማሪ ሥራና ሂደት በሚሹ ጉዳዮች፣ በጋራ በመረባረብ አስተማማኝ ሰላምና የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥረት ለማድረግ ከሁሉም ዜጎችና ከእኛ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

**አመሰግናለሁ።**

# የመደመር ቀን በአዲስ አበባ ንግግር

**ሰኔ 16/2010 ዓ.ም.**

## የተከበራችኹ ኢትዮጵያውያን፤

ከሁሉም በፊት ኢትዮጵያውያን፣ እንዲህ ለፍቅር፣ ለይቅርታ፣ ለአንድነት፣ ለመደመር ተሰባስበው ማየት፣ ምን ያህል ተስፋ እንዳጫረብኝ ስነግራችሁ፣ ታላቅ ክብር እና ከፍተኛ ደስታ እየተሰማኝ ነው፡፡ እናም ለወትሮው የንግግሬን ማሳረጊያ፣ ለዛሬ፣ የንግግሬ መጀመሪያ እንዳደርግ ፍቀዱልኝ - ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ሕዝቦቿን አብዝቶ ይባርክ!!

ገና ሓላፊነት ከተረከብን መንፈቅ ሳይሞላን፣ ፊት ለፊታችን እንደ ተራራ የተቆለለውን ግርዶሽ ሳንገፍ፣ ፊት ለፊታችሁ ቆመን ምስጋናን ለመቀበል የሚያስችል አቅም አላደራጀንም፡፡ የዛሬዋን ቀን እንድናይ የዛሬዋን ቀን ያላዩ፣ እንድንኖር ሲሉ የሞቱ፣ እንድንከብር ሲሉ የተዋረዱ፣ እንድንፈታ ሲሉ የታሰሩ፣ ለሕይወታችን ሕይወታቸውን የገበሩ ሰማዕታትን፣ በዚህ በከበረ ቦታ ቆመን ልናመሰግናቸው ይገባናል፡፡ ያለእኛ ሊኖሩ ይችሉ ነበር፤ ያለነርሱ ግን መኖር አንችልም፡፡

**ይህች የፈጣሪ ጥበብ መጀመሪያ አገር ኢትዮጵያ፤**
**ይህች የሰማንያ ውብ ውብ ጌጦች ሕብር ኢትዮጵያ፤**
**ይህች የሰው ልጅ እስትንፋስ መጀመሪያ አገር ኢትዮጵያ፤**
**ይህች የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት እና የአልበገር**
**ባይነት ተምሳሌት አገር ኢትዮጵያ፤**

ኹለት ወር ሠርቶ ለምስጋና የሚታበይ መሪ ሳይኾን፣ የችግሯን ሰንኮፍ ከሥሯ የሚመነቅልላት መሪ ያስፈልጋታል፡፡

**መሪ ግን ያለ ሕዝብ ፍቅር ባዳ ነው፤**
**መሪ፣ ያለ ሕዝብ አንድነት ባዶ ነው፤**
**አዎ መሪ፣ ያለ ሕዝብ አለኝታነቱ ከንቱ ነው፡፡**

እናም ዛሬ የመጣሁት፣ እስከ ዛሬ ለሰጣችሁን ፍቅር ላመሰግናችሁ ነው፡፡ አዎ የመጣሁት፣ ይህን ከባድ ሓላፊነት ከተረከብንባት የመጀመሪያዋ ቀን ጀምሮ፣ ላሳያችሁን አለኝታነት ላከብራችሁ ነው፡፡ ዛሬ የመጣሁት፣ የተረከብናት አገር፣ ለበርካቶች የሚተርፍ ሀብት ያላት ግን ፍቅር የተራበች አገር መኾኗን ፊት ለፊት ልነግራችሁ ነው፡፡ በመሆኑም እርስ በርስ ያለመመዘኛ የተዋደዳችሁ ዕለት፣ ያኔ እኔንና ከእኔ ጋራ ቀን ከሌት የሚለፉ ባልደረቦቼን አመሰግናችኋል፡፡

ሌብነትን እምቢኝ አሻፈረኝ ያላችሁ እለት ያኔ እንዳመሰገናችሁን ቁጠሩት፡ ይሄ ድንበር የኔ ነው ውጡልን መባባልን አቁመን በፍቅር ተግተን ለሀገራችን መስራት የጀመርን ለት ያኔ ምስጋናችሁን በሌላችሁበት እንደተቀበልኩት ቁጠሩት፡፡ ልጆቻችሁን፣ ከፊደል እኩል የአገር ፍቅር አስተምራችሁ ኢትዮጵያዊነትን ያለበሳችኋቸው ዕለት ያኔ ምስጋናችሁ ይደርሰናል፡፡

ያለ ሌላ ተደራቢ ምክንያት ስለ አገር ፍቅር ብላችሁ ለአካባቢያችሁ ዕድገት መቆርቆር እና መቆጨት ስትጀምሩ፣ ያኔ ምስጋናችሁ ከልብ ይኾናል፡፡ ዓላማችን ሩቅ ነው፤ ግባችንም እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ወደ ቀድሞ ገናናነትዋ እንደምትመለስ ቅንጣት ያህል ጥርጣሬ አይኑራችሁ፡፡ ኾኖም ግን፣ ለውጥ ጥቂት ተጨዋቾችንና ብዙ ተመልካቾችን አይፈልግም፡፡ ለውጥ የሁላችንንም ሜዳ ውስጥ ገብቶ መጫወት የሚፈልግ ሒደት ነው፡፡ ተመልካቾቹ ውጤት ሲኖር ሊያጨበጭቡ፣ ውጤት ሲጠፋም ሊወቅሱ በዙሪያው የሚመለከቱት ጨዋታ አይደለም፡፡ ልዩነቱ የምንጫወትበት ሥልጣን፣ ሓላፊነት፣ ዐቅም፣ ቦታ እና ድርሻ ብቻ ነው፡፡ ምሁራን የበሰለ ሐሳብ አምጡ፤ ባለሞያዎች አዳዲስ አሠራሮችን አመላክቱ፤ የእምነት አባቶች፣ ዘረኝነትንና ሙስናን አጥፍታችሁ፥ ድኻ ተበደለ፣ ፍርድ ተጓደለ በሉ፣ ወጣቶች ወገባችሁን አስራችሁ ለሥራ እና ለዕድገት ተሰለፉ፤ አባቶች ምከሩ፣ እናቶች ዝከሩ፣ ጎልማሶች ምሩ፣ ልጆች በተስፋ ተራመዱ፡፡

አገራችንን ከወደድን ግዴታችንን እንወጣ፤ መብታችንንም እንጠይቅ፣ አገራችንን ከወደድን፥ ሥልጣን ሓላፊነት እንጂ ገዥነት አይኹን፤ ሹመት ማገልገያ እንጂ መገልገያ አይኹን፣ አገራችንን ከወደድን፣ የሚንገላታው እያንዳንዱ ዜጋ፣ ኢትዮጵያዊ ነው፤ ብለን እንቁምለት፤ አገራችንን ከወደድን፣ የምትባክነው እያንዳንዷ ሳንቲም፣ የኢትዮጵያ ናት፤ ብለን እንሣሣላት፤ አገራችንን ከወደድን፣ የምትጠፋው እያንዳንዷ የሥራ ሰዓት፣ የኢትዮጵያ ናት፤ ብለን እንቆርቆርላት፤ አገራችንን ከወደድን፥ የሚበላሸው እያንዳንዱ ንብረት፣ የእናቴ የኢትዮጵያ ንብረት ነው፤ ብለን እንጨኽለት፤ አገራችንን ከወደድን፥ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል፣ አንድ ኢትዮጵያዊ መብቱ ሲጣስ ብሔሩንና ቋንቋውን ሳንመለከት፣ ወገኔ ተነካ ብለን እንቁምለት፡፡

***ኢትዮጵያን በጋራ እንገንባ፡፡ ሁላችንም ለኢትዮጵያ እናስፈልጋታልን፡፡ ለሁላችንም ኢትዮጵያ ታስፈልገናለች፡፡***

ኢትዮጵያ የድህነት ክንብንቧን አውልቃ እንድትጥል ቢተባበሩ፣ ተራራ ሊንዱ የሚችሉት የልጆቿ ፈርጣማ ክንዶች፣ ከተሸበቡበት የስንፍና ግርዶሽ ተላቅቀው ቀን ከሌት ሊተጉ ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ የሰላም ማማ እንድትኾን ከጎረቤቶቿ ጋራ ያላትን ግንኙነት፣ በፍቅር እና በመተሳሰብ እንዲሁም በአብሮ ማደግ መርሕ ላይ የተመሠረተ ልታደርግ ይገባል፡፡

**ኢትዮጵያ አገራችን ታላቅ እና ገናና አገር ናት፡፡**

ከድንጋይ እስከ ወረቀት፣ ከሁለት ሺ ዓመታት በላይ የዘለቀ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ያላት፣ በራሷ ዜማ የምታዜም፣ በራሷም ምት የምትንቀሳቀስ፣ በራሷ ኮርታ የኖረች፣ በራሷም ራሷን ጠብቃ የዘለቀች አገር ናት፡፡ ይህ ሁሉ ሀብታችን፣ ታሪካችንና ኩራታችን ግን፣ ነጻነትን፣ ፍትሕን፣ ዴሞክራሲንና በኢኮኖሚ መበልጸግን ለማብቀል ካልቻለ ኩራት እንጂ ራት አይኾነንም፡፡ ነጻ የሆነች አገር መገንባት እና ነጻ የኾነ ሕዝብ መገንባት ይለያያሉ፡፡

ነጻ ሕዝብ ከሌለ ነጻነት ቦታው የቱ ጋራ ነው? የክልል ወሰኖች፣ ድንበሮች ከኾኑ፤ የሚያስተሳስሩን ድልድዮች ትተን የሚያለያዩንን ግንቦች ከገነባን፤ የሺሕ ዓመታት ነጻነት ትርጉሙ እና ጥቅሙ የት ላይ ነው? ለመናገር እና ለመጻፍ ከፈራንና ከሰጋን፤ ለመደራጀት እና ለመንቀሳቀስ ከተጨነቅንና ከተደበቅን፣ የሺሕ ዓመታት ነጻነታችን ትርጉሙና ጥቅሙ የት ላይ ነው? አንዱ ብሔር ሌላውን፣ ‹መጣብኝ› ካለ፤ ‹ውጣልኝ ሒድልኝ› ካለ፤ ‹ይህኛው የኢትዮጵያ ክፍል፣ የእኔ ብቻ እንጂ ያንተ አይደለም› ካለ፤ ታዲያ ቅኝ ገዥዎችስ ከዚህ የባሰ ምን ያደርጉ ነበር? በመጨረሻም፣ አንድ ልብ እንድትሉት የምፈልገው ጉዳይ፣ ግለሰቦችን ከሕዝቦች እንለይ፤ እሾኹን ከጽጌረዳው እንነጥል፤ አይጥ በበላ ዳዋ አይመታ፤ በአንድ ጠማማ ዛፍ ምክንያት ደኑ አይለቅ፡፡ በዚህ አጋጣሚ፣ ይህ ዛሬ ከሕዝባችን የተሰጠን ወሰን የሌለው ፍቅር፣ ቀን ከሌት ያለዕረፍት ለሚተጉት የሕዝብ አገልጋይ ባልደረቦቼ ጭምር መኾኑን እየገለጽኩ፣ ዛሬ እዚህ ያሳያችኹን ወደር የሌለው ፍቅር፣ ሕዝብ ተቀብሎናል ብለን የሚያኩራራን ሳይኾን፣ለበለጠ ትጋት፣ ለበለጠ ታታሪነት የሚያነሣሣን መኾኑን ከልብ በመነጨ ጥልቅ ስሜት ልገልጽላችኹ እወዳለኹ፡፡

**"ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!"**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**አመሰግናለሁ!**

# የሰመራ ንግግር

**ሰኔ 20/2010 ዓ.ም.**

**የተከበራችኹ የአፋር ብሔራዊ**
**ክልላዊ መንግሥት ሕዝቦች፣**
**የተከበራችኹ ሡልጣኖች፣ ገራዶች እና ዑጋዞች፣**
**የተከበራችኹ የሃይማኖት**
**አባቶች እና የአገር ሽማግሌዎች፣**
**የተከበራችኹ የክልሉ መንግሥት የሥራ ሓላፊዎች፣**
**ክቡራት እና ክቡራን፤**

ከሁሉ አስቀድሜ፣ የሰው ዘር መገኛ ዕንብርት፣ የዓለም የከየት-መጣን ጥያቄ የአስደናቂ ምላሽ ተምኔት፣ የተኣምራዊ መልክዓ ምድር ሰገነት፣ የደግ፣ ጀግና እና ኩሩ ኢትዮጵያውያን ቤት፣ የአገር ወዳድ ሕዝብ መሠረት በኾነችው የአፋር ምድር በመገኘቼ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ስገልጽላችኹ፣ ከፍ ባለ ወገናዊ ኩራት እና ጥልቅ በኾነ የ “እንኳን ተገናኘን” ሐሤት ውስጥ ኾኜ ነው፡፡

የአፋር ሕዝብ፣ ተግዳሮትንና አስቸጋሪ የሕይወት መልክን የሚሸሽ ሕዝብ ሳይኾን፣ አስቸጋሪውን ዕጣ ፈንታ በጥበብ በማከም ወደ በረከትነት የሚቀይር ውብ ሕዝብ ነው፡፡ አፋር፣ በበረሓ ግለት ውስጥ መኖር የሚያስችለውን የቤት ግንባታ ቴክኖሎጂ የፈጠረ፣ አገርንና ዓለምን በግርምት የሚመስጥ የመረጃ

ቅብብል ሥርዓት-ዳጉን የቀመረ፣ የእንስሳት ሀብት ልማትን የኑሮው መሠረት አድርጎ ትውልድን ያሻገረ፣ ከኢትዮጵያውያን ወንድም እኅቶቹ ጋራ በመኾን ዕንቅፋቶቹን በትግል ያስገበረ እና በፍጹም ፍቅር ለዘመናት የኖረ ሕዝብ መካከል መገኘት፣ ክብሩ እና ኩራቱ ፍጹም ከፍ ያለ ነው፡፡

የአፋር ሕዝብ፣ በዓለም የጥንት ነጋድያንና ተጓዦች፣ በዛሬዎቹም ቱሪስቶች፣ ‹ጠንካሮቹ የዓለም ሕዝቦች› ተብለው በመጠራት ለዛሬው ትውልድ ኩራትንና ክብርን ማጎናጸፍ የቻለ ድንቅ ሕዝብ ነው።

የአፋር ሕዝብ፣ በቀይ ባሕር አካባቢ ባለው ስትራቴጂያዊ አሰፋፈሩ መነሻነት፣ ቱርኮች፣ ግብፆች፣ በኋላም የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ወደ መሀል ኢትዮጵያ ለመረማመድ ሲያልሙ አገር ወዳዱ የአፋር ሕዝብ የባዕዳንን ተልእኮ ቀድሞ በመገንዘብ እና በብስለት በመመርመር፣ በር የሌለው አጥር ኾኖ የአገሩን ሉዓላዊነት በዘመናት ውስጥ ያስጠበቀ ጀግና ሕዝብ ነው፡፡

## ክቡራት እና ክቡራን፤

አፋር፣ የሰው ዘር መፈጠርያ ማሕፀን፣
አፋር፣ የዓለም ታላቁ ስምጥ ሸለቆ መሰመርያ ምድር፣
አፋር፣ ሰው የተበጀባት ቀዳማዊት የሕይወት ቅኔ አፈር፣
አፋር፣ የማያንቀላፋ እሳተ ገሞራ ተኣምራዊ ትዕይንት መድረክ፣
አፋር፣ የእልፍ ዕሴቶች እና የውብ ባህሎች መከሠቻ ልክ፣
አፋር፣ የዓለም ዝቅተኛው ቦታ ዳሎል የሚገኝበት ምድር፣
ስለ አፋር ብዙ ማለት ቢቻልም፣ እነዚህ መገለጫዎቻችን፣ ጌጥ እና ኩራታችን መኾን የሚችሉት ተደምረን- በፍቅር እና በትጋት ራሳችንን ለመለወጥ ሙሉውን ሓላፊነት በመዳፋችን ውስጥ ስናኖር ብቻ ነው፡፡

እስከ አሁን የሔድንበት መንገድ ፈታኝ የመኾኑን ያህል፣ ቀጣይ ጉዟችንም መሰናክል እንደ ማያጣው በውል እንገነዘባለን፡፡ የኾነው እና የሚኾነው ሁሉ ቢኾንም፣ የጀመርነው፥ የፍቅር፣ የይቅርታ፣ የአንድነት፣ የመደመር እና የአብሮነት ጉዞ የትኛውንም ጋሬጣ እንደሚያሻግረን ምንም ጥርጣሬ የለንም፡፡

የአፋር ሕዝብ፣ ከታሪኩ እና ከባህሉ መሠዊያ ላይ በክብር ያኖራቸውንና በሕይወቱ ውስጥም በጥበብ የሞሸራቸውን ድንቅ ዕሴቶች፣ በልጆቹ ልብ ውስጥ በመትከል ይህን ታላቅ ሕዝብ፣ ይህን ታላቅ ክልል እና በተራዛሚውም ይህችን ታላቅ አገር ወደ ታላቅነቷ ለመመለስ በጀመርነው ጉዞ ላይ ደማቅ አሻራውን እንደሚያሳርፍ እምነቴ ሙሉ ነው፡፡

## ክቡራት እና ክቡራን፤

በአፋር ምድር፥ ግልጽነት፣ ደግነት እና ሰው አፍቃሪነት ሞልቶ የተትረፈረፈ ነው፡፡ የአፋር ሕዝብ በሃይማኖት ለሚመስሉት ብቻ ሳይኾን፣ የሌላውን ሃይማኖት እና እምነት የሚያከብር፣ በክልሉ ውስጥ ከተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ጋራ በመተባበር እና በመቻቻል አብሮ የሚኖር ድንቅ ሕዝብ ነው። ከምንም በላይ፣ የክልሉ ሕዝብ፣ ኢትዮጵያዊነቱ ጥብቅ እንደ ኾነና በሰንደቅ ዓላማውም እንደማይደራደር እሙን ነው፡፡ እኛ አፋሮች፣ "እንኳን እኛ ግመሎቻችንም የአገራቸውን ሰንደቅ ያውቃሉ" የሚለው አባባል በመላው ኢትዮጵያዊ እየተስተዛዘለ ዛሬ የመድረሱ ምሥጢርም ይኸው ነው፡፡

አፋር የብዙ መልካም ዕሴቶች መገኛ ነው፡፡ ከዕሴቶቹ መካከል የራሱን አካባቢ ሰላም እና ጸጥታ የሚያስከብርበት፣ ፍርድን የሚያስፈጽምበት፣ የታመመን የሚረዳ-የሚጠይቅበት፣ እንግዳን የሚያስተናግድበት፣ በሠርግ እና በመሰል በዓላት ሥራ የሚተጋገዝበት፣ በቀብር ወቅት የቀብር ሥርዓቱን በተገቢው ኹኔታ የሚያስፈጽምበት ብርቱ ወንዶችን አሰባስቦ የሚይዝ የ"ፈኢማ" ቡድን እጅግ የሚደነቅ አገር በቀል ዕሴት ነው፡፡

የአፋርን ምድር ረግጦ፣ ስለ ሰው ልጅ ቅድመ እናቶች፥ "ሉሲ፣ ሰላም እና አርዲ" አለማንሣት፣ ስለ ሰዎች ቅድመ አባት፣ "አርዲ ፒቲከስ ካዳባ" አለመጥቀስ አፋር ሳይደርሱ እንደ መመለስ ይቆጠራል።

በሰው ዘር መገኛ ምንጭነት የታደልነውን ሀብት፣ ወደ ቱሪስት መስሕብነት እና መዳረሻነት በመቀየር ተጠቃሚ ለመኾን በጋራ መሥራት ዋና አጀንዳችን ሊኾን ይገባዋል፡፡ በክልሉ በስፋት የሚገኘውን የፖታሽ ማዕድን ተጠቅመን ለማዳበሪያ ልማት እና የፕላስቲክ መሥሪያ ግብዓት እንዲኾን፣ የአዋሽ ተፋሰስን ተጠቅመን የበረሓ ልማትን በማረጋገጥ፣ ምድራዊ ማርስ በመባል የሚታወቀውን አቤ ሐይቅ እና በውስጡ ያለውን ደን ሥነ ሕይወታዊ ሀብት በመረዳት፣ በመጠበቅ እና ወደ አንዳች የገቢ ምንጭነት በመቀየር፣ ለማኅበረሰባችንና ለአገራችን ኢትዮጵያ ኩራት መኾን እንዲችል መንግሥት በሚያስቀምጠው አቅጣጫ መሠረት ልንረባረብ ይገባል፡፡

የአፋር ክልል ከታደላቸው የተፈጥሮ መስሕቦች ዋነኛው፣ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን ቅኔ የተቀኘለት ታላቁ የአዋሽ ወንዝ፣ ለመስኖ ምቹ ኾኖ ልማትን ከማቀላጠፉ ባለፈ አፈጣጠሩ፣ ከዓመት እስከ ዓመት ያለ ማቋረጥ እየፈሰሰ፣ የአገሩን መሬት እያረሰረሰ በአገሩ ማሕፀን ውስጥ ተመልሶ የሚገባ ነውና ለአገር መውደድ ተምሳሌት ኾኖ እናገኘዋለን፡፡

ጨው የሚታፈስበትና አሞሌ የሚመረትበት የአፍዴራ እና የአሰዓሌ ሐይቆችን ጨምሮ ሌሎች የውኃ አካላት፣ በዳሎል እና ኤርታአሌ የተከማቸ የጨው እና ተፈጥሯዊ ማዕድናት፤ ለእርሻ አመቺ የኾነ ሰፊ መሬት በዋነኛነት ተጠቃሽ ሊኾኑ ይችላሉ፡፡ የክልሉ ሕዝብ ኑሮውን የሚደጉምባቸው፣ የሀብት መጠኑን የሚገልጥባቸው የቀንድ እና የጋማ ከብቶቹ፣ በግብርናው መስክ ከፍተኛ ስኬትን በማስመዝገብ ከክልሉ አልፎ ለተቀረው የአገራችን ክፍል መትረፍ የሚችል ሀብት ነው፡፡ ይህ ሀብት፣ ቁጥርን መሠረት አድርጎ ከመመካት አልፎ በሕይወታችን ውስጥ የሚታይ ለውጥ ማምጣት ይችል ዘንድ፣ የፌዴራል መንግሥት ከክልሉ መንግሥት ጋራ በመተባበር አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

በመጨረሻም፣ አገራችን በተያያዘችው የሰላም፣ የልማት እና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሒደት ላይ የሚፈጠሩ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለመፍታት፣ በአንድነት ከጎናችን ኾናችኹ ጥንካሬ እንደምትጨምሩልን አልጠራጠርም፤ ምክንያቱም፣ አንድም ቀን፣ ለኢትዮጵያ ፍቅርን ለባንዴራ ክብርን አሳንሳችሁ አታውቁምና፡፡ ለወደፊቱም፣ ውበትም ኾነ ጥንካሬያችን የሚመነጨው ከኢትዮጵያዊ አንድነታችን ነው፤ በሚል መንፈስ፣ አንዲት ጠንካራ አገርን ለመገንበት ያላሰለሰ ርብርብ ታደርጉ ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

**"ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!"**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ገደጌ፤ አመሰግናለሁ!**

# የኤርትራ ንግግር

**ሰኔ 30/2010 ዓ.ም.**

## ክቡር ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈ ወርቂ፤

በሀገረ ኤርትራ በተለይም በአሥመራ፣ ፍቅር ከሚያውቀው ሕዝባቸው ጋራ ለአደረጉልን አቀባበል፣ በነበረን ቆይታ፣ የተሰማኝን ጥልቅ ስሜት አስቀድሜ መግለጽ እፈልጋለሁ።

ትላንትና እና ዛሬ፣ እኔ የተሰማኝ፣ የጠፉብኝ ወንድም እና እኅቶቼን በድንገት ያገኘሁ ያህል ስሜት ነው ያለኝ፡፡ በፍጹም የአንድ አባት ልጆች ቤተሰቦች መኾናችንን፣ ከፕሬዝዳንቱ ጀምሮ በየስፍራው ያገኘናቸው የኤርትራ ሕዝቦች አረጋግጠውልናል።

የኤርትራ ሕዝብ፣ የአሥመራ ሕዝብ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እውነተኛ ፍቅር እውነተኛ ወንድማማችነት እንዳለው ማየት ችያለሁ። ከዚህም በላይ ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ በሩቅ ከማውቃቸውም ከምገምታቸውም በጣም በተለየ መልኩ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ አክብሮትና ፍቅር ያላቸው፣ የኢትዮጵያ ሰላም፣ የኢትዮጵያ ልማት የሚያስጨንቃቸው ለኹለቱ አገሮች ዝምድና፣ ለኹለቱ አገሮች ወዳጅነት ብቻ ሳይኾን፣ በሱዳን፣ በሶማሌ፣ በጅቡቲ ጠንካራ መንግሥታት ተፈጥረው ምሥራቅ አፍሪካ በጠንካራ መንግሥታት የሚተጋገዝ እንጂ አንደኛው መንግሥት አንደኛውን መንግሥት የሚያፈርስ እንዳይኾን ሰፊ ሐሳብ እንዳላቸው መረዳት ችያለሁ። ይኼ ለእኛ ትልቅ ዜና ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ በንግግር ካደረግነው በላይ በግል አኗኗራቸውም፣ ከሕዝባቸው ጋራ ተመሳስለው የሚኖሩት የሕይወት ዘዬ ለእኛ ለሁላችንም ትልቅ ትምህርት የሰጠ፣ እንደ ማንኛውም አገልጋይ መንግሥት በሕዝባቸው መካከል እየኖሩ ባልተጋነነ የኑሮ ዘየ አገራቸውን የሚያስተዳድሩ፣ ምናልባትም በአፍሪካ እምብዛም የማይታይ ባህል ስላየሁ፣ በግልም የተማርኩበት እጅግም ደስ ያለኝ መኾኑን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ዛሬ የተስማማነው ስምምት አንደኛውና ዋነኛው መሠረት፣ የኹለቱን ወንድማማች ሕዝቦች በጋራ፣ በሰላም አብሮ የማደግ ነገር የሚያደናቅፈውን ጦርነት እና የጦርነት ወሬ አቁመን፥ ሰላም፣ ፍቅር እና አንድነት በአዲሱ ቋንቋ መደመር አለብን የሚል ነው። ኹለተኛው ከመደመር ባሻገር፣ የኢኮኖሚ ጉዳይ ለኢትዮጵያም ለኤርትራም ወሳኝ በመኾኑ፣ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች በጋራ እየተጋገዝንና እየተደጋገፍን የኹለቱን ሕዝቦች የኑሮ ደረጃ ማሻሻል እንዳለብንም ከልብ ተስማምተናል፡፡

ከድንበር ጋራ ተያይዞ የነበረው ግጭት፣ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ በኩል ሐሳቡን ከተቀበሉ በኋላ፣ ከድንበር ባሻገር፣በኹለቱ አገሮች-ወንድማማቾች መካከል ሰላም፣ ልማት እና አንድነት እንዲመጣ የሚል ጥያቄ ስናቀርብ የቆየን ቢኾንም፣ በኤርትራ በኩል፣ ከዚያ የበለጠ ፍላጎት፣ ከዚያ የበለጠ ተነሣሽነት መኖሩን በተግባር በነበረን ቆይታ ማየት ችለናል። በመካከላችን፣ ከልብ በፍቅር ካለመነጋገር የመጣ እንጂ፣ ሰፊ ልዩነት የለም፡፡ የኤርትራ መንግሥት እና ሕዝብ የኢትዮጵያን ዕድገት፣ የኢትዮጵያን ልማት፣ የኢትዮጵያን ሰላም ይፈልጋሉ፡፡

በግልጽ የተነጋገርነው ጉዳይ፣ ዛሬ ኤርትራ፣ እንደ ዱባይ እንደ አቡዳቢ ኾና ቢኾን ኖሮ፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች በእግራቸው አቋርጠው አሥመራ ይመጡ ነበር፤ በባሕር አይበሉም ነበር። የኤርትራ ዕድገት በቀጥታ ለእኛ ይጠቅመናል፡፡ እንኳን የኤርትራ ዕድገት፣ ቀይ ባሕር ተሻግሮ ያለው የመካከለኛው ምሥራቅ ዕድገትም፣ ለእኛ ወጣቶች ተስፋ ኾኖ እዚያ ለመድረስ ብዙዎቹ በባሕር እየተበሉ መኾኑን እናውቃለን።

የኤርትራ ዕድገት ለኢትዮጵያ በጣም የሚጠቅም፣ የኢትዮጵያ ዕድገት ለኤርትራ በጣም የሚጠቅም፤ የሱዳን ዕድገት፣ የጅቡቲ ዕድገት በአጠቃላይ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት ዕድገት እና ጥንካሬ፣ ለሁላችን የሚጠቅም መኾኑን ከልብ ተስማምተናል።

ስምምነታችን፣ በአንድ ዓመት በኹለት ዓመት የሚያልቅ ሳይኾን፣ ለእነዚህ ኹለት አገሮች፣ ረዥም ዓመታት የጦርነት ወሬ ሳያወሩ በፍቅር፣ በስምምነት እና በመተጋገዝ አብረው የሚኖሩበትን ነገር የሚያሳይ ነው፡፡ እኛ በኢትዮጵያ በኩል የተስማማንበትን ዋና ዋና ሐሳቦች ከልብ ለማስፈጸም በጋራ እንሠራለን፤ የሕዝቦቻችንን አብሮነት ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት እንቀሳቀሳለን፡፡ ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ በቅርቡ ኹለተኛ አገራቸውንና ሕዝባቸውን ሲጎበኙ የሚሰማቸውን መልእክት ለሕዝባቸው እንደሚያስተላልፉ ለኤርትራ ሕዝብ የምናገረው፣ ልክ እዚህ እንዳየነው ፍቅር፣ እዚህ እንዳየነው የወንድማማችነት ስሜት በኢትዮጵያም በኩል፣ ሕዝቡ የናፈቃችሁ፣ የሚወዳችሁ፣ ከእናንተ ጋራ ሠርቶ መለወጥ ማደግ የሚፈልግ መኾኑን በሙሉ ልብ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለኹ።

ኤርትራ፥ እውነተኛ፣ ኹለተኛ አገራችን ናት፡፡ ለእናንተም ኢትዮጵያ፣ እውነተኛ፣ ኹለተኛ አገራችሁ ናት፡፡ ኢትዮጵያ እና ኤርትራ፣ ለሕዝቦቻቸው በቂ ሀብት ያላቸው፣ በቂ ጭንቅላት ያላቸው፣ በቂ ሕዝብ ያላቸው ስለኾኑ፣ ከማንም ሳይለምኑ ኹለቱ አንድ ኹነው፣ ጠንክረው ሌላ ማገዝ የሚችሉበትን ዘመን ከፊት ለፊታችን እንዳለ በሙሉ ልብ መናገር ይቻላል። የኤርትራ ወጣቶች፣ በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች መጥተው የሚማሩበት፣ የኢትዮጵያም ወጣቶች፣ በኤርትራ ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩበት፣ የተማሪዎች-የመምህራን ኤክስቼንጅ፣ የፖለቲካ አመራሮች ኤክስቼንጅ እንዲሁም በሴኩሪቲ ረገድ አንዳችን አንዳችንን ለማጥቃት ሳይኾን ተጋግዘን አንዳችን ሌላችንን ለመጠበቅ እንሠራለን፡፡

ከዚህ በኋላ፣ በወንድማማችነት ስሜት በጋራ ለማደግ ፍላጎት ያለን መኾኑን፣ በተለይም በድንበር የሚዋሰኑ የትግራይ እና የአፋር ሕዝቦች፣ ይህን ሰላም ከምንም ነገር በላይ የሚፈልጉ መኾናቸውን፣ እዚህ መጥቶ ሕዝባቸው ጋራ

መነጋገር፣ ፕሬዝዳንት ኢሳይያስን በአካል ማግኘት፣ መጠየቅ፣ መወያየት፣ ወንድማማች መኾናችንን ማረጋገጥ የሚፈለጉ ስለኾነ ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ ሁል ጊዜም በጉብኝታቸው እና በንግግራቸው የትግራይን ሕዝብ፣ የአፋርን ሕዝብ በድምሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከእርሳቸው የሚፈልገውን የወንድማማችነት አመራር እየሰጡ ሰላሙ ዘላቂ እንዲኾን፣ ሪጅናችን እንዲለወጥ፣ በጋራ እንድናድግ የበኩላቸውን እንደሚያደርጉ ሙሉ እምነት አለኝ፡፡ በዚሁ አጋጣሚ፣ የጀመሩትን አስደሳች የሰላም፣ የፍቅር እና የዕድገት ጉዞ ሳያቋርጡ አመራር እንዲሰጡ በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ።

የአሥመራ ሕዝብ ድንቅ ሕዝብ መኾኑን በተግባር አሳይቷል፤ በፍቅር ተሸንፈናል፡፡ ትላንትና ከአንዳንድ ሰዎች ጋራ ስንነጋገር፣ እኛ ኤርትራውያን በሚሳኤል በትግል አንበረከክም፤ አሉ፡፡ የሚሳኤል፣ ታንክ ትግል ከፈለጋችሁ ሠላሳም አርባም መቶም ዓመት እንዋጋለን፡፡ ለጋራ ኮዝም አንፈራም፤ ለጋራ ኮዝ መሞትንም እንደ ክብር እናያለን፤ ነገር ግን የአሁኑ የኢትዮጵያ አመራር፣ የኤርትራን ሥሥ ብልት አውቋል አሉ፡፡ የኤርትራ ሥሥ ብልት ፍቅር ነው፤ በፍቅር እንሸነፋለን፤ በፍቅር እንታረቃለን፤ በፍቅር የኋላውን ቁርሾ አናስብም፤ ተማርከናል፤ ተደምረናል፤ ስላሉ ለኤርትራውያን ወገኖቼ ማረጋገጥ የምፈልገው፣ በኢትዮጵያም በኩል ተመሳሳይ ፍላጎት እንዳለ ነው፤ ያው የምታውቁት የእናንተ ወንድም እና እኅት ሕዝብ ስለኾነ በፍቅር የሚሸነፍ በመኾኑ፣ ትላንት ላጋጠመው ሁሉ በፍቅር ረስተን ወደፊት ተደምረንና ተጋግዘን አካባቢውን እንድንቀይር ጥሪ አስተላልፋለኹ፤

**አመሰግናለሁ።**

# የአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ንግግር

**ሐምሌ 21/2010 ዓ.ም.**

ይህች ቀን፣ በመንግሥታችንና በእናንተ ከአገር ውጭ በምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን መካከል ለበርካታ ዓመታት ሥር ሰዶ እና ዘልቆ የኖረውን የደመኝነትንና የባላንጣነትን፣ የመጠራጠርንና የመራራቅን ግንብ አፍርሰን፣ በምትኩ የሚያገናኘንን ድልድይ የምንገነባበባት የታላቅ ታሪካዊ ምዕራፍ ጅማሬ ናት፡፡ በዚህች ቀን፣ የአገራችን ሰው በምሳሌያዊ ንግግሩ፣ "ምን ቢከፉ ዘመድ፣ ምን ቢጠም መንገድ" እንዲል፣ በመገናኘት - መቀራረብን፣ በመቀራረብ - ውይይትን፣ በወይይትም - መደማመጥንና ተሳትፎን በማጠናከር ወደ ጋራ መግባባት በሚያመራ ቀና መንገድ ላይ ጉዞ ጀምረናል። ይህን ታሳቢ በማድረግ የዚህ ታሪካዊ ክሥተት መሪ ቃላችን፥ "ግንቡን እናፍርስ፤ ድልድዩንም እንገንባ" የሚል ኾኗል፡፡

በእንግዳ ተቀባይነታችን የዘመናት ዕድሜ ያስቆጠርነው እኛ ኢትዮጵያውያን፣ ከግማሽ ምእት ዓመት ወዲህ በተጣባን ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ አባዜ ምክንያት፣ በከፍተኛ ቁጥር የመሰደድ ክፉ ዕጣ በትከሻችን ላይ መውደቁን በቁጭት የምናስበው ቢኾንም፣ ኢትዮጵያዊነት፥ በአካል አገር ውስጥ ስንኖር ብቻ የሚኖር፣ ከአገር ስንወጣ ደግሞ የሚሸሽ ጥላ አለመኾኑን ስናስብ እንጽናናለን፡፡ ኢትዮጵያዊነት ከደማችን የተዋሐደ፣ ከአጥንታችን ጋራ የጸና፣ በልባችን የታተመ ማንነት እንደ ኾነ፣ ከእናንተ ሕይወት በላይ ምስክር እና አስረጂ ሊቀርብ አይችልም፡፡

ከአገር ስትወጡ በምናባችሁ የቀረፃችኋትን፣ በልባችሁ ያተማችኋትን ኢትዮጵያ፣ በስደት አገርም ከኅናችሁ ትኖር ዘንድ፣ በተናጠል እና በጋራ ከከፈላችኹት መሥዋዕት ባሻገር፣ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ዳያስጶራ ለአገራችን ኢኮኖሚ ምሶሶ እና ዋልታ ከመኾን አልፎ፣ የለውጥ እና የፖለቲካ አማራጭ አስተሳሰቦችም መሠረት ለመኾን በቅቷል፡፡

ለኢትዮጵያ ነጻነት እና ሰላም፣ ዕድገት እና ብልጽግና፣ ዳያስጶራው የአገራችን ማኅበረሰብ፣ በየስፍራው የተበተኑ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ሁሉ ጭማሬዎች እና ተቀጥላዎች አይደላችሁም። ይልቁንም ለሥልጣኔያችን ፈርጦች፣ ለዕድገታችን ዋልታዎች፣ ለሰላማችን ማማዎች፣ ለነጻነታችን ሰንደቆች፣ ለብልጽግናችን ምንጮቹ እናንተ ናችሁ። ያፈራችሁትን ሀብት እና ያደረጃችሁትን ጥሪት ሳይኾን፣ እናንተን ልጆቿን ፈልጋ ለችግሯ እንድትደርሱላት ሳይኾን ዓይናችሁን ለማየት ናፍቃ፣ ስመ ጥርነታችንና ልታደርጉላት የምትችሉትን እገዛ ሳይኾን፣ ፍቅራችሁንና ልጅነታችሁን ጓግታ፣ አገራችሁ በምታውቁት የእናትነት ድምጿ ወደ እቅፏና ማጀቷ ትጠራችኋለችሁ። በአገር ቤት ያሉት የእናንተ ወንድሞች እና እኅቶች የኾኑ ውድ ልጆቿም ቢኾኑ፣ እናንተን ሊተኩላትም ኾነ ሊኾኑላት አይችሉም። እናንተም የእናታችሁ ፍቅር ሲያብሰለስላችሁ እንደ ኖራችሁና በነፍስያችሁ ናፍቆት ዕረፍት አጥታችሁ መኖራችሁን አገራችሁ ታውቃለች።

በኢትዮጵያ እየተካሔደ ላለው ሕዝባዊ ለውጥ፣ በውጭ አገሮች በተለይም በሰሜን አሜሪካ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የቅርብ ተመልካች ብቻ ሳይኾን፣ የተሳትፎ ድርሻውም ከፍተኛ ነው፡፡ በአገር ፍቅር ስሜት ልቡ የሚነደውና በሰሜን አሜሪካ የሚኖረው የዳያስጶራ ኮሚዩኒቲ፣ ጥንታዊት እና ታሪካዊት አገሩን፣ የብዙ ብሔረሰቦች፣ ባህሎች፣ እምነቶች እና ቅርሶች መናኸርያ የኾነችውን ምድሩን፣ በፀረ ቅኝ ግዛት ትግል ለአፍሪካ፣ ለላቲን አሜሪካ እና ለእስያ ሕዝቦች አርኣያ የኾነችውን አንድዩ ኩራቱን፣ ለአፍሪካዊ አሜሪካውያን የነጻነት እና የእኩልነት ትግላቸው ምሳሌ አድርገው በክብር የሚያዩዋትን ኢትዮጵያን፣ ከያለበት አገር ጋራ ሲያነጻጽር በውስጡ ቁጭት መፍጠሩ አይቀሬ ነው፡፡

አገሩ እንድታድግ፣ የእኩልነት እና የዴሞክራሲ ማዕከል እንድትኾን፣ የፍትሕ እና የሥርዓት ተምሳሌት እንድትኾን ይመኛል፤ ተመኝቶም አያርፍም፤ ይሞግታል፤ ይታገላል፤ ይጮኻል፤ የተሳሳቱ ነገሮችን ይቃወማል፤ በተናጠል እና በኅብረት የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ በርግጥም የአገራችን የኢትዮጵያ የዘወትር ሙሾ መቼ እና እንዴት ይቆማል? የሚለው ሐሳብ ሁልጊዜም ከሚያማቸውና ከሚያስጨንቃቸው ዜጎች ውስጥ፣ በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በቀዳሚነት ተጠቃሽ ናቸው ብንል ማጋነን አይኾንም፡፡

በፖለቲካ አመለካከት እና እምነት መለየትን ከተፎካካሪነት ይልቅ ጠላት አድርጎ መፈረጅን መለያው ባደረገው አገራዊ የፖለቲካ ባህላችን የተነሳ፣ አብዛኛው ዳያስጶራ በፖለቲካ አመለካከቱ ምክንያት ከመንግሥት ጋራ ሆድ እና ጀርባ በመኾን መገለል ዕጣ ፈንታው ኾኖ ቆይቷል፡፡ በዚህም አላበቃንም፡፡ በፖለቲካ ልሂቆቻችን ልብ ውስጥ የናኘው ጽንፈኛ መንፈስ፣ የእናሸንፋለንና እናቸንፋለን ንባብ እና ትርጓሜ ሳይቀር ለያይቶ እንዳጫረሰን ሁሉ፣ ባለፉት ኹለት ዐሥርት ዓመታት የነበረው የከረረ አገራዊ ፖለቲካዊ ቅኝትም፣ ከአገር ቤት አልፎ በውጭ በምትኖሩ ኢትዮጵያውያን አገራዊ ስሜት ላይ ታላቅ ጥላ አጥልቶበት መክረሙ ሐቅ ነው፡፡ ክፍፍሉ በዚያና በዚህ የሚሉት ዓይነት አልነበረም፡፡ በእምነት፣ በብሔር፣ በአመለካከት፣ በቋንቋ…ጥያቄዎች ተለያይታችሁ በመልስም ተከፋፍላችሁ ከረጅሙ የመለያየት ግንብ ጋራ በመፋጠጥ ዘመናት አሳልፋችኋል፡፡

እንደ ወጣንበት ዘመንና ምክንያት ወይም እንደ የምርጫችንና አቅማችን፣ አቋማችንና መረዳታችንም መለያየቱ የሚጠበቅ ቢኾንም፣ ጠባችን ከፍቅራችን፣ ልዩነታችን ከአንድነታችን፣ ቂማችን ከይቅርታችን እንዳይበልጥ (አገርን ለመለወጥ እና አገር ቤት ያሉ ወገኖቻችን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማስተማርና ለመምከር ከመሞከራችን በፊት) እስኪ እኛው እዚሁ ያለነው፣ ልባችንንና አስተሳሰባችንን ከእኛ ለሚለዩና እንደ እኛ ለማያስቡ እዚሁ ላሉ ወገኖቻችን ሰፋ አድርገን እንክፈት፡፡

እኛ እዚህ በአንድ ቤት እና በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ያለነው፣ ልዩነታችንን ተቀብለን አንድነታችንን ለመፈለግ አቅሙ ከሌለን፣ ከሌላው ያን መጠበቃችንስ ትዝብት ውስጥ አይከተንምን? ምናልባት የኢሕአፓ ወይም የደርግ ወገን የነበርን ልንኾን እንችላለን፤ የኦነግ እና የመኢሕድ ጥብቅ አፍቃሪዎች የመኖራችንን ያህል፣ የኢሕአዴግ ወይም የግንቦት ሰባት ደጋፊም ጥቂት ሰው አይደለም። የማንም ለመኾን የማይፈልግና ያልኾነም ሊኖር ይችላል። የንጉሡ ሥርዓት ከሁሉ የተሻለ ነው ብሎ የሚያምን ወይም ደግሞ ጭራሽ ከዚህ በፊት ታስቦ የማያውቅ መንገድ አመላካች ርእይ አይኖርም ብለን ማሰብ የለብንም። አገርን የሚያህል ትልቅ አደራ አብረን ከመሸከማችን በፊት አጠገባችን ያለውም በዘሩ፣ በሃይማኖቱ ወይም በፖለቲካ አመለካከቱ፣ ከእኛ ጋራ የማይመስለውን ወይም በተቃርኖ ቦታ የቆመ የመሰለንን ወድማችንንና እኅታችንን ማቀፍና መቀበል እንማር። ይህን በማድረጋችን እምነታችንን ካድን ወይም አቋማችንን ለቀቅን ማለት ሳይኾን፣ ልባችንን በማስፋት ጠብባን የተሰደድንባትን ውድ አገራችንን፣ ለእኛ ብቻ ሳይኾን፣ ለብዙ ሚሊዮኖች አሰፋናት ማለት ነው።

ወደድንም ጠላን፣ ኢትዮጵያዊነት ተፈትሎ የተሸመነበት ድርና ማግ፣ ባለአንድ ቀለም ነጠላ ሳይኾን፣ በሕብረ ቀለማት ያሸበረቀ አውታረ ብዙ ረቂቅ ጥበብ ነው፡፡ የዘር ማንነት ለያየው ያልነው ሕዝብ፣ በእምነት ድልድይ ተሻግሮ ሲዛመድ እናገኘዋለን፡፡ በእምነት አጥር ቅጥር ገንብቶ እዚያና እዚህ ተራራቀ ስንል፣ በጋብቻ እና በኑሮ ተዛምዶና ተጎራብቶ፣ ተቀራርቦና ተቀላቅሎ መኖሩን እናያለን፡፡ ለዚህም ነው ኢትዮጵያችን፣ ከመደመር ውጭ፣ ከአብሮነት፣ ከአንድነት እና ከኅብረት ውጭ ሌላ አማራጭ የላትም የምንለው፡፡ ብዙ ነን፤ ነገር ግን እንደ አንድ እንነሣ!! ልዩ ልዩ ነን፤ ነገር ግን የኅብር ድምፃችንን እናሰማ!! ልዩ ልዩ ባህሎቻችንን፣ እምነቶቻችንን፣ ታሪኮቻችንን፣ ቋንቋዎቻችንን፣ ማንነቶቻችንን እንደምርና ለሁላችንም የምትኾን አንዲት ታላቅ አገር ኢትዮጵያን እንገንባ!!

ከመበታተን፣ ከመከፋፈልና ወደ ትናንሽነት ከመለወጥ ይልቅ የሚያዋጣን ተደምረን መዝለቅ ነው፡፡ ዘመኑ የመደመር፣ የፍቅር፣ የይቅርታ፣ የምሕረት፣ የመቻቻል እና የአብሮነት ነው፡፡

መደመር ስንል፥ ከቂም ከበቀል እና ከጥላቻ፣ ለዘመናት ሲያባላን ከነበረው፣ ሲከፋፍለን ከኖረው ክፋት፣ ተንኮል እና ምቀኝነት እንላቀቅ ማለታችን ነው፡፡

መደመር ስንል፣ ትላንት በታሪካችን ውስጥ በተደጋጋሚ ሲከሡቱ ከኖሩት ኋላ ቀር አስተሳሰቦች፣ መናቆሮች፣ የጅምላ እና የተናጠል ጥላቻዎች መውጣት ማለት ነው፡፡ እንደመር ስንል፣ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን በማስወገድ፣ ሰው ሰው በመኾኑ ብቻ ለክብሩ እና ለነጻነቱ መከበር ዘብ ይቁም ማለታችን ነው፡፡

እንደመር ስንል፣ ከዜሮ ድምር ጨዋታ ወጥተን በአንድነት እና በአብሮነት መንገድ፣ ባለን ላይ በመጨመር ወደ ከፍታው መዝለቅ ማለት ነው፡፡ አስቸጋሪውን ዘመን ለመሻገር ከፈለግን፣ ከምሕረት እና ከይቅርታ የተሻለ መፍትሔ አናገኝም፡፡

ይቅርታ፣ ያለፈውን ስለ ፍቅር እና ስለ ሰላም ማስቀረት ነው። እርቅ ደግሞ፣ ስለ ጋራ ብልጽግና እና ነጻነት ያለውን በማረቅ ማስተካከል ነው። ብልጽግና ማለት የፍቅር እና የሰላም፣ የአንድነት እና የኅብረት ባለጸጋ የኾኑ ሰዎች የሚፈጥሩት እውነተኛ ሀብት ነው። ነጻነት ደግሞ፣ የሰውን ዋጋ እና ክብር የተረዱ፣ ሰውን በሰውነቱ የሚያከብሩ፣ ከእኔ ይልቅ እኛን የሚያስቀድሙ፣ ከራሳቸው በላይ አገራቸውን፣ ከግላቸውም ጥቅም ይልቅ የሌሎችን ፍላጎት ያስበለጡ ሰዎች የሚያጠልቁት የሥልጣኔ ዘውድ ነው።

በአዲሱ የለውጥ ጉዞ የጀመርነው ርምጃ፣ አገራችንን ልናፈርሳት ሳይኾን ልንሠራት፣ በድህነት እና በጦርነት ወይም በረኀብ እና በጥላቻችን፣ የዓለም መሳለቂያ ልናደርጋት ሳይኾን፣ በፍቅር ተግተንና ተዋደን በመሥራታችን የአፍሪካ ፊተኛ የዓለም ቀደምት የምናደርግበት እመርታ ነው። የቀደመ ታሪኳን እያወራን፣ የአሁን ማንነቷን ጥላሸት ልንቀባው ሳይኾን፣ የሚመጣው ትውልድ ሁሉ ቀና ብሎ የሚሔድበትንና ይህ እኮ በእኛ ትውልድ ጊዜ ሠርተን፣ እናት አገራችንን ያለበስናት የክብር ሸማ ነው፤ የምንለውን አንጸባራቂ ታሪክ እንሥራ።

ለዚህም እናት አገራችሁ፣ በሮቿን ከፍታ እጆቿን ዘርግታ፣ ያስተላለፈችላችሁን ጥሪ ለማድረስ ነው እዚህ የመጣኹት። በዚያ ያሉ ኢትዮጵያውንያን ወንድሞቻችሁ እና እኅቶቻችሁ በናፍቆት ይጠብቋችኋል።

ከምትኖሩበት አገር አንጻር፣ አገራችሁን እያያችሁና እያነጻጸራችሁ ማማረር፣ መበሳጨት እና ተስፋ መቁረጥ ውጤት አያመጣልንም:: ቁጭት ግን ሊፈጥርባችሁ ይገባል፤ ለምን እንዲህ ኾን? የሚል ቁጭት መፍጠር አለበት:: እነዚህ የምታደንቋቸው አገሮች፣ ከሰማይ ወርደው ከምድር ፈልቀው እንዲህ አልኾኑም:: በዜጎቻቸው ያላሰለሰ ጥረት፣ ትጋትና እልክ አስጨራሽ ትግል ነው ለዚህ የደረሱት:: የአገሮቹ ዕድገት፣ ምን ዓይነት አገር ወዳድና ትጉሃን ዜጎች እንደነበሯቸውና እንዳሏቸው ማሳያ ናቸው:: እኛም እንችላለን:: አገራችንን ከዚህ በላይ ማሳደግ እንችላለን:: ይህ የሚኾነው ግን በማማረር፣ ተስፋ በመቁረጥ እና በመቆዘም አይደለም፤ ሰልፉ ውስጥ ገብቶ የድርሻን በማበርከት እንጂ::

የዳያስጶራውን ጥያቄዎች የምንመልሰው፣ ከእናንተ ገንዘባችሁን ፈልገን አይደለም:: አገራችሁ የምትፈልገው እናንተን ነው:: የዳያስጶራው ጥያቄዎች፣ የሕዝባችን ጥያቄዎች ናቸው:: የኢትዮጵያውያን ጥያቄዎች ናቸው:: በዳያስጶራነታችሁ የምታነሧቸው ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ቢኾኑም፣ የጥያቄዎቹ መመለስ የሚጠቅመው ግን ሁላችንንም ነው:: ሸሚዝ ሲለበስ በግማሽ አካል ላይ ቢያርፍም እንኳን፣ ጥቅሙ ግን ለሰውነታችን በሙሉ ነውና::

የመንታ ዜግነት ጉዳይ፣ የሕገ መንግሥት ማሻሻያን የሚጠይቅ በመኾኑ አብረን የምናየው ይኾናል፡ እስከዚያ ድረስ ግን፣ የቢጫ ካርድን የተመለከተውን መመሪያ እና አሠራር እያሻሻልነው ነው::

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ጉዳዮች ለማከናወን ራሱን የቻለ ኢንስትቲዩት እንዲቋቋም እያሰብንበት ነው:: የእናንተን ጥያቄዎች እና ፍላጎቶች፣ ለአገር በሚጠቅም መንገድ ለመከታተል ይመቻል::

በዚህ ተቋምም፣ በዋናነት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ በየደረጃው በአመራርነት እንዲሳተፉ ለማድረግ ታስቧል፡፡ የምሕረት ዐዋጁ አንዱ ጥቅም፣ በልዩ ልዩ ወንጀሎች ተከሠው እና ተፈርዶባቸው በውጭ አገር የሚኖሩ ወገኖቻችንን ጫና ማንሣት ነው፡፡ ልንከሠስ እንችላለን፣ ወይም ተከሠናል ብለው በውጭ አገር የሚገኙ ወገኖችም፣ ይህን ዕድል እንዲጠቀሙበት በዚሁ አጋጣሚ አደራ እላለሁ፡፡

ኤምባሲዎቻችን አንዱ ሓላፊነታቸው፣ በውጭ የሚኖሩ ወገኖቻችንን ጉዳይ መከታተል ነው፡፡ የእነዚህ ኤምባሲዎች አሠራር፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ደረጃውን የጠበቀና ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መንገድ እንዲዋቀሩና አሠራራቸው እንዲሻሻል እናደርጋለን፡፡ በዚህ ማሻሻያም የዕውቀት፣ የቴክኖሎጂ እና የሞያ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን፣ ከእናት አገራቸው የተሻለች አገር አያገኙም፡፡ ለዚህም ነው፣ እጅግ ባዕለ ጸጋ በኾኑ አገሮች ኾናችሁ እንኳን የአገራችሁ ነገር የሚያንገበግባችሁ፡፡ ያለፈውን በይቅር ባይነት እለፉት፤ የሚመጣውን በተስፋ ተቀበሉት፡፡ ቋንቋዎቻችን፣ ባህሎቻችን፣ እምነቶቻችን፥ የውበት እና የእሴት ምንጮቻችን እንጂ የግጭት መነሻዎቻችን አይኹኑ፡፡ መቼም ይህን ያህል ሺሕ ዓመት አብረን ስንኖር ሳንጋጭ አልኖርንም፤ ግጭቶቻችንን እየፈታን ኖርን እንጂ፡፡ ከጨለማ ይልቅ ለብርሃን፣ ከጠብ ይልቅ ለፍቅር፣ ከመለያየት ይልቅ ለመደመር፣ ከጥቃቅን ግጭቶች ይልቅ ለታላላቅ የአንድነት ስኬቶች ትኩረት እንስጥ፡፡ አንድ ላይ ኾነን የማናርመው ስሕተት፣ የማናስተካክለው ጥፋት፣ የማንሞላው ጎዶሎ፣ የማናቃናው ጥመት የለም፡፡

**አመሰግናለሁ።**

# የአሜሪካ ሎስ አንጀለስ ንግግር

**ሐምሌ 23/2010 ዓ.ም.**

የኪነ ጥበብ እና የአዲስ ሐሳቦች ማዕከል በኾነችውና የአገራችንን መልካም አየር በምታስታውሰው ሎስ አንጀለስ ካሊፎርያ እና አካባቢዋ የምትኖሩና ከተለያዩ ከተሞች እና ግዛቶች የመጣችኹ ውድ የአገሬ ልጆች ኢትዮጵያውያን፤

እንደዚህ ባለ የሞቀ አቀባበል ስለ ተቀበላችሁኝና ለአገራችሁም ስላሳያችሁት ወደር የሌለው ፍቅር የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ለመግለጽ ቃላት ያጥሩኛል።

የአትላንቲክን ውቅያኖስ ጠረፍ ተከትለው በተገጠገጡ የአሜሪካ ምሥራቃዊ ከተሞች የሚኖሩ በዋሽንግተን ዲሲ ተሰብስበው ከተቀበሉን የኢትዮጵያ ልጆች ጋራ እጅግ መልካም የምክክር እና የትውውቅ ጊዜ ነበረን። እንደ እነርሱ ሁሉ ለእናንተም፣ ከአገራችሁ እና ከሕዝባችሁ የተላከላችሁን የከበረ ሰላምታ ላቀርብላችሁ እወዳለሁ። ዛሬ ደግሞ በምዕራቡ ሰላማዊ የፓስፊክ ዳርቻ ካላችሁ ከእናንተ ወገኖቼ ጋራ ለመተያየት እና ለመወያየት ይህን ጊዜ በማግኘቴ ራሴን እንደ ዕድለኛ እቆጥራለሁ።

እዚህ መምጣት ባትችሉም በካሊፎርኒያ፣ በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች፣ በካናዳ እና በመላው ዓለም ያላችሁ ኢትዮጵያውያን እኅቶቼ እና ወንድሞቼ፣ እናቶቼ እና አባቶቼ፣ ዛሬ በፊታችሁ የቆምኹት፣ ባሕር እና ውቅያኖስ ሳይገድበን፣ የጊዜ መለያየት እና የቦታ ርቀት ሳያራርቀን፣ በአንዲቱ ውድ አገራችን የፍቅር ገመድ

ታስረንና ተደምረን፣ የለያየንን ግንብ እናፍርስ የሚያቀራርበንን ድልድይ እንሥራ፤ የሚል አገራዊ ጥሪ ላቀርብላችሁ ነው።

በሆሊውድ እና በሲልከን ቫሊ ተከብባችሁ ለምትኖሩ ለእናንተ የሐሳብን ጉልበት እና የቃልን ብርቱ ኀይል ማስረዳት የለብኝም። ሐሳብ፥ በቃላት፣ በምስል እና በድምፅ ተከሽኖ በረቀቀ ቴክኖሎጂ እየተወነጨፈ ዓለምን የሚቀርፀው፣ ሁሉን የአሜሪካ ምርኮኛ እና አድናቂ ያደረገው፣ ከዚሁ ከእናንተው ደጃፍ ከካሊፎርኒያ ግዛት ነው፤ ገንዘብም ለሐሳብ ይገዛልና፡፡ ካሊፎርኒያ ያለምክንያት፣ ከዓለም ስድስተኛ የኾነ ብርቱ ምጣኔ ሀብት ያላት ግዛት አልኾነችም። በዚሁ ልክ ደግሞ፣ ዓለምንና ታላላቅ ሥልጣኔዎችንም ያጠፋው፣ በቃላት ተከሽኖ የተዘራ ሐሳብ ነው። አገሩን ጥሎ የኮበለለ ሰው ሁሉ፣ ቀዬውን ያስጣለውም ኾነ ከማያውቀው ምድር አምጥቶ ያስቀረው፣ ሐሳብ የተሸከሙ ቃላት ጦስ ነው።

እኛስ በመካከላችን፣ ለ0ሥርት ዓመታት ጋርዶንና ከፋፍሎን የቆመው የመለያየት እና የጥላቻ ግድግዳ፣ መቼ ከድንጋይ እና ከጡብ ወይም ከብረት እና ከአርማታ የተሠራ ኾነ። እንደሱማ ቢኾን፣ ማፍረሱ በቀለለ ነበር። የልዩነትን ገደል በድልድይ መግጠም እና መቀራረብ ሲገባን በጠብ እና በጦርነት፣ በመናናቅ እና በመገፋፋት፣ በውስጣችን ብሎም በመካከላችን የተገነባውን ግንብ አበሳ እና ዳፋ መገፍገፉ ቢበቃን ይሻላል። ሕዝቦቿ ውብ እና ኩሩ፣ አየሯ እና መልከዓ ምድሯ ማራኪ፣ በሆዷ የተሸከመችው ብልጽግና ልክ የሌለው አገራችንን፣ በምሬት ጥለን እንድንኮበልል ያደረገን፣ መሔጃ አጥተው በአገር ቤት ያሉትንም በምሬት የሞላው፣ የገነባነው የቂም እና የበቀል፣ የስግብግብነት እና የራስ ወዳድነት ግንብ ካልኾነ ምን ሊኾን ይችላል?

ሰው የኔቫዳ በረሓንና የአላስካን በረዶ፣ ምድረ ገነት አድርጎ ብልጽግና ሲዝቅበት፣ እኛ ግን በለምለሙ መሬት ላይ እርስ በርስ ተላለቅን። ለስንት ሊተርፍ የሚችል ሀብት ባለባት ምድር አብረን መኖር ተስኖን፣ በባዕድ ምድር ኪስ ለማትሞላ ምንዳ ክብራችንን ተገፈፍን።

በየበረሓው እና ባሕሩ፣ ወጣቶቻችን የአውሬ እና የግፈኞች ሲሳይ ኾነው እንደ ወጡ ቀሩ። በማያውቁት አገር ጠያቂ ዘመድ ሳይኖራቸው በእስር ቤት በስብሰው ቀሩ። ሌሎች ደግሞ፣ የቤተሰቦቻቸው እና የቀዬአቸው ናፍቆት በዐይናቸው ላይ ቀን ከሌት እንደ ሔደባቸው ዛሬም ይንከራተታሉ። ከእናንተ እንደ ብዙዎቹ፣ ኑሮ ሞልቶላቸው በሥጋ ምቾት የሚኖሩት ደግሞ፣ የሰው ቤት የሰው ነውና ምን ቢመች ማን እንደ አገር እያሉ የአገራቸው እና የሕዝባቸው ጉዳይ እያብከነከናቸው ቀን ከሌት ወደ ምድራቸው የሚመልሱባትን ቀን ይናፍቃሉ። ታዲያ ይህን በመካከላችን ያቆምነውን፣ አገር አልባ ያደረገንን የፍርሃት እና የጥላቻ ግንብ መቼ ነው የምንንደው? ወደ ምድራችን ተመልሰን፣ ለአንዲት ኢትዮጵያ፣ አንቺ ትብስ አንተ ትብስ ተባብለን እንድንኖር የሚያቀራርበንን ድልድይ የምንሠራውስ መቼ ነው?

እኛ ከሦስት ሺሕ ዘመናት በላይ የሚቆጠርላት ታሪካዊት አገር አለችን እንላለን። ከተመሠረተች ገና ኹለት መቶ ኀምሳ ዓመት ባልኾናት፣ በዓለም ላይ ኀያል እና ገናና አገር ውስጥ እንደ ኖረ ሰው የምንማረው ምንድን ነው? ለሰው ልጅ ሕይወት፣ ክብር፣ እኩልነት እና ፈጣሪ ለሰጠው ነጻነት እና ደስታ መከበር ባለ እምነት ላይ የመሠረቱት ድልድይ፣ ዛሬ አሜሪካንን የዓለም አውራ እና የሕዝቦቿ መኩርያ እንድትኾን አድርጓታል። የቀደሙት አገር አቅኚዎች፣ ሕልማቸውን ፍለጋ፣ ያልታወቀውን የምዕራብ ዳርቻ ፍለጋ ብዙ ዋጋን ከፍለዋል። የዛሬዋ አሜሪካ፣ በብዙ አሜሪካውያን የአእምሮ እና የጉልበት፣ የገንዘብ እና የምቾት ብሎም የሕይወት ዋጋ ተከፍሎባት ነው የኾነችውን የኾነችው። እኛስ ለኢትዮጵያችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከድህነት አረንቋ መውጣት እና በዓለም ስም ካላቸው አገሮች ተርታ እንደገና ቀና ብላ መሔድ ያለንን ሳንሰስት እና ሳንዘገይ የምንሰጠው መቼ ነው?

ሕግ በነገሠበትና ሰው በሚከበርበት አገር የምትኖሩ እናንተ ወገኖቼ ሆይ፣ መቼ ነው ይህን ውብ አኗኗር ለአገራችሁ እንደ ስጦታ ይዛችሁ የምትመጡት? መብትን መጠየቅ እና ሓላፊነትን መወጣት ምን እንደ ኾነ ኖራችሁ ያያችሁ የአገራችን ሰዎች ሆይ፣ መቼ ነው ለእናንተ ያገኛችኹትን፣ በተስፋ መቁረጥ እና በሥቃይ ላለው ሕዝባችሁ የምታካፍሉት እና በምሳሌነት የምትመሩት?

ውኃ እና ኤሌክትሪክ በማይጠፋበት፣ ኢንተርኔት እና ስልክ ብርቅ ባልኾነበት አገር የምትኖሩ ሕዝቦቻችን ሆይ፣ መቼ ነው ሕዝባችሁን ለዚህ ማዕርግ የምታበቁት? ሰው ሁሉ የድርሻውን ታክስ በሚከፍልበትና የልፋቱን በሚያገኝበት አገር የምትኖሩ፣ በየብስ እና በአየር በታቀደበት ሰዓት በሚደረስበት አገር የምትኖሩ ሥልጡን ሕዝቦቻችን ሆይ፣ መቼ ነው ታዲያ ቁርሱን በልቶ ለምሳው ሆዱን የሚያከውን፣ ደግሞም አንዲት እንስራ የሚጠጣ ቆሻሻ ውኃ ፍለጋ በባዶ እግሯ ስድስት እና ስምንት ሰዓታት የምትንከራተተውን የአገራችሁን ልጅ በቃሽ የምትሏት?

ልጆቻችሁን በሞቀ አልጋ ውስጥ የምታስተኙ እና ስመ ጥር ትምህርት ቤት የምትልኩ ደግ ወላጆች ሆይ፣ መቼ ነው በየጎዳናው የወደቁ፣ በዐሥር እና በዐሥራ አንድ ዓመታቸው መደመር እና መቀነስ፣ ማንበብ እና መጻፍ ለመማር እንኳ ዕድል ያላገኙ የአገራችሁን ሕፃናት አለሁላችሁ የምትሏቸው?

ምናልባት ይህን ሁሉ መንግሥት ይሥራው ትሉ ከኾነ ተሳስታችኋል፤ መለወጥ እና ማደግ ከፈለግን መንግሥት ሕዝብ ነው፤ ሕዝብም እናንተ ናችሁ። ጥያቄው የሁል ጊዜ ሕልማችሁን ለአገራችኹ እና ለሕዝባችኹ የምትፈጽሙት መቼ ነው? አሁን ያለችን አገር፣ በድህነት የተጎሳቆለች፣ በገዛ ልጆቿ ስግብግብነት እና ራስ ወዳድነት ተግጣ ተግጣ አጥንቷ የቀረ፣ ልጆቿን የምትማፀን ምስኪን እናት ናት። ችግርን ሸሽታችሁም ይኹን ዕድልን አግኝታችሁ ከአገራችሁ የወጣችሁት፣ እናት አገር የሁላችንም ናት። ስለዚህም ሁላችንም አለንልሽ እንበላት።

ዛሬ፣ ኻያ ዘጠኝ ሚሊዮን ወጣቶች እና አዳጊዎች በትምህርት ገበታ ላይ ሲኾኑ፣ ከዚህ ውስጥ ኹለት መቶ ሺሕ ያህሉ በየዓመቱ ከየዩኒቨርስቲው ይመረቃሉ። እነዚህ ሁሉ አዳጊ የአገራችን ልጆች እና የትምህርት ተቋማት ማንን የሚጠብቁ ይመስሏችኋል? መቼ ነው የአገራችንን የትምህርት ልቀት እና ጥራት፣ ዓለም ከደረሰበት ለማድረስ እና አፍሪካን የሚያጥለቀልቅ የተማረ ኀይል ለማምረት እንድንችል ለዚህ ቅዱስ ሥራ ራሳችሁን የምትሰጡት? መቼ ነው፣ በጥናት እና

ምርምር የገዘፈ ስም ያላቸውን ተቋማት ለማሳደግ ወደ አገራችሁ ታጥቃችሁ የምትመጡት?

አገራችን ኢትዮጵያ፣ ሳይንቲስት እና ነጋዴ፣ ሐኪም እና ፈላስፋ፣ መሐንዲስ እና ኢኮኖሚስት፣ ፖለቲከኛ እና ጠበቃ፣ መምህር እና ገበሬ... ሁሉንም ዓይነት ሞያ ያላቸውን በምግባር የተገሩ ሠራተኛ ልጆቿን ትጣራለች። ጥያቄው፣ መቼ ነው ለጥሪው መልስ ሰጥታችሁ አለሁ የምትሏት? በራስ ተነሣሽነትና በልበ ቁርጠኝነት፣ የአገራችንን ድህነት እና መልከ ብዙ እክሎች ሳትጸየፉና ሳታማርሩ በቁርጠኝነት ችግሯን ለመቅረፍ ራሳችሁን ለአገራችሁ የምትሰጡት መቼ ነው?

ነገር ግን ወገኖቼ ሆይ፣ እጅግ በጣም መፍጠን አለብን፡፡ እስከ ዛሬ የትላንቱን ትውልድ ስንወቅስ ከነገው ትውልድ የተበደርነው እጅግ ብዙ ነው። ኢትዮጵያን የመሰለች ታላቅ አገር አሁን ያለችበት ደረጃ በፍጹም አይመጥናትም፡፡ የአገራችን ጉስቁልና እና ድህነት፣ የእርግማን ሳይኾን፣ እኛ ልጆቿ የሚመጥናትን ሥራ ባለመሥራታችን የተፈጠረ ነው፡፡

ከምእት ዓመታት በፊት ግዙፍ አለት ፈልፍላ ቤተ መቅደስ ላነፀች አገር፣ ለዜጎቿ መጠልያ እና የመኖሪያ ቤት የሰማይ ያህል መራቅ አልነበረበትም፡፡ አያሌ እህሎችንና በጣዕማቸው አጀብ ያሰኙ ምግቦችን ለዓለም ያበረከተች ምድር፣ የሕፃናቷን በረኀብ መቀንጨር፣ በዓለም መድረክ ላይ የድርቅ ምድር ተብላ መጠራቷን እያየንና እየሰማን ዝም ብለን ልናይ የምንችልበት ምን ኀሊና አለን?

ገዳን የመሰለ ለዘመናት የዘለቀ የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓት ላላት ሥልጡን አገር፣ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እና ፍትሐዊ አስተዳደር ብርቅ መኾኑ የሚያሳፈር ነው፤ በድንጋይ ላይ ከሺሕ ዓመታት በፊት ስትጽፍ የነበረች አገር፣ ለጋዜጦች እና መጽሔቶች ድርቅ መጋለጥ እና ብዙኀኑ ልጆቿ ማንበብ እና መጻፍ እንኳ አለመቻላቸውን እያወቅን በሰላም መተኛት እና በባዶ ኩራት መወጠር አንችልም፤ የነቢዩ መሐመድን ተከታዮች ለቁሬይሾች አልሰጥም ብላ ሰብአዊ መብታቸውን ያከበረች አገር፣ በሰብአዊ መብቶች ጥሰት መወቀስ አልነበረባትም፤ የታላላቅ ወንዞች መነሻ፣ የሱዳንን መስኖ እና የግብጽን ሥልጣኔ ለዝንተ ዓለም ስታጠጣ

የኖረች የዓባይ እና የተከዜ፣ የባሮ እና የዋቢሸበሌ እናት ኢትዮጵያ፣ በመጠጥ ውኃ ዕጦት ላንቃዋ መድረቅ አልነበረባትም፤ ከወንዞቿ ፏፏቴ እና የፍል ውኃዎቿ ብርቱ እንፋሎቶች ባሻገር፣ አሜሪካንን ያናወጡ ስውር ነፋሶች መነሻ የኾነች ምድር፣ የኤሌክትሪክ መብራት መቆራረጥ እና ብርቅ መኾን ዜጎቿን ማስቸገር አልነበረበትም፤ ግን ደግሞ ያለው ሊካድ የማይችል ሁኔታ ይኸው ነው፡፡

በእውነት ይህን መቀየር አይቻልምን? ብለን እንጠይቅ፡፡ እናንተን የመሰሉ የተማሩ እና በባዕድ ምድር በቀን እስከ ዐሥራ ስድስት ሰዓት፣ ከሳምንት ሳምንት ታከተኝ ሳይሉ የምትታትሩ ልጆች እያሏት፣ ይህን መለወጥ አንችልም? ተቆጭተን ከተነሣን፣ ተባብረን ከሠራን፣ እጅ ለእጅ ከተያያዝን፣ ጥቃቅኑን ችግር እየተራመድን ለታላቁ የአገር ጥቅም በጋራ ከተሰለፍን፣ ዕውቀታችንንና ገንዘባችንን ለምንወዳት እናት አገራችን ብልጽግና ካስተባበርን፣ ስለ ምን አንችልም? ትላንት ፀሐይ ከሞቀ በኋላ ከእኛ ዘግይተው የተነሡ፣ ከእኛ እጅግ ዘግይተው የተፈጠሩ አገሮች ጭምር ተባብረው ሠርተው አይደል እንዴ እዚህ የደረሱት? ዛሬ የተከበሩ እና አንቱ የተባሉ አገሮች በመኾን የቱሪስት መዳረሻ፣ የቴክኖሎጂ መፈልፈያ፣ የሙዓለ ነዋይ ማፍሰሻ፣ የሀብት እና የዓለም ቱጃር ነጋዴዎች መናኸርያ የኾኑት፥ እንደ ሲንጋፖር እና ኮሪያ፣ የተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶች እና ብራዚል ያሉ አገሮች ሕያው ምስክሮች ናቸው። ይህን እኛስ ማድረግ አንችልም?

እናንት በውጭ ያላችኹ ወገኖቼ፣ እናንተ ለኢትዮጵያ የአብራኳ ክፋይ እና ውድ ልጆቿ እንጂ የሩቅ፣ የዘመድ ወይም የጉዲፈቻ እና የእንጀራ ልጆቿ አይደላችሁም፡፡ ቤተኛ እና ባለቤት እንጂ ታዛቢ የውጭ ሰዎች አይደላችሁም!! እንዲህና እንዲያ መደረግ ነበረበት፤ እንዲህና እንዲያ ቢያደርጉ ጥሩ ነው፤ መንግሥት ይህንና ያን ካላደረገ እያሉ በዛቻ ጣት መጠቋቆም የልጆች ተግባር አይደለም፡፡ መኾን ያለበትን፣ መደረግ የሚገባውን፣ ወደ አገራችኹ ገብታችኹ እናንተው አድርጉት፤ ኑና ተሳተፉ፤ ኑና የድርሻችሁን ተወጡ፡፡ ታዛቢዎች፣ የሩቅ አራሚዎች እና የማዶ ተቺዎች አትኹኑ፤ ያ ዘመን አብቅቷልና።

በቀና አስተሳሰባችሁ እና በተሳለ ልምዳችሁ ጠማማውን አቃኑ። ከተካበተ ዕውቀታችሁ እና ከሞላ ጎተራችሁ የአገራችሁን ጎዶሎ ካዝና እና የነጠፈ የዕውቀት ጓዳ ሙሉ። ኋላ ቀር ኹኖ አላስኖርና አላሳድግ ያለውን አሠራር እና ልማድ ሳትጠየፉ፣ በርጋታ እና በትዕግሥት አዘምኑት። 'ፎር ጉድ ብዬ አገሬ ገባኹ' ያላችኹበት ቃላችኹና ከዚህ የተሸኛችኹበት የድግስ ሳሕን ሳይደርቅ 'ወይ ጉድ' በማለት ተማራችኹ አትመለሱ። ስሕተተኛውን ከማማት እና ከማሸሚጠጥ ይልቅ አርሙት። ጥፋተኛውን በምን አገባኝ ማለፍ ወይም የምትፈልጉትን እንዲሠራላችኹ በእጅ መንሻ ማባበል መፍትሔ የለውም። ይልቁንም፣ ፊት ለፊት በመጋፈጥ ልክ እዚኽ እንደምታደርጉት ስሕተቱን ግለጡት፤ በድኻው እና በሠራተኛው እምባ የሚቀልደውን ወንጀለኛ አጋልጡት። ተግቶ ለሚሠራው ሞራል እና ክብር ስጡት።

እናንት ልጆቼ ያልሠራችኹላትን ማን ይሠራላታል? እንደምታውቁት ኹላችንም ከጊዜ ጋራ አላፊዎች ነን፤ ነገር ግን አላፊነታችንን ከተረዳን ሓላፊነትን መቀበል አለብን። ሓላፊነታችንን የምንሸሽ ከኾነ ግን እኛ ካለፍን በኋላ ለሚመጣው ትውልድ የምንተወው ዳፋ ብዙ ነው። አለበለዚያ ተርቦ ምግብ ሲፈልግ ሲፈልግ፣ 'እናንተ ብሉ፤ የልጅ ልጆቻችሁ ይከፍላሉ' ከሚል ምግብ ቤት ገብቶ እንደ ተመገበው ሰው መኾናችን አይቀርም። እርሱ አለመከፈሉ አማልሎት የፈለገውን ሲበላ፣ ሲያድፋፋና ለሌላው ሲጋብዝ አምሽቶ ሊወጣ ሲል አስተናጋጇ የተቆለለ ሒሳቡን አምጥታ ብታስታቅፈው በቁጣ እየተመናጨረ፣ "እናንተ ብሉ፤ የልጅ ልጆቻችሁ ይከፍላሉ አላላችሁም እንዴ? ይኼ ሁሉ ምንድን ነው? የኔ ሒሳብ እንደምንስ ቢደመር እንዴት ነው ይኼን የሚያኽለው?" ብሎ ሲያንባርቅባት፣ አስተናጋጇም በትሕትና፣ "ልክ ነው፤ እርስዎ የበሉበትንና የጋበዙበትን የልጅ ልጆችዎ ናቸው የሚከፍሉት፤ ይኼ ግን እርስዎ መክፈል ያለብዎ አያቶችዎ የበሉት እና የጋበዙበት ሒሳብ ነው፤" ብላ ከነዕዳው እንደተወችው በላተኛ መኾን የለብንም። ያለፈውን ትውልድ ሒሳብ መክፈል እንጂ፣ ለልጆቻችን ሊወጡ የማይችሉትን ዕዳ ትተን መሔድ የለብንም።

ይህ እንዲኾን ከፈለግን፣ ኹሉ ሐሳብ ሰጪ፣ ኹሉ 'እንዲህ ቢደረግ፣ ለምን ይኼን አይሠሩም?' ባይ መኾን የለበትም። ሐሳብ የምትሰጡት ለማን ነው? የምትሰጡትን ሐሳብ፣ ገንዘብ እና ሠራተኛ ከየት መጥቶ እንዲሠራ ነው የምትፈልጉት? ወገኖቼ፣ ሐሳብም ኾነ ሓላፊነት ሰጭም ተቀባይም እኛው ነን፡፡ መመካከር እንጂ መወራወር የሚያዋጣን አይደለም፡፡ ኑ፤ ለዚህ የሚኾን አሠራር እና መዋቅር፣ ሕግ እና ሥርዓት፣ ግለሰብ እና ማኅበረሰብ፣ ትውልድ እና ኅብረተሰብ... አብረን እንገንባ፡፡ ይህ ማለት ግን፣ የምትሰጡንን ሐሳብ መናቃችንና ማጥላላታችን አይደለም። አንዱና ዋናው ድህነታችን የሐሳብ መኾኑን መቼም አንዘነጋውም። ኾኖም ሐሳቡን ብቻ ሳይኾን ማሰቢያውንና አሳቢውንም ደምረን እውነተኛ ለውጥ እናምጣ ለማለት ነው። የማንሸከመውን ሐሳብ አንወርውር፤ተጠያቂ ለመኾን ፈቃደኛ ያልኾንበትን ሥራ በሌሎች ላይ አንጫን። ለሰጠነው ሐሳብ፣ ባለቤት እና ተመስጋኝ ብቻ ሳይኾን፣ ተጠያቂ እና ተሸካሚም እንኹን።

አገራችን የሚጠቀሙባትንና አምጪ አምጪ እያሉ የሚግጧትን ሳይኾን፣ የሚያስታምሟትን ነርሶችንና የሚያክሟትን ሐኪሞች፣ የሚያንጿትን መሐንዲሶች እና አናጺ ግንበኞችን፤ የማይኖሩትንና በጣታቸው እንኳ ለመንካት የሚጠየፉትን በሕዝብ ላይ የሚጭኑ ግብዝ የእምነት መሪዎችን ሳይኾን፣ የሞራል እና የሕይወት ምሳሌነት ያላቸውን አባቶችንና እናቶችን፤ ደስኳሪ ወሬኛ የፖለቲካ አነብናቢዎችን ሳይኾን፣ ሕዝቧ የበላውን በልተው፣ ያደረበት አድረው መርዝ ሰንኮፉን የሚያወጡለትንና በቀናነት የሚመሩትን ሥልጡን መሪ ልጆችን ትሻለች። ለውጥ እና ነውጥ አገሪቱን በአናወጠበት የ1960ዎቹ ዐሥርት፣ አሜሪካንን የመሩት ወጣቱ ጆን ኤፍ ኬኔዲ እንዳሉት፣ "አገሬ ለእኔ ምን አደረገችልኝ ሳይኾን፣ እኔ ለአገሬ ምን አደረግኹላት?" ከምንልበት፣ ታሪክን በላባችንና በደማችን እንጥፍጣፊ ከምንጽፍበት አስደናቂ ታሪካዊ ጊዜ ላይ እንዳለን ከውስጥ ከልቤ ልነግራችኹ እወዳለኹ!!

አንዳችን ጠያቂ ሌላችን መላሽ፣ አንዳችን ተቺ ሌሎቻችን ተተቺ፣ አንዳችን ተከሣሽ ሌሎቻችን ፈራጆች ልንኾን አንችልም፡፡ ኢትዮጵያ የኹላችን ናትና፣ የጋራ እናታችንን ያጎበጣትን ሸክም ኑ አብረን እንሸከመው። መሥዋዕቱን አብረን ከፍለን፣ ድሉንም አብረን እናጣጥመው፡፡ የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲዳብር፣ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ እንዲሻሻል፣ ሐሳብን በነጻነት የመግለጥ መብት በሚገባ እንዲተገበር መሠረቱን አብረን እንጣል። የክልሎቻችን ድንበሮች የሚያራርቁና እና የሚያቆራቁሱን ግንቦች ሳይኾኑ፣ ልክ እዚህ እንደምትኖሩበት አገር ለተሻለና ለሠለጠነ አስተዳደር እና አሠራር የሚጠቅሙን ወሰኖች ብቻ ይኹኑ። በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ተዘዋውሮ ለመሥራት እና ለመኖር ኢትዮጵያዊነት ብቻ እንዲበቃ፣ በሕግ የበላይነት እና በኅሊና ዳኝነት ብቻ የሚሠራ ጠንካራ የፍትሕ ሥርዓት ናኝቶ ይውጣ። ማረሚያ ቤቶቻችን፣ የዜጎች ማረሚያ እንጂ፣ መታጎሪያ እና መሠቃያ እንዳይኾኑ በጀመርነው ቀና እና የላቀ የመደመር ጉዞ ተቀላቅለንና ተደምረን ወደፊት እንገሥግስ።

ይቅርታ እና ዕርቅ ለነገ የሚቀመጥ፣ ቅድመ ኹኔታ የሚደረግለት ጉዳይ አይደለም። የለያየንንና የከፋፈለንን ግንብ የምናፈርሰው፣ ያለፈውን በፈቃዳችን ይቅር ብለን ከልባችን በመተው፣ ቂምንና በቀልን፣ ዐይንን ላጠፋ ዐይንን የመደንቆልን ግፊት እምቢ በማለት በወደፊቱ ላይ በማተኮር ብቻ ነው። ፍትሕ እና ካሳ፣ ከይቅርታ እና ዕርቅ በኋላ እንጂ፣ እንደ ቀብድ እና ማስያዣ የምንጠይቃቸው የመብት ጉዳይ ተደርገው መታየት የለባቸውም። በቂም እና በቁርሾ፣ በጥላቻ እና በመወነጃጀል፣ በመኮራረፍ እና የሌላውን ስም በማጥፋት ማድረግ የምንችለውን ሁሉ ብናደርግም፣ ዛሬ ያለንበት ኹኔታ በተሳሳተ መንገድ ላይ ለመኾናችን የማያሻማ ምስክር ነው። እስኪ ይቅርታንና ፍቅርን እንሞክረው፤ እስኪ አንድነትንና ስለ ሌላው በጎ ማሰብን እንተግብረው።

ዓለም ብዙ ቢቀድመንም፣ ዛሬም ድኻ እና ኋላ ቀር እንደኾን ቢያስብም፣ ውጤቱን የሚወስነው ሌሎች ስለ እኛ የሚሉት ሳይኾን፣ እኔ እና እናንተ ከዚህ ወጥተን የምንናገረው እና የምናደርገው ነው። ስለዚህም፣ አብረን እንዳንኾን የጋረደንን የጥላቻ እና የፍራቻ ግንብ እናፍርሰው።

ተባበረን በአንድነት እና በእኩልነት ማደግ እንድንችል፣ የሚያሻግረንን የፍቅር ድልድይ እንገንባ። ከዚያም ኹላችንም ባለን ችሎታ እና ገንዘብ፣ ርእይ እና አቅም፣ እንደ ሞያችንና ስጦታችን፣ በግልም በአንድነትም ለአገራችን ያለንን እንስጥ፤ እናድርግ። ጊዜው ዛሬ ነው፤ ነገ የውጤት እንጂ የሥራ አይደለም። በይቅርታ ለዕርቅ፣በፍቅር ለአንድነት፣ በእኩልነት ለነጻነት፣ በሰላም ደግሞ ለብልጽግና ቆርጠን እንነሣ።

እኔ እዚህ የመጣኹት፣ ይኼን ጥሪ በአካል ተገኝቼ ላቀርብላችኹና "ግንቡን እናፍርስ፤ ድልድዩን እናድስ" የሚለውን የውድ እናት አገራችንን መልእክት፣ ለእናንተ ለልጆቿ ለማድረስ ነው።

**ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!**

**አመሰግናለሁ።**

# የአሜሪካ ሚኒሶታ ንግግር

**ሐምሌ 23/2010 ዓ.ም.**

በመንትዮቹ ከተሞች ሚኒያፖሊስ እና ሴይንት ፖል ሚኒሶታ ያላችሁ ውድ ወገኖቻችን፤ እንዲህ በጋለ እና እንኳንም ኢትዮጵያዊ ኾንኩ በሚያሰኝ መንገድ ስለ ተቀበላችሁኝ አመሰግናለኹ። ብዙ ኢትዮጵያውያን ከሚኖሩባቸው የአሜሪካን ግዛት አንዷ በኾነችው በሚኒሶታ በመገኘቴ የተሰማኝ ደስታ ወደር የለውም።

እንዲሁም በአሜሪካን አገር ከየግዛቱ እና ከየከተማው እንዲሁም፣ ከካናዳ እና ሌሎች አገሮች ብዙ ርቀት ተጉዛችኹ ወደ እዚህ በመምጣት ይህን ታሪካዊ ቀን ለመካፈል የመጣችኹ ኹሉ፣ እንኳን ደኅና መጣችኹ።

በመጀመሪያ፣ ከአገር ቤት የተላከላችኹን የከበረ ኢትዮጵያዊ ሰላምታ እና የፍቅር መልእክት፣ የራሴንም ጨምሬ ላቀርብላችኹ እወዳለኹ። እንደ ዋሽንግተን ዲሲ እና ሎስ አንጀለስ ኹሉ፣ በዚህ ታሪካዊ ጉዞ ወደ እናንተም ይዤው የመጣኹት መሪ ቃል እና ገዢ መልእክቴ አንድ ነው። እርሱም፣

**“ግንቡን እናፍርስ፤ ድልድዩን እንገንባ!”**

በብዙ የውጭ አገሮች በተለይ ደግሞ በአሜሪካ ውስጥ በስደት የሚኖረው ሕዝባችን፣ ለአገሩ ያለው ፍቅር እና ናፍቆት ከፍተኛ ነው። ይህንም ለማካካስ እንጀራውንና ክትፎውን፣ ጨጨብሳውንና ገንፎውን ከቻለ ከአገር ቤት፣ ካልኾነለትም አገሩ በአፈራው ግብዓት ቀምሞ ትንሿን ኢትዮጵያን ይፈጥራል።

የቀዬው እና የወንዙ ልጆች ከአሉበት ከተማ ሔዶ ይሰፍራል። እዚህም ብዙ ኦሮሞዎች፣ የኢትዮጵያ ሶማሌዎች እና የጎረቤታችን የሶማልያ ዜጎች መኖራችኹን ሰምቼያለኹ። በተጨማሪም፣ በአገራችን ለረጅም ጊዜ ሲካሔድ በቆየው የዴሞክራሲ እና የሰብአዊ መብቶች ትግል ውስጥ የሚኒያፖሊስ ከተማ አንቱ የተባሉ አንጋፋ እና ወጣት አክቲቪስቶችን ያፈራችና አቅፋ የያዘች ከተማ በመኾኗም ልትኮሩ ይገባል።

በአገራችን ታሪክ ውስጥ ዕጣ ፈንታችንን ወሳኝ እና አቅጣጫ አመላካች ጊዜ ላይ እንገኛለን። "ግንቡን እናፍርስ፤ ድልድዩን እንገንባ" የሚለው የጉዟችን መሪ ሐሳብ እንደሚጠቁመው፣ ዛሬ በየከተማው እና በየአገሩ የተበተነው ሕዝባችን፣ ከአገሩ እና ከወጣበት ማኅበረሰብ ጋራ ተደምሮ በአገሩ ጉዳይ እንዳይወስንና እንዳይሳተፍ ለዓመታት የተጋረጠበትን የመለያየት ግንብ መጋፈጥ እና መደርመስ ይኖርበታል። በዚህ ከተማ ወይም በመላው አሜሪካ እና በውጭ በሚኖረው የዳያስጶራ ማኅበረሰብ መካከልም፣ ይህ ግንብ ተጋርጦ፣ ኹሉም በየጎራው እና በየቡድኑ የጎሪጥ እንዲተያይና አንዱ የሌላው ስጋት እንዲኾን አድርጎታል። ኹሉም፣ አገሩን ለቅቆ በወጣበት ዘመንና በተሰደደበት ችግር መነጽር ያያታል። አሳዳጅ እና ተሳዳጅ ኾነናል፤ በጨቋኝ እና በተበዳይ ካምፕ ተከፋፍለናል፤ ከእኛ ዘመን አልፈን መቶ ዓመት፣ አንዳንዴም ምእት ዓመታትን ወደ ኋላ ሔደን የበደልን ገመድ እየጎተትንና ያለፈውን ቁስል እየቆሰቆስን፣አብሮ ለመቀመጥ አይደለም ዐይን ለዐይን ለመተያየት የተሳነን ኹኔታ ላይ ደርሰናል።

በዚኽም የተነሳ፣ ልጆቻችንን ተነጋግረው መግባባት፣ ተቀራርበው መወያየት ወደማይችሉበት የባዕድነት እና የጠላትነት ደረጃ ላይ አድርሰናቸዋል። በዚኽ ያላቻችኹትን ወገኖቻችንን እንደ ሥልጡኖች እና ዘመናዊ የሚቆጥራችኹ በአገር ቤት ያለው ማኅበረሰብም፣ በመደበኛ እና በሌላ አማራጭ ሚዲያዎች የምትልኩትን መልእክት እየወሰደ አርኣያችኹን ሲከተል ይታያል። ከዚኽም የተነሳ ግራ የገባው፣ በጥላቻ እና በጥርጣሬ የተሞላ ሕዝብ ፈጥረናል። በመካከላችን የገነባነው ግንብ አድጎ ሌላውን ብቻ ሳይኾን፣ የምንወዳትን አገራችንንና የነገ ዕጣ ፈንታችንን ጋርዶብናል። አገር ብትፈርስ፣ ትውልድ ተበትኖ የዓለም መሣቂያ ቢኾን፣ በመጠፋፋት ጎዳና ላይ በእሽቅድድም ስንገሠግስ፣ ሳናሸንፍ ተሸናንፈን ከንቱ ኾነን ብንቀር የሚጠቀመው ማነው? እኛም ከሌሎች

ከታሪክ እንማር። የሠሩትን ግንብ አፍርሰው ወደ ብልጽግና እና ሰላም የደረሱትን ደግሞም በሠሩት የመለያየት እና የመከፋፋት ግንብ ዛሬም የሚማቅቁትን ሕዝቦች እውነታ በአንክሮ እናጢን። በመካከላችኹ የተገኘኹት፣ እኛም የለያየንን የጠብ ግንብ አፍርሰን ወደ ተሻለ ነገ የሚያሸጋግረንን የፍቅር ድልድይ እንሥራ ልላችኹ ነው።

ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ፣ የጀርመንን ሕዝብ ለዓመታት በምሥራቅ እና በሰሜን ጎራ ለኹለት የከፋፈለው የበርሊን ግንብ ነበረ። ዘመኑን ቀዝቃዛው ጦርነት ቢሉትም፣ የጦርነት ቀዝቃዛ ግን የለውም። ብዙ የአገራችን ጀግኖች ተካፋይ እና ምስክር በኾኑበት የኮሪያ ጦርነት ማግሥት፣ 'ከጦርነት ነጻ' በተሰኘው ክልል ገደብ ኹለቱን ዘመዳም የኮሪያ ሕዝቦች ሰሜንና ደቡብ በሚል ለያይቶ ያስቀረ ቅጥር ተሠራ። ወንድማማች የኾነ አንድ ሕዝብ ከጦርነት ነጻ በተባለ ቀጣና እና ቅጥር እንዴት ይህን ያህል ዓመት ተነጣጥሎ ሊኖር ቻለ? ስፍራውን ከጦርነት ነጻ ቢሉትም፣ በዚያ ስፍራ ለማለፍ ሲሞክሩ ሕይወታቸውን የከፈሉና እንደ ቅጠል ተቀጥፈው የቀሩ ሰዎች፣ ቀጣናው ከጦርነት ነጻ እንዳልኾነ ምስክሮች ናቸው። ዛሬ የበርሊን ግንብ ከፈረሰ 30 ዓመት ሊኾነው ነው፤ የኮሪያውም የሞት ቀጣና፣ የነጻነት እና የአንድነት መስከ ሊኾን አፋፍ ላይ ይገኛል። እኛን፣ የአንዲት ኢትዮጵያን ልጆች ከፋፍሎ ያራራቀንና ማዶ ለማዶ የለያየንን ግንብስ ምን እንበለው? ይህ ግንብ፣ እስከ መቼ እንዲለያየንና እንዲከፋፍለን እንፈቅዳለን?

በመጀመሪያ ደረጃ መገንዘብ ያለብን፣ አንዳንዶች እንደሚሉት፣ ይህ ግንብ በብዙ መንገድ የተለያየን መኾናችን የፈጠረው አይደለም። ብዙ ቋንቋ መናገራችን፣ ከተለያየ ዘር እና ጎሣ መምጣታችን፣ የማይመሳሰል ሃይማኖት እና ባህል ማንጸባረቃችን፣ የታሪክ መድበላችንና የማንነት እይታችን መራራቁ፣ በሰሜንና ደቡብ፣ በምሥራቅ እና ምዕራብ ተበትነን መኖራችን ወይም ደግሞ በውጭ እና በአገር ቤት ተራርቀን መከተማችን አይደለም ግንቡን የፈጠረው። እነዚህ ኹሉ ውበት እንጂ ችግር አይደሉም። ጌጥ እንጂ ነውር ሊኾኑ አይችሉም። ሀብት እንጂ ኪሳራ አድርገን ልንቆጥራቸው አይገባም። የፈጣሪ ጸጋ እንጂ የእርግማን ቁጣ አድርጎ መቁጠሩም ስሕተት ነው። በርግጥም እነዚህ አይደሉም ግንቦቹ፡፡

እኛን የለያየንና ያራራቀን ግንብ፥ የጥላቻ እና የመናናቅ፣ የጎጠኝነት እና የዘረኝነት፣ የራስ ወዳድነት እና የስግብግብነት ግንብ ነው። መቀራረብ ያቃተን፣ የቂም እና የበቀል ፖለቲካ ግንብ በመካከላችን እንዲቆም ስለ ፈቀድን ነው። ይህ የመለያየት ግንብ መሠረቱ በልባችን ስለ ተተከለ፣ ዛሬም በመካከላችን የማይፈርስ ቅጥር ኾኖ ቆሟል። እንግዲህ ይህን ግንብ ነው እናፍርሰው የምንለው፡፡ ግንብ ይለያያል፤ድልድይ ግን ያገናኛል። ግንብ ያራርቃል፤ ድልድይ ደግሞ ያቀራርባል። ግንብ እይታን ይጋርዳል፤ ጉዞን ያሰናክላል። ድልድይ ግን ገደሉን ዘግቶ ከመዳረሻ ያቀርባል፤ ከፈለጉበት ያደርሳል። የሚገርመው ነገር፣ ድልድይም ኾነ ግንብ የሚሠራው ከተመሳሳይ ድንጋይ እና ሲሚንቶ መኾኑ ነው። ዓላማው እና ተግባሩ ግን ለየቅል ነው። ስለዚህም ነው፣ ያለንን ጊዜ ሀብት፣ ዕውቀት እና በጎ ፈቃድ ኹሉ አስተባብረን፣ የሚለያየንንና የሚያራርቀንን ግንብ ሳይኾን፣ አንድ አድርጎ ወደ ግባችን የሚያደርሰንን ድልድይ እንሥራበት የምንለው።

በሌላው ላይ የገነባነውን የጥላቻን ግንብ አፍርሰን፣ የፍቅርን ድልድይ እንሥራበት። በመናናቅ የገነባነውን ለማንም የማይበጅ የውርደት ግንብ ንደን፣ በመከባበር አንድ የሚያደርገንን የታላቅነት ድልድይ እንገንባ። ‹እኔ ብቻ› የሚለውን የብቸኝነት እና የግለኝነት ግንብ ከሥሩ ነቅለን በመጣል ለኹሉ የሚበቃውንና ኹላችንንም አሸናፊ የሚያደርገንን ‹እኛ› የሚባለውን ግዙፍ ድልድይ ተባብረን እንሥራ። በጎጠኝነት እና በዘረኝነት ያቃቃረንን፣ የጥላቻ እና የመናናቅ አስተሳሰብ የፈጠረውን የመከፋፈል ግንብ እንደርምሰው። ልዩነታችን ውበት እና ኩራት ኾኖልን፣ ከሩቅ ወደ አየነው የታላቋ ኢትዮጵያ እውን መኾን የሚወስደንን የአብሮነት፣ የአንድነት እና ታሪካዊ ድልድይ፣ ያለ የሌለ አቅማችንን አስተባብረን በጋራ መገንባት እንጀምር። የቂም በቀል ፖለቲካ ያቆመውን የጠበበ የጥፋት ግንብ ዓመድ አድርገን፣ በስፍራው ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር፣ የሠለጠነ እና የሰከነ ብስል የፖለቲካ ድልድይ እናቁም።

ታዲያ ይህ ከፊታችን እንደ ጅብራ የተገተረ ግንብ እንዴት ይፍረስ? ድልድዩን የመሥራት ብልኀቱስ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ፣ ተገቢ ብቻ ሳይኾን፣ አንገብጋቢም ነው።

የግንቡን መደርመስ እና ማፍረስም ኾነ፣ የድልድዩን መታደስ እና ተውቦ መሠራት የሚወስነው ዐቢይ ጉዳይ፣ የእናንተ ፈቃደኝነት እና ዝግጁነት ነው። ለመኾኑ እናንተ ይህን ግንብ ለማፍረስ ፈቃደኛ ናችኹ? ደግሞስ የግንቡን ፍርስራሽ አጽድተን፣ የመሻገሪያውንና የመዳረሻውን ግዙፍ እና ውብ ድልድይ ለመሥራት ዝግጁ ናችኹ? የእናንተን አላውቅም፤ እኔ እና በአገር ቤት ያሉ ወገኖቻችን ግን፣ ፈቃደኛም ዝግጁም መኾናችንን ሳበሥራችኹ በታላቅ ቁርጠኛነት ነው።

በጎ ፈቃድ እና ዝግጁነት፣ መልካም መነሻ ብቻ ነው። ግንቡን የምናፈርስበት እና ድልድዩን የምናድስበት፣ ኹነኛ መሣሪያዎች እና ብልህ ሠራተኞች ያስፈልጉናል። ሥራውን የሚሠሩልን ሰዎች ከሌላ አገር የምንቀጥራቸው ወይም ከሚመጣው ትውልድ እስኪወለዱ የምንጠብቃቸው ሳይኾኑ፣ እኛ ራሳችን፣ አንቺ፣ አንተ፣ እርስዎ እና እኔ ነን። ይህን ከፉ የመከፋፈል እና የመራራቅ፣ የጥላቻ እና የመናናቅ፣ የቂም እና የበቀል ግድግዳ እና ግንብ የምናፈርስበት ታላቁ ድጅኖ፣ "ይቅርታ" ይባላል። በአንድ በኩል በተራኪዎቻችን፣ "እነ እገሌ እንዲህ አድርገውኻል" እየተባልን የጠላናቸውን፤ በሌላም በኩል፣ ተሸክመን የኖርነውንም ታሪክ ይቅር እንበለው፡፡ ያኔ አልነበርንም፤ ዛሬም ትላንትን ማስተካከል አንችልም፡፡ ይቅርታ የማያስቀረው በደል፣ የማያርፈሰው የቂም እና የበቀል ግንብ የለም። ቅሬታችንን ይቅር ስንል፣ ልባችን ይነጻል፤ ግንኙነታችን ሊፈወስ ይጀምራል። ስለዚህ ይቅር እንበል፡፡

ይቅር ካላልን ግን፣ ስንናቆር መኖራችን ነው፡፡ ይቅር ካላልን፣ ትላንት ዛሬንና ነገን እንዲያባክንብን መፍቀዳችን ነው፡፡ ይቅር ካላልን፣ ጦርነትን እንጂ ሰላምን ማምጣት አንችልም፡፡ ይቅር ካላልን፣ የማይሞላ ሒሳብ ስናወራርድ መክረማችን ነው፡፡ ይቅር ካላልን፣ ውብ የኾነውን የኢትዮጵያዊነት ሸቱ፣ ጥቂት የሞቱ ዝንቦች እንዲያበላሹት መፍቀዳችን ነው፡፡ ይቅርታ ስንል፣ ይቅር ብሎ መተው ማለት ነው፡፡ የኾነ አካል ይቅርታ እስኪጠይቅ መጠበቅ አይደለም፡፡ በራስ ወስኖ ትቼዋለሁ ማለት ነው፡፡ ይቅርታ ምክንያትን ይሻገራል፡፡ ይቅርታ ቅድመ ኹኔታን ይሽራል፡፡ ይቅር ማለት ተግባሩ እንደ ኮሶ ቢመርም፣ በውጤቱ፥ የበደለኛን ወንጀለኛነት እና ጸጸት እንዲሁም፣ የተበዳይን ቂም እና ቁርሾ በማያዳግም ኹኔታ ያሽረዋል፤ ይሽረውማል።

የጥላቻንና የበቀልን ግድግዳ በመሻር ብቻ፣ የመለያየትንና የመከፋፈለን ግንብ እንንዳለን።

ኹላችንም እንደምናውቀው፣ የፈረሰ ግንብ የተሠራ ድልድይ ማለት አይደለም። ታዲያ የለያየንንና የከፋፈለንን ግንብ ካፈረስን በኋላ፣ የሚያገናኘንንስ ድልድይ የምንገነባው እንዴት ነው? ከግንቡ መፍረስ የተረፈውን ፍርስራሹንና ስብርባሪውን የሚያጸዳው እና የሚያስተካክለው ዕርቅ ነው። ዕርቅ፥ በደለኛውንና ተበዳዩን፣ ባሉበትም በሌሉበትም የሚያርቅ እና የሚፈውስ የድልድዩ መሠረት ነው።, ድልድዩን መገንባት የምንጀምረው በዕርቅ ጠረጴዛ ዙሪያ ተነጋግረን በመግባባት፣ ተወያይተን በመስማማት፣ ተመካክረን በመተማመን ነው፡፡ አንድ ኾነን በመነሣት፣ አንድ ኾነን በመሥራት ነው፡፡ ልዩነትንና የሌላውን መብት በማክበር ነው፡፡ በአጠቃላይ ድልድዩ የሚሠራው በመደመር ነው፡፡ ድንጋዮች በሲሚንቶ ተያይዘው ድልድይ እንደሚኾኑ፣ እኛም በአንድ ላይ በመደመር እና በፍቅር ተያይዘን አገራዊ ድልድዩን እንሠራዋለን።

እኛ ድልድዩን፣ በጥልቅ የአገር ፍቅር እና የወገን ክብር ላይ ከመሠረትነው፣ በሓላፊነት እና ያለንን ሳንቆጥብ በመስጠት ተሸካሚ ምሶሶዎቹን በሥፍራቸው ካኖርን፣ ከዘመን ዘመን ከትውልድ ትውልድ ተሻጋሪ የአንድነትንና የሥልጣኔን ፈር ቀየስን ማለት ነው። በይድረስ ይድረስ ለታይታ ሳይኾን፣ በጥንቃቄ እና በልህቀት አስተሳሰብ ታቅዶ የተጀመረ ድልድይ፣ ዛሬ እኛ ኹሉን ሠርተን ባንጨርሰውም፣ ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን ቀሪውን ሥራ ሊፈጽሙት አይቸገሩም፡፡ እዚህ እናንተ በምትኖሩበት አገር፣ የቀደመው መሠረት ጣይ ትውልድ፣ የማይነቀነቅ እና የማያዳግም አገራዊ ድልድይ በመሥራታቸው፣ ዛሬ ያለው ትውልድ ኹሉ በሚመኛት እና በታፈረች ታላቅ አገር ተከብሮ ይኖራል። ስለዚህም እርስ በርስ መፈራረሱ እና መቆራቆሱ ቀርቶ፣ ዛሬ ዕድል እንደ ፀሐይ በሚያበራበት፣ ሕዝብ እንደ ተርብ በተመመበት ጊዜ፣ ይህን የአንድነት እና የአብሮነት ማማ እና መሰላል የኾነ ትውልዳዊ ትስስር የሚፈጥር ድልድይ መሠረቱን እናኑር እላችኋለኹ። ከጀመርነው እንጨርሰዋለን።

እኛ ያልጨረስነውን መጭው ትውልድ ይጨርሰዋል። እኛ ዛሬ ይህን የአንድነት እና የመተሳሰር ድልድይ ተባበረን በፍቅር በመሥራት ፈንታ፣ በየፊናችን ብንነጉድና ለየግል አጀንዳችን ብንገሠግስ፣ ነገ በአገራችን የምንመካ ኩሩ ሕዝቦች ሳይኾን፣ በትዝታ እና በታሪክ ላይ የተንጠለጠልን፣ በድህነታችንና በስደተኝነታችን የምንታወቅ ሕዝቦች ነው የምንኾነው፤ ወይም ደግሞ ዕጣ ፈንታችን፣ አራቱ ጎማዎቹ ተገንጥለው በአራት አቅጣጫ እንደተበታተኑበት መኪና፣ ጉዟችን የባለኸበት እርገጥ ፈቀቅ የማይል ይኾናል። መነሻ እንጂ መድረሻ አይኖረንም፡፡ አራቱ ጎማዎች በአራት አቅጣጫ ከሔዱ እንኳን፣ መሔድ የሚችሉት ለየብቻቸው ለዚያውም ለውሱን ርቀት ነው፡፡ ጎማዎቹ ተሸክመው ሊወስዱት የተፈለገው መኪና ግን፣ ተራ ዕቃ ኾኖ ይቀራል፤ ከሥፍራውም ሊንቀሳቀስ አይችልም። እኛም በየራሳችን መሔድ እንችል ይኾናል፤ ነገር ግን ኢትዮጵያን ከአልባሌ ሥፍራ፣ ለዘራፊ መጫወቻ እንጥላታለን።

በምትኩ በየሥፍራቸው፣ ከዋናው መኪና ጋራ በሥርዓቱ የተጣመሩ ጎማዎች፣ ምንም እንኳን ለየብቻቸው ቢሽከረከሩ፣ በአንድ አቅጣጫ ከተጓዙ፣ በአንድ መሪ ከታዘዙ፣ ወደ አንድ ግብ ከነጎዱ፣ ያኔ መኪናው ከነተሳፋሪዎቹ እና ጭነቱ ወደ መዳረሻው በሰላም ይደርሳል፡፡ እኛም ልዩነቶቻችንን እንደ ያዝን በአንድ አቅጣጫ፣ ለአንድ አገራዊ ዓላማ ተግባብተንና ተስማምተን፣ ተፋቅረንና ተዋደን ከተጓዝን፣ ኢትዮጵያን የሥልጣኔ ማማ ላይ እናደርሳታለን፡፡

ይህን ለልጆቻችኹ ንገሯቸው፡፡ ኢትዮጵያ የምትባል የብዙ ባህሎችና ወጎች፣ ቋንቋዎች እና እምነቶች፣ልማዶች እና ሥርዓቶች ውብ አገር አላችኹ፤ በሏቸው። መነሻቸውን እንዳይዘነጉ፣ ከአገራቸው ጸጋ እንዳይራቆቱ፣ በማንነታቸው እንዲኮሩ አስተምሯቸው፡፡ ሞያቸውንና ዕውቀታቸውን፣ ሀብታቸውንና ጉልበታቸውን በአገራቸው ለማፍሰስ እንዲመኙ አድርጋችኹ አሳድጓቸው፡፡ እኛ በደረሰብን ነገር ከአገራችን ስለ ሸሸንና ስለ ተሰደድን፣ ከሥረ መሠረቱ የተቆረጠ (disconnected generation) ፣ ማንነቱ የጠፋበት(lost generation) እና መፈጠሩም ሳይታወቅ የተዘነጋ(forgotten generation) አሳዛኝ ትውልድ መፍጠር የለብንም፡፡

ዛሬ ድልድዩን እንገንባና ከአገራቸው እና ከሥር መሠረታቸው ጋራ እናገናኛቸው፡፡ ያለፉት ዐሥርት ዓመታት ምስክሮች ናቸው፡፡ ተገዳድለንና ተጨፋጭፈን፣ ተወጋግዘንና ተቆራቁሰን፣ አስረንና ታስረን፣ አባረንና ተባርረን፣ አሳደንና ተሰደን፣ ተከፋፍለንና ተራርቀን አይተነዋል፤ ሞክረነዋል፤ አልተሳካልንም። ይልቁንም አቆረቆዘን፤ ወደ ኋላ አስቀረን፤ በረኀብ እና በድህነት ስማችንን አስጠራን፤ ማለቂያ እና አሸናፊ በሌለው ጦርነት ማገደን። እርስ በርስ አናከሰን እንጂ ያመጣልን አንዳች ጸጋ እና በረከት የለም፡፡ ስለዚህ ይህ ሠቆቃ ዛሬ እንዲያበቃ፣ ኹላችንም በቃን እንበል፡፡

ድልድይ ለድልድይነቱ አይገነባም፤ ጉዞም በድልድይ ላይ አያበቃም። ድልድዩ የጥላቻ እና የመለያየት ግንብ የጋረደብንን፣ የኹላችን ምኞት እና የፈጣሪም ጸጋ እና ስጦታ ወደ ኾነው መዳረሻ ያሻግረናል እንጂ። ይህም፣ የሰው ልጆች ኹሉ ተፈጥሯዊ ሙብት የኾነውን ሰላም፣ ደስታ እና ነጻነት የምናገኝበት የጋራ አገር እና ሕይወት ነው። ስለዚህም፣ የይቅርታ እና የፍቅርን ድልድይን ከተሻገረን፣ የኀብረትንና የትብብርን፣ የአንድነትንና የስምምነትን መንገድ እንጀምር፡፡ አዎን፣ ከማዶ ወደሚጠብቀን ሰፊ የአንድነት እና የብልጽግና፣ የዕድገት እና የሥልጣኔ፣ የዴሞክራሲ እና የሰላም ከተማ እንገሥግስ። ወደ መጪው ዘመን፣ ተስፋን ሰንቀን፣ አዲሱን መንገድ በአዲስ ልብ እንጀምር፡፡ ክፉ ክፉውን ትተን በነባሩ አኩሪ መሠረታችን ላይ አዲሲቷን ኢትዮጵያን እንገንባ፡፡ ለተለወጠች አገር በተለወጠ ማንነታችን የተለወጠን ማኅበረሰብ እናሳድግ፡፡

እነኾ ለውጡን ጀምረነዋል፡፡ ርግጥ ነው፣ የለውጥ ጎዳና አልጋ በአልጋ አይደለም፡፡ የተጣሉትን ማስታረቅ፣ የጎዱትን መካስ፣ የተጎሳቆሉትን መከባከብ፣ ያዘኑትን ማጽናናት ይገባናል። ለምሳሌ፥ ኦሮሞ እና ሶማሌ ተጎራባች ብቻ ሳይኾን፣ በሥጋ ወደም የተሳሰረ ዘመዳም ሕዝብ ነው። ዛሬ በአንዳንድ ሥፍራዎች እየታየ ላለው ግጭት እና መፈናቀል፣ እዚህ ያላችኹ የአገራችን ሕዝቦች ምን እያደረጋችኹ ነው? የፈረሰውን ብንጠግን፣ በጎ እና ገንቢ ቃልን ብንናገርና ሰላምን ብንፈልግ፣ እዚያ በሕዝቡ መካከል ያለውን ግንብ አፍርሶ ድልድይን ለመገንባት፣ ብሎም ለቀጣይ የብልጽግና እና የሰላም ጉዞ ለመሰነቅ ከባድ አይኾንም ነበር።

ከግለሰብ እና ከቤተሰብ ጀምሮ በየሥፍራው የተጋረጡትን የጥል እና የመለያየት ግንቦች ኹላችንም በአንጻራችን እያፈረስን ለኹላችንም መሻገርያ የሚበቃውንና የሚያቀራርበንን የሰላም እና የፍቅር ድልድይ እንገንባ። ካሰብነው ግብ እንዳንደርስ እና የምንፈልጋትን ዓይነት ኢትዮጵያ እንዳንገነባ ግን የሚከለክለን አንዳች ነገር የለም፡፡

ዛሬ ተስፋ ሰንቀናል፤ ነገ ተስፋችን እውን ይኾናል፤ ከነገ ወዲያ ደግሞ፣ እውን በኾነው ተስፋችን ላይ በኩራት እንረማመዳለን፡፡ ግንቡን ካፈረስን፣ ድልድዩን ከሠራን፣ ከማዶ የምናያት ሰላማዊ እና የበለጸገች ኢትዮጵያ ለኹላችንም ትበቃናለች፤ ለሌሎችም ትተርፋለች።

## ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ፡፡

# የመካላከያ ምርቃት ንግግር

**ነሐሴ 12/2010**

**የተከበራችሁ የጦር መኮንኖች እንዲሁም
መከላከያን በመገንባትና በማደራጀት
ታላቅ ገድል ፈጽማችሁ
ዛሬ በመካከላችን የምትገኙ
ሌፍተናንት ጀነራል አበባው ታደሰና
ሌፍተናንት ጀነራል ዮሐንስ ገብረ መስቀል
ከፍያለ ምስጋና ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ።**

ወታደር አገልግሎቱ በዘመናት መካከል የማይረሳ ስለሆነ በጡረታ የሚገለሉ የጦር መኮንኖች በእንደዚህ ዓይነት ወታደራዊ በዓል ላይ ከእኛ ጋር ተገኝተው ድምቀት በመስጠት ለተቋሙም ለእነሱም ክብር ስለሆነ እንደ ባህል መቀጠል አለበት፡፡

ከሁሉም በማስቀደም ለመከላከያ አዛዥ ስታፍ ኮሌጅ የመኮንንኖች ምረቃ በዓል ላይ ተገኝቼ የመጀመሪያውን ሰርተፍኬት ለመስጠት ዕድል በማግኘቴ እንደ ወታደር የተሰማኝን ልዩ ክብር ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡ በቆይታችሁ አገራዊ እሴቶችንና የጀግንነት ታሪኮችን ከዘመናዊ ወታደራዊ ጥበብና ከዘመናዊ ወታደራዊ ፍልስፍና ጋር አዋሕዶ የመጠቀም ጥበብ ገብይታችሁ፣ ተቋሙን

በዛው ልክ ለማደራጀትና ለመምራት የመጀመሪያውን ስንቅ ሰንቃችኋል፡፡ ይህ የወታደራዊ ሳይንስ ጥበብ ከማያልቅ ውቅያኖስ የሚቀዳ ትንሽ ዕውቀት በመሆኑ በቀጣይነት መትጋት፣ መንደፍ፣ መልፋት የሚጠይቅ ሴክተር ነው፡፡ የመጀመሪያው ምርቃት ለሚቀጥለው ድልድይ የሚያሸጋግር ስለሆነ በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

በአንድ በኩል አገራዊ ወታደራዊ እሴቶችንና የጀግንነት ታሪኮችን ለማጥናት፣ ምርምር ለማድረግ የሚተጋ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ምርጥ ዘመን አመጣሽ ቴክኖሎጂ በአግባቡ የመጠቀም ብቃት የፈጠረ የማድረግ አቅሙ በሁሉም ዐውደ ውጊያ የተመሰከረለት ፕሮፌሽናል አቅም የመገንባት የመንግሥታችን ቀዳሚ ፍላጎት ነው፡፡

ወታደራዊ አመራሩም ከሳይንስ እና ዕውቀት እንዲሁም ሳይንሳዊ ጥበብ ባሻገር የፖለቲካ አመራሩ ፍላጎትና የፖሊሲ አቅጣጫ በሚገባ የማወቅና የመተንተን አቅም ሊኖረው ይገባል፡፡ ወታደዊ ጥበብ አንዱ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ወታደራዊ አቅምና ውጊያ የፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ መሣሪያ ነው፡፡ የፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ የሚሆን መሣሪያ፣ የፖለቲካውን ፍላጎት እና አቅጣጫ በወጉ የሚረዳ፣ የሚተነትንና ለማስፈጸም የሚታመን የጦር መኮንን ለኢትዮጵያ ያስፈልጋል፡፡ የጠላት ወታደሮችን እንዴት እንደሚገድል ሳይሆን የራሱን ሠራዊት ከጉዳት አትርፎ፣ የጠላትን የማድረግ አቅም እንዴት እንደሚያከሽፍ አቅዶ፣ ኦሬንት አድርጎ የሚተገብር መኮንን ከምን ጊዜውም በላይ ዛሬ ያስፈልገናል፡፡ እኛ ላለንበት ቀጣና የነበረን ጥንካሬ ብቻውን በቂ ባለመሆኑ፣ በአምስቱም የጦር ዐውዶች ራሱን ያበቃና ጦርነት መግታት የሚያስችል ቁመና የፈጠረ ተቋም መገንባት እንፈልጋለን፡፡

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ጠላት በአንደኛው የጦርነት ዐውድ ያጣውን ድል በሌላ ዐውድ ለማስቀጠል፣ ለማሸነፍ አልያም ለማክሸፍ ይተጋል፡፡ የመከላከል አቅማችን በአንደኛው ዐውድ የታጠረ ከሆነ በዚያ ግንባር መከላከል ቢቻልም ዋናው ተልእኮአችን ሉዓላዊነትን ማስከበር ነውና በሌላው ዐውድ ያንን ግብ ማሳካት የተሳነን እንደሆነ ተልእኮአችንን አላሳካንም ማለት ነው፡፡

በመሆኑም በአምስቱም የጦር ዐውድ የመግታት አቅም ለማጠናከር ወታደራዊ ሳይንስ ያጠኑ ጀነራል መኮንኖችና መስመራዊ መኮንኖች በእጅጉ የሚያስፈልጉበት ጊዜ አሁን ነው፡፡ ጠላት በምድር ኃይል ኢትዮጵያን መሞከር የማያወጣ መሆኑን በተደጋጋሚ ሞክሮ በመሸነፍ ያውቀዋል፡፡ ይሁን እንጂ መልከዓ ምድራዊ ብልጫችንን በማዛባት በተለያዩ ዐውዶች እድገታችንንና አንድነታችንን የሚፈታተኑ ሙከራዎች ከማድረግ ግን አይቆጠቡም፡፡ ይህንን ለመግታት በሁሉም ዶሜይን አገሪቱን ለመከላከልና ዋናው ተልእኮአችን የሆነውን ሉዓላዊነት ለማስከበር ዝግጁ የሆነ ፕሮፌሽናል አርሚ የመገንባት ሥራ ለነገ የማይተው መሆኑ በጥብቅ እናምናለን፡፡

በሚወሰደው ጦርነት ለማሸነፍ የሚያስችል ቁመና የሌላቸው የቅልበሳ ኃይሎች ዋነኛ ዓላማና ተልእኮ ማሸነፍ ሳይሆን ማክሸፍ ስለሆነ ባልታሰበ ዐውድ ለማሸነፍ የተሰለፈ አርሚ ጉዞው እንዲገታና እንዲከሽፍ በማድረግ ከተልእኮው እንዲስተጓጎል ያደርጋሉ፡፡ ይህ እንዳይሆን ነፃነትና ሥርዓት አልበኝነት ባለመለየት፣ መረን የወጣ ሕግንና ሥርዓትን የማያከብር የመንጋ ፖለቲካ ኢትዮጵያ ውስጥ መቆም ይኖርበታል፡፡ ሕጋዊ ሥርዓትን እያዳከመ በመንጋ የሚሰጥ ፍትሕ ተከትለን የፍትሕ ሥርዓቱን በግል ስሜት የምንነዳው ከሆነ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው ያልተጠናከረው ሥርዓት ከተጠናከረው ሀገር ወደማይወጣው ፈተና የሚያስገባና ሁሉንም በኪሳራ የሚያስጨርስ የመሆኑ በሕግ ልዕልና ጠንቅቆ ማወቅና ማክበር፣ ማስከበር የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታ ሲሆን፣ የአገር መከላከያ ሠራዊት ደግሞ ድርብ ሐላፊነት ይኖረዋል፡፡ ሕግ አልባና አመጽን የሚታገሥ ሥርዓት እንደ ሀገር መቆጠራችንን ከንቱ ስለሚያደርግ ሀገራዊ አንድነታችንን በሕግ አግባብ ማስጠበቅ የዘወትር ተልእኮአችን ይሆናል፡፡

ዘመናዊነት የሕግን የበላይነት ማክበር ነው፡፡ የህግን የበላይነት ያላከበሩ ሕዝቦች በሕግ የሚገዙ ዓምባ ገነኖችን ይፈጥራሉ እንጂ አሸናፊ መሆን አይችሉም፡፡ እንደመር፣ በይቅርታ አንድ አገር እንገንባ ስንል መረን እንውጣ፣ ሕግ አናክብር፣ በየከተማው ሽፍታ ይበራከት ማለት አለመሆኑን በአንክሮ ማስመዝገብ እፈልጋለሁ፡፡ የይቅርታ ዓላማ ባለፍንበት መንገድ ያጣነውን ለማግኘት፣ የገነባነውን ሀገር ለማፍረስ ስላልሆነ፣ እያንዳንዱ ዜጋ ይህ ከአብራኩ የወጣውንና በአነስተኛ ደሞዝ ሕይወቱን እየገበረ የሀገር አንድነትን

የሚያስጠብቀውን ኃይል የመውደድ፣ የማክበር፣ የሞራል ድጋፍ የመስጠት፣ እያንዳንዱ ዜጋ ግዴታ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ለማብሰር እፈልጋለሁ፡፡

የኢፌዲሪ መንግሥት የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ከአለባበስ ጀምሮ ያለበትን ችግር መቅረፍ፣ በዚህ ዓመት ሻል ያለ ውሳኔ ወስኖ በሕወታችሁ ላይ አንድ እርምጃ ወደፊት የሚወስድ ማሻሻያ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ ይህ በቀጣይነት የመከላከያ ሠራዊት መለዮ የተለየ፣ ዩኒፎርሙ ያማረ፣ አረማመዱ የሚያስታውቅ፣ በሰልፉ የሚፈራ፣ የሚማርክና የሚከበር የሚያደርግ መሆኑን፣ መንግሥት በሥልጠናና በፋይናንስም የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

የአገር መከላከያ ሠራዊት መኮንኖች መከላከያ መተኪያ የሌለው ብሔራዊ ሀብት መሆኑን እንድትገነዘቡ እፈልጋለሁ፡፡ የፌዴራል ፍ/ቤት በክልል ፍ/ቤት፣ የፌዴራል ፖሊስ በክልል ፖሊስ፣ የፌደራል ሕግ አውጪ በክልል ሕግ አውጪ፣ የፌዴራል አስፈፃሚ በክልል አስፈፃሚ ሊተካ የሚችል ቢሆንም፤ የሀገር መከላከያን መተካት የሚችል ምንም ዓይነት ተቋም ይኽች ታላቅና ድንቅ ሀገር ስለሌላት፤ ብቸኛ መሆን ብቻ ሳይሆን ባደራረጋችንም ልዩ መሆናችንንም በየዕለቱ በማሳየት፣ የዚህችን ሀገር አንድነት፣ የባንዲራን ክብር፣ ለሕዝቦች፣ ለጎረቤቶች ማሳየት የምንችል፣ እንደ ትናንትናው ጀግኖች ሀገር ወዳዶች፣ በትናንሽ ነገር ተጠልፈን የማንቀርመ ኩሩና አኩሪ ወታደሮችመ ለመፍጠርና ለመሆን የሚደረገውን ጉዞ በልበ ሙሉነት እንድትደግፉ በታላቅ ትሕትና እጠይቃችኋለሁ፡፡

የሀገር መከላከያ በራሱ የፍትሕ አሠራር፣ በግልፅ ፖሊሲና ዶክትሪን የቆመ በዚያም ሥርዓት የሚመራ መሆን አለበት፡፡ አንድ የሀገር መከላከያ ሠራዊት መኮንን ከአንድ ሰው የሥልጣን ዘመን የተሻገረ አገልግሎት እንዲሰጥ ሆኖ የሚዘጋጅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ለረዥም ጊዜ ሥልጣን ይዞ መቆየት ከእንግዲህ በኋላ ማይታሰብ መሆኑን በተደጋጋሚ የገለጽን ስለሆነ፤ የአገር መከላከያ ሠራዊት የፖለቲካ አመራር በምርጫ ሲቀያየር በመምረጥ ያለውን መብት ተጠቅሞ ፍላጎቱን ከመግለጽ ባሻገር፣ የመጣውን የፖለቲካ አመራር ተቀብሎ ሕግና ሕገ መንግሥቱን ማስከበር ግዴታ መሆኑን በድጋሚ ላሳስባችሁ

እፈልጋለሁ፡፡ ስለሆነም የወታደራዊ አመራር ጥበብ መለኪያ የሆነው አንዱ ፕሮፌሽናል ተቋም መገንባት ነው፡፡

ዛሬ የተመረቃችሁ፣ ላለፉት ዓመታት ሳይንስና ጥበብን ያጠናችሁ፣ የተመራመራችሁ፣ ወደኋላ ስትመለሱ ይህንን ዕውቀት ለሌሎች በማካፈል ፕሮፌሽናል አርሚ ለመገንባት፣ ከነገ ጀምሮ በታላቅ ትጋት ሥራችሁን እንድትጀምሩ በዚሁ አጋጣሚ አደራ ለማለት እፈልጋለሁ፡፡ ከእያንዳንዱ የጦር መኮንን ኢትዮጵያ የምትጠብቀው በሀገር አንድነት የማይደራደር፣ በባንዲራ ክብር የማይደራደር፣ በመዝሙራችሁ ላይ ሕዝቦች የሰጡን አደራ በደም አሻራ የታተመ መሆኑን ያንን ማክበር ቃል ኪዳን የገባችሁበትን በየዕለቱ በምትዘምሩት መዝሙር ማክበርና ማስከበር ከእያንዳንዳችሁ ይጠበቃል፡፡

እናንተ ከሕዝባችሁ የተሰጣችሁ አደራ በወረቀት ፊርማ ሳይሆን በደም አሻራ መሆኑን መዝሙራችሁ ራሱ ስለሚገልጽ፤ በደም አሻራ ታትሞ የተፈረመው የሕዝብ አደራ በዚያው የሐላፊነት ስሜት መጠበቅና እንዳይሸራረፍ ማድረግ ከሁላችሁ የሚጠበቅ መሆኑን በድጋሚ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ይህ ተቋም ልዩ ባሕሪዎች ያሉት፣ ያንን ባሕርይ ለማስጠበቅ ለቀጣይ ጉዞ ወሳኝ መሆኑን፣ እነዚህ ባሕርያት አሁን በተማራችሁት ትምህርት ታግዞ በመከላከያ ውስጥ በቀጣይነት የሚተገበሩ፣ ከመስከረም ጀምረው የመከላከያ ሠራዊት አዲስ የተጠናው ስትራክቸር ሥራ ላይ የሚውል፣ አዳዲስ ኃይል ተጨምረው የአገር ሉዓላዊነት ማስከበር የሚችል እውነተኛ የአፍሪካ ኩራት፣ እውነተኛ የቀጠናው ኩራት፣ እንዲሆን ስለምንገነባ፤ በዚህ ግንባታ ውስጥ አንደኛ ኅብረ ብሔራዊነት የፌደራል ሥርዓቱ ኢትዮጵያ ማሳያ መሆኑን እናንተ የፌዴሬሽኑ ብቸኛ ተቋም በመሆናችሁ፣ እናንተ ውስጥ በእያንዳንዱ አሐድ ኢትዮጵያን ማየት ያስፈልጋል፡፡ ያ ሲሆን ብቸኛ መሆናችሁ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያም ማሳያ ማኅተም የሆናችሁ፣ ለሚያያችሁ ለሚሰማችሁ ሁሉ ማረጋገጫ ስለሚሆን መከላከያ ግንባታ ውስጥ መዘንጋት የሌለት አንዱ ቁልፍ ነገር ኅብረ ብሔራዊነቱ የጠበቀ ተቋም ማድረግ ነው፡፡

የሀገር መከላከያ ሠራዊት ከፖለቲካ ወገንተኝነት ራሱን አርቆ ሊኖር የሚያስችል ፕሮፌሽናል ብቃት እንዲኖረው ማስቻል ነው፡፡ የምትደግፉት ወይም የማትደግፉት፣ የምትወዱት ወይም የማትፈልጉት ልምምድ ሳይሆን፤ ወታደራዊ

ሙያ ሊከበር የሚገባው፣ ሙያችሁም ድንበር ተሻግሮ ከፖለቲካ ጋር የሚያያዝ ችግር መከላከል የሚያስችል፣ የእያንዳንዱ ሰው ውሳኔና አቋም በጽኑ ሊይዝ የሚገባ መሆኑን መገንዘብ በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡

ሌሎች ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ መሆን ያለባቸው ተቋማት በሕገ መንግሥቱ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ለምሳሌ ፍርድ ቤት ነፃ የመሆን መብት እንዳለውና ከፖለቲካ ወገንተኝነት የጸዳ መሆኑ ቢገለጽም የሀገር መከላከያ ሠራዊት ግን ያ መብት ብቻ ሳይሆን፣ ጣልቃ ያለመግባት ግዴታ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 87.5 ላይ በግልፅ ተቀምጦአል፡፡ ጣልቃ ለመግባት ሕገ መንግሥታዊ ግዴታውን ያላከበረ ጦር ሕገ መንግሥቱን ሊያስከብር አይችልምና መብትና ግዴታችንን አውቀን በዚያው አግባብ እንድንሠራ፣ ይህንንም መሥሪያ ቤት ውስጥ እንድናሰራጭ ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡ ከእያንዳንዱ አመራር የምንጠብቀው አንድ ቅን አገልጋይ ነው፡፡

1. ለባንዲራ፣ ለመለዮ ለገባው ቃል ኪዳን ታምኖ በቅንነት የሚያገለግል፤
2. ለሕገ መንግሥቱና ለፖለቲካ አመራሩ ታማኝ የሆነ፤
3. በራሱ የሚተማመን፣ ራሱን የሚያስተምር፣ ራሱን የሚያበቃ፣ በአረማመዱ፣ በአስተዳደሩና ባደራረጉ መተማመን የሚታይበት፣ ለትውልድ ኩራት የሆነ መሪ፤
4. ጉጉት ያለው፣ ለዕውቀት፣ ለፈጠራ፣ ለአዳዲስ አሠራር ራሱን የሚያዘጋጅ፣ ወታደራዊ ሳይንስ ከትልቅ ባሕር በጭልፋ እንደቀመሳችሁት ብዙ ምርምር፣ ብዙ ጥናት፣ ብዙ ማንበብ የሚጠይቅ በመሆኑ ተምረን ተመርቀናል ሳይሆን፣ በቀጣይነት ለመማር የሚያስችል በር ተከፍቶልናል በሚል እሳቤ፣ በየቀኑ ራሳችሁን ማስተማርና፣ በማወቅ ተቋም መገንባት እንዳለባችሁ እንደ አንድ ባሕሪ በመያዝ፤
5. አርአያ መሆን እንድትችሉ፤ አርአያ መሆን ማለት ቅድሚያ ለሠራዊት የሚሰጥ እንደ ናፖሊዎን በዘመናት መካከል ስሙ የማይዘነጋ፣ ሲበላ፣ ሲሰለፍ፣ ሲቆጥርና፣ ሲያስቆጥር፣ በሠራዊት መካከል የሚገኝና ‹ኮማንደር ካሉስ እንደ እከሌ› የሚያስብል አርአያነት ከእያንዳንዳችሁ ይጠበቃል፡፡

6. ጀግንነት ነው፤ መከላከያ እያንዳንዱ ወታደርና የጦር መኮንን ጀግና መሆን አለበት ሲባል፤ ተኩሶ መግደል ብቻ ሳይሆን፣ ስሜትንም የሚያሸንፍ፣ ሕገ መንግሥቱን የሚያውቅ፣ ለዚያ የሚገዛ፣ በዚያ የማይደራደር ቁርጠኛ መሆኑን በየዕለቱ የሚያረጋግጥ መሆንም ይጠበቅበታል፡፡ የመጨረሻው ሥርዓት ተኮር መሆን ነው፡፡ ሲስተም ኦሬንትድ መሆን ያስፈልጋል፡፡ መከላከያን ከሌላው ሥርዓት የሚለየው በኦርደር የሚታዘዝ መሆኑን ነው፡፡ ሲስተም የማያከብር፣ በሲስተም የማይገዛ፣ ለግለሰቦች ሪፖርት የሚያደርግ፣ መከላከያ ተቋሙን ብቻ ሳይሆን ቅድም እንዳልኩት ብቸኛ መሆኑን ዘንግቶ ሀገር የሚያፈርስ ስለሆነ፣ ይህ እንዳይሆን በታላቅ ጥንቃቄ ሲስተም መገንባትና ለትውልድ የማሸጋገር ሐላፊነታችሁን በታላቅ ብቃት እንድትወጡ ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡

ከዘመናዊ ወታደራዊ አመራር መንግሥት የሚጠብቀው ሉዓላዊነትን ለመጠበቅና ከፖለቲካ ውግንና ነፃ በሆነ መንገድ የኢትዮጵያን አንድነት፣ የኢትዮጵያን ባንድራ፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማንም አሳልፎ የማይሰጥ፣ በዚህ ጉዳይ የሚመጣውን ማንኛውንም አደጋ ለመከላከል፣ ራሱን ለመትከል የተዘጋጀ ወታደር እንዲሆን ከእያንዳንዳችሁ ይጠበቃል፡፡ ይህን መትከል፣ ይህን ማደራጀት፣ ይህንን መሥራት የጥሩ መኮንኖች ሐላፊነት ነው፡፡ በየዕለት ሥራችሁ የሀገርን ክብርና የባንድራን ክብር በማስተማር ወታደሩ ኢትዮጵያን የመጠበቅና የማስቀጠል ግዴታ እንዳለበት የማስተማር ታላቅ ሀገራዊ አደራ እንዳለባችሁ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ፡፡

በመጨረሻም መከላከያ ውስጥ ጠንከር ያለ ሪፎርም ተጀምሯል፡፡ የሪፎርሙ ዋና ዓላማ ስትራክቸር መቀየር ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ አርሚ ፕሮፌሽናል ብቃቱ ታይቶ፣ ሕገ መንግሥቱን አውቆ፣ የዚችን ሀገር ሰላም ማረጋገጥ እንዲችል፤ ሁሉም ዐውድ በዕውቀት ማቀድ፣ በዕውቀት ማስላሰል፣ ዐውቆት ማድረግና ማሸነፍ የሚችል አርሚ እንዲሆን ሰፊ ሥራ ተጀምሯል፡፡

ለዛሬ በወርቅ የተመረቃችሁ አምስት የወርቅ ተመራቂዎችና ሁለት ሴት መኮንኖች በሚቀጥለው ሳምንት ለጉብኝት ወደ ውጭ ሀገር የምትላኩ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ መከላከያ እናሠለጥናለን፣

መከላከያን ኑሮውን እናሻሽላለን፣ መከላከያን በቅርበት እንደመራለን፣ መከላከያ ቅርብ መሆኑን፣ አለኝታ መሆኑን ለማረጋገጥ ለዚህ ፖለቲክ አክሽን ምላሽ እንዲሰጥ በዚሁ አጋጣሚ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ፡፡

በመጨረሻም ጀነራል ሰዓረ መኮንን ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም ሆነው ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ ተቋሙንም በአዲስ መልክ ለማደራጀት ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል በኢትዮጵያ አንድነትነ በኢትዮጵያ ህልውና አጋጥሞ የነበረውን ችግር በሕግና በሕግ ብቻ አንድም ሰው ሳይጎዳ፣ መከላከያ በሞያው ብቃት አገር መታደግ እንዲችል፣ በአጭር ጊዜ የማይጠበቅ አመራር በመስጠት፣ ከማዕከልም የተላኩ ጀነራሎች በዚያ ዐውድ በቀጥታ በመገኘት፣ በየዕለቱ ሕዝብን ማደራጀት፣ ህዝብን ማረጋጋት፣ ሳላም በማምጣት፣ ሀገራዊ አደራቸውን እንዲወጡ በማድረግ፣ በምዕራብ የሀገራችን ክፍል ጋምቤላን ጨምሮ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ወጣ ወጣ ያሉ ሙከራዎችን ቀድሞ በመረዳት ችግሩ እንዳያጋጥም በመግታት ባደረጉት አስተዋጽዖ፣ የመከላከያ ሚኒስቴራችንን አደረጃጀት በአጭር ጊዜ አስጠንቶ ለመንግሥት ማቅረብ በመቻላቸው፣ እንዲሁም የመከላከያ ሠራዊት የኑሮ ደረጃን ለማሻሻል በተደረገ ሰፊ ክርክር የማሻሻያውን እርምጃ በተሾሙ ማግስት ማጽደቅ በመቻላቸው፣ የኢፌዴሪ መንግሥት ልዩ ምስጋና ሊያቀርብላቸው ይፈልጋል፡፡ በጀነራል ሰዓረ መኮንን ያየነውን መከላከያ የአንድነትና የለውጥ ኃይል መሆኑን የማስቀጠል ፍላጎት በሁሉም ጀነራል መኮንኖች እንዲደገም፣ በጡረታ የተገለሉ ጀነራሎች ለወታደር ጡረታ ስለማይሠራ በየትኛውም ጊዜ ችግር ካጋጠመን እናት ሀገር ጥሪ ልታቀርብላችሁ ስለምትችል በየዕለቱ ከመከላከያ ቀርባችሁ ሁኔታ እያያችሁ በመምከር፣ በማገዝ፣ በመደገፍ፣ ወገናዊነታችሁን ማረጋገጥ እንድትችሉ፣ እንዳትበተኑ፣ አንድ ሆናችሁ አንድ ኢትዮጵያን እንድታጠናክሩ አደራ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ፡፡**

**እንኳን ደስ አላችሁ**

# ምስጋና

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የሰላም ተግባር ዕውቅና በሰጠች ጊዜ ያደረጉት

**ጳጉሜን 5/2010 ዓ.ም.**

**ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጥሪ የተደረገላችኹ እንግዶች፤**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በአዲስ ዓመት ዋዜማ ይህን የመሰለ በዓል አዘጋጅታ በአገራችን እየመጣ ላለው ለውጥ ዕውቅና በመስጠቷ የተሰማኝን ታላቅ ደስታ ለመግለጥ እወዳለኹ፡፡

ይህ በዓል የሚከበረው፣ ከኻያ ዓመታት በላይ በኹለት ሲኖዶስ ተከፍላ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን አንድ በኾነችበት ጊዜ መኾኑ፣ ደስታችንን ዕጥፍ ድርብ ያደርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የረዥም ዘመናት ታሪክ ያላት፣ በዚኽች አገር የነጻነት ታሪክ ውስጥ ጉልሕ ሥፍራ የምትይዝ፥ የባህል፣ የቅርስ፣

የሥነ ጽሑፍ እና የሥነ ጥበብ፣ የዜማ እና የኪነ ሕንጻ ባለቤት መኾንዋን ለእናንተ አልነግራችኹም፡፡ ይህች ታላቅ ቤተ ክርስቲያን፥ ለአገራችን ኢትዮጵያ ሰላም፣ አንድነት፣ የሕዝቦች መከባበር እና ፍቅር፣ ልማት እና ዕድገት የምታበረክተው አስተዋፅኦ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

ይህች ታላቅ ቤተ ክርስቲያን፣ ያሏትን መንፈሳዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊ እና መዋቅራዊ ዐቅሞች በመጠቀም አገራችን የጀመረችው ለውጥ ከታሰበለት ግብ እንዲደርስና ኹላችንንም ተጠቃሚ እንዲያደርገን፣ በማንም የማይተካ ሚናዋን መወጣት አለባት፡፡ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ ሙስና እንዲጠፋ፣ ሌብነት ነውር እንዲኾን፣ እርስ በርስ መለያየት እና መጠፋፋት ከታሪካችን መድረክ እንዲፋቅ፣ ጥላቻ እና መለያየት እንዲወገድ፣ አገልጋዮቿን ኹሉ ተልእኮ ሰጥታ ማሠማራት አለባት፡፡

እናንተ መንፈሳውያን አባቶቻችን እንደምታስተምሩን፣ ለውጥ ከራስ ይጀምራል፡፡ ኹላችንም ራሳችንን ለመለወጥ ከተነሣን ዓለምን መለወጥ ቀላል ነው፡፡ የማይጣፍጥ ጨው ለወጡ የሚተርፍ ጣዕም አይኖረውም፡፡ ኹላችንም ራሳችንን ለመለወጥ እና ያሉብንን ችግሮች ራሳችን ለመፍታት ከቆረጥን፣ የዚኽችን አገር ለውጥ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ለማየት እንችላለን፡፡ ለዚኽ ደግሞ፣ አንጋፋዋ እና ታሪካዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ አርኣያ እንደምትኾነን አልጠራጠርም፡፡ በውስጥ ያሉትን ችግሮች በመፍታት እና ብቃት ያለው፣ ዘመኑን የዋጀ እና በንጽሕና ላይ የተመሠረተ አሠራርንና አስተዳደርን ፈጥራ ለሌሎች ተቋማት አርኣያ እንደምትኾን ተስፋ አደርጋለኹ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ ይህን ዕውቅና እና ክብር ስትሰጥ፣ የሠራነው በቂ ነው ብላ እንደማይኾን አምናለኹ፡፡ ነገር ግን የጀመርነው የፍቅር፣ የዕርቅ እና የመደመር ጉዞ ከመጠፋፋት እና ከመተላለቅ፣ ከጥላቻ እና ከመከፋፈል በእጅጉ የላቀና ወደምንፈልገው የሥልጣኔ ምዕራፍ ያደርሰናል ብላ በማመኗ ነው፡፡ እንደ እርሷ ያሉ ታላላቅ ተቋማት፣ ይህን ጉዞ ካበረታቱትና የሚጠበቅባቸውን በጽናት እና በትጋት ከተወጡ ካሰብነው ቦታ በቶሎ መድረሳችን የማይቀር ነው።

ይህ ዕውቅና እና ሽልማት፣ ይህ ዘመን እንዲመጣ ሲታገሉ እና ሲጸልዩ ለነበሩ ኹሉ እንደ ተሰጠ አድርጌ እቆጥረዋለኹ፤ እኛ የእነርሱ ትግል ውጤቶች ነንና፡፡ ይህ ዕውቅና እና ሽልማት፣ አብረውን በመሥራት የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት ለሚተጉ ኹሉ የተሰጠ ሽልማት እና ዕውቅና እንደ ኾነ አምናለኹ፡፡ ይህ ዕውቅና እና ሽልማት፣ ሥራችንን ‹ሀ› ብለን በወጠንበት ጊዜ መሰጠቱ፣ የአገሪቱ የለውጥ ጉዞ እንዲቃና፣ ቤተ ክርስቲያንዋ በጸሎት እና በሥራ ለማገዝ መወሰንዋን የሚያሳይ ነው፡፡

በአገራችን መወቃቀስ ቀርቶ መበረታታት፣ መነቃቀፍ ቀርቶ መደጋገፍ፣ መገፈታተር ቀርቶ መተባበር፣ መወጋገዝ ቀርቶ መተጋገዝ ባህል እንዲኾን የተሰጠን ሽልማት እና ዕውቅና የራሱን አሻራ የሚያሳርፍ ነው፡፡ ምንም እንኳን መንግሥት እና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው ቢባልም፣ አብረው አይሠሩም ማለት ግን አይደለም፡፡ በአንድ አገር ውስጥ ኾነው ለአንዲት ኢትዮጵያ አብረው ሊሠሩ የማይችሉ ተቋማት አይኖሩም፡፡

የሃይማኖት ተቋማት፥ ራሳቸውን አንጽተው እና አብቅተው፣ ጨለማውን የሚገፉ ብርሃኑንም የሚያሰፉ መኾን አለባቸው፡፡ ጠማማውን የሚያረቱ፣ ቀናውንም የሚያተጉ መኾን አለባቸው፡፡ የጎደለውን የሚሞሉ፣ የጎበጠውንም የሚያቀኑ መኾን አለባቸው፡፡ የሃይማኖት ተቋማት፥ የሚደክመውን የሚያበረታቱ፣ የሚሠራውን የሚያከብሩ፣ የሚያጠፋውን የሚገሥጹ ከኾነ፣ ሕዝብን የሚበድል ፍርድን የሚያጓድል መንግሥት በዚኽች አገር መቼም አይኖርም፡፡ የሃይማኖት ተቋማት የሚጠበቅባቸውን የማይወጡ ከኾነ ግን፣ ለእነርሱም ኾነ ለሌሎች የመከራን ዘመን እንደ ፈቀዱ ማወቅ አለባቸው፡፡

ወጣቶቻችን ሰከን ብለው በመንፈስ እና በዕውቀት የበሰሉ እንዲኾኑ፣ በሕዝቦች መካከል መከባበር እና መፈቃቀር እንዲሰፍን፣ ልዩነቶቻችንን እንደ ችግር ሳይኾን እንደ ጌጥ እንድናያቸው፣ የደቦ ፍርድ ቀርቶ የሕግ የበላይነት እንዲከበር፣ የሃይማኖት አባቶች በየመድረኮቻችኹ አስተምሩ፤ ገሥጹ፤ ምከሩ፤ ውቀሱ፡፡

**ከእናንተ የተሻለ በዚኽ ሊሠማራ የሚችል እዚህ አገር ውስጥ የለም፡፡**

ይህ ዕውቅና እና ሽልማት፣ የበለጠ እንድንሠራ፣ የበለጠም ለውጥ እንድናመጣ ከፊት እንደ ፋና፣ ከላይ እንደ ደመና፣ ከታች እንደ ጎዳና የሚኾንልን ነው፡፡ ስንሠራ፣ ሽልማት እና ክብር እንዳለ ኹሉ ስናጠፋም፣ ወቀሳ እና ቅጣት እንዳለ የሚያስተምረን ነው፡፡ ለአገራችን የበለጠ እንድንሠራ በጸሎታችኹ አስቡን፡፡

## ስለ ተደረገልን ኹሉ
## እግዚአብሔር ይስጥልን፡፡

# የሐዋሳ ኢሕአዴግ ጉባኤ ንግግር

**መስከረም 23/2011**

**የተከበራችሁ ጥሪ የተደረገላችሁ**
**የጉባኤው ተሳታፊዎች፣**
**የአጋር ፓርቲ ወኪሎች፣**
**የወዳጅ አገሮች አቻ ፓርቲ ልኡካን፣**
**ክቡራንና ክቡራት፤**

ኢትዮጵያ፥ በሥልጣኔ ቀደምት፣ ጥንታዊትና ታሪክ ጠገብ አገር ናት። ኢትዮጵያ፥ በወጣቶች እና ሕፃናት የተሞላች አዳጊ እና ወጣት አገርም ናት። ወጣትነት፣ የትኩስነት እና የአዲስነት ዘመን ነውና፣ ኢትዮጵያ፣ ዛሬም ማንነቷን በመፈለግ ላይ ያለች፣ የመጪው ዘመን ተስፋዋ ብሩህ የኾነ አዲስ አገርም ናት። ኢትዮጵያ፣ ከርሰ ምድሯ በታሪክ ብቻ ሳይኾን፣ በሀብትም የጠነከረ፣ መልከአ ምድሯ በሜዳ እና ኮረብታ፣ በመስክ እና ጫካ፣ በወንዝ እና ፏፏቴ የተዋበ፣ አየሯ-ከዳሎል ሙቀት እስከ ራስ ዳሸን ቅዝቃዜን በእቅፏ የያዘች ማሕፀነ ለምለም አገር ነች። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ፣ ተዝቆ የማያልቅ ደርዝ ባህል እና ትውፊት፣ የተሰናሰሉ እምነቶች እና ቋንቋዎች ባለቤት የሆነች፣ በጋብቻ እና በጉርብትና የተደመሩ ልጆቿን በክብር እያኖረች የምትኖር አገር ናት።

ኢትዮጵያ፣ የቀደመውን ጠብቀው እና አክለውበት ለመጪው በሚያስተላልፉ ተተኪ ወጣቶች እየተመራች፣ እየተገነባች የኻያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አብሪ ኮኮብ ለመኾን ብቅ ባለችበት የለውጥ ዘመን ላይ እንገኛለን። ሽግግሩ፣ የአገራችን ገበሬዎች እንደሚሉት፣ “የበሬውን ብልሃትና የወይፈኑን ጉልበት” ያቀናጀ እንዲኾን፣ ቀና ልብ እና አርቆ አስተዋይ አእምሮ ይጠይቃል። የቀደመው ትውልድ ያካበተውን ጥበብ ሳይሰስት ሊሰጥ፣ ዐቅም አካብቶ ለተዘጋጀው ለዚህ አዲስ ትውልድ የመሪነቱን በትር ሊያስረክብ ይገባል። ተተኪ መሪዎችም፣ ስለ ባለፈው ከማማረር እና ለጥፋቶች ሰበብ ከመፈለግ ይልቅ፣ በልምድ ሊገኝ የሚችለውን መልካም ትምህርት አስበው፣ ከቀደመው ትውልድ ምክር በመስማት እና በጎውን በመከተል የተሻሉ መሪዎች መኾን ይጠበቅባቸዋል። እነርሱም ተተኪ መኾናቸውን ለአፍታም መዘንጋት አይኖርባቸውም። ከታች የበቀለውን መጪ ትውልድ ከአሁኑ አቅርበው በመኮትኮት፣ መተካካት፥ የታቀደ ሒደት እንጂ፣ ድንገተኛ የመበላላት ክሥተት እንዳልኾነ ሥርዓት ተክለው ማስመስከር ይኖርባቸዋል። የአንድ መሪ ስኬት መለኪያ፣ እርሱ የጀመረውን አስፍተው እና አጠናክረው የሚቀጥሉ ተተኪ አመራሮችን አፍርቶ ማለፍ መኾኑን፣ ኹላችንም ልብ ልንለው ይገባል።

## ክቡራንና ክቡራት የጉባኤ ታዳሚዎች፤

በላቀ ምግባር እና ተግባራቸው፣ ለኢትዮጵያ የገናናነት ክብር ያላበሷት መሪዎች እንደ ነበሯት ኹሉ፣ ያላትን ገፍፈው በመውሰድ ዕርቃኗን በማስቀረት ለኀፍረት ያጋለጧት መሪዎችም ነበሯት። በልጆቿ መካከል የመከፋፈል እና የመለያየት ክፉ ዘርን የዘሩባት መሪዎች እንደ ነበሩ ኹሉ፣ በጠብ እና ጦርነት ሊጠፋፉ የዘመቱ ልጆችዋን አስታርቀው የሰላም ደሴት ያደረጓት አስደናቂ መሪዎችም እንደ ነበሯት አያጠያይቅም። አገራችን ኢትዮጵያ፣ ኹሉንም እንደ ጠባዕዩና ዓመሉ ችላ እና አሳልፋ ዛሬ ላይ ደርሳለች።

አሁን ጥያቄው፣ እኛ የዛሬዎቹ መሪዎችስ ይህቺን ታሪካዊት አገር ከሠመጠችበት አዘቅት ውስጥ አውጥተን ዓለም ከደረሰበት የሥልጣኔ ተርታ በማሰለፍ የአፍሪካ መሪ እና የዓለም ተምሳሌት እናደርጋታለን? ወይስ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ መኾናችንን ረስተን፣ በ18ኛውና በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ነበሩ

ራስ ወዳድ አያቶቻችን እርስ በርሳችን በርስት እና ጉልት ስንፋጅ እና ስንናጠቅ፣ ጓዳዋን ባዶ አስቀርተን የተስፋ ብርሃኗን እናወድመዋለን? ምርጫው እና ሓላፊነቱ፣ በትላንት ገዢዎቻችን አለበለዚያም በዛሬዎቹ የዓለም ኀያላን አገሮች መዳፍ ውስጥ የወደቀ አይደለም። በእኛው እዚኹ በተሰበሰብነው ልጆቿ ብሎም በየሥፍራው አገራችንን የመምራት ሓላፊነትን ለመቀበል አማራጭ መንገዶችን ጨብጠው ወደ አገራቸው በመትመም ላይ ባሉ የዚህ ዘመን ኢትዮጵያውያን ትከሻ ላይ የወደቀ ነው።

## ጓዶች!!

ፖለቲካዊ ሥልጣን፣ ሕዝብን የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ምንጭ አድርጎ መቀበልን የሚጠይቅ ሲኾን፣ በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ማሳተፍንና ማካተትን፣ መናበብንና መደማመጥን የሚያስችል አዲስ የአመራር ዘዬ ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል። የአመራር ዘዬአችን ስኬታማነት ለማረጋገጥ፡-

- ሕዝብ የሚያዳምጣቸውና የሚከተላቸው የሃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሞራል እና የግብረ ገብ መሪዎች መብዛት፤
- የማኅበረሰብን የአመለካከት እና የአስተሳሰብ ደርዝ የሚያሰፉ እና በሐሳብ ልዕልና የሚያምን ትውልድን የሚቀርፁ የዕውቀት እና የፍልስፍና ልሂቃን መበራከት፤
- በሥራ እና ሀብት ፈጠራ የተካኑ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ባለሀብቶች እና ማኅበራዊ ሓላፊነታቸውን የሚወጡ የምጣኔ ሀብት አንቀሳቃሾች መኖር እና ጎልተው መውጣት፤
- በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ አገር እና ዓለም ከደረሰበት የዕድገት ማማ ላይ በፈጣን ግሥጋሴ የሚያደርሱ ታላላቅ ተመራማሪዎች በዩኒቨርሲቲዎቻችን መበራከት፤
- ግጭት እና ሽብር በበዛበት ዓለም ውስጥ፣ ለሉዓላዊነታችን መከበር እና ለሰላማችን መረጋገጥ በሠለጠነ መንገድ የሚሠሩ ሥልጡን የጦር መሪዎች ትክክለኛ ቦታቸውን መያዝ፤

- በሞያዊ ክህሎታቸው እና በአመለካከታቸው የበሰሉ እና የአገልጋይነትን መንፈስ የተላበሱ አመራሮች በሕክምና፣ በምሕንድስና እና በኮንስትራክሽን፣ በግብርና፣ በፍትሕ ሥርዓት ውስጥና በሌሎች የሥራ መስክ መሠማራት፤
- በሚዲያ፣ በሲቪክ ማኅበራት፣ በዴሞክራሲ ተቋማት እና በሌሎች ቁልፍ የሥርዓት ግንባታ መሠረቶች ውስጥ በሓላፊነት መንፈስ በመሥራት ሕዝብን የማንቃት ሚናቸውን በአግባቡ ለመወጣት መታተር፤ እንዲሁም፣ በስፖርት እና በኪነ ጥበብ ተቀባይነት እና ተሰሚነት ያላቸው መሪዎች መፈጠር እና ማደግ ይኖርባቸዋል።

**ያን ጊዜ ነው፣ አገር ትክክለኛ መሪ አገኘች የሚባለው።**

የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ፣ የትላንትናዎቹን ኢትዮጵያውያን ሳይኾን፣ የዛሬዎቹን እኛን ልትመስል የተዘጋጀች ናት። ስለዚኽም የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ቀድመን መምሰል እና መኾን የሚገባን እኛው ራሳችን ነን። የበለጸገች ኢትዮጵያ፣ ለልጆቻችን ማውረስ እና ማስረከብ የምንሻ ከኾነ፣ ዝርፊያውን ትተን ተግተንና ታጥቀን መሥራት ይኖርብናል። እኩልነት እና ሰላም የሰፈነባት ኢትዮጵያ እውን ኾና ማየት የምንመኝ ከኾነ፣ ሌሎችን ዘርንና ሃይማኖትን መሠረት አድርገን አናጥቃ። በፆታ፣ በሀብት እና በመደብ ልዩነት መቃቃር ትተን በእኩልነት እናከብር። እንደ ራሳችን ኹሉ፣ ለሌሎች ሰላም እና እኩልነት ታጥቀን እንሥራ። የየራሳችን ስኬት፣ በሌሎች ውድቀት ውስጥ ሳይኾን፣ በጋራ ስኬታችን ውስጥ ይገኛል። እኛ እንደኾነው አገራችንም ትኾናለች። ማንም ምንም ቢኾን፣ ኢትዮጵያን ለብቻዬ የሠራኹት እኔ ብቻ ነኝ፤ በእኔ ቁመና እና ቀለም ነው የቀረፅኋት ሊል አይችልም። ኢትዮጵያ በኹላችንም ላብ እና ደም የተሠራች የጋራ ቤት ናትና፤ ባለቤቷም ኹላችንም ነን፤ ኢትዮጵያን ኹላችንም ሠርተናታል፤ ኢትዮጵያም፣ ኹላችንም ዛሬ የተላበስነውን ማንነት እና ህልውና ይኖረን ዘንድ ኢትዮጵያውያን አድርጋ ሠርታናለች። እንኳንና ዛሬ፣ ኹላችንም ካለፍንም በኋላ ቢኾን፣ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ኾና ትቀጥላለች።

## ክቡራን እና ክቡራት፤

ኢሕአዴግ ከዳር እስከ ዳር ያሉ ኢትዮጵያውያን የሚሳተፉበት ድርጅት እንዲኾን፣ በጽናት መሥራት ይጠበቅብናል። በታሪክ አጋጣሚ የአራት ድርጅቶች ጥምረት ኾኖ የተመሠረተው ኢሕአዴግ፣ አጋር ፓርቲዎችን ወደ ግንባሩ ለማስገባት ፍላጎቱ እንደ ነበረው የታወቀ ነው። ቢኾንም፣ ጉዳዩ ለነገ እየተባለ ለረዥም ጊዜ እውን ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል። በ10ኛው ጉባኤ ይህ ጉዳይ ተጠንቶ መቋጫ እንዲያገኝ አቅጣጫ ተቀምጦ የነበረ ቢኾንም፣ ከጉባኤው በኋላ የነበረው አገራዊ ቀውስ ይህን መከወን የሚያስችል ባለመኾኑ ጥናቱ ተጠናቆ ለዚህ ጉባኤ ሊቀርብ አልቻለም፤ ነገር ግን ይህን ጉዳይ በአጭር ጊዜ በማጠናቀቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የኢሕአዴግ ሊቀ መንበርም ኾነ በኢሕአዴግ መሪነት የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የመኾን ዕድሉን ማስፋት ይኖርብናል፡፡ ኢሕአዴግ እንደ ስያሜው፣ “የኹሉም ኢትዮጵያ ሕዝቦች” ፓርቲ ማድረግ የኹላችንም ሓላፊነት ነው።

የጀመርነው ፖለቲካዊ ምኅዳርን የማስፋት እንቅስቃሴ፣ ለአገራችንም ለድርጅታችንም የሚበጅ ስለኾነ አጠናክረን እንገፋበታለን። የሐሳብ ብዝሐነትን መፍቀድ የብሔር ብሔረሰብን ብዝሐነት የመቀበል ያኽል የግድ ለአገራችን ሰላም እና ብልጽግና አስፈላጊ ነው፡፡ የተፎካካሪዎቻችንን ሐሳብ የምንስማማበት ላይኾን ይችላል። ያለን አማራጭ ግን፣ ማገድ እና ድምፃቸውን ማጥፋት ሳይኾን፣ በሰላማዊ እና ሕጋዊ መንገድ ታግለን የእኛን ሐሳብ ሕዝብ እንዲመርጠው ማድረግ ይኾናል። በመሠረቱ ዴሞክራሲ ማለት፣ የምንፈልገው ሐሳብ ብቻ እንዲንሸራሸር መፍቀድ ሳይኾን፣ በሕዝብ ውሳኔ እና ምርጫ ተደማጭነትን መቀዳጀት ማለት ነው፡፡ ወርቅ እና ወርቅ ቅቡን የሚፈትነው እሳት፣ የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ብቻ ይኾናል፡፡

## የተከበራችኹ የጉባኤው ታዳሚዎች፤

በአዲሱ የለውጥ እንቅስቃሴያችን የጨበጥነው ፖለቲካዊ አቋም፣ ያለፈውን ከማፍረስ የሚነሣ አይደለም። ወደድንም ጠላንም ያለፈው መንገድ እዚህ ድረስ

አምጥቶናል፡፡ ብንፈልግም ባንፈልግም ልንመልሰው አንችልም። የእኛ ድርሻ ስለ ትላንቱ አብዝቶ መጨነቅ እና መጠበብ ሳይኾን፣ ነገን በጥንቃቄ መገንባት ነው። አንድ ታዋቂ የፖለቲካ ሰው እንዳለው፣ “ማንም ያለፈውን ታሪኩን የማስተካከል አቅም የለውም። የወደፊቱን መገንባት ግን ይችላል። በትላንት ታሪክ ትርክት ስንሟገት ልንሠራ የምንችለውን ዛሬንና ልንሠራበት የሚገባንን ነገ እንዳናበላሽ የታሪክ ጥናትን ለአጥኝዎች በመተው እኛ ቁርሾዎቹን በመፍታት እና የወደፊት አብሮነትን በማረቅ ዙሪያ ማተኮር ይኖርብናል። ብንስማማም እንኳን፣ ትላንትን መቀየር አንችልም፤ ከተስማማን ግን ነገን መቀየር እንችላለን፡፡”

እንደ አገር እና እንደ ሕዝብ፣ የብዙ ብዙና ውስብሰብ ችግሮች የተከበብን ነን። እንዲያም ለመኾኑ ከበቂ በላይ ምክንያቶችን መደርደር ከባድ አይደለም። ችግሩ የአገር እና የሕዝብ መጻኢ ዕጣ ፈንታ በታሪክ ብቻ አይወሰንም። የተደረገውን በመደጋገም እና አዲስ ነገር በመጣ ቁጥር እንዳልተገራ ፈረስ ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት የምናስቸግር ከኾነ፣ አገራችን የምትመኘውን ፈጣንና ኹለንተናዊ ለውጥ ልናመጣ አንችልም። ዓለም በተንጣለለው ሕዋ ሲዋኝ እና በረቂቅ ሕዋስ ውስጥ ገብቶ የተሰወረውን የሕይወት ምሥጢር ለመረዳት ሲታትር፣ እኛ ከእንፉቅቅ ጉዟችን ጥቂት ፈቅ ለማለት በሞከርን ቁጥር፣ “ይህማ አይኾንም፤ አይደረግም” ካልን በኋላ ቀርነት ጉድጓድ ውስጥ ተቀብረን ለመቅረታችን ማረጋገጫ ምልክት ነው።

አሁን የምንገኘው፣ ያለፈውን በመተቸት የምናለቅስበት ወይም ተኩራርተን የምንሸልልበት ጊዜ ላይ ሳይኾን፣ ተግቶ በመሥራት እና ነቅቶ በመገሥገስ አዲስ ታሪክ መሥራት የምንጀምርበት ታሪካዊ ጊዜ ላይ ነው። መልካም ምኞት ሳይኾን ንቁ ተሳትፎ፣ ጥረት ሳይኾን ፍጥነት፣ ፍጥነት ብቻ ሳይኾን ብልሃት፣ በግል ብቻ ሳይሆን አብሮ የመሥራት እና የመደመር እሳቤን በሙሉ አቅም ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅብናል።

## ጓዶች!!

እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት፣ በብዙ ፈርጅ ብዝሐነት ያለበት አገር፣ ፌዴራሊዝም ተመራጭ የአስተዳደር ሥርዓት ነው። የፌዴራል መንግሥት አወቃቀር ደግሞ፣ የአገሪቱን ታሪካዊ እና ነባራዊ ኹኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ መኾን አለበት። ከአፈጻጸም አንጻር ግን፣ መሠረታዊ ችግሮች አጋጥመዋል። የመጀመሪያው፣ ክልላዊ አስተዳደርን ከብሔር ጋራ ማምታታት ነው። ክልላዊ አስተዳደሮች፣ በክልላቸው ያሉ ሕዝቦችን ኹሉ የሚያስተዳድሩ መኾናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትርክት ውስጥ፣ የብሔር ማንነት እና ኢትዮጵያዊ ማንነት እስከ አሁን ድረስ ሚዛን ጠብቀው መሔድ አልቻሉም። በዚኽም ምክንያት ኢትዮጵያውያን፣ ባለፈው የመቶ ዓመት ታሪካችን፣ አንዴ አንዱን ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላውን ብቻ እንድንጋት በመገደዳችን፣ ኹለቱን ማንነቶች እንደተነባበሩ ማንነቶች ሳይኾን እንደሚተካኩ ማንነቶች የማየት ዝንባሌ ተፈጥሮ ቆይቷል። የፌዴራል ሥርዓት ከገነባን በኋላ የሔድንበት መንገድም፣ የብሔር ማንነት ብቻ ጎልቶ እንዲወጣ የሚያደርግ በመኾኑ፣ አሁን አሁን እየከፈልናቸው ላሉ ውድ ዋጋዎች መነሻ ምክንያት ሊኾን ችሏል። በቀጣይ ግን፣ እነዚኽን ኹለት ማንነቶች ሚዛን አስጠብቀን ለማስቀጠል፣ ሐቀኛ የኾኑ የሕዝብ ለሕዝብ መድረኮችን፣ የባህል ትውውቆችንና ሌሎችም ሕብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያን የሚያሳዩ ኹኔታዎችን ለማጠናከር ከፍተኛ ርብርብ መደረግ ይኖርበታል።

ፉክክራችን በዋናነት፣ ከዓለም ጋራ እንጂ እርስ በርሳችን ሊኾን አይገባም። ከዓለምም ጋራ እንኳ ስንፎካከር በመጠፋፋት መንፈስ ሳይኾን፣ ልቆ በመገኘት እና ለኹላችንም የምትኾን የተሻለች ዓለምን በመገንባት ቀና መንፈስ መኾን ይኖርበታል። እርስ በርስ ግን ከመደመር የተሻለ አማራጭ የለንም። መደመር፣ ኹሉም የየራሱን ጥንካሬ ይዞ ከሌሎች ጥንካሬ ጋራ በመዋሐድ የበለጠ ጠንካራ የመኾን አቅጣጫ እና መንገድ ነው። ማንኛችንም ብንኾን በተናጠል ከኹላችን በላይ ልንኾን አንችልም። ኹላችንም ሙሉ በሙሉ በሌላው ሰው የማይተካ እምቅ አቅም አለን። የአንዳችንን መጉደል በሌላችን ልንሸፍነው እና ልንሞላው

አይቻለንም። የኹላችንም መሰባሰብ፣ በተናጠል ሥርተን ከምናገኘው ድምር በላይ የኾነ የተዋሐደ አካል ለመፍጠር ያስችላል።

## ክቡራን እና ክቡራት፤

በብዙ ብዙ ምክንያት፣ ፖለቲካዊም ኾነ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ፣ መነሻ ምንጩ ብቻ ሳይኾን፣ ማስተካከያ መፍትሔውም፣ ከሞራል እና ግብረ ገባዊነት ደረጃ ቁርኝት ያለው ጉዳይ ነው። የሥራ ፍቅርን፣ የሰው ክቡርነትን፣ የሐሳብ ልዕልናን እንዲሁም የሰላምንና የእኩልነትን ዋጋ፣ በሞራል እና በግብረ ገብ ደረጃው በወደቀ ማኅበረሰብ ውስጥ ማሥረጽም ኾነ መተግበር የሚታሰብ አይደለም። በይቅርታ እና ዕርቀ ሰላም፣ በፍቅር እና መደመር መሻገር የምንሻ ከኾነ፣ አስቀድመን የኅሊና እና የሞራል ተሐድሶን እንደ ግለሰብም እንደ ማኅበረሰብም ማረጋገጥ ይኖርብናል። ዝርፊያ እና ስግብግብነት፣ ጥላቻ እና ዘረኝነት ምንጫቸው፣ የሞራል እና የግብረ ገብ ደረጃ መዝቀጥ በመኾኑ፣ መሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ የእምነት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች በንጹሕ ኅሊና፣ በሞራል ብቃት፣ በቃል እና በግብር ተምሳሌትነት ሕዝባችንን ከጥፋት መታደግ ይኖርብናል።

በመልካም አስተዳደር መስከ የቆለልነውን የችግር ተራራ ደፍረን ልናየው ይገባል። ችግሩን የመልካም አስተዳደር ችግር እያልን ከምናሽሞነምንበት ዐውድ መውጣት ይኖርብናል። ችግሩ መልካም አስተዳደር ከማስፈን በላይ በመኾኑ፣ መጥፎ አስተዳደር ብለን ብንጠራውና የማይታለፈውን ቀዩን መሥመራችንን ብናሥምር የተሻለ ይኾናል። ዜጎች መታወቂያ ለማግኘት፣ ሕክምና ለማግኘት፣ መሠረታዊ የኑሮ ግብዓቶችን በገዛ ገንዘባቸው ለመሸመት የሚያዩትን እንግልት፣ በምንም መልኩ የመልካም አስተዳደር ችግር ነው ብሎ መፈረጅ ችግሩን ማሳነስ ይኾናል። በተመሳሳይ መልኩ፣ የዳቦ ስም ያወጣንላቸውን፥ ኪራይ ሰብሳቢነትን፣ አላግባብ መበልጸግንና ሙስናን በትክክለኛ ስማቸው ሌብነት እያልን በመጥራት በጽኑ መታገል እና ሊታለፉ የማይገቡ ቀይ መሥመሮቻችን መኾናቸውን ማሳወቅ ይኖርብናል።

በመጨረሻም፣ በዚኽ ለሦስት ቀናት በሚቆይ ጉባኤ ተሳታፊ የኾናችኊ ኹሉ፣ ውጤታማነቱን ማረጋገጥ የሚያስችል ንቁ ተሳትፎ እና ጥሞናዊ የመደማመጥ ጊዜ እንዲኖራችኹ እየተመኘኹና ለፕሮግራሙ መሳካት አስተዋፅኦ ያደረጉ ኹሉንም አካላት ከልብ እያመሰገንኹ፣ የኢሕአዴግ 12ኛው ጉባኤ መጀመሩን በኦፊሴል አሳውቃለኹ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት እና ኅብረት**
**ታፍራ እና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!!**
**ዘላለማዊ ክብር ለትግሉ ሰማዕታት!**
**አመሰግናለሁ**

# የጀርመን ፍራንክፈርት ንግግር

**ጥቅምት 21/2011 ዓ.ም.**

**አይነን ሾነን ጉተን ታግ!**
**ኤይቶፒሼ ዲያስፖራስ ኢን**
**ዶችላንድ ኡንት ኤይሮፓ!**
**ክቡራት እና ክቡራን!**

**ከመላው አውሮፓ የተሰበሳባችኹ የአገሬ ልጆች ሆይ፤**

የማይንን ወንዝ ተገን አድርጋ በተቆረቆረችው፣ የገንዘብ እና የኢንዱስትሪ ማዕከል በኾነችው ፍራንክፈርት ተናኝተን በዐይነ ሥጋ መተያየታችንንን እንደ ታላቅ ዕድል እቆጥረዋለኹ። ከአገር የወጣችኹበት ዘመንና ምክንያት እንደ ቁጥራችኹ ብዙ፣ እንደ የመጣችኹበት አገር ለየቅል መኾኑ ግልጽ ነው።

**ለትምህርትም ይኹን ለሥራ፣ በፖለቲካም ይኹን በኢኮኖሚ የተሰደዳችኹ ወገኖቼ…**

ከምንወዳት አገራችንና ኹል ጊዜም ከምትናፍቁት ሕዝባችን፣ እጅግ የከበረ ሰላምታ ላቀርብላችኹ እወዳለኹ።

አገራችን ኢትዮጵያ፣ እንደ ዛሬው ከኋለኞች ተርታ ተመድባ በችግር ከመታወቋ በፊት ከአውሮጳ አገሮች ጋራ ታሪካዊ የኾነ ግንኙነት ነበራት። ከእንግሊዝ ጋራ በትምህርት፣ ከፈረንሳይ ጋራ በባቡር ሐዲድ፣ ከፖርቱጋል ጋራ በጦር ትብብር፣ ከቱርክ እና ከግሪክ ጋራ በንግድ፣ ከስዊድን ጋራ በጤና እና በአየር ኀይል፣ ከሩሲያ እና ከሌሎች የምሥራቅ አውሮጳ አገሮች ጋራ በተለያዩ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስር የነበረን ታሪካዊ ተዘምዶ እስከ ዛሬም የቀጠለ የወዳጅነታችን መሠረት ነው።

**ከጀርመንም ጋራ ቢኾን ጠንካራ ትስስር ነበረን።**

አምስተኛዋ ግዙፍ የጀርመን ከተማ ፍራንክፈርት፣ የታዋቂው ደራሲ ዮሐን ዎልፍ ጋንግ ቮን ጎይተ ከተማ ናት።

በዚህ ታላቅ የጥበብ ሰው ስም የተቋቋመ ስመ ጥር ኢንስቲትዩት በአገራችን ከመኖሩ በተጨማሪ፣ የጀርመን የባህል ማዕከል እና ትምህርት ቤት መቋቋሙ ጠንካራ ትስስር እና ወዳጅነት ስለ መኖሩ አንዱ ማሳያ ነው።

እንደ አገር ከጀርመን ጋራ፣ እንደ አጠቃላይ ደግሞ ከአውሮፓ ጋራ ወዳጅነት ብቻ ሳይኾን ተመሳስሎም አለን።

እንደምታውቁት፣ ለእኛ የቅርብ ጊዜ እውነታ በኾነው ጦርነት እና ግጭት ውስጥ ያላለፈ የአውሮጳ አገር የለም። ለምሳሌ ያኽል፣ በኹለተኛው የዓለም ጦርነት በእጅጉ ከተጎዱት የአውሮፓ ከተሞች መካከል አንዷ ፍራንክፈርት ናት። ብዙ ሕዝብ አልቆባታል፤ መኖሪያ ቤቶቿ የሙታን መንደሮች መስለው ነበር፤ አያሌ የንግድ እና የገበያ ሥፍራዎቿ ወደ ፍርስራሽነት ተቀይረዋል።

ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ ታዋቂ የነበረው እና በወቅቱ ከጀርመን በታላቅነቱ ተወዳዳሪ የሌለው ዋናው የንግድ መናኸሪያዋ ወድሟል። ኾኖም ግን፣ የማይበገሩት እና ለችግር የማይረቱት ፍራንክፈርቶች፣ ከተማቸውን እንደገና ገንብተው የአውሮጳ የፋይናንስ ማዕከል ለማድረግ አርባ ዓመት እንኳ አልፈጀባቸውም።

**ይህ ለእኛ ትልቅ ትምህርት ነው።**

ኻያ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የዓለማችንን ታላላቅ ጦርነቶች የማስተናገድ ክፉ ዕጣ በላያቸው ላይ የተጫነባቸው አውሮጳውያን፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦቻቸውን ዐጥተዋል፤ ለዘመናት የተገነባ ታሪካቸው ዓመድ ኾኗል፤ የልዩነት ግንብ በመካከላቸው ተገንብቶ ቆይቷል።

በዘመኑ አውሮጳውያን፣ እንኳንስ ለሌሎች ሕዝቦች መጠጊያ ሊኾኑ ይቅርና በገዛ አገራቸው ተስፋ ቆርጠው ስደትን የመረጡ ዜጎች ቁጥር ቀላል አልነበረም።

ያ ኹሉ አበሳ የመጣው፣ በጥቂቶች፣ ከሕዝብ ፍላጎት ይልቅ በግል ጥቅማቸው በታወሩ መሪዎች እና የእኛ ዘር ከኹሉም ይበልጣል ባይ ደመ ነፍሳውያን ቅዠት መኾኑ፣ በጸጸት የሚታወስ ክፉ የጦርነቱ ጠባሳ ነው።

የዚኽ አሠቃቂ ጥፋት የፍጻሜ ትርፉ ድህነት፣ ጉስቁልና፣ ስደት፣ ወረርሽኝ እና እልቂት ብቻ ነበረ።

ኾኖም፣ ጠንካሮቹ አውሮፓውያን ከአንደኛው እና ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት እጅግ በፈጠነ ጊዜ አገግመው፣ ዛሬ ላይ እናንተን ጨምሮ ከመላው ዓለም ሚሊዮኖችን እስከ ማስጠለል ደርሰዋል።

**እርስ በርስ መሸናነፍን ትተው ዓለምን ማሸነፍ ችለዋል።**

ይኼን ያሳኩት በአጋጣሚ አይደለም። ወገባቸውን አስረው፣ ተስፋ መቁረጥን አባርረው፣ የደረሰባቸውን መከራ ኹሉ ለነገ ሲሉ ታግሠው፣ ለአገራቸው አንድ ኾነው በትጋት ስለ ሠሩ ብቻ ነው።

እዚኽ ቦታ በፊታችኹ ስቆም፣ አገራችን በኢኮኖሚ በልጽጋ፣ ሰላማችን ሙሉ በሙሉ ተሟልቶ፣ ግጭት ጠፍቶ፣ ዴሞክራሲ ጎልብቶ፣ ሰብአዊ መብቶች በላቀ ኹኔታ ተከብረው ቢኾን፣ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር፤ ግን አይደለም። አሁን በእጃችን

ያሉን ኹለት ነገሮች ናቸው - ነጻነት እና ተስፋ። እነዚኽን ኹለቱን ይዘን፣ በትብብር እና በአንድነት ከሠራን የምንሻት ኢትዮጵያን ከመፍጠር የሚያግደን የለም።

ከጦርነቱ ማግሥት፣ አውሮጳውያን ከመለያየት ይልቅ አንድነትን፣ ከመገፈታተር ይልቅ ትብብርን የመረጡት፣ ጥቅሙ ስለ ገባቸው ነው።

**ሕዝቡ ጦርነትን አምርሮ ቢጠላ፣ ገፈት ቀማሽ ኾኖ ስላየው ነው።**

ዘረኝነትንና የበላይነት አባዜን አምርሮ የተዋጋው ከአደረሰበት ውድመት እና ጥፋት ስለ ተረዳው ነው።
ይህ፣ እንደ አገር እና እንደ ሕዝብ፣ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የሚሰጠን ትምህርት ከፍተኛ ነው።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ውስጥ፣ ብዙዎቹ የለውጥ ጅምሮች፣ በሙሣርያ እና በዐመፅ ተጀምረው፣ በማሸነፍ እና በመሸነፍ፣ በማሳደድ እና በመሰደድ የተደመደሙ መኾናቸው ለኹላችን ግልጽ ነው። አዲስ የሰላም እና የዕርቅ ምዕራፍ ከመኾን ይልቅ፣ የሌላ ዙር ውጊያ እና ዐመፅ መጀመሪያ የኾኑበት አጋጣሚ ብዙ እንደ ነበር የትላንት ታሪካችን ምስክር ነው።

**አሁን፣ ያላየነውን የምናይበት፣ ያልሞከርነውን የምንሞክርበት ዘመን ነው።**

ምኞታችንን ተወት አድርገን፣ መከራዎቻችንን ታግሠን፣ ጥርሳችንን ነክሰን የምንሠራበት፤ ለአገራችን በተባበረ ክንድ የምንተጋበት ወቅት ነው።

በየጎራው ያሉ ኀይሎች አሸናፊ የሚኾኑበትን የፖለቲካ ባህል ከአውሮፓ ተምረን፣ እንደ አገር አሸናፊ የምንኾንበትን መንገድ መያዝ አለብን፤ ይገባናልም።

## የተከበራችሁ ወገኖቼ!

ከሩቁ ኾናችሁ ስለ አገራችሁ ስትሰሙ፣ በአንድ በኩል ትደሰታላችሁ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ትከፋላችኹ።

**አንዳንድ ጊዜ ተስፋ ታደርጋላችኹ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ተስፋ ትቆርጣላችኹ።**

ግን ርግጠኛ መኾን ያለባችኹ አንድ ነገር፣ ኢትዮጵያ ማንም ተነሥቶ በወደደው ልክ እና መልክ እንደ ቂጣ ጠፍጥፎ የሚጋግራት የግል ርስት ሳትኾን፣ ዘመናትን ያስቆጠረች፣ ታላቅ ሕዝብ የመሠረታት፣ ታላቅ አገር መኾኗን ነው።

“እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ጎበኘው” እንደተባለው፣ አንቀላፍታ ይኾናል እንጂ አልሞተችም፤ ደክማ ይኾናል እንጂ አልተሸነፈችም፤ ቀጥና ይኾናል እንጂ አልተበጠሰችም።

ተስፋ ሳንቆርጥ፣ ሳንከፋፈል እና ጊዜያችንን የማይጠቅም ነገር ላይ ሳናባክን፣ ወገባችን አጥብቀን ከሠራን፣ አገራችንን ታላቅ ማድረግ የሚከብድ አይኾንም።

**መቼም፣ ኢትዮጵያዊ ኾኖ፣ የኢትዮጵያን ክፉ ማየት የሚመኝ ጤነኛ ሰው አለ ብዬ አላምንም።**

እዚህ ከተሰበሰባችኹ የአገሬ ልጆች መካከል፣ የአገሩ ነገር ሆዱን የማይበላው፣ ውስጡን የማያንሰፈስፈው ሰው አይኖርም።

ኢትዮጵያዊነትን ከቃላት በዘለለ እና ከስሜት በተሻገረ መልኩ በሥራ የምናሳይበት ዘመን ላይ ስለኾን፣ ለጊዜው የማይጠቅመውን ትተን፣ የሚያስፈልገንን አጥብቀን መያዝ ይኖርብናል።

ወደድንም ጠላንም፣ እንደ አገር ልንሸሻቸው በማንችላቸው ሦስት መሠረታዊ የጊዜ ማዕዘኖች መካከል ላይ እንገኛለን።

ከትላንት ስሕተቶቻችን የምናስተካክለው፣ ዛሬ ተግተን ልንሠራው የሚገባን፣ ለነገ ደግሞ የምንገነባው ኹነኛ መሠረት አለ።

እነዚኽን ሦስቱን አጣጥመን ለመሔድ በምናደርገው ትግል፣ አንዳንድ ጊዜ ወደ አንዱ መነተታችን አይቀሬ ነው።

ከትላንት፣ አያሌ መልካም ነገሮችን እንደ ወረስን ኹሉ፣ ብዙ መስተካከል ያለባቸው ነገሮችንም ወርሰናል። ፍትሕን፣ የሰብአዊ መብት አያያዝን፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን፣ የዳበረ የሥራ ባህልን፣ በሕግ እና በሥርዓት መኖርን፣ ሐሳብን በነጻነት መግለጽን፣ ረኀብንና ድህነትን ማስወገድን በተመለከተ ገና ብዙ የሚቀሩን ሥራዎች አሉ።

እነዚኽን የምናሳካው በማንመልሰውና በማንቀይረው ትላንት ላይ እየተጨቃጨቅን፣ ወርቃማ ዕድላችንንና ጊዜያችንን በማባከን ወይም ጥቂቶች በሚያዘጋጁልን አጀንዳዎች በመተራመስ ሳይኾን፣ ልቡናችን የሚያውቀውን በጎ ሐሳብ ወደ ተግባር በመቀየር ነው።

ጊዜውን መጣያ እንዳጣ ሰው፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ተጥደን፣ ውድ ዕውቀታችንንና ጉልበታችንን በማፍሰስ ሳይኾን፣ ትርጉም ያለው ሥራ ላይ በመሰማራት ጭምር ነው። ጨለማውን ለመግፈፍ ሻማ ማብራት እንጂ፣ የጨለማውን ክብደት እና ጽልመት መስበክ መፍትሔ አይኾንም።

እኔ ለአገሬ ምን ሠራኹ በማለት እንጂ፣ እነ እገሌ አገሬን ጉድ ሠሯት፤ እያልን መዓት ብናወራ፣ ጠብ የሚል ነገር አይኖርም። ይህን ማድረግ ካልቻልን፣ ለአገራችን ያለን ጥልቅ ፍቅር በግብር የሚገለጸው እምኑ ላይ ነው?

## ክቡራን እና ክቡራት፤

ፍትሕ እና ዴሞክራሲ ስለተፈለጉ ብቻ አይገኙም። በሰላማዊ ሰልፍ እና በማኅበራዊ ሚዲያ ዘመቻ፣ ጠዋት ተዘርተው ማታ የሚያፈሩ ዛፎችም

አይደሉም። እነርሱን የሚያበቅሉ፣ አብቅለውም ማሳደግ የሚችሉ ተቋማትን ይፈልጋሉ።

እነዚኽ ተቋማት ባልተገነቡበት፣ ተገንብተውም ባልዳበሩበት ኹኔታ፣ የምንመኘውን ፍትሕንና ዴሞክራሲን ሳይኾን፣ የጠላነውንና የሸሸነውን ሥርዐት አልቦነት እና አፋኝነት አጭደን ምርቱን ማቀፋችን አይቀርም።

**እህሉን ስለ ፈለግነው እና ስለ ዘራነው ብቻ አይበቅልም።**

መሬቱ እህሉን ለማብቀል የሚችል፣ ሰብሉም ተገቢው ክብካቤ የሚደረግለት ከኾነ ብቻ ነው፣ ዛሬ ቡቃያ ኾኖ የሚያጓጓን የለውጥ ሰብል፣ ነገ ኹላችን ስንመኘው የኖርነውን የሥልጣኔ እና የብልጽግና ነዶ ሊያሳቅፈን የሚችለው።

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እየተተከለ ያለው፣ አዲሱ የለውጥ ርምጃ አቅጣጫው በዚኹ የሚመራ ነው።ፍትሕንና ዴሞክራሲን ሊሸከሙ፣ ሊያሣልጡ፣ ሊያሰፍኑ እና ሊያስከብሩ የሚችሉ ተቋማትን በመገንባት ላይ እንገኛለን። በተጓዳኝም ለተቋማቱ የሚመጥን አመለካከት ያላቸው ባለሞያዎችንና ቢሮክራቶችን መምረጥ፣ ማሠልጠንና መመደብ የሳንቲሙ ሌላኛው ገጽታ ነው።

ውጤታማነት እና ቅልጣፌን እንዲያረጋግጥ ተደርጎ ሰሞኑን ያዋቀርነው አዲስ ካቢኔም ከዚኹ ዓላማ እና ግብ የመነጨ ነው። ምርጫ ቦርድ፥ ነጻ፣ ተኣማኒ እና ገለልተኛ እንዲኾን ለማድረግ የሕግ እና የመዋቅር ማሻሻያ እየሠራን ነው። የጸጥታ እና የደኅንነት ተቋማት፣ በሠለጠነ መንገድ የዜጎችን መብት እና ክብር ጠብቀው የሚፈለግባቸውን ሥራ እንዲሠሩ ጠንካራ ሪፎርም በማካሔድ ላይ እንገኛለን።

መከላከያችን በኹሉም መልኩ ኢትዮጵያን የሚወክል እና የሚመስል፤ የዘመነ እና ከማንኛውም ዓይነት ጥቃት አገሪቱን ሊጠብቅ በሚችልበት ቁመና ላይ እንዲገኝ የበኩላችንን እየሠራን ነው። የፍትሕ ተቋማት ለዜጎች መብት መከበር የሚሠሩ፣ በገለልተኝነት፣ በሕግ የበላይነት እና በኅሊናቸው ልዕልና ብቻ እንዲዳኙ፣

በሕዝቡም ዘንድ የሚከበሩ እና የሚታፈሩ ተቋማት እንዲኾኑ ማድረግ፣ የዚኽ ዓመት አንዱ እና ዋናው ሥራችን ነው። በቅርቡ ተከታታይ ርምጃዎችን በፍትሕ ዘርፉ ላይ እንወስዳለን፡፡ የትምህርት ሒደቱ የተሻለና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪ እንዲኾን ለማስቻል፣ ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቶለት በሚመለከታቸውም አካላት እንዲታይ፣ ሰፊ የተግባር እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንገኛለን።

**የትላንቱን ዝንፈት ከመጠገንና በጠንካራ መሠረት ላይ ከማነጽ ጎን ለጎን፤**

የዛሬው ግንባታ ከሥር ከሥሩ እንዲፋጠን፣ አሁን ላለው ትውልድ ሥራ መፍጠር፣ ኢኮኖሚው በሚገባ እንዲያንሠራራ ማድረግ፣ የኑሮ ውድነትን መቋቋም፣ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚፈጠሩ ግጭቶችን ማብረድ እና እንዳይከሠቱ ማድረግ፣ የውጭ ግንኙነታችንን ውጤታማ ማድረግ፣ ለነገ ፋታ የማይሰጡን ተግባራት ናቸው።

**ለነገው ትውልድ የምትኾን ኢትዮጵያን መገንባት ደግሞ ከፊታችን ተዘርግቷል።**

## የአገሬ ልጆች፤

በሦስት ግንባር ከከፈትነው ጦርነት ጋራ የምናደርገው ትግል መደምደሚያው በድል እንደሚጠናቀቅ በፍጹም አልጠራጠርም።

የደቡብ ኮሪያ ፕሬዝዳንት የነበሩት ጄኔራል ፓርክ፣ በጀርመን አገር በነርስነት እና በማዕድን ቁፋሮ ሥራ ተሠማርተው ይኖሩ የነበሩ የዳያስጶራ ዜጎቻቸውን ደመወዝ፣ በመያዣነት በመጠቀም ብድር መጠየቃቸው ይታወሳል። በሒደትም ተመጽዋች የነበረች አገራቸውን፣ ዛሬ ከዕድገት ማማ ማውጣት እና ለጋሽ አገር ማድረግ ችለዋል።

የእኛ ትውልድ - የምታኮራ እና አንጸባራቂ የኾነች ኢትዮጵያን የመገንባት ግዙፍ ሓላፊነት ከፊታችን ተዘርግቷል። ምናልባትም፣ የሚነሣው ቁልፍ ጥያቄ፣ ይህን ማድረግ ይቻለናል ወይ? የሚል ነው።

**ያለጥርጥር አዎ! ይቻለናል! ነው፤ መልሱ።**

ምክንያቱም፣ ኢትዮጵያን ያህል ታላቅ አገር፣ ባለ ክቡር ታሪክ፣ የጠቢባንና የሊቃውንት መፍለቂያ ምድርን፣ የማይበገር እና የማይናወጥ ሕዝብ ይዞ መሸነፍ የማይታሰብ ነው።

ከተባበርንና አንድ ከኾን፣ በትንንሾቹ ጉዳዮች ላይ የተጣዱ ትኩረቶቻችንን ወደ ታላላቆቹ ቁም ነገሮች መልሰን ትልቁ ሥዕል ላይ ካተኮርን፤ ዛሬን ለነገ ስንል ችለን፣ ለኹላችንም የምትኾን አገር ለመገንባት ከቆረጥን፤ ጉልበታችንን በማይረቡ ነገሮች ላይ ካላፈሰስን፤ ምንጮቹን ጅረቶች፣ ጅረቶቹን ወንዞች፣ ወንዞችንም ባሕሮች ለማድረግ ቆፍጠን ብለን ከሠራን፤ ድላችን ሩቅ አይኾንም፤ ይቻለናል፤ የድል ነጋሪትም ይጎሠማል።

## የተከበራችኹ የአገሬ አምባሳደሮች፤

እኔ ዛሬ እዚኽ የቆምኹት፣ እናንተ በአውሮጳ የኢትዮጵያ አምባሳደሮች እንደ ኾናችኁ ከልቤ ስለማምን እና ከኮርያውያን ስለ ተማርኹም ጭምር ነው።

የአገራችኹ ነገር ስለሚያሳስባችኹ፣ ቀን በሥራ ብትደክሙም፣ ሌሊቱን በሐሳብ ተጉዛችኹ ስለ አገራችኹ ስትብሰለሰሉና ላይ ታች ስትሉ እንደምታድሩ በሚገባ አውቃለኹ።

እዚኽ ማስናችኹ ከምታገኙት፣ አገር ቤት ያለው ዘመዳችኹ፣ እኩል ተካፋይ እና የወዛችኹ ተጠቃሚ መኾኑም ድንቅ ነው። ለራሳችኹ በኪራይ ቤት እየኖራችኹ፣ የወላጆቻችኹን ቤት ትሠራላችኹ። እናንተ ለመማር ያላችኹን ዕድል አሳልፋችኹ እና ቀን ከሌት እየለፋችኹ፣ ታናናሾቻችኹን ታስተምራላችኹ።

ይህን ኹሉ የምታደርጉት፣ በርግጥ አገራችኹን ስለምትወዱ ነው። ስለዚህም አምባሳደሮች ብላችኹ አይበዛባችኹም።

ኢትዮጵያውያን ከአውሮፓ ጋራ ያላቸው ትውውቅ፣ ከ500 ዓመታት በላይ ዕድሜ ማስቆጠሩን የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ። በዚኽ ዕድሜ ውስጥ፣ ኢትዮጵያውያን በተደራጀ እና በአሠራር በተደገፈ መልኩም ባይኾን፣ ለአገራቸው የሚኾን ብዙ ነገር እየቀሰሙ በነጠላ እና በቡድን በመኾን ወደ አገራቸው ተመልሰዋል።

እናንተም እንደ እነርሱ፣ ለአገራችኹ የሚበጀውን ሥራ ኹሉ ለመሥራት መትጋት ይኖርባችኋል።ዕውቀትን አሻግሩ፤ ለአገራችኹ የገቢ ምንጭ ፍጠሩ። አዲስ አሠራሮችን አምጡ፤ እንዲኾን የምትመኙትን በጥልቅ መረዳት ጨብጣችኹ ወደ አገራችኹ ኑና ተግባራዊ አድርጉት።

ከማንም አትጠብቁ። ኢትዮጵያ የእናንተ ናት። ማንም ቢኾን፣ የእናት እና የአባቱን ቤት በማገዝ እንጂ በማማረር ለውጥ አያውቅም። ኢትዮጵያም ይህንኑ ትፈልጋለች። ማን ለማን ቅሬታ ያቀርባል? ኹላችንም እኛው ነን። ማን ማንን ያማርራል? ኹላችንም እኛው ነን። ማን ለማን ሥራውን ይተወዋል? ኹላችንም እኛው ነን። አንድ ቤተሰቦች ነን።

## አምባሳደሮቼ ሆይ!

**አሁን በአውሮፓ ቅዝቃዜው እየጀመረ ነው።**

ከክፍለ ዘመናት በፊት፣ በድፍን አውሮጳ በቅዝቃዜው ጦስ ብዙ ሕዝብ ያልቅ ነበር።

የህልውና ጉዳይ ነውና በችግሩ ከመረታት ይልቅ፣ ችግሩ ወደ ብልሃት መራቸው።

የበረዶውን ወቅት፣ በማሞቂያ እና በበረዶ መጥረጊያ የሚያልፉበትን ብልሃት ቀየሱ።

**የሐሩሩንም ግለት ለማብረድ፣ የአየር ማቀዝቀዣዎቻችንን ፈለሰፉ።**

በችግር መቆዘም እና ማማረር ሳይኾን፣ ችግርን እንደ ዕድገት መሰላል እና ድልድይ በማየት ጉዞን በፍጥነት ወደ ላይ እና ወደ ፊት ማድረጉ ይበጃል።

ስለዚኽ፣ አንድ ኾነን ዛሬ እንነሣ! የምንተኛበት ሳይኾን የምንነቃበት፣ የምንከፋፈልበት ሳይኾን ያለንንና የኾነውን ኹሉ በአንድነት አጣምረን የምንነሣበት ጊዜ ነው።

ትላንት ከእኛ ውጭ ነው። ቆርጠን ከተነሣንና ከተጠቀምንበት፣ ያለንም ያለነውም ዛሬ ላይ ነው።

የማግለል ሳይኾን የማቀፍ፣ የመንቀፍ ሳይኾን የማበረታታት፣ ኹሉን ለእኔ የሚል ሳይኾን የመተሳሰብ ባህል ከፈጠርን ደግሞ፣ ገና ያልተነካው ነገም፣ አንጡራ ሀብት እና ወርቃማ ዕድል ኾኖ ከፊታችን ይጠብቀናል።

ዛሬ ላይ በርትተን በመሥራት፣ የነገን የሠለጠነ ማኅበረሰብ እና የበለጸገች ውብ ኢትዮጵያን አብረን እንገንባ።

ከዐሥር ዓመት በኋላ፡- ችግሮቿን ኹሉ ትዝታ ያደረገች፣ የማትፈርስ፣ የማትቀለበስ እና ወደ ኋላ የማትመለስ፣ ለኹላችንም የምትበቃ፣ ለሌሎች የምትተርፍ፣ የአፍሪካ ኩራት፣ የዓለም ፈርጥ የኾነች ኢትዮጵያን አያለኹ።

**ተስፋ አደርጋለኹ።**

በስደት እና በተለያዩ ምክንያቶች፣ አገር እና ቀዬአቸውን ጥለው በየሰው አገር የተበተኑ ሕዝቦቿ፣ በአገራቸው በፈቀዱበት ቦታ እና መንገድ፣ በፍቅር እና በመልካም ጉርብትና፣ በአገራቸው ዘና ብለው የሚኖሩበት ጊዜ ሩቅ አይኾንም።

**ተስፋ አደርጋለኹ።**

የኢትዮጵያ ወጣቶች፣ አውሮጳ መጥተው ለማግኘት ለሚያልሙት ያልተረጋገጠ ቀቢጸ ተስፋ፣ የሰሐራን በረሓ አቋርጠው፣ የሜዲትራኒያንን ባሕር ከፍለው የሚነጉዱበት ዘመን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ያከትማል። ፍሰቱ ወደ አውሮፓ መኾኑ ቀርቶ ወደ ኢትዮጵያ ይቀለበሳል፡፡ ልጆቻችን ወደ አውሮጳ ለጉብኝት እንጂ ለስደት የሚመጡበት ጊዜ ያበቃል።

**ተስፋ አደርጋለኹ።**

ዛሬ በመረጥነው በጎ ጎዳና እና በፈጸምነው ሠናይ ምግባር፣ ልጆቻችንም በክብር ስማችንን እንደሚያነሡ አምናለኹ።
ተስፋ አደርጋለኹ።
ይኼ ኹሉ ውጣ ውረድ አልፎ፣ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች በእግራችን እየተራመድን፣ የዛሬዋን ቀን በደስታ አስታውሰን፣ እንኳንም ለዚኽች ታላቅ አገር ደከምን ብለን ደስ የሚለን ቀን ይመጣል።

**ተስፋ አደርጋለኹ።**

ኹላችንም ወደ ልቡናችን ተመልሰን፣ የትላንቱን በዕርቅ እና በይቅርታ ዘግተን፣ የነገውን በተስፋ እና በፍቅር ሰንቀን፣ የምንኮራባትን ልዩ አገር እንገነባለን።

**ተስፋ አደርጋለኹ፤ አምናለኹም።**

**"ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!"**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ/ኢሽ ዳንከ ኢኔን**

# የፕሬዚዳንት ሙላቱ ተሾመ መሸኛ ንግግር

**ጥቅምት 24/2011 ዓ.ም.**

**የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሣህለ ወርቅ ዘውዴ፣**
**ክቡር ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ፣**
**ክቡር ፕሬዝዳንት አቶ ነጋሶ ጊዳዳ፣**
**ክቡር ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ፣**
**ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ፣**
**ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔ**
**ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ፍቅረ ሥላሴ ወግ ደረስ (እንደተጋበዙ ስለማውቅ) እንዲሁም እጅግ የተከበሩ ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ (በመካከላችን የተገኙ ይመስለኛል፤ እንኳን በሰላም ወደ እናት ሀገርዎ ተመለሱ።)**
**የተከበራችሁ የሃይማኖት አባቶች፣**
**የዛሬ ተፎካካሪዎች ዕድል ከቀናችሁ የነገ ፕሬዝዳንቶችና ጠቅላይ ሚኒስትሮች፤**

ኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ወይም ምእተ ዓመታት እንዲህ ሰብሰብ ብለን በጋራ ገበታ የምንቀርብበት፣ ማዕድ የምንቆርስበት ባህል በመበላሸቱ የቀድሞው ፕሬዘዳንት ወይንም ጠቅላይ ሚኒስትር ብሎ መጥራት እምብዛም ያልተለመደ ተግባር ነበር።

ከእንግዲህ በኋላ ይህ ልማድ ሥልጥኖ ባህላችን እንዲሆን፣ ማገልገል የሚያስከብር፣ ስንወጣም ደግሞ በምስጋና የምንሸኝ እንዲሆን፣ እንደ ባህል እንደ ልማድ እንዲጎለብት እንፈልጋለን፡፡ ተሿሚዎች ተመርጦ ማገልገልን፣ ተመስግኖ መሰናበትን፣ ከተሰናበቱም በኋላ በምክር ሰጭነት ማገልገልን የሚያጎለብት ባህልን በማስጀመር ለማጠናከር እንደዚህ ዓይነት ፕሮግራም ታስቦበት ነው ተደረገው፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ሐላፊዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች፣ ባሉበት ማድረጉ ለራስ ብቻ ሳይሆን ለትውልድ ከምናስተላልፈው አንዱ ቅርስ ሆኖ መቀጠል ስላለበት ጭምር ነው እያካሄድነው ያለነው፡፡

እስካሁን ሐላፊነት ስንወስድ በምርጫ መቀበል በራሱ መሠልጠን መሆኑን፣ በፈቃድ መልቀቅ ጥበብና ዕውቀት መሆኑን፣ በምስጋና መልቀቅ ጥቅሙ ላገለገለ መሆኑን ለማስተማር ጭምር ታስቦ ላለፉት ዓመታት በታማኝነትና በጨዋነት ሃገራቸውን ያገለገሉት ዶ/ር ተሾመ እና ባለቤታቸው ወ/ሮ መዓዛ በእውነተኛ ቋንቋ ለውጡን ወደ ፊት ለመውሰድ ሊለውጡ ሲሉ በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀው ቅድሚያ የምሰጠው ለሃገሬ ሰላም፣ ቅድሚያ የምሰጠው የለውጡን ትክክለኛ መስመር መጓዝ ነው፡፡ ብለው በማሰባቸው እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ሁሉ ይህ ክብር ይገባቸዋል በማለት የተዘጋጀ ራት ነው፡፡

የቀድሞውና ተተኪ፣ ፕሬዝዳንት በአንድ ገበታ የመቀመጥ ባህል እንደሚቀጥል ተስፋ አደርጋሁ፡፡ ይህ ባህል ስር ካልሰደደ እንደ ከዚህ ቀደሙ አደገኛ የሆነው ባህል ስር ሰዶ፣ ጥቁር ደም ፈጥሮ፣ ለትውልድ አጋዳይ፣ የሚያጠላላ ክፉ አሰተሳሰብና ፍላጎትን የሚያሠራጭ ስለሆነ፣ ያገለገለን አክብሮ፣ ምን አልባትም ቢበዛ ወርቅ ሸልሞ መሸኘት እንደሚሻል እንጂ፤ ከሃገር ማሰደድ ለኢትዮጵያውያን ድርብ ሃፍረትና ውርደት ስለሆነ፤ ስናገለግል በታማኝነት፣ ስንጨርስም በሕዝባችን መካከል መኖር እንድንችል፣ ይህንን ባህል መጀመሩ ለሁላችንም አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ማብሠር እፈልጋለሁ፡፡

የዚህ ለውጥ አንዱ ፍሬና ባህል የመፍትሔ አካል መሆን፣ ሁሉም በተቀመጠበት፣ በተሾመበት፣ በሚታገልበት መስክ በጨዋነት ሃገሩን ማገልገል፣ ይሄ እየበዛና እየተለመደ ሲሄድ ባህል እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህ የሚያስፈልገው ለሚወጡት ሳይሆን ላሉትም ጭምር ነው፡፡ አሁን ያሉት ይህንን ልምምድ ካዩ መልቀቅም፣ ሃገርን በጨዋነት ማገልገልም፣ ክብር መሆኑ ይገባቸዋል፡፡ በጉማሬ ጀርባ ላይ ለመቀመጥ ፈቃደኛ የሆነች ወፍ ውኃ ዋና እንደማያስጨንቃት፣ በክብር መሰናበት እንዳለ የሚያውቅ ጠቅላይ ሚኒስትርም ያለስጋት ጊዜው ሲደርስ አቅፎ ያስረክባል ማለት ነው፡፡

ክብርት ፕሬዝዳንት፤ ብዙዎቹ በዚህ ጊዜ ይች ሃገር ወዴት እየሄደች ነው? በማለት በጎን ከመተቸት፣ አቃቂር ከማውጣት፣ ጠጋ ብዬ የበኩሌን አስተዋጽዖ ማበርከት አለብኝ ብለው፣ ከተሻለ ደመወዝ፣ ከተመቻቸ ሥራ፣ የእናት ሃገር ጥሪና የዚህን ሃገር ሕዝብ ማገልገል ክብር መሆኑን ዐውቀው ስለመጡ፤ እናት ሃገር የምትኮራባት መሪ እንደሚሆኑ ያለኝን ሙሉ እምነት አገልጻለሁ፡፡ እንኳን ለዚህ ክብር አበቃዎት ለማለት እፈልጋለሁ፡፡ እርሰዎ እንደሚያውቁት ሃገርን በሴት መመሰል በኢትዮጵያ የተለመደ የአነጋገረ ዘዬ ነው፡፡

እርሰዎ የዚህ ሃገር ርእሰ ብሔር ነዎት፡፡ ይሁንና በቀጣይ የሥራ ዘመንዎ ያደርጋሉ ብዬ የምጠብቀው ፕሬዝዳንትነት እናትነትም ነው፡፡ ከእናት በላይ በጎዳና የወደቀን የሚያነሣ አይኖርምና፣ ከእናት በላይ ጧሪ ያጡ አዛውንቶችን ትክክለኛውን ክብር እንዲያገኙ ሊያደርግ የሚችል ሰው የለምና፣ የተራበን በማጉረስ፣ የታረዘን በማልበስ፣ ፍትሕ እንደሽቀጥ በገንዘብ እንዳይገዛ ለፍትሕ ቆርጦ በመቆም፣ አርአያ ፕሬዝዳንት እንደሚሆኑ ከሙሉ መተማመን ጭምር እንኳን ለዚህ ድርብ ሐላፊነት አበቃዎ እላለሁ፡፡

በዚህ አጋጣሚ በተመሳሳይ መልኩ የፍትሕ ሥርዓቱን ለማዘመን፣ ለማሻሻል፣ ያላቸውን የተሻለ ደመወዝና ሥራ ጥለው፣ የመንግሥትንና የሕዝብን ጥሪ አክብረው፣ ሪፎርሙን ተቋዋማዊ መሠረት ለማስያዝ

የመጡት፣ አዲስ የፍርድ ቤት ፕሬዘዳንት ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊን እንኳን ለዚህ ክብር አበቃዎት፤ እንኳን ተቀላቀሉ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

እንደ ክብርት ፕሬዝዳንትዋ ሁሉ ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ ሥራዎን ይጀምራሉ ብዬ የማስበው ማረሚያ ቤቶችን በመጎብኘት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰው ሊታረም ገብቶ ጨለማ ቤት የሚወረወርበት ዘመን በእርሰዎ የሥልጣን ዘመን ያበቃል ብሎ መንግሥት እና ሕዝብ ተስፋ እንዳለው ልገልጽለዎት እፈልጋለሁ፡፡ ማረሚያ ቤቶቻችን የምናስተምርበት እንጂ የምንገርፍበት እንዳይሆኑ፣ የምንለውጥበት እንጂ የምናሰቃይበት እንዳይሆኑ፣ የምንቀብርበትም ጭምር እንዳይሆኑ፣ በቀጥታ ሥራው እርስዎን የሚመለከት ባይሆንም፣ የመጀመሪያ ሥራዎ ቢያደርጉ መልካም ነው ብዬ የማስበው፤ ትክክለኛ ማረሚያ ቦታዎች ናቸው አይደሉም የሚለውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ምክንያቱም በእርስዎ ተቋም ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የተቋሙ ዓላማ ሰዎች ተምረው ከጥፋቸው እንዲመለሱ ማድረግ እንጂ እንዲጎሳቆሉና የቂም መወጣጫ እንዲሆኑ ማድረግ ስላልሆነ፤ ያ በትክክል እየተፈጸመ መሆኑን ማረጋገጥና ያ ካልሆነም የማያደርጉ አስፈፃሚ አካላትን ተገቢውን መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ አንዱ ተቀዳሚ ተግባር ይሆናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ማረሚያ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ የምርመራ ተቋማት ሰው የማይገረፍበት፣ ሰው የማይሰቃይበት፣ በሕግ አግባብ የሚጠየቅበትና የሚመለስበት መሆኑን፣ ፍትሕ የወል ሃብት መሆኗን በማረጋገጥ ረገድ በእናትነትም፣ በሙያዎም፣ በልምድዎም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጣለብዎ ተስፋ አንፃር ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ፣ ተጨማሪ ጥረትና ድካም የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ለኢትዮጵያ ፍትሕ በንግግር፣ ፍትሕ በተግባር የሚሆንበት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚያውቁት በሕግ የሚመካውን ያህል ፍትሕ ያላገኘ ሕዝብ ነውና፣ በሕግ መመካት ብቻ ሳይሆን ፍትሕን የማይገዛበት የወል ሃብት ሆኖ ለእያንዳንዱ ዜጋ በመሥራት እናትነትዎን እና የፍትሕ ጠባቂነትዎን እንደሚያረጋግጡ ያለኝን እምነት በዚሁ አጋጣሚ ልገልጽልዎ እፈልጋለሁ፡፡

በጥቅሉ አሁን ያለንበት ሪፎርም አዲስ የንጋት ጅማሮ እንጂ ማብቂያ ምዕራፍ ባለመሆኑ፤ ክብርት ፕሬዝዳንት፣ የተከበሩ የፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ሥራችሁን በምትጀምሩበት ወቅት አሁን በሰሞኑ በቴክስትም፣ በስልክም፣ በሚዲያም የእንኳን ደስ አላችሁ ጋጋታው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ያበቃል፡፡ የእንኳን ደስ አላችሁ የምስጋናው መልእክት ልክ እንደ ጠዋት ጀንበር ፀሐይ የማይሞቅ፣ ጨረሩ የማይጎረብጥ ዓይነት ነው፡፡ ወደ መሐል እየገባችሁ ስትሄዱ ሙቀቱ እየበረታ የሚያቀልጥ፣ ብርሃኑም እየበረታ መሄዱ አይቀርም፡፡ የተደበቁ፣ የተሰረቁ፣ የተሸሸጉ ነገሮች ካሉ ጎርጎር ማውጣት ስለሚያስፈልግ፣ ጎርጓሪ እጅ ደግሞ ሳያስበው ምላጭ ሊነካ ስለሚችል፣ በንግግር መቁሰል፣ በሥራ ሂደት እንቅፋት ሊኖር ይችላል፡፡ ከወዲሁ ማሰብና እናንተ በሕዝብ ተወካዮች ፊት ለገባችሁት ቃል ትውልድ ሥራችሁን የሚያወሳው በመሆኑ በመሐል በሚያጋጥሙ ውጣ ወርዶች ሳትሰናከሉ በታላቅ ጀግንነት ለአኅቶቻችሁ አርአያ፣ ለኢትዮጵያም ኩራት እንደምትሆኑ ያለኝን እምነት ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

**የወጣ ሁሉ በጊዜ ኡደት መውረዱ የማይቀር መሆኑን የዛሬው ፕሮግራም የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡**

አሁን በሹመት ያለን ሰዎች የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የቀድሞ መሆናችን አይቀርም፡፡ የቀድሞ መሆናችን ካልቀረ፤ በየዕለቱ የቀድሞ መሆናችንን እያሰብን ከሠራን ቀኑ ሲመጣ የማንሸማቀቅ፣ ቀኑ ሲመጣ ይህን ባደርግ ኖሮ በማለት የቁጭት ንግግር እንዳይኖር በሥልጣን ላይ ያላችሁ ሚኒስትሮች፣ በተለያየ ደረጃ ያላችሁ ሹማምንቶች፣ በታማኝነትና በፍቅር ብናገለግለው በዚያው ልክ መመለስ የሚችል ሕዝብ ስለምናገለግል፣ በማንኛውም ሁኔታ እጃችሁ በሌብነት ውስጥ ሳይቀላቀል፣ ሳትደክሙ፣ ሳትታክቱ ለተሰጣችሁ ድጋሚ ለማይገኝ ዕድል ሕዝባችሁን በማገልገል፣ የቀድሞው ስትሆኑ ሳታፍሩ የምትናገሩ፣ ሳታፍሩ የምትኖሩ እንድትሆኑ በዚሁ አጋጣሚ ከአደራ ጭምር ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ፡፡

የተቃዋሚ፣ የተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ ሐላፊዎች ዛሬ በዚህ ፕሮግራም የጋበዝኳችሁ በፖለቲካ ክርክሮች፣ በሐሳብ ውይይቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ ግጭት፣ ስድድብ፣ ብሽሽቅ ስለሰለቸው፣ በተቻለ መጠን በሠለጠነ መንገድ፣ ሐሳብ ብናመነጭ፣ በሠለጠነ መንገድ የምንከራከር፣ የምንነጋገር እንዲሆን፤ ከእንግዲህ በኋላ ስደት፣ እስር፣ ውርደት ለመሪዎቻችን እንዳይሆን፣ ይህን የሥልጣኔ ጅማሮ ባለቤት ሆናችሁ እንድትመሩትም ጭምር ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ሥራ አመራሮች በመካከላችን ካላችሁ እንኳን በሰላም መጣችሁ፤ እናንተ በሠለጠነ መንገድ ተወዳድራችሁ ስታሸንፉ የቀድሞ ሆነን ለመቀላቀል ዝግጁ መሆናችንን አገልጻለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ፡፡**

# የኢትዮጵያ የፖለቲካ ለውጥ ጉባኤ ንግግር

**ኅዳር 15/2011 ዓ.ም.**

## የተከበራችኹ የዚኽ ታላቅ ጉባኤ ተሳታፊዎች፤

ዛሬ እዚኽ የቆምኹት፣ ብዙዎች ዋጋ በከፈሉለት፣ ጥቂቶች ለማየት ባልታደሉት፣ ለዘመናት ስንናፍቀው እና ስንታገልለት በቆየነው ጉልሕ የታሪክ ምዕራፍ ፊት ነው። የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው ግለሰቦች እና ቡድኖች፣ እርስ በርስ ለመጠፋፋት የሚሻኮቱበት ዘመን አልፎ፣ ለአንድ አገር እንደሚታገሉ ልዩ ልዩ አካላት ኾነው የሚታዩበት አዲስ ዘመን መጥባቱን ለማብሠር ነው የቆምኹት። የአገራችን ታሪክ፥ እጅግ በሚያስደስቱ፣ በሚያስቀኑና ምንጊዜም ስንተርካቸው በኩራት በምንናገርላቸው ዕሴቶች የተሞላ ነው። በተቃራኒው ደግሞ፣ የፖለቲካ ባህላችን እጅግ ኋላ ቀር ብቻ ሳይኾን፣ ከአገሪቱ ታሪክ እና ክብር ጋራ አብሮ በማይሔድ በሤራ ፖለቲካ እና በመጠላለፍ አሻጥር የተሞላ ነው።

ይህን ጉባኤ ስናካሒድ፣ አገራችን በፖለቲካ መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆማለች። በዚኽ ሰዓት ትልቅ ጥያቄ የሚኾነው፣ አሁን የገጠመንን ወርቃማ ዕድል እንጠቀመው ወይስ ከዚኽ በፊት እንዳደረግነው የዛሬውንም ዕድል በከንቱ በማባከን ጉዟችንን ወደ ኋላ እንመልሰው? የሚል ነው። ባለንበት ቆመን ስንሻኮት

ወደ ማንገናኝበት ጽንፍ እንሒድ? ወይስ ከስሕተቶቻችን ተምረን ለዚኽች አገር እና ለሕዝቦቿ የሚጠቅም የፖለቲካ ማሻሻያ እናካሒድ? የሚሉት ምርጫዎች ከፊታችን ቀርበውልናል። የዚኽች አገር ዕጣ ፈንታ፣ ለእነዚኽ ጥያቄዎች በምንሰጠው ምላሽ ላይ ይወሰናል።

በትክክልም፣ ልንከተለው የሚገባን የለውጥ ሞዴል፣ በቀውስም ቢኾን የሚመጣውን አብዮታዊ (ነውጠኛ ለውጥ) ይኹን ወይስ ቀውስን የቀነሰ መሠረታዊ ለውጥ (ፋንዳሜንታል ሪፎርም) አቅጣጫን ይከተል? የሚለው ጥያቄ፣ የኹላችንንም የጋራ መግባባት የሚሻ ታላቅ ጉዳይ ነው። ማንም ቢኾን፣ ወደፊት የሚያራምደውንና የሚሻለውን የለውጥ ሞዴል እንጂ፣ ራሱን በራሱ በልቶ የሚጨርሰውን፣ የገነባውን የሚያፈርሰውን፣ ጉዞውን ወደ ባዶ መነሻ የሚመልሰውን የለውጥ ሞዴል ወዶ እና ፈቅዶ ይመርጣል ተብሎ አይታሰብም።

በፈረንሳይ፣ በሩሲያ፣ በምሥራቅ እስያ እና ላቲን አሜሪካ አገራት ተግባራዊ የተደረጉ አብዮታዊ የለውጥ ጉዞዎች፣ አገራቱን ካጎናጸፏቸው ተደማሪ የድል ውጤት ይልቅ፣ ለአያሌ ሕይወት መጥፋት እና ንብረት መውደም፣ ለታሪክ ሽረት እና ለሞራል ውድቀት ምክንያት መኾናቸው በማስረጃ ተደግፎ የሚገኝ ነው። በአንጻሩ በአሜሪካ፣ በእንግሊዝ፣ በጀርመንና ጃፓን የተካሔዱ መሠረታዊ የማሻሻያ ለውጦች፣ አገራቱ ዛሬ ከሚገኙበት የሙብት እና የብልጽግና ምኩራብ ደረጃ ለመድረሳቸው አንድ ምክንያት መኾናቸው፣ ከዓለም ታሪክ በተጨባጭ የምናረጋግጠው እውነት ነው።

የፖለቲካ ታሪካችን ጉዞ በአመዛኙ፣ ሤራን፣ ጽንፈኝነትን፣ኢ-ዴሞክራሲያዊነትንና ጥላቻን የተሞላ ኾኖ ቆይቷል። አንዱ አንዱን አጥፍቶ ታሪኩን በሌላው መቃብር ላይ በመመሥረት ላይ አተኩሮ ሲሠራ ይህም እንደ ጀብድ እንጂ እንደ ጥፋት ኾኖ አይታሰብም። ኹል ጊዜም አብዮትን እንጂ መሠረታዊ ማሻሻያንና ሪፎርምን አንፈልግም። ምንም እንኳን፣ አድካሚው እና ከባዱ ጉዞ፣ መሠረታዊ ለውጥን በውጤታማነት መተግበር ቢኾንም፣ በእኛ ግን እንደ ስንፍና እና ሽንፈት ተደርጎም ይታሰባል።

ለአንድ አገር፣ የተለያዩ ሐሳቦች እንደ ጸጋዎች መታየታቸው ቀርቶ፣ እንደ ጠላት መሣሪያዎች ይታዩ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ‹ፖለቲካ› የሚለውን ቃል ከሰማበት ጊዜ ጀምሮ፣ ምኅዳሩን ከብዶ በተጫነው መገዳደል፣ መተላለቅ፣ ማሳደድ እና አንዱ አንዱን ማሰር፣ እንደ ዕጣ ፈንታ አብሮት በመዘገበ ቃላቱ ተጽፎ ሲከተለው ኖሯል።

በዚህም የተነሣ፣ “ፖለቲካ እና ኤሌክትሪክን በሩቁ” እስከ ማለት ተደርሷል። ዛሬ ያለንበት ጊዜ እና ኹኔታ፣ የዘመናት ችግሮቻችንን መልሰን የምንደግምበት አይደለም። ኢትዮጵያችን ዕድሎቿን በማበላሸት በቂ ልምድ አላት። ከዚኽ በኋላ ለኢትዮጵያ ዕድልን መጠቀም እንጂ ማበላሸት ሰበር ዜና አይኾንም። ኋላ ቀርነትን፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊነትንና ኢ-ፍትሐዊነትን የሚታገሥ ትከሻ፣ ዛሬ ማናችንም የለንም። ሕዝቡም፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የነገረን ይኼንኑ ነው። እኛም ይህን በመገንዘብ ባለፉት ወራት፣ የአገራችንን የፖለቲካ ባህል፣ የፖለቲካ ሥርዓትንና የፖለቲካ ተቋማትን በመሠረታዊነት ለማሻሻል እና ወደሚፈለገው ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችሉ ተከታታይ ሥራዎችን ስንሠራ ቆይተናል።

በተለይም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጠናከር የሚያስፈልጉን ተቋማት፥ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ተኣማኒ እንዲኾኑ ለማስቻል፣ የሚጠበቅብንን ኹሉ ለማድረግ በመታገል ላይ እንገኛለን። መታወቅ የሚኖርበት ትልቁ ጉዳይ፣ ዛሬ፣ እንኳንስ በአንዲት አገር፣ በአንድ ቤተሰብ እንኳን፣ አንድ ዓይነት ሐሳብ ያላቸው አባላት አይገኙም። ዘመናችን ልዩ ልዩ ሐሳቦችን በጸጋ ማስተናገድንና በማቻቻል መቀበልን የግድ የሚጠይቅበት ወቅት ነው። በምናምንበት በየራሳችን እየሠራን፣ ነገር ግን ለአንዲት  አገር በጋራ መሥራት አዲሱ ባህላችን መኾን አለበት። ያለን አንድ አገር ነው፤ የምንታገለው ለአንድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። የተለያየ ሐሳብ ብቻ ሳይኾን፣ የጋራ ሐሳብም አለን። የሚያግባባን ሐሳብ ብቻ ሳይኾን፣ የማያግባባንም ሐሳብ አለን። የምንከተለው የፖለቲካ ባህል፣ ሥልጡን መኾን አለበት የምንለውም እነዚኽን ኹለቱን አቻችሎና አጣጥሞ ይዞ መሔድ ስለሚያስፈልገው ነው።

መንገዱን፥ በይቅርታ፣ በመደመር እና በዕርቅ እንጀምረው። በተለያዩ የፖለቲካ መሥመሮች ኾነን ስንታገል ባለፉት ዘመናት የፈጠርናቸው ቁርሾዎች ይኖራሉ። ይህ ጉባኤ፣ እነዚኽን ቁርሾዎች የምንተዉበት መኾን አለበት። ፈተናዎቻችንን ተደምረን እንፍታቸውና ወደ ሥልጣኔ እንሻገር። ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ዕርቅን አርአያ ኾነን እንድናሳይ፣ መጀመሪያ፣ የፖለቲካ ልሂቃን ዕርቅን እንልመደው። ዕርቅ ስንል፣ የፖለቲካ አመለካከቶቻችንን እናስታርቅ ማለታችን አይደለም። እኛ የፖለቲካ ልሂቃኑ እንታረቅ ማለታችን ነው። የሐሳብ ልዩነትን በሐሳብ ልዩነት እንታገል እንጂ በጠላትነት አንተያይ ማለታችን ነው። ሸርንና ሤራን፣ ቁርሾንና ደመኝነትን እንተው ማለታችን ነው። የአንዲት አገር ሰዎች፣ ለአንዲት አገርም የምንሠራ ዜጎች መኾናችንን አምነን እንሥራ፤ ማለታችን ነው። በክርክር፣ በውይይት፣ በጤናማ ፉክክር እና የዴሞክራሲን ሒደት በመቀበል የሠለጠነ ፖለቲካን እናራምድ ማለታችን ነው። ይህን ማድረግ ከቻልን፣ ተያይዘን ወደ አዲሲቱ ኢትዮጵያ እንሻገራለን። አለበለዚያ ግን ተያይዘን መክሰራችን አይቀሬ ነው።

አብዮታዊ(ነውጠኛ) የለውጥ ሞዴል ለኢትዮጵያችን አይበጃትም፤ ለማለት መነሻው ብዙ ነው። ኢትዮጵያ ተስፋ ያነገበች እንጂ ተስፋ አልባ አገር አይደለችም። በጥድፊያ እና በሩጫ ተሞልተን፣ ከዚህ በፊት ከሞከርናቸው አብዮታዊ የለውጥ ሞዴሎች፣ እንደ አገር ያጨድነውን መከራ እና ግፍ፣ የታቀፍነውን እልቂት እና ውድመት ዛሬም በመድገም በታሪክ ፊት በትውልድ ስንወቀስ የምንኖር መኾን አይገባንም። ዴሞክራሲ ውጤት ብቻ ሳይኾን ሒደትም ነው። እንዲያውም ከውጤቱ በላይ ሒደቱ ወሳኝ ነው። ዴሞክራሲያዊ ምርጫም፣ የማሸነፍ እና የመሸነፍ ጉዳይ አይደለም። ዴሞክራሲያዊ ምርጫ፥ ነጻ፣ ገለልተኛ፣ ተኣማኒ እና ሕጋዊ የኾነ ምርጫ ማካሔድ ነው። የምንፈልገው ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ ነው። ነጻ፣ ገለልተኛ፣ ተኣማኒ እና ሕጋዊ የኾነ ምርጫ ማካሔድ ከቻልን ማንም አሸነፈ ማን፣ የምታሸንፈው ኢትዮጵያ ናት፡፡ ምክንያቱም፣ በአገራችን በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብት ለማድረግ ችለናልና።

ይህን ባህል በመገንባት፣ ስሙ፣ ታሪኩ፣ በወርቅ ቀለም የሚጻፈው የአሸናፊው እና የተሸናፊውም ነው። እንዲያውም ከምርጫው አሸናፊ በላይ ተሸናፊነቱን በጸጋ የተቀበለው፣ የበለጠ ስሙ በክብር ሊነሣ የግድ ይላል። በታሪካችን ማሸነፍን የሚቀበል አሸናፊ አላጣንም። ዋነኛው ችግራችን፣ መሸነፍን በጸጋ የሚቀበል ቀና ተሸናፊ አለማግኘታችን ነው።

በራቀው ዘመን፣ በአውሮፓ፣ በእስያ እና በላቲን አሜሪካ ሕዝቦች ብቻ ሳይኾን፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት፣ በቅርባችን ባሉት በመካከለኛው ምሥራቅ እና በዓረብ አገሮችም ጭምር፣ አብዮታዊ(ነውጠኛ) የለውጥ ሞዴል ተግባራዊ ለማድረግ መሞከሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። መማር የምንሻ ከኾነ፣ በርግጥ ዛሬ፣ ሶሪያ ያለችው በየትኛው የፖለቲካ አዘቅት እና ማጥ ውስጥ እንደ ኾነ እንመርምር። የሺሕ ዘመን ከተማ ደማስቆ፣ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ዓመድ ኾናለች። የመን፣ ሊቢያ ወይስ ሊባኖስ? የትኞቹ ናቸው አብዮትን ሞክረው ከፍታን የተቀዳጁት? አንዳቸውም፣ ቀድሞ እንደ አገር ከነበሩበት ደረጃ፣ ዝቅታ እንጂ ያረጋገጡት ግሥጋሴ የለም። ከለውጥ ጉዟቸው ጋራ ተያይዞ በተጫናቸው የመከራ ቀንበር ሳቢያ፣ ትከሻቸው ጎብጧል እንጂ ቀና አላለም። እኛም እነርሱን ተመልክተን፣ ከሕዝባቸው ጋራ እንደ ሕዝብ ልባችን ተሰብሯል። ያን ውጤት አልባ እና የጥፋት መንገድ፣ ኢትዮጵያውያን የሚመርጡትም ኾነ የሚሹት የለውጥ ሞዴል ሊኾን አይገባም።

አገራችንን፣ በጥልቅ ውቅያኖስ ላይ ወደ መዳረሻ ግቧ በመቅዘፍ ላይ እንዳለች መርከብ መስለን ልንመለከታት እንችላለን። የመርከባችን ጉዞ እንዲፈጥን፣ በውስጡ የተሳፈረውም ሕዝባችን፣ ካሰበው የሰላም፣ ዴሞክራሲ እና የብልጽግና ዳርቻ እንዲያደርሰን በኢንጅኑ ላይ የሚስተዋሉ ብልሽቶችንና ጉድለቶችን ማስተካከል እና መጠገን እንደሚገባን እናውቃለን። ያን ጥገና እና ማስተካከያ ግን የምናካሒደው፣ መርከቧን ውቅያኖስ መካከል አቁመን፣ ኢንጅኑን አጥፍተንና ከጉዞ ውጭ በመኾን አይደለም። የዚኽ ትውልድ አባላት፥ ሞተሩ ሳይጠፋ፣ ኢንጅኑ ከእሽክርክሪት ሳይገታ እዚያው በዚያው ጉዟችን ሳይቆም ጥገና ማካሔድ ይኖርብናል።

“ሮም በአንድ ቀን አልተሠራችም” እንደሚባለው፣ በመሠረታዊ የለውጥ ርምጃ የምንፈልገው፣ ኹሉንም ጉዳይ በአንድ ጀምበር አከናውነን ላንጨርሰው እንችላለን። ግን እንጀምረው። እንዲያድግ፣ እንዲዳብር፣ ትውልድ እንዲሻገር አድርገን እንጀምረው። በተስተካከለ እና በቀና ጎዳና ላይ እንጀምረው፤ እንማርበታለን። እኛ እንኳ ቢያቅተን፣ የእኛ ልጆች እና የልጅ ልጆች እጅግ ወደ ላቀ ደረጃ ያደርሱታል። እንከራከር ብቻ ሳይኾን እንማማር፤ እንፎካከር ብቻ ሳይኾን እንተባበር፤ እንተቻች ብቻ ሳይኾን እናመቻምች። ያን ነው ኢትዮጵያ የምትፈልገው። ወደ ነገ የሚያሻግረን ሥልጡን የፖለቲካ ባህል ግንባታ እና መሠረታዊ የለውጥ ሞዴል ነው።

ተስፋ አደርጋለኹ፤ ይህ ጅምራችን የአገራችን ትንሣኤ አንዱ ማብሠሪያ እንደሚኾን፤ ወደ ኋላ ላንመለስ ቃል የምንገባበት እንደሚኾን አልጠራጠርም።

**“ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት እና ኅብረት ታፍራ ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!”**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ንግግር

**ኅዳር 28/2011 ዓ.ም.**

የኢትዮጵያ ተስፋዋ በእናንተ እጅ ላይ ነው፡፡ ይህን በዓል፣ ነገን እያሰባችኹ እንደምታከብሩት ተስፋ አደርጋለኹ፡፡ እኔም ዛሬ ላይ ኾኜ ለእናንተ ይህን መልእክት ሳስተላልፍ፣ ምን ዓይነት ኢትዮጵያ ነው ለእነዚህ ልጆቻችን ማውረስ ያለብን? ብዬ አስባለኹ፡፡ አሁን የምታዩዋት ኢትዮጵያ፣ በትክክለኛው መልኳ እየታየቻችኹ አይደለም፡፡ የግጭት ዜናዎች፣ መፈናቀሎች፣ የሌብነት እና የዝርፊያ ዜናዎች፣ መከፋፈሎች እና መለያየቶች እየታዩዋችኹ እንደ ኾነ ይሰማኛል፡፡

ግድየላችኹም፤ ፈጽሞ ይህን ለእናንተ አናወርሳችኹም፡፡ የእናንተ ኢትዮጵያ፣ ከዚኽ በብዙ ዕጥፍ የተሻለች እንደምትኾን እመኑ፡፡ አሁን የምታዩት፣ አገራችን ኢትዮጵያ ከችግሮቿ ኹሉ ተላቅቃ ለእናንተ የተሻለች ለመኾን የምታደርገውን ትግል ነው፡፡ አሁን የምታዩት፣ ኢትዮጵያ የተባለችውን የጋራ ቤታችንን፣ ለኹላችንም የምትመች፣ የምትበቃና ኹላችንንም የምታስተናግድ አድርገን በተሻለ ኹኔታ እንደ ገና ስትታደስ ነው፡፡ እዚኽም እዚያም፣ በእድሳቱ ምክንያት የተፈጠሩትን ነገሮች ታያላችኹ፡፡ መቼም በየሠፈሩ ቤት ሲታደስ ምን ያህል እንደምትቸገሩ ታውቃላችኹ፤ ዕቃው ይዝረከረካል፤ ግድግዳው እና ጣራው ይወላለቃል፤ በሩ ይነቀላል፤ ወለሉ አስቸጋሪ ይኾናል፡፡

ይህ ኹሉ ግን ጊዜያዊ ነው፡፡ ሠሪ ሥራውን በሚገባ ሲጨርስ፥ እጅግ የተሻለ፣ ያማረ፣ ለኑሮ የተመቸ እና ለቤተሰቡ ሁሉ የሚስማማ ቤት ይኾናል፡፡ ያ ሁሉ ድብልቅልቅ፣ ቤቱን ለማሣመር መኾኑን ስለምታውቁ እናንተም ትታገሣላችኹ፡፡ ኢትዮጵያ አገራችኹም እንዲህ ነው እየኾነች ያለችው፡፡ በኹሉም ነገሯ የተሻለች እንድትኾን ልጆቿ ጉልበታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ሀብታቸው፤ ከዚያም አልፈው ሕይወታቸውን ሠዉተው እየሠሯት ነው፡፡

እንደምታውቁት፣ በዚኽች ጥንታዊት አገራችን እንኮራለን፡፡ በታሪኳ፣ ለነጻነት በአደረገችው ተጋድሎ፣ የብዙ ብሔሮች አገር በመኾኗ፣ ዓለምን ባስደነቁት ቅርሶቿ፣ ልዩ ልዩ እምነቶች በጋራ የሚኖሩባት በመኾኗ እንኮራለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ዴሞክራሲን ለመገንባት፣ ፍትሕን ለማስፈንና ድህነትን ለማስወገድ በሚገባን መጠን አልታገልንም፡፡ በዚኽ ረገድም፣ መልካም ታሪክ አልገነባንም፡፡ የገነባናቸው መልካም ታሪኮች በኩራት እንደምንከባከባቸው ኹሉ፣ የደከምንባቸውን ነገሮችም ለማረም መሥራት ይኖርብናል፡፡

የእናንተ ሓላፊነት ትልቅ ነው፤ የምትረከቧት አገር ታላቅ ናትና፡፡ በቋንቋ፣ በባህል እና በወግ ከእናንተ የሚለዩ፣ ነገር ግን ለኢትዮጵያ ውድ ልጆቿ የኾኑ በሰሜንና በደቡብ፣ በምዕራብ እና በምሥራቅ፣ ብዙ ወንድሞች እና እኅቶች አሏችኹ፡፡ ነገ የምትማሩት፣ የምትሠሩት እና የምትኖሩት ከእነርሱ ጋራ ነው፡፡ በቋንቋ እና በባህል፣ ከእናንተ ከተለየው ከሌላው ወገናችኹ ጋራ ስትገናኙ፣ ብዙ ታሪኮች፣ ጥበቦች፣ ወጎች፣ ተረቶች ትማራላችኹ፡፡ ቋንቋዎቹን ማጥናትማ ከቻላችኹ በብዙ ታተርፉላችኹ፡፡ አገራችኹ ሰፊ ናት፤ ብዙ ሀብትም አላት፤ አብራችኹ ኾናችኊ እንድታለሚትና እንድታሠለጥኗት እየጠበቀቻችኹ ነው፡፡

ክፋትን፣ ጥላቻንና ቂምን የሚነግሯችኹን አትቀበሏቸው፡፡ የልጆች ኅሊና ብሩህ ነውና ፍቅር፣ አንድነት እና ደግነት የበለጠ ይስማማዋል፡፡ ጥላቻ እና ቂም ራስን የሚያጠፋ መርዝ ነው፡፡ ለነገዋ ኢትዮጵያ የሚጠቅማት ነገር የለም፡፡ ፍቅር እና አንድነት ግን የሚያስተሳስር ገመድ ነው፡፡ የእናንተ ልቡና ፍቅርን፣ ይቅርታንና አንድነትን ነው ማብቀል ያለበት፡፡ የየአካባቢያችን ተረቶች የሚነግሩን ይህን ነው፡፡ ወላጆቻችኹን፣ በሠፈር ያሉ አዛውንትን ጠይቋቸው፡፡ በሌላ የኢትዮጵያ ቋንቋ የሚናገሩ ወገኖቻችኹን ስታገኙም ጠይቋቸው፤ ተረቶቻችንን ይንገሯችሁ፤

ወጎቻችንን ያውቋችኋ፤ በየባህላችን ያለውን የመከባበር እና የመተሳሰብ ነገር ይተርኩላችኋ፤ ትደነቃላችሁ፡፡ ተመሳሳይ የሆነ የፍቅር፣ የአንድነት እና የይቅርታ መልእክት ከኹሉም ታገኛላችኹ፡፡

ኢትዮጵያ በተስፋ እየጠበቀቻችኹ ነው፡፡ ስለ አገራችኹ ዕወቁ፤ ባህሎቻችኹን ዕወቁ፤ ታሪኮቻችኹን አጥኑ፤ ስታድጉ አገራችኹን ከዓለም ታላላቆች ተርታ ለማሰለፍ ተመኙ፡፡ የነገዎቹ የፓርላማ አባላት፣ ፕሬዝዳንቶች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች፣ አምባሳደሮች፣ መምህራን፣ ሐኪሞች፣ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች፣ መሐንዲሶች፣ አብራሪዎች፣ መርከበኞች፣ ባለ ብዙ ሞያ ሞያተኞች እናንተ ናችኹ፡፡ እናንተ ካላደጋችኹላት፣ ኢትዮጵያ ሰው ከዬት ታመጣለች? ለምን እንደምትማሩ ሰዎች ሲጠይቋችኹ፣ “ለኢትዮጵያ ለአገራችን ሰው ለመኾን ነው” በሏቸው፡፡

በርቱና ተማሩ፤ ተማሩና ድረሱላት፤ እርስ በርስ ተፋቅራችኹና ተባብራችኹ፣ ልዩነቶቻችኹንም ጌጦቻችኹ አድርጋችኹ የነገዋን ኢትዮጵያ ገንቡ፡፡ የኢትዮጵያ ተስፋዋ በእናንተ እጅ ላይ ነው፡፡

# የጅማ ዩኒቨርስቲ ምርቃት ንግግር

**ኅዳር 29/2011 ዓ.ም.**

በዛሬዋ ዕለት፣ ከጅማ ዩኒቨርስቲ የምትመረቁ ሐኪሞች፣ የረዥሙ የትምህርት ጉዞ ዋነኛው ምዕራፍ ላይ በመድረሳችኹ፣ እንኳን ደስ አላችኹ፤

በቤተሰባዊ ፍቅር ወልዳችኹ፣ አሳድጋችኹ፣ አስተምራችኹ እነዚኽን የመሰሉ ልጆች ለአገር በማበርከታችኹ፣ ወላጆች፥ እንኳን ደስ አላችኹ፤

አስተምራችኹ፣ አሠልጥናችኹ እና ቀርፃችሁ እነዚኽን የመሰሉ ሐኪሞች በማድረሳችኹ፣ መምህራን፥ እንኳን ደስ አላችሁ፤

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሕክምና ሞያ ያለውን ፍቅር እና ክብር፣ በብዙ መልኩ ሲገልጽ መኖሩን በተጨባጭ ከምንረዳባቸው ኹነቶች መካከል፣ ልጆቻችንን፥ "ምን መኾን ትፈልጋላችኹ?" ብለን ስንጠይቃቸው ከሚጠቅሷቸው ሞያዎች መካከል "ሐኪም መኾን" ከግንባር ቀደሞቹ አንዱ መኾኑ ነው፡፡ በጥንቱ አገራዊ ትርክት ውስጥ፣ ሐኪሞች ሰልፋቸው፣ ከጠቢባን ተርታ ነበር፤ ይባላል፡፡ በርግጥ "ሐኪም" የሚለውን ቃል እኛ ከዐረብኛ ቋንቋ የቀዳነው ሲኾን፣ ዐረብኛው ደግሞ ከፋርስ ቋንቋ የወሰደው መኾኑን የታሪክ መዛግብት ይጠቁማሉ፡፡ "ሐኪም" የሚለው ቃል በጥንታዊ ትርጓሜ ሲፈታ፣ በአንድ በኩል፥ ጠቢብ ማለት ሲኾን፤ በሌላ በኩል ደግሞ፥ ዳኛ፣ መሪ፣ አስተዳዳሪ የሚሉ ፍቺዎችን በውስጡ አካትቶ ይይዛል፡፡ እኛ እንደ አገር፣ ሐኪሞቻችን፣ ኹለቱንም የፍቺ መልኮች፣ ማለትም፣ ጠቢብም መሪም እንዲይዙ እንፈልጋለን፡፡

በጤናው ዘርፍ፣ እንደ አገር የጣልናቸው ግቦች እንዲሳኩ፣ እናንት የሕክምና ባለሞያዎች፣ ጥበባችኹን ለሕዝባችኹ ያለስስት ትለግሱ ዘንድ ይጠበቃል፡፡ እንደ መሪነታችኹም፣ ሕዝቡን ከበሽታ ወደ ጤና፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ በአጭር ከመቀጨት ወደ ረዥም ዕድሜ መርታችኹ ታሻግሩት ዘንድ ከፍተኛ ሓላፊነት አለባችኹ፡፡ ስለ ግል እና አካባቢ ጤና፣ ስለ ጤነኛ አኗኗር እና ስለ ጤናማ ማኅበረሰብ ግንባታ በአገር ደረጃ ያለውን አመለካከት ወደሚፈለገው ደረጃ ለማሸጋገር በሚደረገው ጥረት ውስጥ፣ የፋና ወጊነቱ ሚና የእናንተ ድርሻ መኾኑን መገንዘብ ይኖርባችኋል፡፡ በመኾኑም፣ ከአዘቦታዊ (ዕለት ተዕለት አካሚነት) አዙሪት ውስጥ ሰጥሞ ከመጥፋት ይልቅ፣ የላቀውን አገራዊ ራእይ በመጋራት እና አዙሪቱንም በመሻገር፣ ለአጠቃላዩ አገራዊ ጤና ዘርፍ የሚያስብ፣የሚሠራና የሚደክም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አባል የኾነ ማኅበረሰብ እንዲኖረን የበኩላችሁን አስተዋፅኦ ታደርጋላችኹ የሚል ተስፋ አለኝ፤

## ጥሪ የተደረገላችኹ እንግዶች፣
## የተመራቂዎች ቤተሰቦች፣
## ውድ ተመራቂዎች፤

እንደ ዛሬው፣ ዓለም ሠለጠንኹ ብሎ ከመደምደሙ በፊት፣ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ፣ “የሐኪሞች ሦስቱ እሴቶች” ተብለው የሚታወቁ ዋና ጉዳዮች ነበሩ፤ ይባላል፡፡ ሕሙማንን መከባከብ፣ ዕውቀቱን ለሌሎች ማስተማር እና ለእያንዳንዱ በሽታ መፍትሔ እስኪገኝ ድረስ መመራመር ናቸው፡፡ እኒኽ ሦስቱ፣ አንድ ሐኪም፣ ሙሉ ሐኪም ለመባል ሊጎናጸፋቸው የሚገቡ ዕሴቶች ነበሩ፡፡ በዚኽ ደረጃ የሚፈረጅ ሐኪም፣ ሕሙማኑን፥ ደንበኞቹ ወይም ገበያው አድርጎ አያስብም፡፡ ኹሉም ሕሙማን፣ ሐኪማቸውን አምነው ሕይወታቸውን በጸጋ የሚያስረክቡ ወገኖቹ ናቸው፡፡ በማናቸውም የሕክምና ተግባሩ ወቅት፣ እየተከባከባቸው መኾኑን፣ ለፈውሳቸውም እየሠራ መኾኑን በቃልም፣ በተግባርም ማረጋገጥ አለበት፡፡ “ሐኪም ሰውነትን ከማከሙ በፊት ልብን ማከም አለበት፤” የሚባለውም በዚኹ የተነሣ ነው፡፡ በክብካቤ የሚያክሙትንና የሚያድኑትን ሐኪሞች፣ ኅብረተሰባችን የመለየት እና አመኔታውን የመስጠት

ችግር ኖሮበት አያውቅም፡፡ ይልቁንም፣ “እጃቸው መድኃኒት ነው” እስከ ማለት የሚደርስ ዕውቅናን መስጠት የሚያውቅ ማኅበረሰብ ነው ያለን፡፡

በዛሬዋ ዓለማችንም ኾነ በአገር ደረጃ፣ የመመዘኛ ቅቡልነትን አግኝተው በጤናው ዘርፍ የአገልግሎት ስኬት መለኪያ ተደርገው የተቀመጡት ሦስቱ ነጥቦችም ቢኾኑ፣ ከዚያው ከጥንቱ የሐኪሞች ዕሴቶች የተቀዱ እና ጥብቅ ትስስርም ያላቸው እንጂ እንግዳ፣ ባዕድ ጉዳዮች አይደሉም፡፡ ኹላችኁም እንደምታውቁት አዲሱ መመዘኛ፣ ከሒደት ይልቅ ለውጤት እና ስኬት የላቀ ዋጋን የሚሰጥ ነው፡፡ በመኾኑም፣ ሕሙማን ዜጎች በሕክምና ተቋማት ውስጥ የሕክምና አገልግሎት አግኝተው በአግባቡ ለመዳን ያላቸው ተስፋ፣ በሕክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማቱ ውስጥ ታክሜ እድናለኹ፤ ሲል ተገልጋዩ ሕዝብ የገነባው የእምነት ደረጃ፣ በሕክምና ተቋማቱ ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ቅልጣፌ እና ከብክነት የጸዳ መኾን ዋነኛዎቹ መመዘኛዎች ናቸው፡፡

“አንጀቴ ተቆርጦ ከሆዴ ከወጣ፣ እንግዲህ ሐኪሙ ምን ሊቀጥል መጣ” የሚለው ጥንታዊው የሕዝባችን ሥነ ቃልም ቢኾን፣ ሕዝባችን ሐኪሞቹን በዋናነት የሚፈልጋቸው፣ ‘አንጀቱ ከመቆረጡ በፊት’ ለመዳን፣ ለመፈወስ መኾኑን ያስረዳናል፡፡ ያ ማለት ደግሞ፣ በመከላከሉ ላይ ከታመነ፣ እስከ ፈውስ የሚያሻግረው ግልጋሎት ላይ የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠሩለት የሚፈልግ መኾኑን ጠቋሚ ነው፡፡ በዚኽ ረገድ፣ በሕክምና ማስተማሪያ ዩኒቨርሲቲዎች እና የሕክምና አገልግሎት በሚሰጥባቸው ተቋሞቻችን ውስጥ ያላችኹ የሕክምና ባለሞያዎቻችን፣ እርስ በርስ ከመማማር ጀምሮ፣ በጋራ በመሥራት፣ በቅንጅት በመመራመር፣ ጥንታዊ ዕውቀቶቻችንን በዘመናዊ ሳይንሳዊ አጠናን በመፈተሽ እና በጥንቱ ዕውቀት እና በዘመናዊው ሳይንስ መካከል ድልድዮች በመኾን ለላቀ የአገልግሎት ደረጃ እና ለሞያ ሥነ ምግባር መረጋገጥ አበክራችኹ መሥራት ይጠበቅባችኋል፡፡

በአገር ደረጃ፣ የጤና ዘርፍ ሽፋንንና የአገልግሎት ጥራትን የማረጋገጥ ርምጃ፣ ከአመራር ቁርጠኝነት ጋራ እንጂ፣ ኹል ጊዜም ከሀብት እና በጀት ጋራ የሚያያዝ እንዳልኾነ ከኩባ መማር ይኖርብናል፡፡ እንደ ሌላ ሌላውን ትተን፣ አንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም፣ በጤና ዘርፍ አገልግሎታችን ውስጥ የሚፈጠረውን ብክነት፣

ምርምርን መሠረት አድርገን ማስቀረት ብንችል፤ ለምሳሌ፥ በሆስፒታሎቻችን ውስጥ አማካይ የኦፐሬሽን ቆይታ ጊዜን፣ አላስፈላጊ ምርመራንና የግብዓት አጠቃቀምን ብቻ በግማሽ ማሻሻል ብንችል፣ አሁን ካለን የጤና ተቋም፣ መሣሪያ፣ ባለሞያ እና በጀትን በዕጥፍ ሳንጨምር የአገልግሎት አድማሳችንን ግን በዕጥፍ ማሳደግ እንችላለን፡፡ በሌላም በኩል፣ ጤናን በሕክምና ብቻ ማረጋገጥ አይቻልምና ሌሎች ባለሞያዎችንና ኅብረተሰቡንም በጤና ትምህርት፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ እና መከላከል ላይ በሚያተኩር የጤና አጠባበቅ ሥራ ጭምር በማገዝ እና ትኩረት እንዲሰጥ በአገኛችኹት አጋጣሚ ኹሉ በማስተማር የበኩላችሁን አስተዋፅኦ መወጣት ይኖርባቿኻል፡፡

ውድ ተመራቂዎች፣ በመጨረሻ አንድ ነገር ላስታውሳችኹ፡፡ ሕክምና፣ የመደመር እና የማያቋርጥ ለውጥ ሳይንስ ነው። ለውጥ እና መደመር፣ የጤና ቁልፍ ናቸው። የምታክሙት ሰውነት፣ የብዙ ሕዋሳት እና አካላት ድምር ሲኾን፣ ከሕፃንነት እስከ አዛውንትነት በለውጥ ሒደት ውስጥ ነው። በሞያችኹ እና በአገራችን ያለውን የለውጥ ሒደት መቀላቀል ብቻ ሳይኾን፣ ለመምራትም ዝግጁ ልትኾኑ ይገባል። ለውጡ፣ የብቻ ሩጫ ሳይኾን፣ የጋራ ማራቶን ነው። ፈጥኖ ለመቅደም ሳይኾን፣ ረጅም ርቀትን አብሮ በመሮጥ፣ ብዙ ሰዎችን ይዞ ወደ ተሻለ ደረጃ የማድረስ ሩጫ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ከራሳችኹ የሞያ አጋሮች ጋራ መደመርን ይጠይቃል፤ ብሎም ከሌሎች ዘርፎች፣ በአገራችንና ከዚያም ባሻገር ከሚከናወኑ በጎ ነገሮች ኹሉ ጋራ በመደመር የላቀ ነገር ለመሥራት ራሳችኹን አዘጋጁ። ስንደመር፣ ለብቻችን የማንችላቸውንና የሚቻሉ የማይመስሉንን ነገሮች ማድረግ እንችላለን። በመደመር፣ የዛሬ ችግሮቻችን ለነገ ስኬታችን ዕድል ይኾኑልናል። ዕድል ደግሞ፣ የስኬት በር እና ድልድይ ነው።

አሁን አንዱን ምዕራፍ ጨርሳችኹ፣ሌላኛውን ምዕራፍ በመጀመር ዋዜማ ላይ ነው ያላችኹት፡፡ በቀጣዩ ምዕራፍ፥ ሕዝብ የሚመርቃችኹ፣ አገር የሚኮራባችኹ፣ ወላጅ የሚመካባችኹ፣ መንግሥት የሚተማመንባችኹ እንደምትኾኑ ተስፋ አደርጋለኹ፡፡

ታጥቃችኹ በመነሣት፣ ምርጫችኹን በእጃችኹ ውሰዱ! ቀላሉን ሳይኾን፣ ትክክለኛውን መንገድ ምረጡ! በምቹው ሳይኾን፣ በጠቃሚው ጎዳና ላይ ቀና ብላችኹ ሒዱ! የቅርቡን ብቻ ሳይኾን፣የሩቁንም ተመልከቱ! የማይቻለውን በማብሰልሰል ሐሞታችኹን አታፍስሱ! ይልቁንም የሚቻለውን ለማድረግ ክንዳችኹን ዘርጉ!

አገሩ እና ጊዜው ለለውጥ ዝግጁ ነው፤ እናንተስ? ሕዝቡ እና ምድሩ፣ በመደመር እና በእመርታ፣ ከችግር እና ከጉስቁልና አረንቋ ለመውጣት በማኰብኰብ ላይ ነው፤ እናንተስ? ከዚኽ ቀጥሎ ምን እንደምናደርግ፣ ዓለም በሞላ ወደ እኛ እያየ ነው፤ እናንተስ? ይህን የመደመር እና የለውጥ እመርታ ለመምራት እና ለመቀላቀል ዝግጁ ናችኹ?

ጤነኛ፣ ደስተኛ እና የበለጸገ አገር እና ትውልድ መፍጠር ሕልማችን ነው። ወደዚህ ትምህርት ቤት ሕልም ይዛችኹ እንደ መጣችኹ፣ ከዚኽም ስትወጡ የበለጠ እና የጠራ ታላቅ ሕልም ይዛችኹ ልትወጡ ይገባል - አገርንና ወገንን የሚለውጥ ሕልም። ሕልማችኹን አትጣሉ። የዛሬ ችግር፣ የነገ ሕልማችን እውነተኛነት ማረጋገጫ እና መፈናጠጫ እንደ ኾነ ልነግራችኹ እወዳለኹ። ሕልም ካለ ይታለፋልና ሕልማችኹን ወደ ትጋት እና ጠንካራ ሠራተኛነት በመለወጥ ነገ ደግሞ ከዛሬው የችግር ወንዝ ማዶ በሌላ ድል እንደምንገናኝ ተስፋዬ የላቀ ነው።

በመደመር እንለወጣለን፤ በመለወጥም እንደመራለን። መልካም የአገልግሎት ዘመን ይኹንላችኁ፡፡

**"ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!" ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**አመሰግናለሁ !**

# የግብር አከፋፈል ንቅናቄ ማስጀመሪያ ጉባኤ ንግግር

**ታኅሣሥ 12/2011 ዓ.ም.**

"አንድ አገር ከኋላ ቀርነት፣ ከፍ ወዳለ ሥልጡንነት ለመቀየር ቢያንስ ቢያንስ ሦስት ነገሮች መኖር አለባቸው፡፡ እነርሱም፡- ሰላም፣ የግብር ሥርዓት እና አስቻይ የኾነ የፍትሕ ሥርዓት ናቸው፡፡ ሌላው በጊዜ ሒደት ይመጣል፤" ሲል ስኮትላንዳዊው የምጣኔ ሀብት ሊቅ አዳም ስሚዝ የተናገረው፣ ከዛሬ ኹለት መቶ ዓመታት በፊት ነው፡፡

የሰላም አለመኖር ምን ሊያስከትል እንደሚችል፣ እኛ ለሌላው እናስተምር ይኾናል እንጂ አዲስ ትምህርት እንደማያስፈልገን ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም፣ ሰላም፣ የኹሉም ነገር መሠረት መኾኑን እንድንረዳ የሚያደርጉ አያሌ የታሪክ አጋጣሚዎች አሉን፡፡ እንደ አገር፣ አኩሪ የሥልጣኔ ታሪኮችን የፈጸምነው፣ አንጻራዊ ሰላም በአገኘን ጊዜ እንደ ኾነ ነጋሪ አያስፈልገንም፡፡ በሌላውም ዓለም፣ የዳበረ ሥልጣኔ ያላቸው አገሮች፣ ከማንም በላይ ለረዥም ዘመን በሰላም ለመኖር እንደ ቻሉ እናውቃለን፡፡

ፍትሕ፣ የሰው ልጅ መንግሥትን ከመሠረተባቸው ምክንያቶች አንዱ ነው፡፡ ያለ ጠንካራ የፍትሕ ሥርዓት፣ ጠንካራ አገር ልትኖር አትችልም፡፡ የሰላም ዋነኛው መሠረትም፣ የትክክለኛ ፍትሕ መስፈን ነው፡፡ ፍትሕ እና ሰላም፣ እንደ ዶሮዋ እና ዕንቁላሉ፣ ምክንያት እና ውጤት እየኾኑ የሚጓዙ እንጂ፣ ተነጣጥለው የሚኖሩ ነገሮች አይደሉም፡፡

ለሰላም ፍትሕ፣ ለፍትሕም ሰላም ያስፈልጋል፡፡ የሥልጣኔ ሞተሮችን ለማበርታት፣ የሥልጣኔ ዕንቅፋቶችንም ለመቅጣት፣ ጠንካራ የፍትሕ ሥርዓት ወሳኝ ነው፡፡ ሰላምንም ኾነ ፍትሕን በአገር ላይ ለማስፈን መንግሥት እጅ እና እግር የሚያገኘው፣ ግብር መሰብሰብ ሲችል ነው፡፡ አለበለዚያ መንግሥት የሚባለው አካል፣ ለምልክት የተቀመጠ፣ ምንም ማድረግ የማይችል ሽባ ይኾናል፡፡

ማኅበራዊ ደኅንነትን ማስከበር፣ የሰው ልጅ መንግሥት የሚባለውን ተቋም ከመሠረተባቸው መሠረታዊ ምክንያቶች አንዱ ነው፡፡ ሠርተን ለመኖር የሚያስችለን አገር ጸንቶ እንዲኖር፣ ሕግ የሚያስከብርና ሰላም የሚያሰፍን መንግሥት ያስፈልጋል፡፡ ይህን መንግሥት እንዲሠራ ደግሞ፣ አገራዊ የገንዘብ ዐቅም ያስፈልገዋል፡፡ ይኼ አገራዊ አቅም በዋናነት የሚገነባው፣ ከዜጎቹ እና ነዋሪዎቹ ግብር በመሰብሰብ ነው፡፡

ግብር ቀላል ቢኾንም፣ ለመንግሥት ግን እንደ ኦክስጅን አስፈላጊ ነው፡፡ አገርን ከፍ ለማድረግ ከሚያስፈልጉ ሦስት ቀላል ነገሮች መካከል፣ ግብር አንዱ የኾነውም ለዚኽ ነው፡፡ ግብር ለምን ቀላል ነገር ኾነ? በቀላሉ ስለሚገኝና ስለሚሰበሰብ ነው? አይደለም፡፡ ለከፋዩ የሚቀል ዕዳ ስለኾነም አይደለም፡፡ “ላብ ደምን ያድናል” እንደሚባለው፣ ግብር ደግሞ፣ የብዙዎቻችንን ሕይወት ለመታደግ የሚያስችል አገራዊ ዐቅምን ይፈጥራል፡፡ ግብር ባለመክፈል በአገር ላይ ከሚደርሰው ኪሳራ በላይ፣ ግብር በመክፈል የሚገኘው ሥልጣኔ፣ ለኹላችንም ኪስ የማይጎዳ እና ርካሽ ስለኾነ ነው፡፡

ዜጎች በሚከፍሉት ግብር፣ መንግሥት የመሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት፣ የግል ዘርፉ ጠንካራ እና ተወዳዳሪ እንዲኾን ምቹ ኹኔታን ይፈጥራል፡፡ ጠንካራ እና ተወዳዳሪ የግል ዘርፍ ደግሞ፣ ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድልን ከመፍጠሩም በላይ ትርፋማነቱን የሚያረጋግጥ እና ለመንግሥትም ትልቅ የገቢ ምንጭ በመኾን የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ጠንካራ የግል ዘርፍ እንዲኖር ደግሞ፣ ጠንካራ መሠረተ ልማት ያስፈልጋል፡፡ ኹለቱንም ዓይነት ማለትም፣ ገበያንና ልውውጥን የሚያሣልጡ ቁሳዊ መሠረተ ልማቶችን ጨምሮ ቁሳዊ ያልኾኑ

መሠረተ ልማቶች እንደ ዴሞክራሲ፣ ፍትሕ፣ ጸጥታ እና የመሳሰሉት መሠረተ ልማቶች እጅግ በጣም ወሳኝ ናቸው፡፡

በአገራችን የጀመርነውን ሰፊ የዴሞክራሲ ግንባታ በዘላቂነት ለማስቀጠል፣ ተቋማትን መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ጠንካራ እና ገለልተኛ የዴሞክራሲ ተቋማት መኖር ደግሞ፣ የዜጎችን የዴሞክራሲ ተሳትፎ በእጅጉ ያሳድገዋል፡፡ በእንግሊዝኛው፣ “No taxation without representation” እንደሚባለው፣ “ያለ በቂ ተሳትፎ እና ውክልና፣ ግብር የመክፈል ግዴታ ሊኖር አይችልም፡፡” ታዋቂው አሜሪካዊ የታሪክ ሊቅ፣ አልበርት ባሽኔል ሐርት፣ በአንድ ወቅት ሲናገር፣ “ግብር ማለት የሠለጠነ ማኅበረሰብ እንደ ሠለጠነ ለመኖር ሲል የሚከፍለው ዋጋ ነው፤” ያለው እዚኽ ላይ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ የሥልጣኔ መሠረታዊ መገለጫዎች የሚባሉት፥ የተስተካከለ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ፣ ማኅበረሰባዊ ደኅንነት፣ የዳበረ የፍትሕ ሥርዓት፣ የላቀ የዕውቀት እና የጥበብ ዐቅም፣ በምግብ ራስን መቻል እና መሠረታዊ ጤናን ለኹሉ የማዳረስ ብቃት ናቸው፡፡ እነዚኽን ሳይቋረጡና ከደረጃቸው ሳይወርዱ ለማስቀጠል የሚቻለው ባለ ማቋረጥ ግብርን ለመሰብሰብ የሚችል ሥርዓት እና ዐቅም ስንፈጥር ብቻ ነው፡፡

የታሪክ ባለሞያዎች እንደሚሉት፣ የግብር ታሪክ፣ ከሰው ልጅ የሥልጣኔ ታሪክ ጋራ የሚቀራረብ ዘመን ያለው ነው፡፡ ግብርን በተመለከተ የተጻፈው ጥንታዊው ሰነድ የተገኘው፣ በኢራቅ ‹ላጋሽ› በተሰኘ ቦታ ሲኾን፣ የተጻፈው በሸክላ ላይ ነበር፡፡ ይህ ስድስት ሺሕ ዓመታትን ያስቆጠረ የግብር ሰነድ፣ የሰው ልጅ የሥልጣኔ ታሪክ፣ ግብርን ከመክፈል ጋራ ምን ያህል እንደ ተያያዘ የሚያመለክተን ነው፡፡

ኢትዮጵያ እንድታድግ፣ እንድትሠለጥን፣ ሰላም እና ደኅንነቷ የተሟላ እንዲኾን፣ ለዜጎቿ እና ለነዋሪዎቿ መሠረታዊ ፍላጎቶችን በበቂ ኹኔታ ማቅረብ እንድትችል፣ ድህነትን አሸንፋ ወደ ብልጽግና እንድትገሰግሥ ከፈለግን፣ ስለ ግብር ያለንን ደካማ አመለካከት መቀየር አለብን፡፡

ግብር የሚያጭበረብር ሰው እንደ አራዳ መቆጠሩ ቀርቶ፣ አገሩንና መንግሥቱን እንደሚጠላ ብቻ ሳይኾን፣ ስለ ራሱ እና ስለ ልጆቹ የዛሬ እና የወደፊት ህልውና ምንም የማይጨነቅ ሞኝ ተደርጎ ሊቆጠር ይገባል፡፡ ያገኙትን ኹሉ በልቼ ልሙት እንደሚል ሰው ያለ ሞኝ ከቶ ከየት ይመጣል፡፡ ግብር በመክፈሉ፥ አገሩን፣ መንግሥቱንና ልጆቹን እንደሚወድ በይፋ የሚያሳይ ኩሩ ዜጋ መፍጠር አለብን፡፡ በተመሳሳይ፣ ግብር ሰብሳቢዎችም እንደ ደመኛ ሳይኾን፣ ለሥልጣኔ የሚከፈልን ዋጋ በጥንቃቄ እንደሚሰበስቡ ታማኝ ባለ አደራ ዜጎች ራሳቸውን የሚያዩበትን ባህል መገንባት አለባቸው፡፡

በአሁኑ ሰዓት የምንሰበስበው ግብር፣ ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት ጋራ ያለው ጥምርታ በመቶኛ 10.7 ብቻ ነው፡፡ በዚህም፣ ከሰሐራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገሮች እንኳን ስንወዳደር እጅግ ዝቅተኛ ከሚባሉት ወገን ነን፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት፣ በአገራችን የተፈጠሩ አለመረጋጋቶች ደግሞ፣ በግብር አሰባሰባችን፣ በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ኾነውበት እንደ ነበረ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ ኾኖም ግን፣ አንድ ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር፣ አገሩ እንድታድግና እንድትለወጥ በሚፈልገው ዜጋ ቁጥር እና የእውነት ግብር በሚከፍለው ዜጋ ቁጥር መካከል ያለውን ሰፊ ክፍተት ካላጠበብነው በቀር፣ የምናስባትን አገር ልናያት የምንችለው በሕልማችን ብቻ ነው፡፡ በድርጊት ያልተደገፈ ፍላጎት፣ ስያሜው ሕልም ሳይኾን፣ የቀን ቅዠት ነው፡፡

ግብርን በወቅቱ አለመክፈል፣ በተጭበረበረ ደረሰኝ መነገድ፣ ያለ ንግድ ፈቃድ መሥራት፣ ባለሥልጣናት ላይ ተደግፎ በሕገ ወጥ ንግድ ላይ መሠማራት፣ ግብርን መሰወር፣ የኮንትሮባንድ ንግድ፣ ሙስና እና የተበላሸ አሠራር፣ የግብር ሥርዓታችንን በካቴና እንዳሰሩት ኹሉም ሰው ሊያውቀው ብቻ ሳይኾን፣ ከልቡ ሊዋጋውም ይገባል፡፡ እንዲኽ የሚያደርጉ አካላት፣ ጠላቶቻችን ናቸው፡፡ የዜጎችን ደም እየመጠጡ እንደ ኾነ ተረድተው፣ ከአሁኗ ሰዓት ጀምሮ ከድርጊታቸው ያለ ማንም ነጋሪ ሊቆጠቡ ይገባል፡፡ የፈሰሰ ውኃን ማፈስ እንደማይቻለው ኹሉ፣ ያለፈውን ለመማር እንጂ መቀየር አይቻልምና የእስከ አሁኑ ይብቃን ብለን ኹላችንም የፊታችንን የተሻለ ለማድረግ እንትጋ፡፡

በመንግሥት በኩል፣ የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ አሠራሮችን ዘርግቷል፡፡ እንደ መንግሥት፣ ብዙ ጊዜ አጭበርባሪዎችን የምንቀጣውን ያኽል፣ ግዴታቸውን የሚወጡትን ስናመሰግን አንታይም፡፡ አሁን ግን ለዚኽ የሚኾን አሠራር ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡ የግብር አሰባሰባችን ዘመናዊነትን የተላበሰ እንዲኾን ከማስቻል በተጨማሪ፣ የግብር ሥርዓታችንን፥ ፍትሐዊ፤ ተገማች እና ቀላል እንዲኾን ማድረግ ከመንግሥት የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

ግብር ከፋይ፣ የግብር ግዴታውን ለመወጣት፣ ለቀናት ደጅ የሚጠናበት፣ ለአላስፈላጊ ወጪ እና እንግልት የሚዳረግበት አሠራር፣ ከምገኝበት የቴክኖሎጂ ዘመን የማይጠበቅ እና በአፋጣኝ መቅረት ያለበት እንደ ኾነ እናምናለን፡፡ በመኾኑም ከተንቀሳቃሽ ስልክ ጀምሮ ሌሎች ፈጣን የክፍያ ሥርዓቶችን መጠቀም የሚያስችል ማሕቀፍ ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡ ግብር የሚከፍሉትን ዜጎች፥ በቢሮክራሲ፣ በጉቦ፣ ባልተገባ አሠራር እና በእንግልት የሚቀጣው የመንግሥት ሓላፊንም ኾነ ሠራተኛን፣ ግብር ከሚያጭበረብሩ የአገር ጠላቶች ለይተን አናያቸውም፡፡ ገንዘብ ለአገሩ ሊከፍል የመጣን ሰው፣ አክብሮ እና ጋብዞ ከመቀበል ይልቅ፣ ያልኾነ ቢሮክራሲ የሚፈጥር ሰውንም ኾነ አሠራርን ከእንግዲህ ፈጽሞ አንታገሠውም፡፡

ኢትዮጵያ የኹላችን እናት ናት፡፡ ማንም ልጅ እና የእንጀራ ልጅ የለም፡፡ አንዱ በሚከፍለው ግብር ሌላው የሚንደላቀቅበት ምክንያትም አይኖርም፡፡ በመኾኑም፣ የተሳሳተ መሥመር ውስጥ ያላችኹ ኹሉ፣ ቀኑ ከመጨለሙ በፊት ወደ ትክክለኛው አሠራር እንድትደመሩ ጥሪ አቀርባለኹ፡፡ ቤንጃሚን ፍራንክሊን እንደተናገረው፣ "በዚኽ ዓለም፣ ከግብር እና ከሞት በስተቀር ርግጠኛ ሊኮንበት የሚችል ምንም ነገር የለም፡፡"

በዛሬው ቀን፣ የአገራችኹን ዐቅም ለማሳደግ፣ የኢትዮጵያንም ዕድገት ወደሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ፣ የእናታችንም ጓዳ ሙሉ እና የተትረፈረፈ እንዲኾን ለማስቻል፣ "የግብር የበጎ ፈቃድ አምባሳደሮች" ኾናችኍ የተሠየማችኹ ዜጎች፣ እንደ እናንተ ያለ የእናትን ጓዳ የሚሞላ ዜጋ እንዲበዛ፣ የበኩላችኹን እንደምትሠሩ እተማመናለኹ፡፡ ቀጣዩ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ታሪክ ሲጻፍ፣

ስማቸው ደምቆ ከሚጠቀሱ ወገኖች መካከል እንድትኾኑ መመረጣችኹንም ላስታውሳችኹ እወዳለኹ፡፡

“ግዴታዬን እወጣለኹ፤ መብቴንም እጠይቃለኹ” በሚል መሪ ቃል የምንጀምረው ግብር መክፈልን ባህል የማድረግ፣ የግብር መሠረታችንን የማስፋት፣ ግብር ከፋዮችን የማበረታታት እና ግብር አጭበርባሪዎችን የመቅጣት አገራዊ ንቅናቄ በይፋ የተጀመረ መኾኑን በዚኽ አጋጣሚ አበሥራለኹ፡፡ “የቄሣርን ለቄሣር፣ የፈጣሪን ለፈጣሪ” ሰጥተን በውጤት እንደምንገናኝም አምናለኹ፡፡

**“ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!”**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ**

# የመከላከያ ቀን ንግግር

**የካቲት 8/2011 ዓ.ም.**

**Excellencies,**
**Chief of staffs of friendly countries,**
**Distinguished invited guests**
**የቀድሞ ኤታማዦር ሹም**
**Chief of staff's ሳሞራ የኑስ፤**
**እንዲሁም ጀነራል ሰዓረ መኮንን**
**በጥቅሉ ለሃገር መከላከያ ሠራዊት**
**አባላትና አመራሮች በሙሉ፤**

በቅድሚያ እንኳን ለዓመታዊው የመከላከያ የሠራዊት ቀን አደረሳችሁ አደረሰን ለማለት እወዳለሁ።

ለጠላቶቹ የፍርሃት ምንጭ፤ ሁሌም ለወዳጆቹ፣ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ኩራት የሆነው ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን በዘመናት ሁሉ ያጋጠሙትን የውጭም ሆነ የውስጥ የሉዓላዊነት ፈተናዎችን በከፍተኛ ወኔና ቁርጠኝነት የተወጣ፣ የሃገር መከታና አለኝታ የሆነ ተቋም በመሆኑ፣ በዚህ ታላቅ ሠራዊት ውስጥ በማገልገላችሁ በማገልገላችን ታላቅ ኩራት ሊሰማችሁ፣ ሊሰማን ይገባል። ሃገራችን ከፍም ሆነ ዝቅ ባለችባቸው የታሪካችን ክፋዮች ሁሉ በጽናትና በታማኝነት፣ በቁርጠኝነትና ከምንም በላይ ሃገርንና ወገንን ቅድሚያ በመስጠት ታላቅ መሥዋዕትነትን የተወጣ ተቋም ነው። በዚህም ከሃገራችን

ሕዝቦችም አልፎ ለሰላም ማስከበር በተሰማራባቸው ሃገራትና ሕዝቦች ሁሉ በውጤታማነቱና በሕዝባዊ ወገንተኝነቱ ምስጉን ሠራዊት ነው።

ይህም ሆኖ ግን አሠራሩንም ሆነ ሙያዊ ክህሎቱን ዘመኑ ከሚጠይቀው ነባራዊና ንድፈ-ሐሳባዊ ደረጃ ጋር ከማስተሳሰር አንጻር በርካታ ውስንነቶች ነበሩት። ውስጣዊ አሰራሩም ግልፅነት የጎደለውና ለብልሹ አሠራሮች የሚጋብዝ ነበር። እነዚህንና ሌሎችንም ክፍተቶችን በመድፈን የሃገር አለኝታነቱን ለማስቀጠል መከላከያ ሠራዊትና አመራሮቹ ባለፈው አንድ ዓመት ገደማ የለውጥ ጊዜያት በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ሰጥተን የሠራንበትና ስኬታማ ውጤቶችም ከተገኙባቸው ተቋማት አንዱና ዋነኛው ነው።

የመጀመሪያውና ዋነኛው ለውጥ የሲቪል ቁጥጥርን ማረጋገጥ ነው። እንደሚታወቀው የፕሮፌሽናል መከላከያ ግንባታ አንዱ መለኪያ የሲቪል ቁጥጥርን ማረጋገጥ ነው። ይህንንም በመገንዘብ በሕዝብ ምርጫ በየተወሰነ ጊዜ የሚመረጡ የሕዝብ ወኪሎች በወታደራዊ ጉዳዮች ላይ ዋነኛውን ውሳኔ እንደሚወስኑ የሚያስችል ቁመና መፍጠር ነው። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች የሕዝብ ውክልና የሚረጋገጠው መርጠው በሚወክሏቸው እንደራሴዎቻቸው መሆኑ ይታወቃል። ለዚህም ነው፤ ሲቪል የሚቆጣጠረው ወታደራዊ ኃይል በተሻለ የአንድ ሃገር ዴሞክራሲ ዋልታ ተደርጎ የሚቆጠረው።

ከዚህም ባሻገር መከላከያ ሠራዊት በየጊዜው ሊቀያየር ከሚችለው የአስፈጻሚው አካል ጋር ሳይወጣና ሳይወርድ በቀጣይነት ሙያዊ ክህሎቱን እንዲያሳድግ የሚያደርግ በመሆኑም ጭምር ነው። አንድ ወታደር ከምልምል ሠልጣኝነት እስከ መጨረሻው የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹምነት ድረስ እስከ አርባ ዓመት የሚፈጅ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ይህ ሙያዊ እድገት ሳይገደብ ሊቀጥል የሚችለው ከፖለቲካዊ ወገንተኝነት በጸዳ መልኩ ሙያዊ ልቀቱን ጠብቆ ማደግ ሲችል ብቻ ነው። ከዚሁ ጋር በማያያዝ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የማስተላልፈው መልእክት፤ አሁን እየተገነባ ያለው የመከላከያ ሠራዊት፣ ዛሬ የሁላችንንም ሃገር ሉዓላዊነት የሚጠብቅ፣ ነገ የሕዝብ ፈቃድ ሆኖ ሥልጣን ብትይዙም ተረክባችሁ የምታስቀጥሉት ተቋም መሆኑን ነው። እንደ አጠቃላይ በሁሉም ዘርፎች፣ በዋናነትም በአገር መከላከያ ሠራዊት ዙሪያ ጅምላ ፍረጃ

ለዛሬም ሆነ ለነገ እኛነታችን ምንም የሚጨምረው ነገር ስለሌለ፤ ይሄንን መጥፎ አባዜ እስከ ወዲያኛው አሽቀንጥረን የምንጥለበት ጊዜው መሆኑን ተገንዝበን ሁሉንም በዜሮ ማባዛት እና አፍርሶ የመገንባት ባህል አገራችንን ወደኋላ ሲጎትት እንጂ ወደፊት ሲያራምዳት አላየንም፡፡ ይልቁኑም የያዝነውን ለማሳደግ እየጨመርንበት ስንሄድ፣ ያለው ላይ ማስተካከያዎችን ስናደርግ በጊዜ ሂደት የተሟላና ሁሉን ያማከለ ሥርዓት በአገራችን መትከል እንችላለን፡፡

ይህ እንዲሆን ጥፋት ሲታይ እንኳን በባለቤትነት ስሜት መጠቆም እና እንዲታረም መወትወት እንጂ፣ ተቋሙን እንደ ተቋም ማጠልሸት የወታደሩ የማድረግ አቅም ዋነኛ ምሰሶ የሆነውን ሞራል ይሸረሽራል። በመሆኑም በሀገር አለኝታና ኩራት ተቋም ላይ እንደዚህ ያለ የጅምላ ሂስ አፍራሽ በመሆኑ በአንክሮ ልንመለከተውና ልናሻሽለው ይገባል።

ሌላው በጉልህ የሚነሣው መከላከያ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር ያለውን መራራቅ መቅረፍ ነው። ባደጉት ሃገራት የመከላከያ የጥናት ዘርፍ ከአካዳሚው እና ከግሉ የጥናት ዘርፍ ጋር በመቀናጀት ፈር ቀዳጅ የሆኑ ውጤቶችን የሚያስገኝ ነው። ከጥንታዊው ሰረገላ ጀምሮ እስከ ኢንተርኔት፣ ሰው አልባ በራሪ ቴክኖሎጂ (ድሮን) እና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሊጂያዊ ውጤቶች የተገኙት ከመከላከያ ጓዳ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። በቅርቡ የሳይበር ኮማንድ፣ በጊዜ ሂደት ደግሞ የህዋ ምኅዳር እንደ ዐውዶች መያዛቸው መከላከያ በቴክኖሎጂ መስኮች ከፍተኛ ጥናትና ምርምሮችን እንዲያደርግ፣ ከአካዳሚውና ከጥናት ተቋማት ጋር በቅንጅት እንዲሠራና ይህንንም በተሻለ መልኩ ለማገዝም በአዲሱ ዐዋጅ የእጩ መኮንንነት ምልመላ ከሲቪልም ጭምር እንዲሆን ተደርጎ የተሻሻለ በመሆኑ በተለያየ የትምህርት ዘርፍ የተመረቃችሁና የወታደራዊ ሙያ ዝንባሌ ያላችሁ ወጣቶች በዚህ ዕድል በመጠቀም ዘመናዊ ተቋም የመገንባትና የቴክኖሎጂን ልቀት ለማረጋገጥ ልትጠቀሙበት እንደሚገባ ልጠቁማችሁ እወዳለሁ።

## ውድ የሠራዊታችን አባላት፤

መከላከያ ሠራዊትን የማዘመን ጉዳይ የአንድ ወቅት ሥራ አይደለም። የስጋቶች ሁኔታና የማድረግ አቅም በየወቅቱ ይለያያል፡፡ ቴክኖሎጂ የሚፈጥራቸው

አቅሞችና ስጋቶች በየቅጽበቱ ይቀያየራሉ። በዚህ ተለዋዋጭ ምኅዳር ውስጥ ብቁ ሆኖ ለመገኘት ከዘመን ጋር አብሮ መዘመን ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ተማሪና አዳጊ ተቋም መገንባት ይኖርባችኋል። ለዚህም በተቋም ደረጃ ከሚደረጉ ማሻሻያዎች ባሻገር እያንዳንዳችሁም በግል ሁሌም ተማሪና አዳጊ መሆን ይጠበቅባችኋል።

## የተከበራችሁ የሃገራችን ሕዝቦች፤

ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት ከአብራካችሁ ተከፍሎ የወጣና ለሃገራችን ሰላም ዋስትና ለመስጠት ሌት ተቀን የሚዋደቅ፣ ባልተመቸ አኳኋን ውስጥም የላቀ ውጤት እንዲያመጣ የምንጠብቀው የሀገር መከታችን ነው። ሆኖም የሚከፍለውን የመሥዋዕትነት ደረጃ ቀረብ ብሎ ካለማየት በሚገባው ደረጃ ክብር አለመስጠት ይስተዋላል። ይህን ባህል ለመቀየር፤ ዩኒፎርም የለበሱና መለዮ አድርገው በሕዝብ መገልገያ ስፍራ የሚገኙ ወታደሮች ከሁሉም ተገልጋይ በፊት ቅድሚያ በመስጠት ለሙያውና ለወታደሮቹ ያለንን ክብር ማሳየት ይኖርብናል።

በዚህ ረገድ ሚዲያውን ጨምሮ አጠቃላይ የኪነ ጥበቡ ማኅበረሰብ መከላከያ ሠራዊታችን በሚፈለገው ደረጃ እንዲቀረፅና በሕዝብ ዘንድ ያለው እምነት እንዲያድግ የማድረግ ከፍተኛ አቅም አላችሁ፡፡ በተቃራኒውም ክብርን ማጠልሸት በሚችል መንገድ ማስተጋባትም እንዲሁ ትችላላችሁ፡፡ ቁምነገሩ ግን በማጠልሸት ውስጥ ምንም የሚገኝ ነገር የለም። ዛሬ እንደዋዛ ያጠለሸነው ወታደር ነገ ወራሪ ኃይል ቢመጣ ምን ሊገጥመን እንደሚችል ለኢትዮጵያውያን መናገር አያስፈልግም። እንደምታውቁት በአሜሪካ ሆሊውድ፣ በወታደርነት አገርን ማገልገል ትልቅ ክብር እንደሆነ፣ ውትድርና እንደ አንድ ሙያ ብቻ ሳይሆን አገርን በማፍቀር የሚመርጡት ሙያ እንደሆነ በማሳየት በኩል የሚጫወተው ሚና እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ አሜሪካ በተሸነፈችባቸው ዐውደ ውጊያዎች ጭምር ወታደሮቿ ምን ዓይነት ገድል እንደሠሩ በማሳየት የወታደሮቻቸውን ጀግንነትና አገልጋይነት ለማጉላት እስከዚያ ርቀት ይሄዳሉ፡፡

የሶማሊያን ሰላም፣ የሱዳንን ሰላም ለማረጋገጥ ሄዶ ሕይወቱን የገበረውንና ኢትዮጵያን ያስከበረውን ጀግና ሁሌም ማስታወስና ማክበር ከእያንደንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል።

በዚህ ረገድ በእኛም በኩል አስፈላጊውን ትኩረት ሰጥቶ የመሥራት ውስንነት ቢኖርም በአብዛኛዎቹ ፊልሞቻችን፣ ቀልዶቻችንና ጽሑፎቻችን የሚሣለው የወታደርና ወታደራዊ አዛዥ ገፀ ባሕርይ ቀረጻ ጥንቃቄ እንደሚጎድለው መታዘብ ይቻላል። በቀጣይ ሙያተኞች ሙያዊ ነጻነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእውነታ የቀረበ ሥራ እንዲሠሩ ከማስቻል አንጻር በመከላከያም በኩል ለጥበበኞች በርን መክፈትና ለጥናትና ምርምር አጋዥ መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ሳልጠቁም አላልፍም።

የመከላከያ ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም አዲሱን የለውጥ መንፈስ ተከትለው በቀድሞ በደርግ የሠራዊቱ ከፍተኛ መኮንኖች፣ በኢሕአዴግ ከፍተኛ ጀነራል መኮንኖች እነ ጀነራል ሳሞራ የኑስ፣ እነ ጀነራል አበባው ታደሰ፣ እነ ጀነራል ባጫ ደበሌ በዚህ ሥነ ሥርዓት እንዲገኙ ማድረጋቸው የመደመር ጉልበት ማሳያ ስለሆነ፤ ይህ ባህል ወደፊትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፤ ሁሉም መሥሪያ ቤቶች ከመከላከያ በመማር ያገለገለን በማክበር፣ የሚያገለግልን ለመፍጠር በኅብረት አሁንም በመደመር ይህችን ታላቅ ሀገር ወደ ላቀ ከፍታ የማሸጋገር የጋራ ሐላፊነታችንን እንድንወጣ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና**
**ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ።**

# የደብረ ብርሃን ንግግር

**የካቲት 23/2011 ዓ.ም.**

**የተከበሩ ፕሬዝዳንት ኡሁሩ ኬንያታ የኬንያ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት እና የኢትዮጵያ ወዳጅ፤**
**የተከበሩ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው የአማራ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት፤**
**የተከበራችሁ የሃይማኖት አባቶች፣ ሚንስትሮች**
**ከሁሉ በላይ የደብረ ብርሃን ከተማ እና አካባቢዋ ነዋሪዎች እንኳን ደስ አላችሁ፤**
**እንኳን ደስ አለን።**

ደብረ ብርሃን ማለት አቶ ገዱ እንዳሉት ስያሜዋን ያገኘችው ከገጠማት ክሥተት ቢሆንም የተራራ ብርሃን ማለት ነው። የተራራ ብርሃን ተብላ እንድትጠራ ያስቻላት ያ ክሥተት አሁን ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር አያይዘን ብንመለከተው፤ ደብረ ብርሃን የብርሃን ተራራ ለከተማዋ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያም የብርሃን ምስጢር የምትገልጥ መሆን አለባት፡፡ የብርሃን ምስጢር፤ ብርሃን ሲጠፋ ጨለማ ይመጣል እንጂ ጨለማ ስለጠፋ ብርሃን አይመጣም፡፡ ፍቅር ስለጠፋ ጥላቻ ይመጣል እንጂ ጥላቻ ስለጠፋ ፍቅር አይመጣም፡፡ ብርሃን ሁልጊዜ በጨለማ ላይ ሥልጣን አለው፡፡ ፍቅር ሁልጊዜ በጥላቻ ላይ ብርታት አለው።

ይህንን አንፀባራቂ ስም የአገራችን ምሳሌ ማድረግ አንድንችል ብርሃን በባሕሪው ወደ ሰማይ ስታበሩት እና ማረፊያ ስትከለክሉት ምንም ነገር አያሳይም፡፡

ብርሃንን ብርሃን የሚያሰኘው ወደ ምድር ሲበራና ማረፊያ ሲያገኝ ብቻ ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ አንድነት፣ ስለ ሰላም፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ አብሮነት መናገር በትልቅ ጨለማ ውስጥ ትንሽዬ ባትሪ ማሳየት የሆነበት ዋናው ምክንያት፤ ጥቂቶች ባትሪ የያዙ ወደ ምድር ሳይሆን ወደ ሰማይ እያበሩ ስለሆነ ነው፡፡

እኛ የኢትዮጵያን አንድነት፣ የኢትዮጵያን ሕዝቦች እኩልነት፣ የኢትዮጵያን ሰላም የምንሻና ለዚሁ ዓላማ የምንታገል ሰዎች፤ ዛሬ ቁጥራችን ጥቂት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ገና መሬቱን እያለሰለስን ስለሆነ፣ ዘር እየዘራን ስለሆነ የዚህ ሐሳብ ተጋሪዎችና ለኢትዮጵያ አንድነትና እኩልነት የምትታገሉ ታጋዮች በሙሉ መገንዘብ ያለባችሁ ገና የአሥራ አምስትና እና የሃያ ዓመት ጠንካራ ጉዞ የሚጠበቅብን መሆኑ ነው።

እኛ ዛሬ የምንዘራው መልካም ዘር የሚበቅለው ከአሥር አመት በታች ላሉ አዲስ ትውልድ እንጂ ባለፉት ሠላሳ፣ አርባ ዓመታት በመከፋፈል፣ በመጠላላት፣ በመገፋፋት የተካኑና ያደጉት ላይ አይደለም። እነዚህ ላይ መሥራት ባትሪን ወደ ሰማይ እንደማብራት ይሆናል፡፡ ሥራችን ጥረታችን ከአሥር አመት በታች ያሉ ኢትዮጵያውን የአንድነትን፣ የሰላምን የፍቅርን ኃይል ወይም የብርሃንን በጨለማ ላይ ያለውን ብርታት ተረድተው ከሃያ ዓመት በኋላ ያቺ የምንናፍቃት የምንመኛት፣ ከድህነት የተገላገለች፣ በእኩልነት በጋራ የሚኖርባትን ኢትዮጵያን የሚያዜሙ፣ የሚጠብቁ፣ የሚመሩ ትውልዶችን መፍጠር ነው።

ይህን ለማድረግ የጀመርነው ትግል ጠንካራ እንደሆነ ስለምናውቅ በምንም ዓይነት ወጀብ፣ በምንም ዓይነት ግርግር ወደ ኋላ የማንል እና የኢትዮጵያን አንድነት፣ የኢትዮጵያን እኩልነት፣ የኢትዮጵያ ሰላም፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ የጀመርነው ጥረት፣ የምናበራው ባትሪ በተለያየ ምክንያት ብረሃኑ እያጠረ ወይም የሚያበራብት አቅጣጫ እየተዘበራረቀ ሲሄድ የምናቆም አለመሆናችንን፤ በጽኑ ለማቆም የምትተጉ ኃይሎች በዚሁ አጋጣሚ እንድትገነዘቡ እፈልጋለሁ። የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ ምሁራን ኢትዮጵያን ለመከፋፈል፣ ኢትዮጵያን ለማለያየት ሀብታቸውን፣ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን የሚያጠፉ ብዙ ኃይሎች፣ በአገር ውስጥና በውጭ አሉ።

ይህ ጉዳይ እምብዛም የማይገዳችሁ ኢትዮጵያውያን ለዚህ ጉዳይ ጊዜ አታባክኑ። በቂ ኃይል ስላለ። ጊዜ ካላችሁ ጉልበት ካላችሁ ለሰላማችን ለአንድነታችን ለዚህች ታላቅ ሀገር ዳግም ውልደት በጋራ እንድነሠራ ጥሪዬን አቀርባለሁ፤ እፈልጋለሁ። የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ የመኖር ፋይዳን መገንዘብ ከዐድዋ ድል ብቻ ሳይሆን ከደብረ ብርሃን መማር ይችላል። ደብረ ብርሃን ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች በተለይ የኦሮሞና አማራ ተዋዶ፣ ተዋሕዶ፣ ተስማምቶ፣ ተጋብቶ፣ ተዋልዶ በፍጹም ሰላምና ፍቅር የሚኖርበት ከባቢ ነው። ይህንን ልቦና፣ ይህንን እሳቤ በሁሉም የአገሪቱ ከባቢ ለማብዛት በጋራ መሥራት ይኖርብናል።

በቅርቡ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ እናደርጋታለን በሚል የጀመርነውን ፕሮጀክት በሚመለከት በዚሁ አጋጣሚ እዚህ ለተገኛችሁ የደብረ ብርሃን ሕዝቦች እና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማብሰር የምፈልገው፤ እንዳልነው አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ እናደርጋታለን፡፡ አዲስ አበባን አበባ የምናደርጋት ለአዲስ አበቤዎች ወይም ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ፣ ለመላው ዓለም የመሄጃ፣ የማረፊያ፣ የመስከኛ፣ የማሰቢያ፣ የመደሰቻ ስፍራ እንድትሆን ጭምር ነው፡፡ አደስ አበባ ለእኛም ለተቀረው ዓለምም ትበቃለች። ከዐድዋ ነፃነት መማር የሚያስፈልገን ነገር ከወራሪ ኃይል ነፃ የወጣው ይህ ኢትዮጵያዊ ከታሰረበት የድህነት፣ የኋላ ቀርነት፣ የመከፋፈል ባርነትም ነፃ ለመውጣት በጋራ መዋጋት ይኖርበታል። ሳናጣ፣ ሳንቸገር፣ ሳያንሰን አይረባ ቦታ እየዋልንና እየተጨቃጨቅን ይችን ታላቅ አገር ለመከፋፈል፣ ለመበተን ከሚተጉት ጋር ከመትጋት፤ የዚህችን አገር አንድነት በመጠበቅ በየትኛውም ቅጽበት ማለፍ ኩራት መሆኑን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያን በስድስት ምሰሶ፤ ከአሁን ጀምሮ በሚቀጥሉት ዓመታት ዳግም ህዳሴዋን፣ እድገቷን፣ ብልጽግናዋን እና አንድነቷን ለማምጣት ባለ ስድስት ምሰሶ አዲስ እሳቤ የሰነቅን ሲሆን፤ በተለያየ መንገድ በዝርዝር በቅርቡ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የምናሳውቅ ይሆናል፡፡

ስድስቱ ምሰሶዎች አንደኛው ሰላም ነው። ሰላም ከሌለ አብሮ መኖር፣ ሰላም ከሌለ ሀገር መገንባት፣ ወጥቶ መግባት ስለማይቻል ሰላም አንደኛው ምሰሶ ሆኖ በሚቀጥሉት ዓመታት ኢትዮጵያን የምንገነባበት ይሆናል።

ሁለተኛው ዲሞክራሲ ነው፡፡ የኢትዮጵያውያን በሃይማኖት፣ በዘር፣ በአስተሳሰብ በርካታ ሐሳቦች የያዝን ስለሆነ ሊያቀራርበን፣ ሊያከባብረን፣ አብሮ ሊያኖረን የሚችለው አንዱ መንገድ ለጊዜው ያለው ዲሞክራሲ ብቻ ነው፡፡ የአፍ ዲሞክራሲ ሳይሆን የተግባር ደሞክራሲን ኢትዮጵያ ውስጥ ማረጋገጥ ይኖርብናል።

ሦስተኛው ብልጽግና ነው፡፡ የኢትዮጵያውያን መሬት፣ ውኃ፣ ማዕድን፣ ለቱሪዝም ምቹ የሆነ እና እየተማረ ያለ፣ እያደገ ያለ፣ በአካባቢያችን ካሉ አራት አምስት አገራት አንጻር እንኳን ሲወዳዳር የላቀ ወጣት ዜጎች ያላት አገር ናት። ይህንን ኃይል በመሰብሰብ፣ በመደመር፣ የሚሻለውን አቅጣጫ በማመላከት፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ የሁላችን ተግባር ይሆናል።

አራተኛው ምሰሶ አገራዊ አንድነት ነው። ምንም ሰላም ቢኖር፣ ምንም ዲምክራሲ ብናስፋፋ፣ ብልጽግናን ብናመጣ የኢትዮጵያን አንድነት የማናስቀጥል ከሆነ ታጥቦ ጭቃ ነው። የኢትዮጵያን አንድነት ማስቀጠል እንደ አራተኛ ምሰሶ ይዘን የምንሠራበት ይሆናል።

አምስተኛው ፍትሕ ነው። በኢኮኖሚ ፍትሕ፣ በሥልጣን ፍትሕ፣ በወጥቶ መግባት ፍትሕ፣ ሰዎች በሚያስቡት የማኅበራዊ ፍትሕ፣ ዲሞክራሲያዊ ፍትሕ እና ኢኮኖሚያዊ ፍትሕ ለማረጋገጥ ኢትዮጵያውያንን በእኩል ዐይን የሚያይ፣ በእኩል ዐይን የሚዳኝ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሕግ ፊትና በሀገራቸው እኩል የሚሆኑበትን ሥርዓት መፍጠር ይሆናል። ፍትሕ ከሌለ ቅድም ያነሣሁዋቸው ሰላም፣ ዲሞክራሲ እና ብልጽግናን እንዲሁም አገራዊ አንድነትን ማረጋገጥ አይቻልም።

ስድስተኛው አገራዊ ክብር ነው። ኢትዮጵያዊነት ክብር መሆኑን፣ የኢትዮጵያን ፖስፖርት መያዝ የማያሳፍር መሆኑን፣ በሄድንበት ሳንሸማቀቅ ኢትዮጵያዊ ነኝ የምንልበትን ክብር መመለስ ያስፈልጋል። ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ብልጽግና፣ ፍትሕ፣ ሀገራዊ አንድነት እና አገራዊ ክብርን ለማረጋገጥ የምንሠራው ሥራ እልህ አስጨራሽ ነው።

ኢትዮጵያውያን እንደ መልካችን፣ እንደ ባህላችን፣ እንደ ቋንቋችን አንድ ስፍራ መሰባሰብ እንችገራለን፡፡ ነገር ግን የተከበራችሁ አባቶችና በተለይም አዳጊዎች ሁላችንም ማለፋችን አይቀርም፡፡ ካለፍን በኋላ የሚዘከር ታሪክ እንዲኖረን እዚህ ፊት ለፊት እንዳሉ ሁለት ጀግኖች ለእውነት፣ ለአንድነት፣ ለመቀራረብ፣ ለፍቅር እንትጋ፡፡ ለዚሁ ዓላማም እንሥዋ። ማንም ዘመኑን በሙሉ ሀብታም ቢሆን፣ ድሀ ኦሮሞ ቢሆን፣ አማራ፣ ትግራይ ቢሆን፣ ጉራጌ፣ ዘላለም መኖር አይችልም፡፡ ዘላለም የምትኖር ኢትዮጵያ ነች።

ዘላለም የምትኖረዋን ኢትዮጵያን ለማበልጸግና የሕዝቦቿን አንድነት ለመጠበቅ ብዙ ኃይሎች ይተጋሉ፡፡ የኢትዮጵያ አንድነት፣ የኢትዮጵያ ሰላም፣ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም ያስጨንቃል። ነገር ግን በዐድዋ ብዙዎች ታርደው፣ ብዙዎች ተሠውተው፣ ኢትዮጵያ ነጻነቷን መጠበቅ እንደቻለች ሁሉ፤ ዛሬም በክፋት፣ በጥላቻ፣ በመነቋቆር፣ በመገፋፋት ሊለያዩን የሚፈልጉትን ኃይሎች ከአዳጊ ሕፃናት ጋር በመሆን ታሪክ እንደምንደግም በልበ ሙሉነት ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

የኢትዮጵያን ክብርና የኢትዮጵያ ብልጽግና ለማምጣት ባትሪያችንን ወደ ሰማይ ሳይሆን ባትሪያችንን ወደ ምድር እናብራ፡፡ ያም ምድር ከአሥር ዓመት በታች ያሉ ያልተበረዙ፣ ያልተመረዙ፣ ንጹሕ እንቦቃቅላ ኢትዮጵያውያንን፤ ፍቅርን፣ ሰላምን፣ አንድነትን፣ ከእኛ ወርሰው፣ አሁን የተፈጠረው ባለፉት ዓመታት የተዘራበትን አረም የሚያስተጋባውን ትውልድ ሳይሆን፣ አሁን የምንዘራውን ፍቅር ዘርተን የሚዋደድ፣ የሚከባበር፣ በመጭው የቴክኖሎጂና የዓለም ውድድር ውስጥ ከዓለምም ችግር በዕውቀት ተወዳድሮ የአገር ህልውናና ክብር ማረጋገጥ የሚችል ትውልድ ለመፍጠር፤ ሳንታክት ተጋግዘን መሥራት፤ የእያንዳንዱ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ፍላጉትም፣ ግዴታም፣ ሙብትም፣ የማስተዋል ውጤትም፣ እንደሆነ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

በመጨረሻም ደብረ ብርሃን ለኢንድስትሪ ምቹ ከሚያሰኛት አንዱ ነገር ሀብትና ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ከየትኛውም ጫፍ ቢመጡ ተቀብላ ለማስተናገድ፣ ሰላማቸውን ለመጠበቅ፣ በትጋት ሥርታ ትርፋማ እንዲሆኑ ለማስቻል፣ ያላት ቁርጠኛነት ነው፡፡

ይህን ቁርጠኛነት መጠበቅ ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ሌሎች አካባቢዎችም እንዲማሩ ማድረግ የእናንተ ድርብ ሐላፊነት ይሆናል። ባለሀብቶች ከምን ጊዜውም በላይ ወደ ኢትዮጵያ እየጐረፉ ይገኛሉ፡፡ ዕውቀታቸውን እና ሀብታቸውን ለማስቀረት፣ ሥራ አጥ ወንድሞቻችንን ሥራ ለማስያዝ፣ በፌስ ቡክ ከመናቆር እያመረትን ኤክስፖርት ማድረግ እንድንችል ባለሀብቶች አይተኬ ሚና አላቸው፡፡ የአገር ውስጡንም ባለሀብት፣ የውጭውንም ባለሀብት በከፍተኛ የሐላፊነት ስሜት በማገዝ አብረን ለማደግ የጀመራችሁትን መልካም ጅምር እንድታስቀጥሉ በታላቅ ትሕትና አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።

ደጋግምን እንድንመጣ፣ ደጋግመን ከእናንተ እንድንገናኝ፣ የእናንተን ለልማት፣ ለእድገት፣ ያላችሁን መሻት ማየት እንዲሆንልን፣ ባለሀብቶች ተበራክተው እንዲመጡና እንደዚህ ዓይነት ድንቅ ሥራ እንዲበራከት መንግሥት እንደ ሁልጊዜው ሁሉ በከፍተኛ  ቅርበት ከክልሉ አመራር ጋር የሚሠራ መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

**እንኳን ደስ አላችሁ!! ነፃነታችን አንድነታችን ሰላማችን ይቀጥላል!!**

ለነፃነት ትላንት ዋጋ እንደከፈልነው አሁንም ለኢትዮጵያ አንድነት እና እኩልነት መከፈል ያለበት ማንኛውም ዋጋ ካለ በየትኛውም መንገድ ለመክፈል እና የኢትዮጵያን ክብር ለማስቀጠል መንግሥት ቁርጠኛ አቋም እንዳለው በዚሁ አጋጣሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

## አመሰግናለሁ።

# የአንድ ዓመት የለውጥ ሂደት መዘከሪያ ፕሮግራም ንግግር

**መጋቢት 24/2011 ዓ.ም.**

**የተከበራችሁ የፌደራልና የክልል የሥራ ኃላፊዎች**
**የተከበራችሁ የቀድሞ ፕሬዝዳንቶች**
**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች**
**መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ**

በመጀመሪያ ዘለዓለም እንደአሁን የሆነለት፤ ትናንት ዛሬና ነገን አስተሣሥሮ ለዚች ድንቅ መዓልት ያበቃን ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ዓመት በሄድኩበት ስፍራ ሁሉ በፍቅር፣ በደስታ፣ ከጎንህ ነን በሚል ስሜት የደገፋችሁኝ ወገኖቼ፤ እንዲሁም ሰኔ 16 የተሰነቀልኝን የሞት ድግስ ተሻምታችሁ በመውሰድ የሞታችሁልኝ፣ የቆሰላችሁልኝ፣ የደማችሁልኝ፣ ወገኖቼ፤ በዋሽንግተን ዲሲ፣ በሎስ አንጀለስ፣ በሚነሶታ፣ ከመላው አውሮፓ የተውጣጣችሁ በፍራንክፈርት በዚያ ብርድ ሙሉቀን መሪያችን ይመጣል፤ እናደምጠዋለን ብላችሁ ቆማችሁ የጠበቃችሁኝ።

ለዘመናት ተለያይታችሁ ከነበራችሁበት አስፈሪ የተራራቀ ስፍራ ድልድዩን በመገንባት በአንድ ላይ ኢትዮጵያ እያላችሁ ያዜማችሁ ዳያስፖራ ወገኖቼ በሙሉ፤ ያለእኔ ኢትዮጵያ፤ ያለእኔ ኢትዮጵያውያን መኖር ትችላላችሁ። እኔ ግን

ያለእናንተ ምንም የማልረባ ነኝ። ኢትዮጵያዊነት ዘመም ካለበት ቀና እናድርገው የሚለውን ፕሮጀክት አብረን ስንጀምር ኢትዮጵያዊነት ታክቲክ ወይም ቴክኒክ ሊሆን አይደለም። ኢትዮጵያዊነት የማይቋረጥ ፏፏቴ፣ የማይፈረካከስ ዐለት፤ የነበረ፣ የሚኖር ድንቅ ምስጢር መሆኑን በመገንዘብ ነው። የተወደዳችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦች፤ ለውጡ እንደ ውኃ ፈሳሽ፣ እንደ እንግዳም ደራሽ የመጣ አልነበረም። ብዙዎች የሞቱለት፣ የተገረፉለት፣ የታሠሩለት፣ የተሰደዱለት፣ ያለቀሱለት የጸለዩበት የሁላችን ድምር ውጤት እንጂ፤ የጥቂት ግለሰቦችም አልነበረም።

ይህ በብዙዎች ዋጋ የመጣን ለውጥ በተባበረ ክንድ፣ በመደመር ሐሳብ መጠበቅና ማስቀጠል ከመላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚጠበቅ አደራ ይሆናል። ባሳለፍነው አንድ ዓመት ሺህዎች ተፈቱ፤ ከቂሊንጦም ከካይሮም።የተለያዩ ተገናኙ። እንዲወጡ፣ እንዳይገቡም የታገዱ እገዳው ተነሣላቸው። የሚታኮሱ አፈሙዝ አዘቅዝቀው ለሰላም ወደ ሀገራቸው ገቡ። የሚሠጉም እፎይ አሉ። አምና በዚህ ጊዜ የሀገሪቱ ቀጣይነት ልጡ የተራሰ ጉድጓዱም የተማሰ ይመስል ነበር። ተንሸራትተን እንዳንወድቅ፣ ገብተንም እንዳንሰበር በሠጋንበት ጊዜ በኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንድና በፈጣሪም ርዳታ ያ ክፉ ጊዜ፣ ያ ጨለማ ተገፎ ለሁላችንም የፌሽታ፣ የደስታ ብርሃን እንደመጣ መዘጋት፣ አለማመስገንም ተገቢ አይሆንም።

ቀደም ሲል የጥበብ ሰዎች በግጥም በመነባንብ እንዳሉት፤ ፖለቲካችን ባልተሟሸ ጀበና እንደተጣደ ቡና በረባ ባልረባው ቱግቱግ የማለት ባሕሪ አለው። የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች የኢትዮጵያ ሕዝብ ዝምታው እንደ ሬሳ ቁጣው እንደ አንበሳ ሲታገሥ እንደ እግዜር፣ ሲነሣበትም እንደ ነብር መሆኑን ማሰብ ይኖርብናል። ዝም ሲል የሞተ እንዳይመስለን፤ ሲቆጣም ይቅርታን የማያውቅ እንዳይመስለን። በዚህ በዝምታና በለውጥ መካከል ያሉ ሕዝቦች ለውጥ ሲታከልበት የሚገጥመውን ፈተና በጋራ አይተነዋልና ልተርከው አልሻም።

ተርቦ የከረመ ሰው፣ መጀመሪያ ያገኘውን ዳቦ በተለየ ፍቅርና አድናቆት እንደሚጎርሰው ሁሉ ለውጡን በአንድ ልብ ከጎረስን በኋላ ረሃባችንን አስታግሠን የዳቦው ዓይነት፣ ጣዕም እንደሚፈልግ፣ ቆይቶም ማጣቀሻውን እንደሚመርጥ ረሃብተኛ፤ አሁን ግራና ቀኝ ማማተራችንና መመልከታችን ሰዋዊ

ባሕሪ ነውና። ለጠገበ ሰው የደረቀ ዳቦ ብቻ ሳይሆን ጣፋጭ ከጎኑ ማስቀመጥ ግዴታችን መሆኑን ተገንዝበን ለሕዝባችን የባለፈውን ድል መናገር ብቻ ሳይሆን፤ አዳዲስ ድል በማስመዝገብ ኢትዮጵያውያንን ዳግም እንደምናኮራ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

## ውድ ኢትዮጵያውያን

ለውጡ እንደ ጤዛ ታይተው የሚጠፉ ችግር ፈጣሪዎች ያመጣል። ነገር ግን ዝናቡን ፈርተን ክረምቱን ማስቀረት አይሆንልንም። ዝናቡ አፈር ይወስዳል፣ ያጓራል፣ ይረብሻል። ለውጥ የሚያከብደው ባልተለወጠ ባሕል ሲሆን ነው። ለውጥ የሚያስቸግረው ባልታደሰ ተቋም ሲጀመር ነው። ለውጡን ስንጀምር አዲስ ሐሳብ፣ ለውጡን ስንጀምር የሚያሻግር የመደመር ፍልስፍናን ብናበሥርም ባልተለወጠ ተቋምና ባልተለወጠ ባሕል ነውና መንገራገጩ አይቀሬ ነው።

ለዚህም ሲባል ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታችን አይተኬ ሚና የሚጫወተውን የምርጫ ቦርድ ስናደራጅ፤ ከአንዴም ሁለቴ ታሥራ ለፍትሕ የታገለችውን፤ በጀግንነት ለመላው ኢትዮጵያውያን አርአያ የሆነችውን ብርቱካን ሚደቅሳን ያመጣነው።

የፍትሕ እጦት ኢትዮጵያውያንን እንዳንገሸገሸ ስለምናውቅ እናት፣ እኅት፣ ሚስት ሆና፣ ፍትሕ የሚሸቅጡትን በመለየት፣ በማስተማር ለማንም ዝቅ ሳትል፤ በሕግና ሕግ ብቻ ፍትሕን ለኢትዮጵያ እንድታመጣ ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊን ለፍትሕ ሥርዓት እንዳመጣን አይዘነጋም።

የጸጥታ ተቋሞቻችን ላለፉት ዓመታት በጀግንነት የፈጸሙት ገድል እንደተጠበቀ ሆኖ የሚነሣባቸውን ስሞታዎች ለመቅረፍ በተለየ ትኩረት ከሠራንባቸው የሪፎርም ሥራዎች አንዱ SSR (Security Sector Reform) ላይ በማተኮር መከላከያ፣ ፖሊስንና ደኅንነትን የሚጨምረው ነው።

እንዲሁም የኢትዮጵያ ግማሽ አካል የሆኑና ኢትዮጵያን የሚሸከሙ ሴቶች በዋናው የሥልጣን ጥግ በካቢኔ ግማሽ በግማሽ ሆነው፤ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ

ጊዜ ለአፍሪካና ለመላው አለም አስተማሪ የሆነ ድርጊትም የፈጸምነው በዚሁ ዓመት ነው።

ኢኮኖሚን በሚመለከት በተለያዩ ምክንያቶች በዝርዝር ሳንገልጽላችሁ የቆየን ቢሆንም፤ ዛሬ አንደኛ ዓመታችንን ስናከብር ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በኩራት ላበሥር የምፈልገው፣ ባለፉት ሰባት ወራት ብቻ ወደ ኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት፣ በብድር፣ በርዳታ፣ በሬሚትታንስና በአገልግሎት 13 ቢሊዮን ዶላር ማምጣት ችለናል።

ውድ ኢትዮጵያውያን እንድትገነዘቡ የምፈልገው ባለፉት መቶ ዓመታት በሰባት ወር 13 ቢሊዮን ኢትዮጵያ አምጥታ አታውቅም። ይህን ማድረግ ባንችል ኖሮ የነበርንበት አዘቅት በቀላሉ መሻገር የምንችለው አልነበረም። በርካታ ኤል ሲ. ዎች ተከፍተው የግሉ ሴክተር ከውጪ ሊያስገባ የሚፈልጋቸውን ዕቃዎች በወረፋ ምክንያት የነበረበትን ተግዳሮት ለመፍታት 8 ቢሊዮን ዶላር ገደማ ለግል ሴክተር በዚህ ሰባት ወር ያወጣን መሆኑን በኩራት ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

በዚሁ የኢኮኖሚ ግስጋሴያችን የዕዳ ጫናን ለመቀነስ፣ ተጨማሪ ርዳታን ለማምጣት፣ በጅምር የቀሩ ፕሮጀክቶቻችንን ለመቀጠል፣ በተለይ ስምንተኛ ዓመቱን ዛሬ ያከበረው የሕዳሴው ፕሮጀክት የነበረበትን አደገኛ አደጋ ለመከላከልና ፕሮጀክቱን ለመጨረስ የሚያስችል ቁርጠኛ አመራር እንደሰጠንም በኩራት ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

ኢትዮጵያውያን ሰይፍ ያስፈልገናል። በአማራና በትግራይ ሕዝቦች መካከል ሰይፍ ያስፈልገናል። ያ የሚያስፈልገን ሰይፍ - ሰላም፣ ይቅርታና ፍቅር ነው። በሶማሌና በአፋር ሕዝቦች መካከል እንዲሁ ሰይፍ ያስፈልገናል ፤ ሰላም፣ ይቅርታና ፍቅር። በጌዲዮና በጉጂ ሕዝቦች መካከል ሰይፍ ያስፈልገናል፤ ሰላም ይቅርታና ፍቅር።

## መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች፤

የለመድነውን አንገት የሚቀላውን ሰይፍ ሳይሆን የሰላሙን የይቅርታውንና የፍቅሩን ሰይፍ በመምዘዝ ኢትዮጵያን እንደ ጥንቱ ታላቅ የማድረግ ፕሮጀክት ከየአንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ እንጂ ከአንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ብቻ የማይጠበቅ መሆኑን እንዲሁ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያውያን "አንተ ጤና እንድታድር ጎረቤትህ ጤና ይደር" ይላሉ። ጎረቤት ብቻ ሳይሆን ወንድም የሆነው የኤርትራ ሕዝብ ጥርስና ከንፈር መሆን ሲገባው ላለፉት ሃያ ዓመታት ዓይንና ቅንድብ ሆኖ መቆየቱ የማይዘነጋ ጉዳይ ነው። ለኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን እንደ ጥርስና ከንፈር በደስታ ጊዜ የሚከፈት በር በኀዘን ጊዜ የሚሸፈንና ውስጣዊ ማንነትን የሚገልጽ እንጂ ጎን ለጎን እንደ ዓይንና ቅንድብ ተቀምጦ የማይተያይና የማይነካካ መሆኑ ተገቢ አልነበረም።

ኢትዮጵያውያን ባለፈው ዓመት በርካታ ሰበር ዜናዎች በርካታ ድሎች ማስመዝገባችን መላው አለም በአንድ ድምፅ የመሰከረው ነውና እኔ ያንን በመደጋገም ጊዜያችሁን ላባክን አልፈልግም። ያለፈው ዓመት ወይም ለውጡ በድል ብቻ የታጀበ ግን አይደለም። የሐሳብ ብዙኅነት ባለመዳበሩ ነጭ ወይም ጥቁር፤ ክፉ ወይም ደግ፤ ጥሩ ወይም መጥፎ በሚል ሁለት ጽንፍ የተከፈለው ፖለቲካችን ጠዋት ያሞገሰ እንደሆን ከሰዓት ፈጥፍጦ ይጥላል።

ይህንን ክፉ ባሕል በንግግር በስድብና በፌስቡክ ብቻ ብናበቃው መልካም ነበር። ነገር ግን ወገን ወገኑን እንዲገደል፣ እንዲሰደድ፣ እንዲቸገርም ጭምር አሳፋሪ በሆነ መንገድ ኢትዮጵያውያን ሊያዩት፣ ሊሰሙት፣ የማይፈልጉት ችግር እንዲሁ ተስተናግዷል። ድሉን በጋራ እንዳመጣነው ሽንፈቱንም በጋራ ልንቀበለው ይገባል።

ከሁሉም የከፋው ደግሞ የወረስነው የሤራ ፖለቲካና መጠራጠር ነው። አቅፎ ማለፍ ሳይሆን ጥሎ ማለፍ የለመደው የኢትዮጵያ ፖለቲካ በረባ ባልረባው በሚቆሰቆሱ ነገሮች የራሱን ወገን ማፈናቀል፣ ጅምላ ጥላቻ፣ ስድብ መከፋፋት፣ ተስፋ አስቆራጭ ዜናዎችን መስማት የቅርብ ጊዜ ዜናዎቻችን መሆናቸውን ኢትዮጵያውያን ማስታወስ ይኖርብናል።

ያገሬ ሰው "ባጭር ታጥቆ፤ ጋሻ ነጥቆ፤ ዘገር ነቅንቆ ይዋጋል አጥብቆ" እንደሚለው ታላቅ ሀገር ይዘን ታናሽ እንዳንሆን። ጀግና ሕዝብም ይዘን ሰነፍ እንዳንሆን። በአንድ ማዕድ ማብላትና መብላት ለዓለም ያስተማረ ሕዝብ ጥላቻና ስድድብን፤ መፈናቀልና መገዳደልን እንዴት አበቀልነው? ይህ ነገር ወደ ተረጋጋ ሁኔታ የመጣውን አፍሪካን የሚያስተምር እንዳይሆን ኢትዮጵያውያን በአንክሮ ልንመለከተው ይገባል።

## ውድ ወገኖቼ

ታሪክ አለን፥ የሚያኮራ። የሚነገር፤ የሚዘከር። ነገር ግን በማይታውቅ ጊዜ የተወጋነው ማደንዘዣ እንድናንቀላፋ አድርጎናል። ሌሎች የአፍሪካ ወንድሞቻችን በቀኝ ገዥዎች ያሳብባሉ። እኛ በማን ማሳበብ እንደምንችል አላውቅም። ውድ ኢትዮጵያውያን እንንቃ ልላችሁ ግን እወዳለሁ።

ኢትዮጵያውያን ወላጆች ልጆቻቸው ሙሉ ሰው እስኪሆኑ ድረስ ማስተማር፤ ማሳደግ ወጋቸው ነው። ልጆች ሙሉ ሰው ሲሆኑ ደግሞ ወላጆቻቸውን በተራ መጦርም እንዲሁ ባሕላችን ነው። ዛሬ ግን ኃላፊነት መውሰድ በተሳነው በዚህ ትውልድ የሚፈጠሩ ልጆች ሲያድጉም ሲያረጁም የሚጦሩ እንዳይሆኑና የሚጦር ትውልድ እንዳንፈጥር እንዳንዱ ዜጋ በማስተዋልና በአንክሮ ነገሩን እንዲያስብ እፈልጋለሁ።

ልጆቻችን አብሮነት ዋጋ እንዳለው፤ በጋራ መኖር ክብር እንደሆነ፤ ኢትዮጵያን ያቆየናት በጋራ እንደሆነ የወደፊት ዕጣ ፈንታዋም የልጆቿ መደመርና መሰባሰብ እንደሆነ ደጋግመን መናገርና ማስተማር አለብን። የምንሠራው፣ የምንናገረው ሁሉ ኢትዮጵያችንን ትልቅ የሚያደርግና የሚያኮራ እንዲሆን ከአደራ ጭምር ልለምናችሁ እወዳለሁ።

ዕውቀታችን፣ ሀብታችን፣ ጉልበታችን፣ ጊዜያችን ለኢትዮጵያ ዕድገት እንጂ ኢትዮጵያውያንን ለማፈናቀል እንዳይውል እንዲሁ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። የጀመርነው የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንጭጭ በመሆኑ እንጨቃጨቅ፣ እንነጋገር፣ እንወያይ። ነገር ግን ንግግራችንና ውይይታችንን ከአደባባይ ወደ አዳራሽ እንመልስ። ንግግራችን የኢትዮጵያን ልማት፣ የኢትዮጵያን ዕድገት፤

የኢትዮጵያን አንድነት የሚጎዳ እንዳይሆን። እያለማን እንጨቃጨቅ። አንድ መሆናችንን ጥያቄ ውስጥ ሳናስገባ እንጨቃጨቅ።

መላው የኦሮሞ ሕዝብ፣ የአማራ ሕዝብ፣ የትግራይ ሕዝብ፣ የሶማሌ ሕዝብ፣ የአፋር ሕዝብ፣ የቤኒሻንጉል ሕዝብ፣ የጋምቤላ ሕዝብ፣ የሐረሪ ሕዝብ እንዲገነዘብ የምፈልገው እኔ ዐቢይ እባላለሁ። አሕመድ ካልተጨመረ ግን እኔን መለየት ያስቸግራል። ኦሮሞ ብሎ ኢትዮጵያ ካልተባለ፤ አማራ ብሎ ኢትዮጵያ ካልተባለ፤ ትግራይ ብሎ ኢትዮጵያ ካልተባለ፤ ሶማሌ ብሎ ኢትዮጵያ ካልተባለ ያስቸግራል። ኦሮሞ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ኬንያም ስለ አለ። ትግሬ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ኤርትራም ስለ አለ። አፋር ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ጅቡቲም ስለ አለ ኤርትራም ስለ አለ። የአባታችንን ስም ጥለን ብቻችንን አንታወቅምና ኢትዮጵያ ሁሌም ኩራታችን ትሁን።

## እጅግ የምወዳችሁና የማከብራችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ

ኢትዮጵያ ለማኝ ሀገር መሆኗን ላስታውሳችሁ እወዳለሁ። ድንቅ አርቲስት ፈጥረን እንደሆነ የለማኝ ሀገር አርቲስት መሆኑን መካድ አይችልም። ድንቅ ሳይንቲስት ፈጥረን እንደሆነ የለማኝ ሀገር ሳይንቲስት መሆኑን መካድ አይችልም። ጥበበኞች አሉን፤ ባለ ሀብቶች አሉን፤ ባለ ዕውቀቶች አሉን። ኢትዮጵያ ካልተለወጠች ግን የደኻ ሀገር ባለ ሀብትና ባለ ዕውቀት ስለሚያስብል ኢትዮጵያን ያልቀየረ፤ በግል በዝርፊያም ይሁን በሥራ የመጣ ማንኛውም ሀብት ከንቱ መሆኑን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። እየለመኑ ፉከራ፣ እየለመኑ ቀረርቶ ስለማያዋጣ በሰከነ መንገድ ኢትዮጵያን እያሳደግንና እየቀየርን፣ ከአደባባይ ወደ አዳራሽ የተቀየረውን ውይይትና ንግግር ብናመጣ ለሥልጣኔ፣ ለዕድገት ወደፊት ለምናደርገው ጉዞ እንደሚበጅ በዚሁ አጋጣሚ ላሳስብ እወዳለሁ።

### ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በሙሉ

ኢትዮጵያ ምትክ የሌላት ብቸኛ ሀገራችን ናት። ይህችን ብቸኛ እናት፤ አባቶቻችን እምዬ ብለው ይጠሯት ነበር፡፡ እምዬ ኢትዮጵያን ከሚያፈርስና ከሚያጠፉ፤

ከሚያደኸይና ከሚያቆረቁዝ ተግባር ተቆጥበን፤ በሰከነ፣ በተደመረ፣ በሚያዘልቅና በማያርቅ ኢትዮጳያዊ ማንነት ይህችን ሀገር በጋራ እንድንገነባ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

አንድ ዓመት የመጣንበት ጉዞ እጅግ የሚያስደምም፣ የሚያስደንቅ ባለብዙ ድል እንደሆነ ሁሉ ያሉበት ችግሮችም እንዲሁ ዘርፈ ብዙ ናቸው። በሚቀጥለው አንድ ዓመት ኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንድ አተኩረን ብንሠራ ብዬ ጥሪ ላቀርብላችሁ የምፈልገው፤

የመጀመሪያው በይቅርታ፣ በትዕግሥት ጎንደርና መቀሌ፤ ባሕር ዳርና አዲግራት፣ ፤ ጅግጅጋና አዳማ፤ አሶሳና ጋምቤላ እንደ ወንድማማች በጋራ እየዘመርን፤ በማንግባባበት እየተወያየን፤ ኢትዮጵያዊነትን የምናደምቅበት ዓመት እንዲሆንልን በታላቅ ትኅትና ጥሪዬን አቀርባለሁ።

የጀመርነው ተቋማዊ ለውጥ ሁሉን አሟልቶ፤ መሬት ረግጦ፤ የኢትዮጵያንም ፍላጎት ሊያሟላ ባለመቻሉ መንግሥት ከሁሉ ነገር ቅድሚያ ሰጥቶ የጀመረውን ተቋማዊ ሪፎርም አጠናክሮ ይቀጥላል። ገለልተኛ፣ ነጻ፣ ሁሉን ኢትዮጵያዊ በእኩል ዓይን የሚያገለግሉ ተቋማትን የመገንባት ሥራውን ከሰላም ከይቅርታና ከፍቅር ቀጥሎ ግምት ሰጥተን፣ ጊዜ ሰጥተን የምንሠራው ሥራ እንደሆነ ከወዲሁ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

በኢኮኖሚ መስክ በርካታ የሚሠሩ ሥራዎች ያሉ ቢሆንም፤ በተለይ ቱሪዝምን በሚመለከት በመጪው መስከረም ብሔራዊ ቤተ መንግሥት ለመላው ኢትዮጵያ ከአስደሳች ሥራዎቹ ጋር ክፍት ይደረጋል። እስከዚያኛው መስከረም አዲስ አበባን እንድ ስሟ አበባ ማድረግ በሚለው ፕሮጀክት ቢያንስ አንድ አራተኛውን ጨርሰን ለሕዝብ ይፋ እናደርጋለን።

እነዚህን ሥራዎች ስንሠራ ከየክፍለ ሀገሩ፣ ከየክልሉ፣ ከየከተማው ኢትዮጵያውያን በሀገር ውስጥ ቱሪስትነት እንዲመጡ ነው። ከመላው አፍሪካ አፍሪካውያን ወንድሞቻችን በቱሪስትነት ይመጣሉ። ከሌላውም ዓለም በርካታ ዜጎች ይመጣሉ። ይህ ደግሞ በአዲስ አበባ ውስጥ ለወጣቶች የሥራ ዕድል

ይፈጥራል። ታሪካችንን፣ ማንነታችንንና ባሕላችንን በማወቅ በቱሪስት ሴክተር ከፍተኛ ዕድገት እንደምናመጣ ተስፋ ተጥሏል።

በግብርና ዘርፍ ከሁሉ በላይ በትናንሽና መካከለኛ መስኖ በዚህ ዓመት የጀመርናቸውን ሥራዎችና ጥናቶች አጠናክረን ፍሬያማ ሥራ እንደምንሠራ ከወዲሁ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ሌላው የትኩረት መስክ የማዕድን ዘርፍን ማጎልበትና የውጭ ምንዛሬን ማስገኘት ነው። በመላው የኢትዮጵያውያን ትብብር በሀገራችን በምናረጋግጠው ሰላም ገለልተኛና ጠንካራ ተቋማትን በመፍጠር፤ ባለ ሀብቶችን በብዙ መስክ ውስጥ በማሠማራት ለወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን ከወዲሁ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

የሕግ የበላይነትን በሚመለከት የጀመርነው ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵውያን የሚያስፈልግ መሆኑን በጽኑ የምናምን ቢሆንም የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ፣ የጀመርነውን ለመጨረስ፣ የፍጻሜውን ፍሬ ለመቋደስ ስለሚያግዘን ሁሉም ሕግ የሚያስከብሩና ሕግ የሚተረጉሙ አካላት ዘንድሮ ያሻሻልናቸው ሕጎች እንደ ተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱን ዜጋ ከጥቃት የሚከላከሉና ፍትህሕ በገንዘብ ሳይሆን ከፍርድ ቤት ደጅ ማግኘት የሚያስችሉ ሥራዎችን በጠንካራ መሠረት ላይ የሚጣሉበት ጊዜ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ ብቻ ሳይሆን ባሉበት እንዲጠናከሩም በከፍተኛ ጥረት መንግሥት ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን ይሠራል።

በሚቀጥለው ዓመት፤ በምርጫ ቦርድ ውሳኔ የሚኖረን ምርጫ ፍጹም ነጻ፤ ዲሞክራሲያዊ በመሆን ዳግም ለአፍሪካ አዲስ ትምህርት ለመስጠት አርአያ የምንሆንበት እንደሚሆን የላቀ ተስፋ አለኝ። ኢትዮጵያውያንም በዚያው ስሜት እንዲጠባበቁ ልናገር እፈልጋለሁ። ባለፈው ዓመት ስትጠብቁ፤ ቢሆን ስትሉ፤ የጎደለ ያልተሟላ ካለ ቆሜ ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ትኅትና ኢትዮጵያውያንን ዝቅ ብዬ ይቅርታ መጠየቅ እፈልጋለሁ።

ቁጣችሁ ተግሳፃችሁ ለእኔ ሽልማቴ ነበር። ኢትዮጵያውያን ካልጠበቁ እንደማይቆጡ ስለማውቅ። በእኔ ተስፋ ጥላችሁ ቢያደርግ ብላችሁ ፈቅዳችሁና ወዳችሁ የጎደለ ነገር ካለ በዳተኝነትና በእንዝላልነት ሳይሆን ምናልባት ከዕውቀት ማነስና ከሁኔታዎች አለመመቸት እንጂ ያለኝን ጊዜ ሁሉ በታማኝነት ያገለገልኳችሁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ልገልፅላችሁ እወዳለሁ።

የኛ ሩጫ ሁሉ የሀገራችን ህዝቦች ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፤ እኩል ሆነው በነጻነት የሚኖሩባት ኢትዮጵያን መፍጠር ነው። ኢትዮጵያን ከፍ ማድረግ፣ ትውልዷን ማንቃት፣ ዘመም ያለችውን ሀገሬን ማቅናት እንጂ ከዚያ የተለየ ሸፍጥም፣ ሐሳብም፣ ተግባርም አልነበረኝም።

ይህ ኢትዮጵያን ዘመም ካለችበት ቀጥ የማድረጉ ፕሮጀክት እናቶች ባትጸልዩ፣ ምሁራን ባትጽፉ፣ ወጣቶች ባታበረታቱ፣ አርሶ አደሮች ባትተጉ፣ ዲፕሎማቶች ተግታችሁ ባትሠሩ፣ ወታደሮች ድንበራችሁን ተግታችሁ ባትጠብቁ እንደማይሳካ ዐውቃለሁ። ላደረጋችሁት ሁሉ ፈጣሪ ወሮታውን ይክፈላችሁ። ሁሌም እንደምለው አሁንም ኢትዮጵያ የነበራትን ታሪክ አድሳ፣ ለአፍሪካና ለዓለም ምሳሌ ሆና፣ ፍሬዋን ለአፍሪካውያን በመመገብ አርአያ መሆኗን እንደምትቀጥል በታላቅ ኩራት ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

ዲያስፖራዎች የጀመራችሁት ሀገራችሁን የመርዳት፣ ለሀገራችሁ የመቆም፣ በአንድ አዳራሽና ስታዲየም መሰባሰብ ቀጥሉ። በሁኔታዎች መቀያየር ዐቋማችሁ እንዳይቀያየር ስሜታችሁን ገዝታችሁ፤ ኢትዮጵያን አግዝፋችሁ፤ ተደምረን፣ በውጭና በሀገር ውስጥ ያለን ዜጎች ይህችን ታላቅ ሀገር መልሰን ታላቅ እንድናደርግ በትኅትና እለምናችኋለሁ።

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ህዝቦቿን አብዝቶ ይባርክ አመሰግናለሁ።**


፳፻፲፩
መጋቢት
ከመጋቢት
እስከ መጋቢት

# ከመጋቢት
# እስከ መጋቢት

## ንግግሮች: እንግሊዘኛ


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

መጋቢት
፳፻፲፩
ዓ.ም. ታተመ

# 60th Anniversary of ECA Speech

**May 14, 2018**

As we all know, every anniversary involves a critical and reflective engagement with the past, the present and the future. It is with this sense of purpose that we should reflect a mile stone achieved and ensure we apply lessons learned and design a better Economic Commission for Africa (ECA) together.

It was 60 years ago that His Imperial Majesty Hailesellasie made a strong appeal at the first session of the ECA on December 1958. He recounted the plight of the African continent plunged in paradox; endowed with valuable natural resources yet mired in the senseless poverty, dependent on others to finance its own development and propel transformation.

In his speech, Emperor Hailesellasie urged the support of members states to raise the living standards of people through the promotion and diversification of exports, improved agricultural techniques, establishment of regional common market and the creation of a research hub to inform policy.

Every time I recall these prophetic statements from the Emperor, I ask where we are today on each of the points he raised a long time ago. The answer is simple and straight forward. Each of these issues are as relevant today as they were back then. In some cases, they are even more so today than six decades ago. Food security is far from assured and our regional and continental economic integration programs are far behind where they need to be. I can go on and on, however I am with you today, to not merely recount the past, but to celebrate our collective achievements of which there are many.

Importantly, I am also here to challenge us to learn from history and look into the future by exercising wisdom that comes with maturity.

The Economic Commission for Africa has indeed been at the forefront of cutting-edge policy research, thought leadership and advice since day one. In fact, it has been our very own in-house think tank that helped us champion our continental aspiration with the zeal of a missionary. However, in the spirit of African unity, the ECA did not walk alone. Founded only five years after the ECA, the Organization of the African Union, OAU, has been championing the African cause since the signing of the charter of the organization in 1963. The OAU had met many objectives but at its heart was the liberation of the continent from colonial rule, racism, discrimination and exploitation.

Ethiopia may have celebrated the 122nd anniversary of the victory of the battle of Adwa this year. However, freedom was a long time coming in our continent. It was delayed but unstoppable. African independence leaders helped orchestrate and intensify the struggle to bring freedom to the entire continent throughout the decades. The OAU was spectacular in that regard. Unfortunately, despite expelling our colonial oppressors out of the continent, we started turning increasingly against each other.

We dampened our spirits and conflict became the norm. We even became highly valued customers for weapon manufacturing companies around the world until we learned our lesson at a very high cost.

Slowly, and steadily we started developing homegrown means to prevent and to resolve our conflicts by ourselves. The transformation of the Organization of African Unity into the African Union was a turning point in this respect. Today, the African Union is able and ready to intervene in all sorts of government sponsored abuse of human rights than the OAU could. It also does not recognize a new leader who comes to power through non-constitutional means. With such political accomplishments on its record, the African Union is also now accelerating its impact in economic integration of the continent which was already an objective, identified in the 1963 charter, but deprioritized as internal strife and civil war took precedence.

A recent example of the success witnessed in this regard is the historic signing of the Agreement establishing the African Continental Free Trade Area in Kigali in March of this year, which was signed by 44 African countries. The Protocol on Free Movement of Persons was another

success and signed by more than half the membership. The opening of our skies with a launch of the single African Air Transport market is yet another addition. Equally important the African Union reform process under the able leadership of his excellency Paul Kagame, President of the Republic of Rwanda, and current Chairperson of the AU assembly of Head of States, facilitates economic integration. I applaud the African Union leadership for this hope inspiring initiatives and accomplishments. Needless to say, the ECA has been there with us throughout our efforts to identify our challenges and address them in our own way.

Excellencies, ladies and gentlemen, today our deliberations at this conference are being held under the theme “African Continental Free Trade Area in Physical Space for Job and Economic Diversification.” The theme is timely and considerable value to each of our countries. As policy makers, finance ministers and central bank governors will look to you for leadership. Leadership that will insure trade is not an end in itself, but the means to advance the wellbeing of Africans.

I am sure many of you are aware that here in Ethiopia, we have been engaged in an ambitious program of upgrading our infrastructure, building industrial parks and formulating industrial policy and strategies to support the development of our industry. Our efforts have led to meaningful improvement in foreign direct investment to a significant part because we have established an increasingly more business friendly Ethiopia. Our efforts have also yielded tangible results, as evidenced in the growing share of the industrial sector's contribution to our economy.

With the African Continental Free Trade Agreement in place, and once it enters in to force in particular, I am confident that the opportunities for us to attract more investment will only increase. The continental free trade agreement should be shaped and implemented so as to enable Africa to create opportunities for its citizenry; to spur our industrialization agenda, to ensure inclusive development for all Africans, in particular women and the youth. Together we will grow. Together we will give our young people a stake in the future of our continent; we will harness their energy and creativity for the collective wellbeing.

We need to increasingly engage the private sector in ensuring economic integration and introduce aggressive policies to broaden women's access to economic opportunities. Ethiopia is fully aware of the opportunities that the free trade agreement offers and it is ready to follow Rwanda and Ghana for their pioneering role in the ratification of the agreement. I wish to urge all of you to do so to ensure that it can come into force sooner.

Ladies and gentlemen, imagine the progress we could make if we silenced the guns, empowered our communities and build stronger intuitions. Imagine, if you don't radiate a negative energy. Imagine if we don't invest all our resources to kill each other. Imagine if we love each other as the nations and as Africans and nurture our values to transform our citizens.

What should Africa become by 2030? What about 2063? How can the ECA continue to assist the continent to attain this collective vision? How do we enhance the competitiveness of African industries on the global market? How do you foster south-south and north-south economic cooperation?

Ministers, governors, experts, ladies and gentlemen, we must all employ our talent to build a competitive Africa. The African Continental Free Trade Agreement is in fact an important step that has heralded the establishment of the world's largest free trade area. On this anniversary ECA shall look back with pride and look forward with hope. ECA shall marshal all its resources to support the African Continental Free Trade Agreement. ECA has been with us for 60 years.

I am confident it will be there for the next phase of African development.

I thank you for your attention and I declare the conference is officially opened.

**Thank you very much.**

# FOCAC Address

## September 2, 2018

**Excellency Mr. Xi Jinping, President of the People's Republic of China;**
**Excellency Mr. Cyril Ramphosa, President of the Republic of South Africa and Co-Chair of FOCAC;**
**Excellency Mr. Paul Kagame, President of the Republic of Rwanda and Chairperson of the African Union;**
**Excellencies Heads of States and Government;**
**Distinguished Guests;**
**Ladies and gentlemen;**

It is a great honor for me to join this extraordinary gathering of FOCAC 2018 here in Beijing. At the outset, allow me Excellencies, to express my profound appreciation for the excellent hospitality extended to us since our arrival to this beautiful city of Beijing.

I would like to thank the Government of the People's Republic of China for organizing this 7th Summit which will further solidify China-Africa partnership.

**Excellencies,**

Africa is a continent of dynamic development. The continent that was once coldly dismissed as "hopeless" is now being widely applauded for its rising socio-economic progresses. In this regard, East Africa, for instance, is registering a significant stride on the economic front with a 5-9% GDP growth in 2017. This trend is projected to continue, owing to abundant trainable workforce and the growing middle-income population in the region making it a hotspot for foreign direct investment.

Africa's youthful population is the very foundation of the new trajectory that will assure a bright future for our continent. Sixty percent of the African population is under the age of 25 which promises the continent an unprecedented demographic dividend.

Through our continental organization, we are actively exploring a path of development suited to our conditions and accelerating Africa's integration process. In this developmental journey, China has continued to play a critical role and remains a key partner for growth and prosperity across the developing world. We consider China as a successful economic model and a key ally in shared and equitable global development and prosperity. Indeed, China has continued to deliver on its responsibility as an emerging global power – as a custodian of the global shared future, shared aspiration and shared growth.

Over the years, we have registered significant achievements in social, economic and political fields by forming a lasting Sino-Africa partnership. This year's Forum on China-Africa Cooperation (FOCAC) gives us the opportunity to reflect on our performance to date and bring our collective experience to bear on shaping the future of cooperation between China and Africa.

Under the framework of FOCAC and the One Belt and One Road Initiative, China has been our steadfast ally in

the effort to build an economically advanced and socially inclusive Africa. It plays a pivotal role in enhancing connectivity, infrastructural development, industrialization and modernization of agriculture in the African continent.

As African leaders, we are striving towards meeting the Sustainable Development Goals as well as our continent's own Agenda 2063. The strong partnership and cooperation we have forged with China is aligned with and critical for the achievement of these goals of growth and sustainable development. Indeed, the FOCAC and the One Belt and One Road Initiative will continue to be the cornerstones of our relation with China and we are fully committed to the worthy goals set forth in these initiatives.

**Your Excellencies,**

Ethiopia's relations with China remain a critical aspect of our foreign policy and we continue to cherish our partnership based on mutual benefit and win-win cooperation. Over the last decade, Ethiopia envisioned

to realize a structural transformation of the economy and sought to advance industrialization as a crucial pillar of its development policy. With the aim of making the country a leading manufacturing hub, Ethiopia has carried out a series of policy and institutional measures with a view to facilitating the move towards rapid industrial growth and development. Ethiopia has registered significant progress in this regard and is one of the fastest growing economies in the world. China has been a very important strategic partner in this story of Ethiopia's drive toward economic transformation.

**Your Excellencies,**

This Summit will be pivotal to further strengthen ties between China and Africa as all countries work towards setting new goals through mutual consultation and consensus.

Our continent would like to see increased cooperation with China to lift our citizens out of poverty, create more and better jobs, and transform the economy and society as a whole. I am confident that FOCAC will play a critical role in this endeavor.

Let me, at this juncture, express the government of Ethiopia's satisfaction with the implementation of the outcomes of the Johannesburg FOCAC Summit. We would like to commend the relentless efforts and commitments demonstrated to implement them. We are confident that the initiatives we will launch at this Summit will similarly push our countries to new development frontiers.

**Excellency President Xi Jinping,**

Finally, I would like to personally express my appreciation to you for your dedication to realize Africa's transformation and to further strengthen your country's relationship with Africa. I would also like to reaffirm my country's determination to deepen and sustain the cooperation between China and Ethiopia and with Africa at large. In this vein, my administration will work tirelessly to further expand our partnership and broaden our engagement.

**Let me end here by wishing us fruitful deliberations.**

**Thank you.**

# 33rd IGAD Opening Summit

**September 12, 2018**

**Excellencies, Heads of States and Government,**
**Excellency Chairperson of the of**
**African Union Commission,**
**Distinguished guests,**
**Ladies and gentlemen,**
**All protocols observed!**

It gives me an immense pleasure and honor to welcome you all to this Extraordinary Summit of the IGAD. We Ethiopians welcomed our new year yesterday and I would like to say to you Happy Ethiopian New Year.

The 33rd Extra-Ordinary Session of the IGAD Assembly of Heads of State and Government comes at a time when

we are celebrating region-wide, grandiose achievements of peace and reconciliation. It comes at a historic time when each one of us has started believing that our region can in fact be a paradise of blossoms through the aggregated efforts of all of us. Our gathering here today is a bearer of light to the opportunity we have, to lay the groundwork for a prosperous and harmonious path for generations to come.

One among the positive developments in our region has been the reconciliation process in South Sudan. As leaders of the region, the efforts that all of you have exerted in the process have been highly remarkable. Your perseverance and devotion to the cause of the people of South Sudan as well as your boundless resolve to seek a lasting solution to the prolonged conflict in South Sudan deserves sincere gratitude and earnest appreciation.

**Excellencies,**

It would be remiss of our efforts in bringing about lasting peace in South Sudan if I do not mention the leadership role and wisdom of H. E. President Omar

Hassan Al-Bashir in assisting the South Sudan parties to iron out their differences; and decide to sign the Peace Agreement.

It is a source of satisfaction for us all that we are witnessing IGAD's continued track record of bringing about tangible results, as the South Sudan case demonstrates. We can confidently claim that IGAD is living up to its objectives, for its prime reason of existence has been to coordinate and expedite our efforts towards regional integration and the realization of a sustainable development which would benefit the entire peoples of our region.

Indeed, IGAD's support to the aspirations of the people of South Sudan for peace and their yearning for inclusive democracy is unwavering. Words fail me to suitably express my sense of happiness as we will witness the signing of the Revised Agreement of the Resolution of the Conflict in South Sudan. The eyes of the world are upon us as the South Sudan leaders commit today to a path for reconciliation and lasting peace in their country

This indeed is a major milestone and a great stride toward building lasting peace. As we witness this historic milestone, we remember and grieve for the victims of violence, and hope this agreement closes that dark chapter in South Sudan.

By signing this agreement, South Sudan leaders exercise leadership and demonstrate courage to bring a peaceful resolution of the conflict that has been unraveling for so long. Nonetheless, a mere signing of this agreement will not solve the problem for the agreement is not self-executing. Lasting peace requires the commitment of every one of us to work in earnest for a more peaceful, democratic and unified South Sudan. The leaders of South Sudan can count on the full support of IGAD nations in their effort to fully observe the spirit and letters of this agreement.

Even while so committed for a sustainable peace, bear in mind that differences will abound. Maturity and leadership will be tested on how you handle any such differences. We should not always fall back into conflict and war for every disagreement that ensues among the political leaders.

However strong your differences, you must not allow a single drop of blood to be spilled and lives to be lost due to your inability to compromise. It matters not how polarizing the point of departure might be. In times like these, all parties must show commitment to dialogue and take immediate steps to ensure calm and restore trust.

Building resilient institutions that can handle any such differences in the most impartial and independent manner should be given the ultimate focus by South Sudan and of IGAD members. Only then that we can avoid repeating the failures of past agreements.

Coming on the heels of the Ethio-Eritrea peace deal, this agreement demonstrates Africans ability to overcome their own conflicts and secure the blessings of peace. A pattern for an African solution to an African problem is, therefore, emerging.

**Excellencies,**

A new era of peace, friendship, mutual trust and hope is indeed heralding in our region. As you all know, the state of war between Ethiopia and Eritrea has come to an end.

And peace is proving its contagious power as its spirit is fast spreading in the region. The Tripartite Declaration among Ethiopia, Eritrea and Somalia is such a testament as it seeks to foster comprehensive cooperation on a range of issues. The strong expression of will by leaders of Djibouti and Eritrea to resolve their differences peacefully adds another layer of hope for the consolidation of peace in our region.

We have seen significant development toward peace between Djibouti and Eritrea and the betterment of the relations between Eritrea and Sudan. Ethiopia is working actively to address these conflicts. This stems from our firm understanding of the fact that the lives of communities in our region are intertwined by a shared interest and blood; and are destined for a common fate.

As part of this development, Eritrea has decided to rejoin the IGAD family of nations.

Allow me, Your Excellencies, to seize this opportunity to urge all our Member States to welcome back the State of Eritrea as it rejoins IGAD.

As members of the IGAD family, we should work in earnest towards integrating our economies. Through economic integration, we can help address the most pressing task we face in the region: creating job opportunities for the millions of youth. To this end, we should address the infrastructural barriers and harmonize our trade rules to promote trade and investment among our nations. We have so much that we have to work for. We should always recognize that we have so much in common than that which divides us.

**Excellencies,**

Finally, let me use this opportunity to express our profound gratitude to the outgoing Chairperson of the Joint Monitoring and Evaluation Commission, H.E. Festus Mogae, for his selfless commitment and continued contribution to the efforts in the peace process of South Sudan.

**Thank You!**

# World Economic Forum Speech

**January 23, 2019**

**Dear Friends,**
**Ladies and Gentlemen,**

Thank you for the warm welcome in this cold winter. I am honored to be with you for the first time in Davos. And I am most grateful for the opportunity to share with you Ethiopia's renewed vision and sustained commitment to positive reforms.

Ethiopia is today among the fastest growing economies in the world, consistently averaging over 9 percent growth in the last decade. Ethiopia's GDP has multiplied tenfold in 25 years.

Poverty has been halved and education enrollment has markedly increased. Significant investment in infrastructure has contributed to the growth and attracted FDI, making Ethiopia one of the leading FDI destinations in Africa. These are tremendous successes and reflect the real commitment of our government and our people to development and progress. Our challenges, however, remain formidable.

To reinforce our upward trajectory and achieve even more rapid and sustainable growth, Ethiopia has embarked on a comprehensive reform process since last April which cuts across politics, economics, and society. We aim to establish a virtuous cycle between these elements, and amongst our partners to enable us to meet our challenges in a mutually profitable manner.

**Ladies and Gentlemen,**

Allow me to explain this virtuous path of reform. Our reform is deeply rooted in the philosophy of Medemer, an Amharic word for “coming together” or “Synergy”. Medemer is a holistic reform to organic change and is building on the gains of the past while reminding us of our rich heritage.

It also reflects on modern realities strengthening the synergy in politics, economics, technology, and society. Ethiopia is indeed undergoing a period of political and economic renaissance.

**The Medemer reform is people-centered and has three interdependent pillars:**

**The first pillar is a vibrant democracy;**
**The second one is economic vitality and;**
**The third pillar is regional integration and openness to the world.**

Today, we meet at a time of great opportunity for Ethiopia and for you. In the spirit of partnership, please allow me to briefly address each of these aspects.

On the political front, we are working tirelessly to fulfill the constitutional promise of building a democratic and pluralistic political order based on our first pillar, a vibrant democracy. Guided by this principle, we have acted quickly and decisively. In the past 9 months alone, we have released all political prisoners — in the thousands.

We have also invited individuals and groups based abroad to return home and join us in a spirit of positive-sum, not zero-sum, politics. We have restored licenses to independent media, issued an amnesty law, and repealed restrictive laws of the past. We will also have a revised civil society law very soon.

We believe it is not possible to sustain growth, attract investment and allow all Ethiopians to benefit from the growth dividend without embracing democracy and persuading the world to invest in our economy. In sum, we see democracy and development as inter-linked, and we have acted decisively on this understanding.

**Ladies and Gentlemen, Friends,**

The second pillar of our reform is economic vitality. We are determined to bring Ethiopia firmly into the center of the international market. To do so, we will leverage the collective power of our people, especially women and youth, and build the private sector to drive more inclusive and socially sustainable growth.

We cannot hope to progress as a nation and as an economy if we disqualify half of our population from full and equal participation. Women are now occupying key government positions including the Ministry of Defense, Ministry of Trade, Ministry of Transport, and the newly established Ministry of Peace. We have achieved gender parity in our Cabinet. We now have the first woman as President of the Federal Supreme Court. And, recently, our parliament has elected the first woman Head of State in modern Ethiopia.

This is important progress, but it is not enough. Ethiopia is a large market of over 100 million people, of which 60 million are under the age of 24.

With half a million school leavers annually, our core objective is to sustain fast-paced economic growth and to create both more and better jobs. We must create the conditions to enable a demographic dividend and to harness the potential of our young and energetic population. To do so, we have to invest in the aspirations of our youth by improving educational standards and create fresh opportunities through careful planning and strategic repositioning.

This requires unleashing the potential of the private sector. Here are four steps that we are taking to make this not mere rhetoric, but a firm reality:

First, we will make it easier for small and medium size enterprises (SMEs) to grow and flourish, since they are the engine room of our economy. We are reprioritizing access to credit for SMEs since two-thirds of our SMEs report not having access to finance.

Second, we will ease and mainstream regulations needed to start a business and provide a better policy environment. We will make it easier to do business for everyone who wishes to invest in our country. Ethiopia is undergoing significant institutional reforms and is reviewing its investment code, commercial code, and other business regulations to enhance the ease of doing business in Ethiopia and increase our global competitiveness.

Third, we will make the private sector an integral part of our economy, as it should be. Ethiopia is committed to reforming its state-owned enterprises and crowding in more private capital. We are committed to opening up the economy to international investors in telecoms,

logistics, energy, aviation, railways, and industrial parks. This has the added benefit of creating the space to reallocate government expenditure to social services. We are confident that international capital and expertise will deliver significant value for Ethiopians, and contribute to our development agenda.

Fourth, we will continue to foster Public-Private Partnerships as we see this as more than merely a business proposition, and a deal to be struck. We see it as the way to build balanced long-term partnerships aimed at triggering faster economic growth and profit. At the same time, we will ensure our citizens realize their full potential and live a prosperous, healthy and safe life.

We, therefore, look to the next generation of PPPs to be more balanced in delivering growth and yield, and representing a fresh way to contemplate the relationship between business and government and offering a shared formula for social and economic growth and inclusiveness.

**Ladies and Gentlemen,**

The third and final pillar of our renaissance is regional integration and openness to the world. Regional integration and trade will be crucial to the future of our continent, allowing us to grow beyond primary commodities and accelerate our development. Addis Ababa is the seat of the African Union and so must lead by example. Our determination explains our active engagement in discussions on the African Continental Free Trade Area and our sense of urgency to finalize Ethiopia's accession to the World Trade Organization.

History has demonstrated time and again that neighbors with intimate, rules-based, and diverse trade and economic relations are unlikely to resort to conflict. That is why we believe integration must be viewed not just as an economic project but also as crucial to securing peace and reconciliation in the Horn of Africa. The adage from our ancestors is: "If you want to go fast, go alone; but if you want to go far, go together." In this spirit, Ethiopia has ended two decades of military stalemate with Eritrea and is enhancing co-operation with neighboring countries and re-configuring the geopolitics in our region.

Ethiopia believes that an Africa at peace with itself can counteract the chaotic push of mass migration. As such, Ethiopia aims to increase the influx of smart capital into the African continent. There is a strong case to be made for investing in our continent. Even the most conservative asset allocation of an investment portfolio should prudently consider this option. If just 2% of the $40 trillion in Organization for Economic Cooperation and Development (OECD) pension assets were invested into Africa over the coming five years, it would exceed the total foreign direction investement that we've seen in the last five years by more than three times. For investors considering the record of return, this offers higher-than-average rewards and diversification of risk; for Ethiopia, it would catalyze transformation.

To realize this great opportunity, we appreciate the fundamental need to de-risk our politics and economics, which would reduce the premium sought by prospective investors. Part of that process is to build trust and confidence and to lead by example. I believe that our record over the last year shows this to be so.

**Dear Friends,**

Let me conclude. Ethiopia has embraced a great vision and embarked on bold reforms. Improving the political environment and the business climate is our priority. Building an open society and a vibrant economy is our shared aspiration and our proposition to you. But we must all act fast.

Our record over the last nine months should illustrate our resolve. This is an agenda for action; a blueprint for a model of virtuous and sustainable growth.

Looking at what we have accomplished in less than a year, I am optimistic and excited about the opportunities that are ahead. Ethiopians are born runners and we excel in marathons. Take it as a signal of our intentions and level of commitment and stamina.

Now is our time. Rating agencies forecast – and I quote – that "growth will average 8% over 2018-2021, making Ethiopia the fastest-growing of the sovereigns we rate".

I say to you: Carpe diem, yes, seize the day – but also trust in the future. Come and see what we have to offer, and invest in our potential. Whether you are an entrepreneur, a CEO, an industrialist, or just a lover of nature or history, or beauty, Ethiopia has something for you.

**I thank you.**

# 32nd AU Summit Dinner Speech

**February 9, 2019**

**Your Excellency Mr. Paul Kagame, President of the Republic of Rwanda and Chairperson of the African Union;**
**Your Excellencies Heads of State and Government;**
**Your Excellencies African First Ladies;**
**Your Excellency Mr. Moussa Faki Mahamat, Chairperson of the African Union Commission;**
**Distinguished Guests;**
**Ladies and Gentlemen;**

I would like to warmly welcome you all to our gem, Addis Ababa - a grateful host of the African Union, and also thank you for gracing us with your presence tonight. This special evening is the first of its kind in that it brings together African leaders, cultural

icons and the Ethiopian community in such a celebratory setting. Intended to honor our togetherness, which is reflected in our collective past, present, and future, this gathering also embodies the spirit of our ever-growing Pan-African zeal.

Tonight, we also celebrate a great statesman who made a monumental contribution to the liberation of Africa and the establishment of the Organization of African Unity: the late Emperor Haile Selassie.
There is no need to remind those of you in this room, the glowing contribution of Emperor Haile Selassie. Articulated clearly in his majesty's acceptance speech as the First Chairperson of the Organization of African Unity in 1963, he had at the time shared that, "An awareness of our past is essential to the establishment of our personality and our identity as Africans."

Our gathering today, therefore, also recognizes our past, celebrates the commendable work of those who came before us, and inspires our efforts to build on their successes. I would like to take this opportunity to thank the African Union for recognizing Emperor Haile Selassie's efforts in the liberation struggle and in fostering Pan Africanism.

As we reflect on those that came before us and their victories for Africa, it is my hope that through this occasion we honor and soberly recommit to the path that has been paved by our Founding Fathers and Mothers.

This evening is also a reminder that it is incumbent upon us to roll up our sleeves and continue the work begun by our predecessors, so we can realize Agenda 2063 for those who will come after us.

ለረጅም ዘመናት በተናጠል ለመፍጠር ያልቻልናቸው ስኬቶችና ያልደረስንባቸው ከፍታዎች ላይ ለመድረስ በፍቅር ተደምረን፣ እንደ ጉልበትና ካፒታል ሁሉ የሁሉንም ዜጎች ሐሳብና ዕውቀት አሰባስበን በመጠቀም ድል እናድርገው።

አዲስ ዓመት፣ አዲስ ምዕራፍ የሚጀመርበት እንደመሆኑ መጠን ከተስፋ የሚሻገር ተጨባጭ ለውጥ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ለመፍጠር የጋራ መግባባት እንዲኖረን፣ ከራሳችን ጋር እንድንታረቅ ያስፈልጋል፡፡ ዓመቱ አሮጌውን አውልቀን አዲሱን እኛነታችንን የምንላበስበት፤ ከሥርዓት አልበኝነት ወደ ሕግ የበላይነት የምንሸጋገርበት፤ ከደቦ ፍርድ ወደ ገለልተኛና ሁሉን በፍትሐዊነት ወደሚያስተናግድ ፍርድ የምንሻገርበት፤ ተጠየቅን ባህሉ ያደረገ ማኅበረሰብ ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ የምንጥልበት ዓመት ይሆናል፡፡ ከሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርና የጥቁር ገበያ፣ ወደ ዘመናዊና ግልጽ የባንክ አገልግሎት የምንመጣበት፤ በዕውቀታችን፣በወዛችን፣ በትጋታችን ኃጢአት የሌለበት ገቢ ለማግኘት የምንወስንበት፤ ሌብነትና ሙስናን ፍጹም የማንታገሥበት መልካም ዓመት ይሆናል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ጎራ ለይተው አንዳቸው ሌላቸውን የሚኮንኑበት ዘመን አብቅቶ ግንባር ፈጥረው ለተሻለ ሥርዓት እና ለጠራ የፖለቲካና ኢኮኖሚ አስተሳሰብ የሚተጉበት፤አክቲቪስቶችና የነጻነት ታጋዮች ለሀገራዊ የጠራ ግንዛቤ የሚባትሉበት፤ምሁራን ከጥግ ወደ መካከል ዘልቀው አስተሳሰብና ዕውቀታቸውን የሚያጋሩበት ዘመን ይሆናል፡፡

ጋዜጠኞች፣ አራተኛ መንግሥትነታቸውን በእውነት የሚያስመሰክሩበት፤ እውነትን ፈልቅቆ በሚያወጣው የምርመራ ሞያቸው አማካኝነት ሌብነትን፣ ሕገ ወጥነትንና ብልሹ አሠራሮችን ሁሉ የሚታገሉበት ዓመት ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በአዲስ ዓመት ለውጦቻችንን ተቋማዊና ዘላቂ እንድናደርጋቸው ይጠበቃል፡፡ ኢትዮጵያ የአንድ ሰሞን ሆይ ሆይታን፣ የጥቂት ግለሰቦችን ለውጥ የምትሻበት ወቅት ላይ አይደለችም፡፡ እናት ሀገራችን፣ ግለሰቦች ሲከፉ የሚከፋት፣ ግለሰቦች ቅን ሲሆኑ የሚቀናት ዘመን እንዲያበቃ ሁሉም ሰው በየተሰማራበት ሞያው ለዘላቂ ቁምነገር የሚተጋበት ዓመት እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ከታች እስከ ላይ የምንገኝ የሕዝብ አገልጋዮች በመጭው ዓመት ወደ ቢሮዎቻችን ስንገባ በተለወጠ የአገልጋይነት ስሜት መሆን አለበት፡፡ አዲስ ዘመን አዳዲስ ዕድሎችንና አዳዲስ ፈተናዎችን ይዞ ይመጣል፡፡ አዳዲስ ዕድሎችን የሚጠቀም አዳዲስ ፈተናዎችንም የሚፈታ አዲስ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ሁላችንም ቀና ልብ፣መልካም አእምሮ እና የፈረጠመ ወኔ ልናበረክት ያሻናል፡፡

## ውድ ወገኖቼ!

አዲስ ዓመት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን አሮጌው ዘመን በአዲስ ዘመን የሚተካበት ተራ የቁጥር ጨዋታ ከመሆን በላይ በዙሪያችን ያለው ተፈጥሮና የሕይወት ዑደትም የሚለወጥበት ወቅት ነው። በዝናብና ብርድ ተሸፍኖ የነበረው ክረምት ብርሃን በሞላው መስከረምና የጸደይ ወቅት ይተካል። በወንዙ፣ በባሕሩና ሐይቁ የነበረው ውኃም ይጠራል። መስኩ በልምላሜ ላይ አደይ አበባን ጨምሮ ያጌጣል። የጅራፉን ጩኸት እና የቡሄ ጭፈራውን ተከትሎ፣ የኀመን ምንቸት ውጣ የሥጋ ምንቸት ግባን ተከትሎ ዕንቁጣጣሽ፣ አበባየሆሽ እንኳን ደኅና መጣሽ፤ በሚል ዜማ መሞላቱ በዚህ የተነሣ ነው።
አሮጌውን ዓመት ሸኝተን ወደ አዲሱ ዓመት በምንሸጋገርበት በዚህች የዋዜማ ሰዓት ከየትኛውም የቅርብ ዘመን ሽግግር በላቀ ደረጃ ባፈረስነው የልዩነት ግንብና በገነባነው መሸጋገሪያ ድልድይ የተነሣ በሕዝባችን ልብ ውስጥ መልካም የተስፋ ስንቅ ማኖር በመቻሉ አያሌ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ዜጎቻችን በዓሉን አብረውን ሊያከብሩ ከጎናችን ተሰልፈዋል። በቀጣይም በበዓል ብቻ ሳይሆን

በሰላምና ዴሞክራሲ ግንባታ፣ በልማትም ጭምር ከጎናችን እንደሚቆሙ እንተማመናለን። በጋራም ለድል እንበቃለን፡፡
በተጨማሪም ከታሪካዊቷ የሰሜን ጎረቤታችን ሀገር ኤርትራ ጋር ከ ሃያ ዓመታት በኋላ በፈጠርነው ዕርቀ ሰላም የተነሣ ከሃያ ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ዕንቁጣጣሽ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሀገረ ኤርትራ ምድርም የሚከበር መሆኑ የአዲሱን ዓመት ክብርና ደስታ ድርብ ድርብርብ ያደርገዋል።
በመጨረሻም አዲሱ ዓመት እንደ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሁሉ፣ እንደ ኤርትራና ኤርትራውያን ሁሉ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን በሚወዱ ሁሉም የአፍሪካ ሀገራትና የተቀረው የዓለም ሕዝቦች ልብ ውስጥ የተስፋ ብርሃኑን ይፈነጥቅ ዘንድ እየተመኘሁ፤ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የጤናና የብልጽግና ይሆንላችሁ ዘንድ ልባዊ ምኞቴን በመግለጽ እሰናበታለሁ።

**በድጋሚ እንኳን ለ 2011 ዓ.ም. አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን!!**

**ኢትዮጵያ፣ በልጆቿ ጥረት**
**ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ**
**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የተላለፈ መልዕክት

**ጥቅምት 3/2011 ዓ.ም.**

የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅ ተማሪዎች ማለት የአንዲት ሀገር «ነገዎች» ናቸው፡፡ የአንዲት ሀገር መጻኢ ዕድል በዋነኝነት የሚወሰነው ያችን ሀገር ለመረከብ እየተዘጋጀ ባለው ትውልድ ማንነት ነው፡፡ ሀገር በዋናነት የምትገነባው በዕውቀትና በክሂሎት በመሆኑ ዕውቀት ለመገብየትና ክሂሎት ለመጨበጥ በየትምህርት መስኩ የተሠማሩት ወጣቶች ማንነት የነገዋን ኢትዮጵያ ማንነት ይወስነዋል፡፡

የተማረ ሰው ማለት ዕውቀት የሰበሰበ ሰው ማለት ብቻ አይደለም፡፡
የተማረ ሰው ማለት እንዴትና ምን መማር እንዳለበት የሚያውቅ ነው፡፡
የተማረ ሰው ማለት ነጻ ሆኖ ማሰብ የሚችል ነው፡፡
የተማረ ሰው ማለት ለነገሮች ትክክለኛ ብያኔ መስጠት የሚችል ነው፡፡
የተማረ ሰው ማለት የሚጠበቅበትን ለመሥራት ራሱን በራሱ የሚቀሰቅስ ነው፡፡
የተማረ ሰው ማለት ተንትኖ (Analitical)ና አንጥሮ (Critical) ማሰብ የሚችል ነው፡፡
ከጠቅላላው ወደ ነጠላው (Deductively)ና ከነጠላው ወደ ጠቅላላው (Inductively) በመሄድ ለማሰብ የሚችል ሰው ነው፡፡

የተማረ ሰው ማለት ከሌሎች ጋር ሲኖር የሚገጥመውን ግጭት በሠለጠነና ለሁሉም በሚጠቅም መልኩ ለመፍታት የሚችል ነው፡፡ ችግሮችን በመጠናቸው ልክ የሚረዳና መፍትሔ ለማፍለቅ የሚችል ነው፡፡ የራሱን ስሜትና ጠባይ እንዴት ማስተዳደር እንደሚችል የሚያውቅ ነው፡፡ የሥራና የኑሮ ሥነ ምግባር ያለው ነው፡፡ ጾታ፣ ጎሳ፣ ሃይማኖት፣ ቀለምና ዕድሜ ሳይለይ ለሰው ዘር ሁሉ እኩል አመለካከት ያለው ነው፡፡ ከለውጥ ጋር እንዴት መሄድ እንዳለበት የሚረዳ ነው፡፡ ለኪነ ጥበብ፣ ለሥነ ጥበብ፣ ፍቅር ያለው ነው፡፡ የማያውቃቸውን ባህሎች፣ ቋንቋዎችና አካባቢዎች ለማወቅ ጉጉትና ጥረት ያለው ነው፡፡

እነዚህ ሐሳቦች በዓለም ላይ ትምህርትን በሚመለከት የሚያጠኑ ሊቃውንት የተማረን ሰው ለመበየን ከሚያነሷቸው ሃምሳ መመዘኛዎች መካከል የሚገኙ ናቸው፡፡ እናንተ የኛ «ነገዎች» በእነዚህ መመዘኛዎች ራሳችሁን እንደምትለኩ እተማመናለሁ፡፡ እየተዘጋጃችሁ ያላችሁት ተምራችሁ ሥራ ለማግኘት ብቻ አይደለም፡፡ የሚጠበቅባችሁ ከዚህም በላይ ነው፡፡ የምትማሩት ሀገርን እንድትረከቡ ነው፡፡ የምትማሩት የዚህችን ሀገር ነገ እንድታሳምሩላት ነው፡፡ እናንተ የዚህች ሀገር ነገዎች ናችሁና፡፡

የኮሌጅ ግቢዎቻችሁን ለነገው ሐላፊነት የመዘጋጃ ቦታዎች አድርጓቸው፡፡አብያተ መጻሕፍቱ ዋና ማዕከሎቻችሁ ይሁኑ፡፡ በርትታችሁ አንብቡ፡፡ የምትማሩትን የትምህርት ዘርፍ ብቻ አይደለም፡፡ሁለገብ ዕውቀት እንዲኖራችሁና ሁለገብ የሆኑ የሀገራችሁን ችግሮች መፍታት እንድትችሉ እንደ ንቧ ከየዓይነቱ ቅሰሙ፡፡ አንዲት ሀገር የማያነቡ ግን የተማሩ (Literally Illiterate) ሰዎች በብዛት የሚገኙባት ከሆነች ትጎዳለች፡፡ ሌላው ቀርቶ ሕግና መመሪያ አንብቦና ዐውቆ የሚሠራ ሠራተኛ ልታጣት ችላለች፡፡

ያላችሁበት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ትንሿ ኢትዮጵያ ናት፡፡ ከልዩ ልዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የመጡ ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ በእምነት፣ በባህል፣ በቋንቋና በታሪክ ከማትገናኙት ሰው ጋር በአንድ ግቢ ውስጥ ልትመደቡ ትችላላችሁ፡፡ ይህ ግን ነገን ለሚረከብ ትውልድ በሚሊዮን ብር የማይገኝ ዕድል ነው፡፡ የተማረ ሰው አንዱ መለኪያ ከሌሎቹ ጋር እንዴት መኖር እንደሚችል ዘዴና ብልሃት መያዝ ነውና፡፡

ዛሬ ከገዛ ወገናችሁ ጋር በሰላም፣ በፍቅር፣ በመከባበርና በመተማመን በአንድ ግቢ ውስጥ ለመኖር ከአቃታችሁ የውጭ የትምህርት ዕድል አግኝታችሁ ስትሄዱ ፈጽሞ በባህልም ሆነ በታሪክ ከማታውቋቸው ተማሪዎች ጋር እንዴት ነው አብራችሁ የምትማሩት? በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የምትማሩት እናንተ ራሳችሁን ማዘጋጀት ያለባችሁ በመላው ዓለም በሚገኙ ቦታዎች ለመሥራት እንድትችሉ ነው፡፡ ፉክክሩ ከወገናችሁ ጋር አይደለም፤ ከዓለም ጋር ነው፡፡ ከዓለም ጋር ለመኖር ደግሞ መነሻው ከገዛ ወገን ጋር ለመኖር መቻል ነው፡፡ ከልዩ ልዩ አካባቢ ከመጡ ወገኖቻችሁ ጋር በሰላምና በሠለጠነ መንገድ እንዳትኖሩ የሚያደርጓችሁ ሰዎች የነገውን ዓለም አቀፋዊ ጉዞአችሁን እያሰናከሉባችሁ ነው፡፡

ዛሬ በኮሌጅ ግቢ ውስጥ ከልዩ ልዩ የሀገራችሁ ልጆች ጋር እንዴት አብራችሁ መኖር እንደምትችሉ ካወቃችሁ ነገ ይህችን የብዙ ማኅበረሰቦች ሀገር ማስተዳደር ለእናንተ ቀላል ይሆናል፡፡ ዕድሉን ተጠቀሙበት፡፡ የማታውቁትን ቋንቋ ለማወቅ፣ ሰምታችሁ የማታውቁትን ታሪክ ለመስማት፣ ያልለመዳችሁትን ምግብ ለመልመድ፣ አዳዲስ አካባቢዎችን ለመጎብኘት፣ ከአዳዲስ ባህሎች ጋር ለመኖር፣ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችሁ ጋር ለመተዋወቅና ለመዛመድ ይህንን ዕድል ተጠቀሙበት፡፡ ከምታውቁትና ከለመዳችሁት ማኅበረሰብ ውጭ ሌላ ወዳጅ አፍሩ፡፡ የቡድን ሥራዎች ሲሰጧችሁ ከማትቀርቡት ሰው ጋር ለመቀራረብና አዲስ ነገር ለመማር ተጠቀሙበት፡፡

የባህል፣ የቋንቋ፣ የአመለካከትና የእምነት ልዩነቶች እንዴት ለአንዲት ሀገር እንደሚጠቅሙ እናንተ ካላሳያችሁ ታድያ ከማን እንጠብቃለን? ክርክሮችና ወይይቶችን ልመዱ፡፡ ነገኮ የምረጡኝ ዘመቻ የምታደርጉ የዚህች ሀገር መሪዎች ናችሁ፡፡ የሠለጠነ የውይይትና የክርክር ሥርዓት መመንጨት ያለበት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ነው፡፡ በመረጃና በማስረጃ ማመን፣በተጠየቅና በፍሬ ነገር መወያትና መከራከር ለሕዝባችን ባህሉ እንዲሆን እናንተ ካልሠራችሁ ሌላ ማን ይሠራል? የተማረ ሰው ሁለገብ ነው ብለናል፡፡ ሁለገብ ሰው የሚወደውን ነገር ብቻ ሳይሆን የማይወደውንም ያውቃል፤ ያከብራል፡፡

የሚያምንበትን ብቻ ሳይሆን የማያምንበትንም ይሰማል፣ ያደንቃል፤ለሚደግፈው ብቻ ሳይሆን ለማይደግፈው ነገር መብትም ይከራከራል፡፡ ከሁሉም ማኅበረሰብ ባህል ውስጥ አዳዲስ ዕውቀት፣ ልምድና አሠራር፣እንደሚገኝ ያምናል፡፡

በኮሌጆቻችሁ የግጥም፣ የሥነ ሥዕል፣ የሀገርህን ዕወቅ፣ የባህል፣ወዘተ መድረኮች እንዲስፋፉ አድርጉ፡፡ የካምፓስ ሕይወትኮ ችኮ አይደለም፡፡ ዕውቀትኮ መዝናኛ ነው፡፡ የየባህሉን ሙዚቃ፣ሥነ ቃል፣ ተረቶች፣ ተረኮች፣ ወጎች፣ ቀልዶች፣ አለባበስ፣ የምግብ አሠራር፣ አሣሣል፣የበዓላት አከባበር፣ ወደ አንድ መድረክ አምጡት፡፡ መዝናኛዎቻችን ሱስ፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ስካር፣ኢሞራላዊ ተግባራት መሆን የለባቸውም፡፡ የየአካባቢዎቻችንን ባህሎች እያወቅንና እያስተዋወቅን እንዝናና፡፡ ዕውቀት መዝናኛ ይሁን፡፡ እየተዝናናችሁ ትንሿን ኢትዮጵያ ካምፓሳችሁ ውስጥ ግለጧት፡፡ ማንኛውም ባህል የሚያድገው ባለቤቶቹ ስንጠቀመውና ሌላው ሰው ሲያውቀው ነው፡፡ ምዕራባውያን እያደረጉት ያሉት ይሄንን ነው፡፡ ባህላቸውን ያስተዋውቁናል፤ ከዚያም እንድንጠቀምበት ያደርጋሉ፡፡ እኛም የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ባህሎች እንድናውቅና እንድንጠቀምባቸው ኮሌጆቻችን ዋና ማገናኛዎች ናቸው፡፡

ይህንን ሁሉ የምታጣጥሙበትንና የነገዋ ኢትዮጵያ ገንቢዎች ሆናችሁ የምትወጡበትን ካምፓስ የግጭትና የጥላቻ መናኸሪያ ለማድረግ ተፍ ተፍ የሚሉ ካሉ ገሥጹዋቸው፡፡ አርሚቸው፡፡ ተቃወሚቸው፡፡ ከልክ በላይ ከሄዱ ደግሞ ለጸጥታ አካላት አጋልጣችሁ ስጧቸው፡፡ እነርሱ የእናንተን ጣፋጭ የኮሌጅ ሕይወት ለማበላሸትና የሀገራችንን መጻኢ ዕድል ለማሰናከል የተሰለፉ ናቸው፡፡ ልዩነታችን ውበታችን ነው በሏቸው፡፡ ጥላቻን በፍቅር፣ ቂምንም በይቅርታ አሸንፋችሁ አሳዩዋቸው፡፡ «ዛሬ ከተለያየ ቦታ መሰባሰባችን አይግረማችሁ፤ ነገ ወደ ተለያየ ቦታ ለመሄድ መንገዳችንን እያመቻቸን ነው» በሏቸው፡፡የትናንቱን እያነሡ በቁርሾ አዘቅት ውስጥ ሊጥሏችሁ የሚያስቡትንም «እኛ የነገዎች ነን» በሏቸው፡፡

ባልተግባባንባቸው ነገሮች ሁሉ አንጣላም፡፡ ነገ ወይ እንግባባባቸዋለን ያለበለዚያም ለየባለቤቱ ትተናቸው በተግባባንባቸው እንቀጥላለን፡፡ አንድ ሀገር የገነባነው በመሠረታዊ ነገሮች ተስማምተን እንጂ በሁሉም ነገር ተስማምተን አይደለም፡፡ ዋናው የመግባቢያ ሥርዓት ማደራጀት ነው፡፡ ልዩነትን በሠለጠነ መንገድ የሚያስኬድ ባህል መገንባት ነው፡፡ ልዩነቶች የማያስደነግጡት ማኅበረሰብ መፍጠር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በዕውቀት መስክ ላይ ከተሠማራችሁት ከእናንተ የተሻለ ለኢትዮጵያ ከወዴት ይመጣላታል?

በሉ ፍጠኑ፤ ተነሡ፤ ወገባችሁንም ታጠቁ፤ ጊዜ የለንም፡፡ሀገራችሁና ቤተሰቦቻችሁ እየጠበቋችሁ ነው፡፡ ከትናንቱ እጅግ ዘግይተናልና ለነገ መፍጠን አለብን፡፡መፍጠን እንጂ መሄድ ብቻ አያዋጣንም፡፡ ለሌላው ጊዜ የለንም፡፡ ጊዜው የትምህርት፣ የሥራና የሀገር ግንባታ ነው፡፡ ይህንን ለማደናቀፍ የሚመጡባችሁን ሁሉ «አሁን ጊዜ የለንም፤ እኛ ነገን እየገነባን ነው» በሏቸው፡፡

**መልካም የትምህርት ዘመን ይሁንላችሁ፡፡**

# ካንሰርን በጋራ እንከላከል

**ኅዳር 6/2011 ዓ.ም.**

መንግሥት ለሕዝቡ ቃል በገባው መሠረት በሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ሀገርን በመዝረፍና የዚህችን ሀገር መጻዒ ተስፋ ለማጨለም የሚንቀሳቀሱ አካላትን፣ የሰኔ 16ቱ ጥቃትን ጨምሮ የተለያዩ ወንጀሎችን በማቀነባበር የተጠረጠሩትን ተከታትሎ ለፍርድ ለማቅረብ ተግቶ እየሠራ ነው፡፡

መንግሥት ይህንን እያደረገ ያለው፤ በአንድ በኩል ባለፉት ዘመናት ሕዝቡ በግልጽ ሲጠይቃቸው የነበሩ የፍትሕ ጥያቄዎች በመሆናቸው ሲሆን፣በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት ይህንን ለማድረግ የሕግ ግዴታ ስላለበት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት ዓመታት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይህንን የፍትሕ ጥያቄ ሲጠይቀው ነበር፡፡ ከሕዝብ የሚሠወር ምንም ነገር የለም፡፡ ምንም እንኳን በድብቅ የተደረገ ቢመስልም፣ የሚደረገው ግን በሕዝብ መካከል ነውና ግመል ሰርቆ አጎንብሶ ለመሄድ የሚቻል አይደለም፡፡ ይህንን ያስተዋለው ሕዝብ ግፉና መከራው አንገፍግፎት አደባባይ ወጥቶ ፍትሕን ጠይቋል፡፡ ሀገር ተዘርፋ፣ ወገንም ተሰቃይቶ ከማለቁ በፊት ለውጥ እንዲመጣ ታግሎ አሁን ለደረስንበት የተስፋ ዘመን አድርሶናል፡፡ ስለዚህም መንግሥት የሕዝብን ጥያቄ መመለስ ውዴታው ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ነው፡፡ ፍትሕ የተበደለን ሕዝብ የመካሻ አንዱ መንገድ ነውና፡፡

በአንድ ሀገር ውስጥ የመንግሥት መኖርን የግዴታ ከሚያደርጉት መሠረታዊ ምክንያቶች አንዱ ፍትሕን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ፍትሕን ማረጋገጥ ማለትም ሁሉንም ዜጋ በሕግ ፊት እኩል ማድረግ ነው፡፡ ፍትሕ የሚረጋገጠውም ንጹሐን በኩራት ቀና ብለው የሚሄዱበትና ወንጀለኞች ደግሞ የትም የማይደበቁበት ሥርዓት ለመፍጠር ስንችል ነው፡፡

አገራችን የቤትና የእንጀራ ልጅ ሊኖራት አይገባም፡፡ ቢሊዮኖችን መዝብሮ በነጻነት የሚኖርና አንድ ብር አጥቶ ከቆሻሻ ገንዳ ውስጥ ምግብ የሚፈልግ ሁለት ዓይነት ዜጋ ሊኖራት አይገባም፡፡ የውጭ ጠላት እንኳን የማይፈጽማቸውን አሰቃቂ ሰይጣናዊ መከራዎች በሕግ ማስፈጸም ስም በዜጎች ላይ አድርሰው የሰላም እንቅልፍ ተኝተው የሚያድሩ ወንጀለኞች እና የመከራ ዶፍ የወረደባቸው፣ አካልና ኅሊናቸውን የተጎዱ፣ ተሸማቅቀው የሚኖሩ ሁለት ዓይነት ዜጎች ሊኖራት አይገባም፡፡

ሀገር፣ በአንድ በኩል ከመቀነታቸው ፈትተውና ከልጆቻቸው አፍ ነጥቀው ለሀገራዊ ፕሮጀክቶች የሚያዋጡ ሀገር ወዳዶች፣ በሌላ በኩል በድሆች ገንዘብ ቁማር የሚጫወቱ ሁለት ዓይነት ዜጎች ሊኖሯት አይገባም፡፡ አንዳንዶች በድብቅ እስር ቤቶች መከራ የሚቀበሉበት፣ ሌሎች ደግሞ በድብቅ ቦታዎች የሕዝብን ገንዘብ የሚሠዉሩበት ሀገር ሊኖረን አይገባም፡፡ ለውጥ እንዲመጣ መሥዋዕትነት የሚከፍሉ እና ለውጡ እንዲጨናገፍ ሌሎችን የሚሠዉ ሁለት ዓይነት ዜጎች በአንድ ሀገር መኖር አይገባቸውም፡፡ ለዚህም ነው ፍትሕን በተገቢው መንገድ ማረጋገጥ የሚያስፈልገን፡፡

ኢትዮጵያን ጹሐን ዜጎች እንጂ ወንጀለኞች በኩራት የሚኖሩባት ሀገር መሆን የለባትም፡፡ የፈጸሙት እንዲቀጡበት፣ ሊፈጽሙ ያሰቡት እንዲጠነቀቁበት፣ እነርሱን ሊከተሉ የሚከጅሉት እንዲማሩበት ሲባል ወንጀለኞቹን የማደንና ለሕግ የማቅረቡ ሂደት ገና ይቀጥላል፡፡ ተጀመረ እንጂ አልተፈጸመም፡፡ ዓላማው፣ በአራቱም አቅጣጫ አገሪቱን ከወንጀለኞች ነጻ ማድረግ ነው፡፡

ወንጀለኞችን የሚያስተሳስራቸው ጥቅም ብቻ ነው፡፡ «ገበያ ቢመቻት እናቷን ሸጠቻት» እንደሚባለው ወንጀለኞች ጥቅም እስከአገኙ ድረስ ወገኔ ለሚሉትም አይራሩም፡፡ ለእነርሱ ወገናቸው ኪሳቸውና በቀላሉ አፉን የሚዘጋላቸው

የጥቅም ተጋሪያቸው ነው፡፡ ወንጀለኞች የሚሠሩትን ዐውቀውትና ተዘጋጅተውበት ነው የሚሠሩት፡፡ ነገ ሊያዙ እንደሚችሉ ያስቡታል፡፡ ለዚህም መሸሸጊያቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ የጥንት ሽፍቶች መሸሸጊያቸው ጫካ ነበር፡፡

ዛሬ ግን ጫካው አልቋልና መደበቂያቸውን ብሔር ወይም ጎሳ ለማድረግ ይኳትናሉ፡፡ ሲበሉ ዞር ብለው ያላዩትን ሕዝብ ሲያዙ ይፈልጉታል፡፡ ራሳቸው የዘረፉትን ሕዝብ፣ ሲደረስባቸው ለመደበቂያነት ይፈልጉታል፡፡ የወንጀለኞች መመሪያ «ጥቅምን ለብቻ መከራን ለጋራ» የሚል ነው፡፡ ወንጀለኛ ወገንም፣ ብሔርም፣ ዘርም፣ ሞራልም የለውም፡፡ ወንጀለኛ ወገን ቢኖረው ኖሮ ሌባ ልጅ ሌብነትን ከእናቱ መቀነት ባልጀመረ ነበር፡፡ ነፍሰ ገዳይ ወንድሙ ወይም ሚስቱ ላይ ባልጨከነ ነበር፡፡

ወንጀልና ካንሰር አንድ ናቸው፡፡ ሰውነታችን በውስጡ ያሉትን እያንዳንዱን የራሱን ሴሎችና የአካል ክፍሎችን የሚረዳበትና የራሱ ካልሆኑ ባዕዳን የሚለይበት አሠራር አለው። ባዕድ የሆኑና ሰውነታችንን የሚተናኮሉ ጎጂ ነገሮች ሲገቡ ሰውነታችን በውስጥ አሠራሩ ይለያቸዋል፤ ይዋጋቸዋል፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ወራሪ ካላሸነፈው ወይም ሕመምን የመከላከል አቅማችን ከፍ ባሉ ደዌዎች ካልተዳከመ በቀር፣ ይህ ሰውነታችን ጤናውን የሚያስጠብቅበት የተፈጥሮ ጸጋ አለው።

አሳሳቢውና ለመከላከል አዳጋች የሚሆነው የሰውነታችን አንድ ክፍል የሆኑት ሴሎቻችን ከሰውነት የመተዳደሪያና ተሳስቦ የመኖሪያ ሥርዓት ማፈንገጥ ሲጀምሩ ነው።አንዳንድ ጊዜ በሰውነታችን ያሉ ሴሎች ሐላፊነታቸውን ይዘነጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜም ለመላው ሰውነት የተመደበውን ንጥረ ነገርና ግብአት ሁሉ ወደ ራሳቸው በመውሰድ ከተገደበላቸው በላይ ያድጋሉ።ነገሩ በጊዜ ተደርሶበት ገደብ ካልተሰጠው መላውን ሰውነት በመውረርና የአካላትን ተግባር በማዛባት ለከፉ ስቃይ ብሎም ለሞት ሊዳርጉት ይችላሉ። ይህ ሕመም «ካንሰር» ይባላል።

ካንሰርን በልምምጥ፣ በልመናና በአማላጅ ማዳን አይቻልም። ካንሰርን በዝምታ መመልከትም ሞትን በእያንዳንዷ ቀን በዝምታ እንደመጋበዝ ነው፡፡ በዝምታ የምትታለፍ እያንዳንዷ ቀን ለካንሰሩ ጉልበት ናት፤ ለተቀረው የሰውነት ክፍል

ግን ሞት። ካንሰሩ በአንደኛው የሰውነታችን ክፍል ላይ ጎልቶ ሊታይ ይችላል፡፡ ያ ማለት ግን ለካንሰሩ መገኘትና መስፋፋት ተጠያቂው ያ የሰውነት ክፍል አይደለም፡፡ የአንጀት ካንሰር ስለተያዘን ጥፋቱ የአንጀት አይደለም፡፡ ወይም አንጀት ሁሉ ከሰውነት ተነጥሎ ይውጣ አያስብለውም።

በካንሰሩ የተጠቃውና የካንሰሩ መራቢያ የሆነው አንጀት፣ ጉበት፣ ሳምባ፣ አንጎል፣ ሌላም ቢሆን አስፈላጊው ኬሚካላዊ፣ የጨረር ወይም የቀዶ ሕክምና በአስቸኳይ ተደርጎ የአካሉ ጤና ካልተመለሰ፣ በአንዱ የሰውነት አካል የጀመረው ካንሰር ሰውነትን ሁሉ ወርሮ በመጨረሻም ሰውዬውን ይገድለዋል። ካንሰር ከየትኛውም የሰውነት ክፍል ይጀምር ሌላ መጠሪያ የለውም «ካንሰር» ነው። ወደ የትኛውም የሰውነት ክፍል ይሰራጭ «ካንሰር» ካንሰር ነው።
ካንሰርን በሕመም ማስታገሻ ወይም በቫይታሚንና በምግብ ብቻ ለማከም መሞከር ዕድሜን ማሳጠር ነው። ካንሰር ቶሎ ከተደረሰበት የመዳኑ ተስፋ ከፍ ያለ ሲሆን ከዘገየ ግን በሰውነት ሁሉ ይሰራጭና ሕክምናውን የተወሳሰበ ያደርገዋል፡፡

በካንሰር ሕክምና፣ የሕክምናው ሂደት አካሚውን ጨካኝ ሊያስብለው ይችላል፡፡ በካንሰር የተያዘው የሰውነት ክፍል ተቆርጦ ይወገድ ሲባል፤ ለምሳሌ፡- እግር፣ እጅ፣ጉበትና ኩላሊት በጤናማነታቸው ዘመን ያላቸውን ጥቅም ከግንዛቤ አስገብተን እንሳሳ ይሆናል፡፡ሆኖም ግን ሙሉ ሰውነትን ለማዳን ሲባል የሚከፈሉ ዋጋዎች ናቸው። ለካንሰር ዝምታ ወይም መተው መፍትሔ አይደለም፡፡ ሙሉ አካልን ወርሮ በሞት እስኪደመደም ድረስ ካንሰርነቱን አይተውም፡፡

ካንሰር እንደ ወንጀለኛ ሰው፣ አንድ አስከፊ ጠባይ አለው፡፡ ስለራሱ ካልሆነ ስለ አለበት አካልም ሆነ ማንነቱን ስላገኘበት የሰውነት ክፍል ፈጽሞ አያስብም፡፡ ያንን የሰውነት ክፍል ለመኖሪያና ወደ ሌሎች ለመስፋፊያ ብቻ ነው የሚፈልገው፡፡ ሁሉን ይጎዳል፤ ብቻውን ግን ይጠቀማል፡፡ የጉበት ካንሰር ስለተባለ ለጉበት የሚጠቅመው ነገር የለም፤ ይጎዳዋል እንጂ፡፡ ሁሉን ለራሱ በማድረግ ሰውነትን ያከሳል፣ ያሰቃያል፣ ይዘጋል፣ ለሕመምና ለከፍተኛ ወጪም ያጋልጣል፤ የካንሰርና የወንጀለኛ መፈክሩ «ሁሉን ለእኔ፣ ሁሉን ወደ እኔ» የሚል ነው፡፡ባገኘበት ሁሉ ራሱን ከማስፋፋት በላይ ሌላ ምንም ተግባር የለውም፤

ደኅናውን ሴል ሁሉ ይበክላል፤ ይገድላል፡፡ ካንሰርን ስናክም ደኅናዎቹ ሴሎችና የሰውነት ክፍሎች ለጊዜው ሊጎዱ ይችላሉ፡፡ በተለይ ካንሰሩ የጀመረበት አካል ክፍል የተጎዳ መስሎ ይታያል፡፡ እውነቱ ግን ከዚህ በተቃራኒ ነው፡፡

ከማንኛውም የሰውነት ክፍል ክብካቤና ጥንቃቄ የሚያገኘውና የሚፈልገው ያ የታመመው ካንሰሩ የተነሣበት ክፍል ነው፡፡ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች በሙሉ የሕክምናው አካል ሆነው፣ አብረውት ሊቆሙ፣ መድኃኒቱ እንዲደርሰው፣ ዕረፍት እንዲሰማው ሊያደርጉት የሚደክሙት እርሱን ነው፡፡ እነርሱ የሰውነት ክፍሎች እንጂ ሰውነት አይደሉምና፡፡ ለእነርሱም ያ በካንሰር የተጠቃው አካል በጣም ያስፈልጋቸዋል፡፡

የሰውነት ክፍሎቻችን በጥቂት የካንሰር ሴሎች ምክንያት እርስ በእርሳቸው አይጣሉም፤ አይባሉም፤ አይናከሱም፤ አይካሰሱም፡፡ እንዲያውም ካንሰሩን የጋራ ጠላት አድርገው በአንድነት ሊዋጉት ይነሣሉ፡፡ ካንሰሩ ከሰውነት ክፍል ስሙን እንጂ ሌላውን እንደማይወስድ ያውቃሉ፡፡ እዚያ ቦታ መሽጎ ሁሉንም ሊያጠቃ እንደተዘጋጀ ያምናሉ፡፡ በእርስ በርስ ፍትጊያ ጊዜ ማጥፋት ለካንሰሩ ዕድሜ መቀጠል መሆኑን ይረዳሉ፡፡ አብረው ተባብረው ካልተነሡም ዕጣ ፈንታቸው ሞት መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡ ስለዚህም ሁሉም በተያዘው የሰውነት ክፍል ላይ ሳይሆን በካንሰሩ ሴል ላይ ለይተው ይዘምታሉ፡፡

እንደ አንዳንድ ወንጀለኛ፣ የማኅፀን ካንሰር አንድ አስገራሚ ጠባይ አለው፡፡ በዚህ ካንሰር የተያዘች ሴት በመጀመሪያ አትነቃበትም፡፡ አረመኔው ካንሰር እንደያዛት ሳይሆን እንደአረገዘች ነው የምታስበው፡፡ እየቆየ ሲሄድ ግን በማኅፀኗ የተሸከመችውን ሴት እየበላት ይሄዳል፡፡ እርሷም መንምና ዕጢውን መሸከም ከማትችልበት ደረጃ ትደርሳለች፡፡ ወንጀልም እንዲሁ፤ ለፈጻሚው መጀመሪያ ጥቅም ያስገኘለት ቢመስለውም እየቆየ ግን ራሱን እየበላው ሄዶ መሸከም ከማይችልበት ደረጃ ላይ ያደርሰዋል፡፡ ወንጀል እንደ ካንሰር ነው ያልነው ለዚህ ነው፡፡ ወንጀለኛ የአንድን አካባቢ ሕዝብ የሚፈልገው ሊጠቅመው፣ ሊሠራለት፣ ሊታገልለት ወይም ሊያለማለት አይደለም፡፡ መልከ ጥፉን በስም ለመደገፍ እንጂ፡፡ አራዊት እንኳን የማይፈጽሙትን ኢሰብአዊ ድርጊት በሰው ዘር ላይ የሚፈጽም ሰው በምን አንጀቱ ለወገኑ ይራራል? በየትኛው ልቡ ለወገኑ ያስባል? በየትኛውስ አእምሮው ለወገኑ ይቆረቆራል፡፡ ‹‹ልብማ ቢኖራት መች እንዲህ

ትሆን ነበር» እንደተባለው ወንጀለኛ ልብም፣ አንጀትም፣ ኅሊናም፣ አእምሮም የለውም፡፡ ማሰቢያው ጥቅም ብቻ ነው፡፡ ጥቅም ካገኘ ይዘርፋል፣ ያጠፋል፣ ይገላል፣ ያሰቃያል፣ ያወድማል፡፡

አሁን የተጀመረው ሥራ ሀገር የገደሉ ወንጀለኞችን፣ እነርሱ ለሌላው በነፈጉት ፍትሕ ፊት የማቅረብ ሥራ ነው፡፡ ካንሰርን የማዳንና የመከላከል ሥራ ነው፡፡ ሞኝ በሄደበት ብልህ፣ ክፉ በሄደበት ደግ፣ ጨካኝ በሄደበት ሩኅሩኅ፣ አጥፊ በሄደበት አልሚ አይሄድም፡፡ የጠላነውን ደግመን አንሠራውም፡፡ ስለዚህም በተገቢ ደረጃና አያያዝ፣ የሚገባቸውን ፍትሕ እንዲያገኙ ማድረግ አለብን፡፡ ሁኔታው ስሜትን የሚፈትን ቢሆን እንኳን እኛ ግን ከእነርሱ መሻል አለብን፤ ከስሜት ይልቅ ለልቡና ቦታ እንሰጣለን፡፡ ለፍትሕ የቆምን መሆኑን ተገቢው ፍትሕ እንዲሰጥ በማድረግ እናሳያለን፡፡

ወንጀለኞቹ ገና ከየጎሬያቸው ይወጣሉ፡፡ «ሌባ ባያፍር የሌባ ዘመድ ያፍር» የሚለው ብሂላችን ወንጀለኛን ወገኔ ነው የሚል ማኅበረሰብ እንደሌለን ማሳያችን ነው፡፡ በወንጀል የሚያፍር እንጂ ወንጀለኛን የሚደብቅ ሕዝብ እንደሌለን መግለጫ ነው፡፡ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ የተሸሸጉትን ወንጀለኞች አጋልጦ ለሕግ በማስረከብ ወንጀል የሚያሳፍር መሆኑን እያሳየ ነው፤ ይቀጥልበታልም፡፡ የወንጀለኞች መኖሪያ መሆን ያለባቸው ማረሚያ ቤቶች እንጂ ብሔሮችና ብሔረሰቦች አይደሉም፡፡ የቅጣቱ ዋና ዓላማም አጥፊዎችን መቅጣትና ድርጊቱን መኮነን ብቻ አይደለም፡፡ ዳግም እንዳይመጣ አስተሳሰቡን ማረም ጭምር ነው፡፡

**የሀገር ካንሰር ለሁላችን የመጣ፣ ሁላችንም ልንከላከለው የሚገባ የጋራ ሐላፊነታችን ነው፡፡**

**ኢትዮጵያ፣ በልጆቿ ጥረት እና ሕብረት**
**ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# ለመውሊድ የተላለፈ መልእክት

**ኅዳር 10/2011 ዓ.ም.**

በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ ለምትኖሩ መላው የእስልምና ተከታይ ወገኖቼ፤ እንኳን ለ1493ኛው የነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዓ.ወ) የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ፡፡

በእስልምና የወራት አቆጣጠር ራቢ አል አወል በሚባለው በሦስተኛው ወር በ12ኛው ቀን በየዓመቱ የሚከበረው ይህ የልደት በዓል በተለምዶ በእኛ ሀገር መውሊድ ወይም መውሊደል ነቢ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ወጣት፣ ዐዋቂ፣ ሕፃን፣ ወንድ፣ ሴት፣ ከተሜ፣ ባላገር፣ የተማረ፣ ያልተማረ፣ ሀብታም፣ ድሃ፣ ሙስሊም፣ ክርስቲያን ወዘተ... ሳይለይ የሚያሳትፍ ከመሆኑም ባሻገር፣ በመኖሪያ ቤት፣በመስጊድ እንዲሁም በእስልምና የመድረሳ ት/ቤቶች በተለያዩ የእምነቱ ሥርዓት የሚካሄድ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ኢትዮጵያውያን ሙስሊም ወገኖቻችን በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በድምቀት የሚያከብሩት ይህ የመውሊደል ነቢ በዓል በሙስሊሙ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያውያን በጋራ የሚከበር ወደ መደመር የፍቅር ሰገነት ከፍ ያለ ልዩ በዓል ነው፡፡

በኢትዮጵያችን በሙስሊሙ በዓል ክርስቲያኑ፤ በክርስቲያኑ በዓል ዋቄፈታው፤ በኢድ በፋሲካው፣ በመውሊድ በገናው እና በእሬቻው የእንኳን አደረሰህ፣ እንኳን አደረሰሽ ቅብብሉ የማንለያይና የተዛመድን መሆናችንን አጉልቶ የሚያሳይ ነው።

መስተጋብራችንም መልካም ምኞት እስከ ታከለበት ዝይይር በሚዘልቅ የፍቅር ሸማ ተከብክቦ ወደፊትም ደምቆ ይቀጥላል፡፡

መውሊደል ነቢ በመሠረታዊነት ነቢዩን እና በነቢዩ አማካኝነት ለዓለም የወረደውን የእስልምና አስተምህሮቶች በመዘከር ለሕፃናት በትረካ የሚተላለፍበት በዓል ሲሆን የዲኑ ኡለማዎችም በግጥምና በመንዙማ ለፈጣሪያቸው ምስጋና በማቅረብ ያሳልፉታል፡፡
ዕለቱን በበጎ ሥራ፤በምጽዋት፣ የተመረጡ የቁርአን ክፍሎችና የመውሊድ ምንባብ በመስማት፣የመንዙማ ፕሮግራሞች በማካሄድ ከዚያም አልፎ የተቸገሩን በመርዳትና የታመሙትን በመጠየቅ፣ ብሎም ራሳችንን ከክፉ ተግባራት በማራቅ እምነታችንን የምናጠናክርበትም ዕለት ነው፡፡

በመሆኑም መላ የሀገራችን ሙስሊሞች እና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ እንደ ሁል ጊዜው በመውሊደል ነቢ በዓልም የነበሩንን የሰላም፣ የመረዳዳት፣ የመከባበር እና የመጠያየቅ ባህል በማስቀጠል የሀገራችንን ሁለንተናዊ ለውጥ እና ሕዳሴ ለማረጋገጥ የበኩላችሁን እንድትወጡ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

**በመጨረሻም በዓሉ የሰላም፣ የፍቅር፣ የይቅርታ እና የመደመር በዓል እንዲሆንላችሁ ከልብ እመኛለሁ፡፡**

**መልካም የልደት በዓል!!**

# ‹ቤት ለእንግዳ›ን በተግባር

**ኅዳር 11/2011 ዓ.ም.**

**ከኅዳር 9 እስከ 10 ቀን 2011 ዓ.ም. የተደረገው የአፍሪካ ኅብረት 11ኛ ልዩ ስብሰባ በሰላም ተጠናቅቋል፡፡**

በስብሰባው ላይ የአፍሪካ ኅብረት ጽ/ቤትን የኅብረቱን ተልዕኮዎች በብቃት ሊያሳካ በሚችልበት መንገድ ለማደራጀት የሚያስችል ውሳኔ ተላልፏል፡፡ የአህጉሪቱ ዋና የለውጥ ኃይል የሆነውን ወጣቱንና አፍሪካን ተሸክመው እዚህ ያደረሷትን ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስችሉ ውሳኔዎችም ተወስነዋል፡፡ በየክፍለ አህጉሩ ትብብርንና የጋራ ተጠቃሚነትን ማምጣት ስለሚቻልበት ሁኔታ እና ቀጣይ ጉዞም በስፋት ተመክሯል፡፡ እንግዳን መቀበል ባህላችን ነው፤ ስንል እውነታችንን እንጂ ለማለት ያህል የምንለው አለመሆኑን ከምናሳይባቸው አጋጣሚዎች አንዱ የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ነው፡፡ ጠላ ጠምቆ፣ አልጋ ለቅቆ፤ ከፍቶት እንኳን ቢሆን እንግዳው ሰው ከፍትፍቱ ይልቅ ፊቱ እንደሚበልጥበት በመረዳት ደስ ብሎት ስቆ፣ወንበር አቅርቦ፣ እግር አጥቦ፣ ከጣመው ከላመውም መግቦ መቀበል በሁሉም ኢትዮጵያውያን ባህል ውስጥ የሚገኝ አብሮን የኖረ ብቻ ሳይሆን፤ የማንነታችን ማእዘን ሆኖ በፍቅር ያኖረን ውብ ዕሴታችን ነው፡፡ የምንልበት ቋንቋ እና የምናቀርብበት መንገድ ይለያይ እንደሆን እንጂ «ቤት ለእንግዳ ነው» የሚለው ባህላችን ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ በፍቅር የምንጋራው መለያ ቀለማችን ነው፡፡ እንግዳው እንደ ቤተኛ ብቻ ሳይሆን ከቤተኛውም በላይ ክብካቤ ይደረግለታል፡፡

ሰሞኑን በኅብረቱ ስብሰባ ምክንያት መንገዶች በአንዳንድ ቦታ ሲዘጉ ነበር፤ ለተወሰኑ ደቂቃዎች የትራፊክ መጨናነቆች ነበሩ፡፡ አንዳንድ ሀገራዊ መርሐ ግብሮችም ወዲህና ወዲያ የመሆን ዕጣ ገጥሟቸዋል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን የኅብረተሰቡ ትብብር እንደ ሁል ጊዜው ሁሉ እንግዶቻችንን እጅጉን ያስገረመ ነበር፡፡ ሕዝባችን ይህንን ያደረገው እንግዳ ተቀባይ ድንቅ ሕዝብ ከመሆኑም ባሻገር የእንግዳ አይዘንብህ ምርቃት እና በቸር የተቀበሉትን መንገደኛ በቸር የመሸኘት ሀገራዊ ሐላፊነት በድርብ የተሰጡት ታላቅ ሕዝብ ስለሆነ ነው፡፡ በሰላም ተስተናግዶ ወደ ሀገሩ፣ ወደ ቤቱ የተመለሰ ተስተናጋጅ እግር በጣለው ቦታ እና ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ አስተናጋጁን ያመሰግናል፤ ይመርቃል፡፡ እንግዳው ሰው በሰላም ተስተናግዶ ከቤቱ እስኪሸኝ ድረስ ግን እንግዳ ተቀባዩ ቤተኛ የእንግዳውን ሰላምና ደኅንነት የመጠበቅ ሐላፊነቱን በሚገባ ሊወጣ ይገባል፡፡ ሀገራችን የአፍሪካ ኅብረትና የአፍሪካውያን መዲና ስትሆን ይህንን ሐላፊነት በብቃት እንደምትወጣ በአፍሪካውያን ወገኖቻችን በጽኑ ታምኖባት ነው፡፡

የተጣለብንን ሐላፊነት እና የተሰጠንን እምነት ደግሞ ባህል፣ እምነት እና ሕይወት፤ እንግዳ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከነፍሱ ላይ ያተሙለት ታላቁ ሕዝባችን፣ በየደረጃው ያሉ የጸጥታ አካላትና ፖሊስ በጋራ በመሆን አኩሪ በሆነ ትጋት እና የመናበብ ትብብራዊ አብሮነት በብቃት ተወጥተዉታል፡፡

ሰሞኑን እየወሰድናቸው ካሉ እርምጃዎች ጋር በተያያዘ የጸጥታ ጥበቃው ጠበቅ ሊል እንደሚችል ኅብረተሰቡ ይገነዘባል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሕዝብ ለለውጥ ሌት ተቀን እንደሚደክመው ሁሉ፣ ለውጡን ለማደናቀፍም ሌት ተቀን የሚደክሙ እኩያን የመኖራቸው ነገር ከማናችንም ቢሆን የተሰወረ አይደለም፡፡ ዕንቅፋት ፈጥረው የሀገራችንን ገጽታ እንዲያበላሹ በምንም መልኩ ዕድል ፈንታ አንሰጣቸውም፡፡ ሕዝቡም ለዚህ ዓላማ ሲባል ያጋጠሙትን ጊዜያዊ ፈተናዎች በትዕግሥት ያለፋቸው በዚሁ እምነቱ መነሻነት እና በባህሉም ካካበተው የእንግዳ ተቀባይነት የአዝማናት እውነት እንደሆነ እሙን ነው፡፡

ስብሰባው ውጤታማና ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ሀገራዊ ሐላፊነታችሁን የተወጣችሁትን ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በዚህ ታላቅ ሐላፊነት ውስጥ ዲፕሎማቶቻችንን፣ አሽርካሪዎቻችንን፣የበረራ አስተናጋጆቻችንን፣ ፓይለቶቻችንን፣ የአውሮፕላን ጣቢያ ሠራተኞቻችንን፣ባለሆቴሎቻችንንና የሆቴል ሠራተኞቻችንን፣ የትራፊክ ፖሊሶቻችንን፣ የጸጥታ አካሎቻችንን፣የአዲስ አበባ ወጣቶችን፣ ተማሪዎቻችንን በአጠቃላይ መላውን የሀገራችንን ሕዝቦች በተለይ ደግሞ የአዲስ አበባን ነዋሪዎች በራሴና በኤፌዴሪ መንግሥት ስም በተለየ አክብሮት እና ፍቅር ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡

**ቆርጠን፣ ተባብረንና እና ኢትዮጵያን አስቀድመን በመደመር ከሠራን፣ የሚፈትነን እንጂ የሚያቅተን ጉዳይ በፍጹም አይኖርም!!**

**ኢትዮጵያ፣ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር! ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን አብዝቶ ይባርክ፡፡**

# የብሔር ብሔረሰቦች (የኢትዮጵያዊነት) ቀን መልእክት

**ኅዳር 28/2011 ዓ.ም.**

**ይህ ቀን፣ የኢትዮጵያዊነት ቀን ነው፤**
**ይህ ቀን፣ የሕብራዊ አንድነታችን ማክበሪያ ቀን ነው፤**
**ይህ ቀን ብዙዎች ስንሆን አንድ፣ አንድ ስንሆን ብዙዎች መሆናችንን የምናስብበት ቀን ነው።**
**ይህ ቀን ሀገራችን አንድ፣ ጸጋዎቿ ግን ብዙዎች መሆናቸውን የምንገልጥበት ቀን ነው።**

አንድነትና ብዙነት ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ዩኒቨርስ ራሱ አንድ ሥርዓት ሆኖ፣ ነገር ግን በብዙ መልኩ የሚገለጥ ነው፡፡ አንዱ ዩኒቨርስ በአያሌ ልዩ ልዩ ነገሮች የተሞላ ነው፡፡ ያ ባይሆንማ ዓለም ራሷ ልሙጥና አሰልቺ በሆነች ነበር፡፡ አንድና ልዩ ልዩ መሆን ለዓለም ጌጧ ብቻ አይደለም፤ ህልውናዋም የተመሠረተው አንድና ልዩ ልዩ ከመሆን ነው፡፡ ልዩ ልዩ ፍጡራን እርስ በርስ እየተመጋገቡና እየተደጋገፉ፣ እየተዛመዱና እየተዋሐዱ ነው ዓለም ጸንታ እንድትኖር ያደረጓት፡፡ በዕፅዋትና በእንስሳት መካከል ያለውን መመልከት ብቻ ለዚህ በቂ ነው፡፡በተመጋግቦት ሠንሠለት (Food chain) ያለውን የፍጡራን ለአንድ ዓላማ ተደጋግፎ የመኖር ሥርዓት መመልከት የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል፡፡

ኢትዮጵያችን መንትያና ምትክ የሌላት አንዲት ሀገራችን ናት፡፡ ኢትዮጵያዊነትም በብዙ ኅብር የሚገለጥ የዚህች ሀገር ዜጎች ድምር ጸጋቸው ነው፡፡ አንዲቱ ኢትዮጵያ በብዙ ኅብርና በብዙ መልክ ነው የምትገለጠው፡፡ እነዚህ የአንድ አካል ልዩ ልዩ ክፍሎች የሆኑት መልኮቿና ኅብሮቿ፣ ብሔርና ብሔረሰቦቿ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያዊነት ደግሞ የሁሉም ድምርና ውሕደት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አጥር ሠርተው ቅጥር ተክለው የተቀመጡ አልነበሩም፤አይደሉምም፡፡ ሲጋቡ፣ ሲዋለዱ፣ ሲዛመዱ፣ ሲወራረሱ፣ አንዱ ወደ ሌላው በመሄድ ሲኖሩ የቆዩ ናቸው፡፡ ዛሬ የአንዱ ባህል አድርገን የምንናገረው ነገር፣ ያ ሕዝብ ጠብቆና አደራውን ይዞ ለኢትዮጵያ ያቆየላትን ባህል ነው፡፡ ሀገር እንዳትጠፋ ሁላችንም ተካፍለን ነው ጸጋዎቿን ጠብቀናቸው የቆየነው፡፡

ለዚህም ነው የአንዱ ባህል የሁላችንም፤ የአንዱ ቋንቋ የሁላችንም፤ የአንዱ ዜማ የሁላችን፤ የአንዱ አለባበስ የሁላችንም ነው የምንለው፡፡ ያ ባህል በዚያ ሕዝብ በኩል ተጠብቆ የኖረ የኢትዮጵያ ባህል ነው፡፡ ሳይጠፋብን ተከባክቦ፣ ሳንረሳው አስቦ፣ ሳይበላሽ ጠብቆ ስላቆየን፣ ሁላችን ነን ያንን ሕዝብ የምናመሰግነው፡፡ ሁሉም የእኛ ነውና፡፡

ከዘመናት በፊት እንዴት አብረን ስንኖር እንደ ነበር፣እንዴት ስንወራረስ እንደኖርን ተረቶቻችን ታላቅ ምስክሮቻችን ናቸው፡፡ አዳዲሶቹ የጥላቻ ትርክቶች ከመምጣታቸው በፊት፣አብረው የኖሩት ተረቶቻችን ምን ያህል እንደ ስፌት የተሳሰርን፣ እንደ ቤተሰብ አብረን የኖርን፣የተዛመድንና የተጋመድን መሆናችንን ይመሰክራሉ፡፡

ከቋንቋቸው መለያየት ውጭ ብዙዎቹ ተረቶቻችን በይዘታቸውና በቅርጻቸው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ለብልጥ፣ ለሞኝ፤ ለንጉሥ፣ ለወታደር፤ ለፈሪ፣ ለደፋር፤ ለቁጡ፣ ለትዕግሥተኛ፤ ለታታሪ፣ለሰነፍ፤ የምንወክላቸው የእንስሳት ገጸተ ባሕርያት ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ጀግንነት፣ለወገን ሟችነት፣ ታታሪነት፣ ብልሐት፣ ትዕግሥተኛነት፣ ሀገርን መውደድ፣ ወላጅን ማክበር፣ የሰውን አለመመኘት፣ አደራ መጠበቅ፣ ታማኝነት፣ ቃልን ማክበርና ሌሎችም በተረቶቻችን ሁሉ የሚመሠገኑ ዕሴቶቻችን ናቸው፡፡

ከመቀሌ እስከ ሞያሌ፣ ከኩርሙክ እስከ ቶጎ ጫሌ ብንሄድ እነዚህን ዕሴቶች በየተረቶቻችን ውስጥ እናገኛቸዋለን፡፡ በተቃራኒ ደግሞ ሌብነት፣ ነፍሰ ገዳይነት፣ ቅሚያ፣ ችኩልነት፣ ቃል አባይነት፣ ፈሪነት፣ ሀገር ሻጭነት፣ ከሐዲነት፣ በተረቶቻችን ውስጥ ይኮነናሉ፤ ይወገዛሉ፡፡

ኢትዮጵያችን ከሰጠችን ጸጋዎች አንዱ ብዙም አንድም ሆነን ለመኖር መቻላችን ነው፡፡ ብዙነታችን ሳይነጣጥለንና ሳይከፋፍለን፣ አንድነታችንም ሳይጠቀልለንና ሳይውጠን በዝተንና መልተን ኖረናል፡፡ አንድነታችን ለብዙነታችን ጥንካሬው ሆኖ፤ ብዙነታችንም ለአንድነታችን መገለጫው፣ ጌጡና ሀብቱ ሆኖ ኖረናል፡፡ አንድነታችን ለብዙነታችን ማሠሪያ ገመዱ፣ መቆሚያ ዓምዱ ነው፡፡ ብዙነታችን ደግሞ ለአንድነታችን ማንቀሳቀሻ ሞተሩ፣ ማዋቀሪያ ቋሚና ማገሩ ነው፡፡

ኢትዮጵያዊነት እንደ ወይን ጠጅ እያደር እያማረና እየጠነከረ የሄደው ብሔር ብሔረሰቦች ባህላቸውን፣ ዕሴታቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ቅርሳቸውንና ታሪካቸውን የሚመግቡት በመሆኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነት እንደ ኩሬ ውኃ ጸጥ ብሎ የተኛ አይደለም፡፡ በብሔር ብሔረሰቦች መስተጋብር ምክንያት እንደ ባሕር የሚታደስ፣ የሚሳለጥ (ዳይናሚክ)፣ እያደገ፣ እየዳበረና እየጠነከረ የሚሄድ የሕዝቦች ዕሴትና ሕልም ነው፡፡

ማንም ለማንም ባዳ አይደለም፡፡ ይህ ለዚያኛው፣ በሌላ ቋንቋ የሚናገር ወገኑ ነው እንጂ፡፡ የኛው ልጆች በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ተወልደው የዚያኑ ሀገር ቋንቋ ለምደውታል፡፡ በብዙ ነገራቸው የኛው ወገኖች ሆነው በባህልና በቋንቋ ግን ከኛ ይለያሉ፡፡ ማንም ግን እነርሱን ባዕድ ናቸው አይልም፡፡ በሀገርም ውስጥ እንዲሁ ነው፡፡ በሌላ ቋንቋ የሚናገርና ሌላ ባህልን የለመደ ወገናችን ነው፤ ያኛው፡፡ የእምነት ታሪኮቻችንም ሆኑ አፈ ታሪኮቻችን የሚነግሩን ወደኋላ ስንሄድ ግንዳችን አንድ መሆኑን ነው፡፡

እንግዳ ትርክቶችን ሰምተን ካልሆነ በቀር ባህላችን የሚነግረን ሌላውን አክብረንና ወደን እንድንቀበለው ነው፡፡ በየቤታችንኮ «ጥቁር እንግዳ» በጣም የተከበረ ነው፡፡ ጥቁር እንግዳ ማለት ደግሞ ከዚህ በፊት መጥቶ የማያውቅ አዲስ ሰው ነው፡፡ የማናውቀውን ሰው አክብረን ማስተናገድን እንጂ ገፍቶ ማባረርን ባህላችን ፈጽሞ አያስተምረንም፡፡ በሁላችንም ባህሎች ውስጥ ከኛ ባህልና ቋንቋ

*ውጭ የሆኑ ወገኖችን የምንቀበልባቸው ባህላዊ ሥርዓቶች አሉን፡፡ ተገፍቶ ለመጣ ሰው ጥብቅና የምንቆምባቸው ባህላዊ ሥርዓቶች አሉን፡፡ አብሮን ለመኖር ለመጣ ሰው ከብሔረሰቡ አባል የበለጠ መብት የሚሰጡ ባህሎች አሉን፡፡ ከሌላ ቦታ የመጣ ሰው ልጅ፣ ቤተሰብ፣ ወራሽ የሚሆንባቸው የከበሩ ሥርዓቶች አሉን፡፡በዚህ መልኩ ስንደመር ነው የኖርነው፡፡ እኛ አንድም፣ ልዩ ልዩም ነን፡፡*

*ኢትዮጵያን በጋራ ነው የመሠረትናት፤ በጋራ ነው ያቆየናት፤ በጋራ ነው የሞትንላት፤ በጋራ ነው ያስከበርናት፤ በጋራ ነው እዚህ ያደረስናት፡፡ የአንዱ ታሪክ የሌላችን ነው፤የአንዱ መከራም የሌላችን ጭምር ነው፡፡ በአንደኛው ድንበር በኩል የመጣ ጠላት ወገናችንን ሲያጠቃ «ሆ» ብለን የዘመትነው፣ ያ ሕዝብ የአብራካችን ክፋይ ስለሆነ ነው፡፡ እርሱን መንካት እኛን መንካት መሆኑን ስለምናምን ነው፡፡ አፍንጫ ሲመታ ዐይን እንደሚያለቅስ የሚናገረው ብሂላችን ይህንኑ የሚያስረግጥ ነው፡፡*

*ከዚህ ታሪካችን፣ ባህላችንና ልማዳችን ውጭ ጠላትነትን፣ ጥላቻን፣ መገፋፋትንና መራራቅን የሚዘሩብንን ኩሩው ባህላችን አይታገሣቸውም፡፡ የዘሩትን ክፉ ዘር እንነቅልባቸዋለን እንጂ እንዲያበቅሉት አንፈቅድላቸውም፡፡ ልዩነቶቻችንን አጉልተው፣ ገደል ያራራቀን ለሚያስመስሉት የአንድነት ታሪካችንንና ባህላችንን ከፍ አድርገን እናሳያቸዋለን፡፡*

*«እንኳን ሰውና ሰው ጉልቻና ጉልቻ እንኳን ይጋጫል» ብለን የምንተርት ነንና ቅሬታዎችን በይቅርታ፣ ዝንፈቶችን በፍትሕ እናርማቸዋለን፡፡ የሚለያዩን ሲመስላቸው ይበልጥ እንደመራለን፤ የተቃረንን ሲመስላቸው ይበልጥ እንደ ድርና ማግ ተሳስረን አንድ ሸማ እንሆናለን፡፡*

*ከግብርናው ባህላችን እንደ ተማርነው ያለፉትን መልካሞቹን እንይዛለን፤ የስሕተት አረሞችንም በጋራ እናርማለን፡፡ እነሆ አዲሱን የለውጥ ጎዳና በመደመር መንፈስ ጀምረናል፡፡ ለውጡ በሕዝቡ ትግል ለሕዝቡ የመጣ ነው፡፡ ይህንን ተሥፋ ሰጭ ለውጥ የሰላም መደፍረስ፣ የብሔር ግጭቶች፣ የጅምላ ፍርድና ስሜታዊነት ለአደጋ እንዳያጋልጠው እንደ ሰጎን ዐይናችንን ሳንነቅል እንጠብቀዋለን፡፡*

ኢትዮጵያ አምልጠውኛል ብላ በቁጭት የምትቆጥራቸው አያሌ ዕድሎች አሏት፡፡ ይህ የአሁኑም ከእነዚያ አንዱ እንዲሆን መፍቀድ የለብንም፡፡ አሳክተን ለልጆቻችን ማስረከብ ይጠበቅብናል እንጂ፡፡ ነገ የዚህ ለውጥ ስኬት ታሪክ፣ ተረክና ተረት ሆኖ በየቋንቋችን መነገር እንዲችል ዛሬ የሚከፈለውን ሁሉ ከፍለን ከዳር ማድረስ አለብን፡፡

ይህ በዓል የኢትዮጵያዊነት በዓል ነው፡፡ ሁላችንም «ሆ» ብለን ወጥተን የኢትዮጵያዊነትን ልዩ ልዩ ጸጋዎች እያሳየን፣ እያከበርንና እየጠበቅን የምናከብረው የኅብራዊ አንድነታችን መገለጫ በዓል ነው፡፡ ልዩነቶቻችን የአንድነታችን ጸጋ፣ አንድነታችንም የልዩነቶቻችን ተደማሪ ዋጋ መሆኑን የምንገልጥበት ታላቅ በዓል ነው።

**መልካም በዓል ይሁንልን።**

# በሰብአዊ መብት አያያዝ ዙሪያ የተላለፈ መልእክት

**ታኅሳስ 3/2011 ዓ.ም.**

አገራችን ኢትዮጵያ በለውጥ ጉዞ ላይ ናት፡፡ በለውጥ ጉዞ ላይ ናት ስንል የሚለወጥ ነገር አላት ማለታችን ነው፡፡ ከሚለወጡት ነገሮቻችን አንዱ የዜጎች የሰብአዊ መብት አያያዝ ነው፡፡ኢትዮጵያውያን በየዘመናቱ ታግለው የመንግሥት ለውጥ እንዲመጣ ካደረጉባቸው ምክንያቶች አንዱ ሰብአዊ መብታቸውን የሚያከስብር ሥርዓት ለማስፈን ነበር፡፡ የሰብአዊ መብት አያያዝም ሆነ ሌሎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመሠረታዊነት እውን ሊሆኑ የሚችሉት በግለሰቦች ፍላጎት መመራቱ ቀርቶ የጋራ ፍላጎታችን በወለዳቸው ተቋማት መመራት ሲጀመር ነው፡፡ተአማኒ የሆኑ የዴሞክራሲያዊና የፍትሕ ተቋማት ባልተመሠረቱበት ሁኔታ ግለሰቦች እንዳሻቸው ሲሆኑ መመልከት በታሪኩ በተደጋጋሚ ለተመለከተው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንግዳ አይሆንም፡፡

ሕዝባችን ሁል ጊዜም ቢሆን አምባገነናዊ ሥርዓትን ለመገርሰስ ሲታገልና መሥዕዋት ሲሆን ግፍ እንዲቆም፣ ፍትሕ እንዲሰፍን እንጂ፤ ሌሎች ግፈኞችን ለመተካት አይደለም፡፡ በሕዝብ ትግል ሥልጣን ላይ የወጡ አካላት ግን ከራሳቸው ፍላጎት ውጪ የሕዝብን ፍላጎት ማሟላት አልቻሉም፡፡ ሕዝቡ ከነገ ዛሬ ይሻሻላል ብሎ በትዕግሥት ቢጠብቅም፤ በተደጋጋሚ ድምፁንም ቢያሰማም ችግሩ ግን ከመሻሻል ይልቅ እየባሰ መጣ፡፡

በተለይም የዴሞክራሲ ምኅዳሩ እየጠበበ፣ ዜጎች በብሔራቸውና በያዙት የፖለቲካ አስተሳሰብ ምክንያት የሚደርስባቸው በደል እየከፋ፣ የሰብአዊ መብት ጥሰቱ እየባሰ፣ ሙስናው ሀገሪቱን እስከ አንገቷ እየዋጣት መጣ፡፡ ሕዝባችንን እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ «በደልና ግፍ በቃን» ብሎ እንዲነሣ ያደረጉትም እነዚህ መከራዎች ነበሩ፡፡

«ግፍ በአገር ሲናኝ፣ ኩበት ሰጥሞ ድንጋይ ይዋኝ» እንደሚባለው፤ ሀገር የሚዘርፉ ጁንታዎች በኩራት በከተሞቻችን እየተንፈላሰሱ፣ ሕግ ያልፈረደባቸው ዜጎቻችን ተፈጥሯዊ የሆኑትን መብቶቻቸውን በመጠቀማቸው ብቻ፣ ውኃ ውኃ የሚያሰኝ ግፍ ይፈጸምባቸው ጀመር፡፡ በሃብት፣ በንብረትና በፖለቲካ ተሳትፎ ከሚሠራው ግፍ በባሰ በዜጎች ሰብአዊ መብት ላይ የሚሠራው ግፍ «ምነው ባልተወለድኩ» የሚያሰኝ ሆነ፡፡ በፖሊስ፣ በደኅንነት፣ በፍርድ ቤቶች፣ በማረሚያ ቤቶችና በሌሎችም የመንግሥት ሐላፊነቶች ላይ በሚገኙ ባለሥልጣናት ፈቃጅነትና መሪነት፣ ኅሊናቸውን ሽጠው ለሆዳቸው ባደሩ የግፍ ሠራዊት ተላላኪነት በዜጎቻችን ላይ አራዊት የማይፈጽሙት ሰቆቃ ይወርድባቸው ነበር፡፡ ግፍ ፈጻሚዎቹ ከሳሽም፣ ምስክርም፣ መርማሪም፣ አሳሪም፣ ዐቃቤ ሕግም፣ ዳኛም፣ ሆነው የግፉን ድራማ ተውነውታል፡፡

ኢትዮጵያ የዓለምን በጎ አስተሳሰብ የቀረጹት የሦስቱ ታላላቅ እምነቶች፡- የክርስትና፣ የእስልምናና የይሁዲነት ሀገር ናት፡፡ አብዛኛው ሕዝባችን ሃይማኖተኛ ነው፡፡ ለሞራል ድንጋጌዎች ከፍተኛ ቦታ የሚሰጥ ማኅበረሰብ አለን፡፡ ታዲያ እነዚህ ሰዎች እንዴት ነው ይሄንን ሁሉ ግፍ ሊፈጽሙ የቻሉት? እነዚህ ሰዎች ማኅበረሰባችንን ቢወክሉ ኖሮ ሊያጠፉ ቢችሉ እንኳን እንዲህ ግፍ በልተው ግፍ ባልተነፈሱ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ሰውነትንም አይወክሉም፡፡ ስግብግብነት፣ አምባገነንነትና የሥልጣን ጥማት ጫፍ ላይ ሲደርሱ ሰውን ወደ አውሬነት እንዴት እንደሚቀይሩት ማሳያ ናቸው፡፡

አሁን ወሳኙ ጥያቄ «ምን እናድርግ?» የሚለው ነው፡፡ መልሱ ሦስት ነው፡፡የመጀሪያው ግፈኞች የግፋቸውን ዋጋ በሕግ እንዲቀበሉ ማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ «ፍርድ ለልጅ፣ጥራጊ ለደጅ» ይተርፋል እንዲሉ ይህ ግፍ በልጅ ልጆቻችን ዳግም እንዳይፈጸም የሚያደርግ አስተማማኝ ሥርዓት

መዘርጋት ነው፡፡ ሦስተኛው ከእነርሱ የተሻልን መሆናችንን በተግባር ማሳየት ነው፡፡ ገፈኞች ግፍ ፈጽመው በሰላም ተኝተው እንዲያድሩ መፍቀድ የለብንም፡፡ እነርሱ ያንን ሁሉ ግፍ ፈጽመው ምንም ሳይመስላቸው በልተው የሚጠግቡ፣ ተኝተው የሚያድሩ ሆነዋል፡፡ እኛ ግን ግፉ ይሰቀጥጠናል፣ ያመናል፣ ዕረፍትም ይነሣናል፡፡ በተለይ ደግሞ የተፈጸመው በአንድ በኩል በዜጎቻችን ላይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በማናውቀው ሁኔታ በየመንደራችን በሚገኙ ድብቅ እስር ቤቶች መሆኑን ስናውቅ ሕመሙ ይብስብናል፡፡ በሕዝባችንም ላይ ይህ አሰቃቂ ግፍ ማንም የማይረሳውን ጠባሳ ጥሎ ያልፋል፡፡ ስለዚህም ይህን ግፍ የፈጸሙ ሁሉ በሕግ ፊት ተገቢውን ቅጣት አግኝተው ተተኪዎቹ ትምህርት፣ ተጎጅዎቹም የኅሊና ዕረፍት እንዲያገኙ ማድረግ አለብን፡፡ እኛ ባንይዛቸው እንኳን የእነዚያ ንጹሐን ደም ካሉበት ይዞ ያመጣቸዋል፡፡

ይህ የእነርሱ አረመኔያዊነት ፈጽሞ መደገም የለበትም፡፡ እነርሱ ስለተቀጡና እኛ ስለተቆጨን ብቻ ግን ከመደገም አናስቀረውም፡፡ ይህንን ግፍ የፈጠሩትን ቀዳዳዎች መድፈን፣ ሕጎችን ማሻሻል፣ አሠራሮችን ማስተካከል፣ ተቋማትን ማብቃት፣ የዝርፊያንና የአምባገነንነት በሮችን መዝጋት አለብን፡፡

አሁን እያከናወንናቸው በሚገኙ የሪፎርም ሥራዎች ጠንክረን መግፋት ያለብን ለዚህ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የዜጎችን ዴሞክራሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶችን በሚገባ የሚያከብርና የሚያስከብር ሥርዓት መገንባት አለብን፡፡ በፍርድ ቤቶቻችን፣ በምርጫ ቦርድ፣ በመገናኛ ብዙኃን ተቋሞቻችን፣ በመከላከያና በደኅንነት ተቋማት፣ በፖሊስና በማረሚያ ቤቶች፣ እየወሰድናቸው የሚገኙ ማሻሻያዎች ዓላማቸው ይሄንን ዘላቂ ሥርዓት እውን ለማድረግ ነው፡፡ ለወደፊቱም በሌሎች ተቋማት ላይ ማሻሻያው ይቀጥላል፡፡

ይህን ግፍ የፈጸሙ ሰዎች በሄዱበትም ሆነ እኛ እንድንሄድ በሚፈልጉት መንገድ መጓዝ የለብንም፡፡ እነዚህ ሦስቱ መርሖቻችን ሊሆኑ ይገባል፡፡

ገፈኞች በጥላቻ ተሞልተው ይኼንን ሁሉ ፈጸሙ፡፡ እኛ ግን ጥላቻቸውን መውረስ የለብንም፡፡ ገፈኞች በጭፍን አእምሮ ይሄን ሁሉ ግፍ በወገናቸው ላይ አዘነቡ፤ የእኛን አእምሮ ግን በበቀል እንዲጨፈን ማድረግ የለባቸውም፡፡

ግፈኞች ሕግን የማያከብሩ፣ ፈጣሪን የማይፈሩ ሆነው የመከራ ዶፍ በሕዝባቸው ላይ አወረዱ፤ እኛ ግን ፈጣሪን እንፈራለን፤ ሕግንም እናከብራለን፡፡ በምንም መልኩ ግፈኞቹ ራሳቸውን እንጂ፣ ግፈኞቹ የበቀሉበትን ሕዝብ ግፋቸው እንደማይመለከተው እናምናለን፡፡ የትኛውም ብሔር ወይም የትኛውም ዘር ግፈኞችን፣ ገራፊዎችንና ጨቋኞችን ሊያበቅሉ ይችላሉ፡፡ አንድ ብሳና ባጠፉ ጫካውን ሁሉ እንደማንቀየመው፣ ግለሰቦች ባጠፉ የምንቀየመው ወይም ጣት የምንቀስርበት ብሔር አይኖርም፡፡

አብዲሳ አጋን፣ ጻጋዬ ገብረ መድኅንን ወይም ታደሰ ብሩን ያፈራው የኦሮሞ ሕዝብ ጽዩፍ የሆኑ እኩያንን የማያበቅልበት፤ ጀግናው አሉላ አባነጋን ወይም ማኅሌታይ ያሬድን ለሀገር ያበረከተው የትግራይ ሕዝብ ታሪክ የማይረሳው በደል የፈጸሙ ወንጀለኞችን የማያፈራበት፤ እነ ቴዎድሮስን፣ በላይ ዘለቀን ወይም ገብርዬን የሸለመው አማራ ሌሎች ግፈኞችን ከውስጡ ሊያስገኝ የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም፡፡

ወንጀለኛ ራሱን ችሎ ወንጀለኛ ለመሆን ከምንም ጋር መለጠፍ እና ማንም ላይ መደገፍ አያስፈልገውም፡፡ ወንጀለኛ እንዲሁ በቁሙ ወንጀለኛ ነው፡፡ ግፍ የሠራው ሰው የሚናገረው ቋንቋ ኦሮሚኛ ቢሆን ኦሮሞውን፣ ትግሪኛ ቢናገር ትግሬውን፣ ከአማራ ክልል ቢወለድ አማራውን፣ ከሲዳማ ቢመጣ ሲዳማውን የሚወቅስ ሰው ካለ እሱ ከታሪክ የማይማር ደካማ ነው፡፡ እኛ ታሪካችንን በሚገባ የምንረዳና ነጋችንን ለማቅናት የምንተጋ እንጂ፣ ለአንድ ገጽ ብለን መጽሐፍ የምንቀድ ሞኞች አይደለንም፡፡ ትናንትም ሆነ ዛሬ፣ ነገም ወደፊትም ወንጀለኞች መፈጠራቸው አይቀርም፡፡ ሁሌም ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር፣ «ወንጀለኞቹን» ሊደበቁበት ከሚፈልጉት ብሔር ነጥለን ማየትና እስከ መጨረሻው ለፍርድ ማቅረብ እንደሚገባን ነው፡፡ እነርሱ ሊደበቁበት የሚፈልጉት ብሔር በምንም መንገድ የእነርሱን ግፍ ተመልክቶ የሚያለቅስ እንጂ ለእነርሱ ግፍ የሚያጨበጭብ ነው ብለን አናምንም፡፡ ይህ ምን ጊዜም የማይቀየር አቋማችን መሆን አለበት፡፡ ፈጽሞ የእነርሱን ስሕተት አንደግመውም፤ ፈጽሞም በቀደዱልን ቦይ አንፈስስም፡፡ እነርሱ እንደ እኛ እንዲሆኑ እንፈልጋለን እንጂ፣ እኛ እንደ እነርሱ አንሆንም፡፡

ቂምና በቀልን ልናስበው አይገባም፤ ፍርድና ፍትሕን እንጂ፡፡ ይህን ሁሉ የምናደርገው እንደ እነርሱ ከጥላቻ ተነሥተን ሳይሆን የሕግ የበላይነት መስፈን ስላለበት ነው፡፡ እንዳይደገም ስለምንፈልግ ነው፡፡ ሌሎች ትምህርት እንዲያገኙ ስለምንሻ ነው፤ያንን የግፍ ታሪክ መዝጋት ስላለብን ነው፡፡ ወንጀለኞቹ ማንም ይሁኑ ማን፣ ከየትኛውም ብሔር ገብተው ይደበቁ፣ የትኛውም ወገን ይጨሀላቸው፣ በወንጀል እስከ ተጠረጠሩ ድረስ ካሉበት አድነን ለሕግ ማቅረባችን ግን አይቀሬ ነው፡፡ ሀገራዊ ወሰንም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ድንበር ወንጀለኞችን ለፍርድ ከመቅረብ አይታደጋቸውም፡፡ ለዚህ መንግሥት ቁርጠኛ ነው፡፡ በአንድ በኩል ራሳችንን ከወጥመዳቸው እየተከላከልን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ግፈኞች ፍትሕ እንዲያገኙ መሥራታችንን እንቀጥላለን፡፡ ግፍ ሠርቶ መደበቅ፣ ዘርፎ መንደላቀቅ አይቻልምና፡፡

ከእንግዲህ እምነታችን በግለሰቦች ፍላጎት ላይ የተንጠለጠለ ሳይሆን በጠንካራና ተአማኒ ተቋማት ላይ ነው፡፡ ግለሰቦች፣ ፍላጎታቸውና ጠባያቸው እንደ የጊዜው ተቀያያሪ መሆኑን በታሪካችን ከበቂ በላይ ተጽፏል፡፡ አሁን አዲስ ታሪክ መጻፍ ይገባናል፤ ያስፈልገናልም፡፡ ሙሉ አቅማችንን ማፍሰስ የሚገባን የሁላችንም ፍላጎት ተቀናጅቶ በሚፈጥራቸው ጠንካራ ተቋማት ላይ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ተቋማት ዘላቂና በጊዜ ሂደት የማይቀያየሩ፣ ሰቆቃን የሚያስቀሩ፣ ሁላችንንም እኩል የሚያይ ሥርዓት የሚዘረጉ እንጂ ለግለሰቦች ፍላጎት የሚገዙ አይደሉም፡፡

**ኢትዮጵያ፣ በልጆቿ ጥረትና ኅብረት**
**ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# ለክርስትና እምነት ተከታዮች የገና መልእክት

**ታኅሣሥ 28/2011 ዓ.ም.**

ለመላ የክርስትና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በሙሉ፤ እንኳን ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ፡፡

የገና በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ሲል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በከብቶች በረት መወለዱን የምናስብበት ታላቅ በዓል ነው፡፡ ኃይል፣ ሥልጣን፣ ጦርነትና ጭቆና የለመዱት የዚያን ዘመን ሕዝቦች ግን ንጉሥ አድርገው የሚገምቱት በእግሩ ረግጦ፣ በእጁ ጨብጦ፣ በጦሩ ቀጥቅጦ፣ በሰይፉ ቆራርጦ የሚገዛቸውን ነበርና በትሕትና፣ በፍቅር፣በይቅርታና በሰላም የመጣውን ጌታ ለመቀበል አልቻሉም፡፡

ክብርና ነጻነትን፣ ሰላምና ፍትሕን፣ ዕድገትና ብልጽግናን በተሳሳተ መንገድ ነበር ሲፈልጉት የነበሩት፡፡ በጦር አንደበትና በፈረስ ጉልበት ነበር ንጉሣቸውን የሚፈልጉት፡፡ የተሳሳተውን መንገድ እንደ ትክክል ስለቆጠሩትና ስለለመዱት፣ ትክክለኛው ንጉሥ በትክክለኛው መንገድ ሲመጣ እንግዳ ሆነባቸው፡፡ እንደ ሄሮድስ ያሉት ጦር ናፋቂዎች ለሰላም ጥሪው ሰይፍ መዘዙ፡፡ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ደግሞ ጥቅማችንን፣ ክብራችንንና ሥልጣናችንን እናጣለን ብለው ስለሠጉ ፍቅርን በጠብ፣ ይቅርታንም በብጥብጥ ሊያጠፉ ተነሡ፡፡ ከዚያ በፊት በሮማውያን ጭቆና ሲሰቃዩ የነበሩ የኀበዝ አለቆች፣ የመጣላቸውን ሰላም ማጣጣም አቅቷቸው ተሸነፍን በሚል ድርቅታ ደብቀውት የነበረውን ሰይፍና

*ጎመዳቸውን እንደገና ማዘጋጀት ጀመሩ፡፡የቤተልሔም ሕዝብም የክርስቶስ መወለድ በሕይወቱ የሚያመጣለትን ድኅነትና ለውጥ ሊገነዘበው ስላልቻለ በሩን ዘግቶ ተኛ፡፡ ድንግል ማርያምም ልጇን የምትወልድበት ሥፍራ አጣች፡፡ ጥቂት እረኞች ብቻ ነበሩ ነገሩ የገባቸውና፣ እየሆነ በነበረው ነገር በውል የተጠቀሙት፡፡*

*ወቅቱ እስራኤላውያን የተከፋፈሉበት ወቅት ነበር፡፡ የሮም ደጋፊና ተቃዋሚ፤ ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያንና ኤሴያውያን፤ አይሁዳዊና ሳምራዊ፣ ጸሐፍትና ቀራጮች፣ የሄሮድስና የጲላጦስ፣ ዐርበኛና ባንዳ በሚሉ የመከፋፈያ ጥጋጥጎች እስራኤላውያን እዚህ እና እዚያ ሆነው ይቆራቆሱ ነበር፡፡ ክርስቶስ የተወለደው በዚህ ጊዜ ነው፡፡ሁሉም አልቀበለው ያሉት ነገሩን ከየጥቅማቸው አንጻር ብቻ ስላዩት ነው፡፡ እነርሱን ብቻ ካላከበረ፣ ካልጠቀመና ለእነርሱ ብቻ ካልመጣ ብለው እምቢ አሉት፡፡ የእነርሱ ብቻ እንጂ የሌሎችም ጭምር እንዲሆን አልፈለጉትም፡፡*

*ሰብአሰገል ከሩቅ ሀገር ዜናውን ሰምተው ሲመጡ፣ እዚያው ቤተልሔም ያሉት ግን ዐይኔን ግንባር ያድርገው ብለው በግዴለሽነት ትተውት ነበር፡፡*

*የሮማውያንን ጭቆና፣ የጥንታዊት ሀገራቸውን መፈራረስ፣ የታሪካቸውንና የማንነታቸውን መዳከም እያነሡ ይቆጫሉ፣ ይበሳጫሉ፡፡ ነገር ግን የጠፋውን ለመፈለግ፣ የወደቀውን ለማንሣት፣ የደከመውን ለማበርታትና የተሰበረውን ለመጠገን ከመጣው ከክርስቶስ ጋር ለመሆን ግን በፍጹም አልፈለጉም፡፡ ችግሩን ያውቁታል፤ መፍትሔውን ግን ትተውታል፡፡ ተባብረውና ተስማምተው የማያውቁት አይሁድና ሮማውያን እንኳን፣ ክርስቶስን ለመቃወም ሲሉ የጋራ ግንባር ፈጠሩ፡፡*

*የክርስቶስን ልደት ስናከብር እነዚህን ሁሉ ነገሮች አብረን ልናስባቸው ይገባል፡፡ የክርስቶስ ልደት የልዩነትን ግንብ ያፈረሰ፣ የጠብን ግድግዳ የናደ፣ የጥላቻን መጋረጃ የቀደደ፣የተዋረዱትን ያከበረ፣ የተለያዩትን አንድ ያደረገ፣ የተበተኑትን የሰበሰበ ነው፡፡ የክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት «እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ እጅጉን ይልቃል» ተብሎ*

እንደተጻፈው፤ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ካደረጋቸው ነገሮች ሁሉ ይህ ስጦታ ታላቁ ስጦታ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ በዓል የክርስትና አስተምህሮ መሠረት የሆነ ታላቅ በዓል ነው፡፡ አንድ ነገር ታላቅ ስጦታ ስለሆነ ብቻ ሁላችንንም አይጠቅምም፡፡ በቤተልሔም ከተማ ከነበሩት እንኳን ብዙዎቹ በክርስቶስ ልደት ሳይጠቀሙ ቀርተዋል፡፡

ልዩነቱ የተፈጠረው ስጦታውን በመቀበልና ባለመቀበል ነው፡፡ አብሮ በመሥራትና ባለመሥራት ነው፤ ዐውቆ በመጠቀምና ባለመጠቀም ነው፡፡

የቤተልሔም ሰዎች በከተማቸው የዓለምን ታሪክ የሚለውጥ ተአምር እየተሠራ መሆኑን አልተረዱም፡፡ እንኳን ታሪክ ሊሠሩ ታሪክ ሲሠራ ለማየትም አልፈቀዱም፡፡ ሌሎች ከሩቅ ሀገር ይህንን ታሪክ ለማየትና ለመስማት ሲመጡ ነው የደነገጡት፡፡ ሄሮድስም ራሱን ለመፈተሽ አልፈለገም፡፡ ሥልጣኑን በመሣሪያ ኃይል የሚያስጠብቅ መስሎት የቤተልሔም ሕጻናትን ነው ያስፈጀው፡፡ የሚገርመው ነገር የክርስቶስን መወለድ በቸልታ ያለፉት ግዴለሾቹ የቤተልሔም ሰዎች መከራው ግን አልቀረላቸውም፡፡ ሄሮድስ የጨረሰው የእነርሱን ልጆች ነው፡፡ መከራን በመጋፈጥ እንጂ በመተኛት ለማምለጥ አይቻልምና፡፡ ሊቃውንተ አይሁድም ዕውቀታቸውን እየጠቀሱ በመራቀቅ ጊዜውን ያለተሳትፎ አሳለፉት፡፡ ከተማሩት ሊቃውንት ይልቅ ያልተማሩት እረኞች ተጠቀሙ፡፡ ዛሬም እንኳን በታሪክ የምናስታውሰው እነርሱኑ ነው፡፡ የተናቁት የቤተልሔም ከብቶች ያደረጉትን አስተዋጽዖ ያህል በዳዊት ከተማ በመኖራቸው በታሪካቸው የሚመጻደቁት ቤተልሔማውያን አንዳች ለማድረግ አልቻሉም፡፡

የክርስቶስን መወለድ ስናስብ ሀገራችንንም እናስባት፡፡ በቤተልሔምና በዙሪያዋ የነበሩ ሁኔታዎች ዛሬም በሀገራችን አሉ፡፡ ቤተልሔማውያን በእጃቸው ያገኙትን ጸጋ መጠቀም አልቻሉም፡፡ በቅናት፣ በግዴለሽነት፣ በጥቅም ሽኩቻ፣ በየወገኑ በመከፋፈልና በሥልጣን ጥም ተነክረው ዕድላቸውን አባከኑት፡፡ እኛም በዘመናችን ያገኘነውን ሀገራችንን የመለወጥ፣ የማሻሻል፣የማሳደግና የማዘመን ዕድል እንዳናጣው እንደልባም ሰው ማሰብ አለብን፡፡ እንደ ቤተልሔማውያን በቅናት ተቃጥለን፣ በግዴለሽነት ተኝተን፣ በጥቅምና በሽኩቻ

ተባልተን፣በመከፋፈል ተበታትነን፣ በሥልጣን ጥም ሰክረን ያገኘነውን ዕድል ከእጃችን ላይ እንዳንጥለው የምናስብበት ጊዜ ላይ ነን፡፡

ክርስቶስ ሁሉን ነገር ትቶ በረት ላይ እንዲተኛ ያደረገው ለእኛ ለወገኖቹ ያለው ፍቅር ነው፡፡የሚያሰልፈው የመላእክት ሠራዊት አጥቶ አይደለም፤ በመብረቅ ማጥፋት፣ በንፍር መምታት ተስኖትም አይደለም፡፡ ፍቅር ያድናል፣ ይቅርታ ይጠግናል ብሎ እንጂ፡፡ ወገናችንን በእውነት የምንወድ ከሆነ ሰላምን እንጂ ሰይፍን ለምን እናስቀድማለን? ፍቅርን እንጂ ጠብን ለምን እንሰብካለን? አንድነትን እንጂ መለያየትን ለምን እናመርታለን? ይቅርታን እንጂ ጥላቻን ለምን እንተክላለን? ይህ በዓልኮ ሰውና መላእክት፣ ፍጡርና ፈጣሪ፣ ነፍስና ሥጋ፣ ሰማይና ምድር አንድ የሆኑበት በዓል ነው፡፡ መለያየትንና መጠፋፋትን እየዘራን እንዴት ልናከብረው እንችላለን?

ይህ በዓልኮ «ሰላም በምድር ይሁን» የተባለበት ነው፡፡ የጦርነትን ዘገር እየነቀነቅን እንዴት ልናከብረው እንችላለን? ይህ በዓልኮ እረኞችና ከብቶች መጠለያ ያጣውን ጌታ ያስጠለሉበት በዓል ነው፡፡ ታድያ ዛሬ ሂድ፣... ውጣ፣.... ልቀቅ፣.... እያልን የገዛ ወገናችንን እያሳደድን እንዴት ልናከብረው እንችላለን? ይህ በዓልኮ ለወገን ጥቅም ሲሉ ራስን የመስጠት በዓል ነው፡፡ ለራሳችን ጥቅም ስንል ወገኖቻችንን እያጋደልን እንዴት ልናከብረው እንችላለን? ይህ በዓልኮ ሰውና መላእክት አንድ ሆነው የሰላም መዝሙር የዘመሩበት ድንቅ በዓል ነው፡፡ ተለያይተን የጦርነት ነጋሪት እየጎሰምን እንዴት ልናከብረው እንችላለን?

ሰብኣ ሰገል የተወለደውን ሕጻን ለማግኘት ከሄዱበት ዐውድ ብዙውን ነገር ቀይረው ወደ ሀገራቸው መመለሳቸውን መጽሐፍ ይናገራል፡፡ እኒያ የጥበብ ሰዎች የሰላሙን ንጉሥ ካገኙት በኋላ በሌላ መንገድ፤ በሌላ ኃይለ ቃል እና በሌላ እምነት የመልስ ጉዟቸውን አድርገዋል፡፡ ሲሄዱ በሄሮድስ ቤተ መንግሥት በኩል ቢሆንም ሲመለሱ ግን ጎዳናቸውን ቀይረዋል፡፡ ሲመጡ «የአይሁድ ንጉሥ የት ነው?» እያሉ ቢፈልጉትም አግኝተውት ሲመለሱ ግን «የዓለማት ንጉሥ» ብለው ተናግረዋል፡፡ «ወዴት አለ?» ብለው እየፈለጉት መጥተው ነበር፡፡ አግኝተውት ሲመለሱ ግን «አገኘነው» ብለው ተደስተዋል፡፡ ከእነዚያ የጥበብ መንገደኞች መካከል ኢትዮጵያውያን ዋኖቻችንም ነበሩበት፡፡

እኛ የእነርሱ ልጆችም ዛሬ ሰላምን፣ ፍቅርን፣ ትሕትናን፣ አብሮነትን እና መከባበርን አስቀድመን መደመር አለብን፡፡ እንዲያ ከሆነ የነገ ተነገ ወዲያ በዓሎቻችንን «ሰላማችን ወዴት አለ?» በሚል ጥያቄ ሳይሆን «ሰላማችንን አገኘነው» በሚል የማረጋገጫ ቃል እንደምናከብር ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ እኛም ከትዕቢት ይልቅ ትሕትናን ገንዘባችን ብናደርግ ወደ ጥላቻ እና ወደ መከፋፈል ከሚወስደው መንገድ ወጥተን በሌላ የፍቅር፣ የመደመር፣ የአብሮነት እና የመተማመን ጎዳና ወደ ከፍታችን እንደምንጓዝ እምነቴ የጸና ነው፡፡

«የመጣው እና ይመጣ ዘንድ ያለው ለውጥ በሁላችንም ጥረት የመጣ ነው» ከሚለው የባለቤትነት ስሜት ጀምሮ «ለሁላችንም የሚበጅ ነው» እስከሚለው የመተማመን ጫፍ ድረስ ቅን መሆን ብንችል፤ «የእገሌ እና የእንቶኔ ለውጥ» ከሚል መጠቋቆም ተላቀን እና እጅ ለእጅ ተያይዘን፣ ለሁላችንም የምትበጅ ኢትዮጵያን እንደምንገነባ ቅንጣት ጥርጣሬ የለኝም፡፡

ፈጣሪ ሀገራችንን የምናሳድግበትንና ራሳችንንም ለታላቅነት የምናበቃበትን ዕድል ሰጥቶናል፡፡ እንደ ቤተልሔም ሰዎች ስንዘናጋ፣ እንደ ሄሮድስ ሾተል ስንሞርድ፣ እንደ ሊቃውንተ አይሁድ በትንሽ በትልቁ ስንጨቃጨቅ፣ እንደ ዘመኑ ሰዎች ስንከፋፈል፣ እንደ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ሥልጣንና ጥቅም ቀረብን ብለን በኩርፊያ ስናምጽ፣ ዕድሉ እንዳያልፈን፡፡ እንደ እረኞችና እንደ ሰብአ ሰገል ዐውቀን እንጠቀምበት፡፡ የሚጠበቅብንን አድርገን የሚገባንን እናግኝ፡፡ታሪክ ማለፉ ላይቀር ወቀሳና ከሰሳን ለትውልድ አናስተላልፍ፤ እኛ በሌሎች እንደተማርነው ሁሉ፣ ሌሎችም ነገ በእኛ መማራቸው አይቀርምና፡፡

**ኢትዮጵያ፣ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፣**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**መልካም በዓል!**
**አመሰግናለሁ፡፡**

# ለክርስትና እምነት ተከታዮች የጥምቀት መልእክት

**ጥር 10/2011 ዓ.ም.**

***ለመላ የክርስትና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በሙሉ፣ እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ!***

በሀገራችን በድምቀት ከሚከበሩትና ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ከሚያሳዩት በዓሎቻችን ውስጥ አንዱ የጥምቀት በዓል ነው፡፡ ቀደምት አባቶቻችን እና እናቶቻችን ይህንን በዓል እንድናከብር ሥርዓት ሲሠሩ በአንድ በኩል በትሕትና ስለ ዝቅ ማለት እና ስለ መለወጥ፣ በሌላም በኩል ደግሞ ስለ መደመር ሊያስተምሩን የፈለጉ ይመስለኛል፡፡ የቃና ዘገሊላን በዓል ያስከተሉትም መለወጥ ምን ማለት እንደሆነ ይበልጥ እንድንረዳው ነው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላእክት ትቶ በባሕር መካከል ተገኘ እንላለን፡፡ ዝቅ ያለው ከፍ ሊያደርገን፣ የወረደውም ሊያወጣን ነው፡፡ ሕዝባችን ወደ ሥልጣኔ ሠገነት ከፍ እንዲል ከፈለግን፣ እኛ ዝቅ ማለት አለብን፡፡ መውረድ አለብን፡፡ ሳይወርዱ መውጣት፣ ዝቅ ሳይሉ ከፍ ማድረግ ፈጽሞ አይታሰብም፡፡ እርሱ በመንበሩ ሆኖ «ኑ» አላለንም፡፡ እንደማንችል ያውቃልና ወደኛ መጣ፡፡ ሕዝቡን ይህንን አድርግ፣ ይህንን ሥራ፣ እንዲህና እንዲያ ሁን ማለት ለውጥ አያመጣም፡፡ ይልቅስ ወደ ሕዝቡ እንውረድ፡፡ ችግሩን እንቅመስለት፣ መከራውን እንይለት፣ ተሽከርካሪ ወንበሮቻችንን፣ ያማሩ ቢሮዎቻችንን ትተን

ወደታች፤ ወደ ችግሩ ዝቅ እንበል፡፡ ሐኪሙ ወደ ሕመምተኞች፣ ባለሥልጣኑና ባለሞያው ወደ ባለጉዳዮች፣ ሥራ አስኪያጁ ወደ ተራዎቹ ሠራተኞች፣ መምህሩ ወደ ተማሪዎች፣ በአጠቃላይም አገልጋዩ ወደ ተገልጋዮች እንውረድ፡፡ ሕዝቡን ወደ እኛ ውጣ አንበለው፡፡ ክርስቶስ ወደ ባሕሩ ሰው ፍለጋ ሲወርድ መላእክቱም አብረውት ወረዱ፡፡ እኛ መውረድ ከጀመርን ሌሎችም ተከትለው ወደ ሕዝቡ ይወርዳሉ፡፡ የሕዝቡንም ችግር ያያሉ፡፡ አይተውም ይፈታሉ፡፡

አስቀድሞ የሕዝብን ችግር ለመፍታት ወደ ሕዝብ መውረድ የለመደ ኑሮውም ሕይውቱም የሕዝቡ ነውና በኋላ ከሥልጣኑ ሲወርድ አይጨንቀውም፤ አይጠበውም፡፡ በፊትም ቢሆን ወደ ሕዝብ የወረደ እና ውክልናውም ሆነ ውግንናው ከሕዝብ ነውና የመውረድ ኑሮ ግር አይለውም፡፡

ይህ በዓል የመለወጥ በዓል ነው ብለናል፡፡ ከተለወጡት ውስጥም አንዱ ውኃ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከውኃው መለወጥ በፊት በነበረው ታሪኩ ውኃን የሚያስታውሰው በቁጣ መሣሪያነቱ ነው፡፡ የሰው ልጅ በውኃ ጠፍቷል፡፡ አሁን ግን ክርስቶስ ወደ ውኃው መጣ፡፡ የመዓቱን ውኃ የምሕረት አደረገው፡፡

በሀገራችንም ሕዝባችን በክፉ የሚያስታውሳቸው አያሌ ሞያዎችና ተቋማት አሉ፡፡ በቢሮክራሲያቸው፣ በግፋቸው፣ በማሰቃያነታቸው፣ በሰብአዊ መብት ጥሰታቸው፣ በአሳዳጅነታቸው፣ በኢፍትሐዊነታቸው፣ በአድሏዊነታቸው፣ ለተወሰኑ አካላት ጥቅም በመቆማቸው የተነሣ በመዓት የምናስታውሳቸው ተቋማት አሉን፡፡ አሁን የሚሻለን ምርጫ አልባ ምርጫ እነዚህን የክፋት መታወሻዎች እንደ ውኃው ሁሉ ወደ በረከትነት መቀየር ነው፡፡ ለመዓት የነበረው ውኃ ለምሕረት እንደተለወጠው ሁሉ በክፉ ሥራቸው የምናስታውሳቸውን ተቋሞቻችንንም ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ እንዲሠሩ አድርገን እንለውጣቸው፡፡ ሕጋቸውን፣ አሠራራቸውን፣ አደረጃጀታቸውን፣ ዕሴቶቻቸውን፣ አስተሳሰባቸውንና አካሄዳቸውን ሁሉ ለፍትሕ እና ለእኩልነት ወደ ወገነ መልክ እንለውጣቸው፡፡

ክርስቶስ ከመንገድ ጠርጎ ያስወገደው ነገር አለ፡፡ ለውጦ እንድንጠቀምበት ያደረገውም አለ፡፡ እኛም ከመንገዳችን ማስወገድ ያለብን ነገር አለ፡፡ ፈጽሞ እንዳንሄድ፣ ነጻ እንዳንወጣ፣ አንገታችንን እንድንደፋ፣ ቅስማችን እንዲሰበርና

መንፈሳችን እንዲታወክ ያደረገውን ነገር ከመንገዳችን ገለል እናደርገዋለን፡፡ እርሱ የማይለወጥ ነው፡፡ የማይለወጥን ነገር ለመለወጥ መነሣት ነፋስን እንደሚከተል ሰው ትርፉ ድካም ነው፡፡ ግን ደግሞ ሁሉን አስወግደን አንዘልቀውም፡፡ በምሬታችን፣ በቁጣችን፣በደረሰብን ግፍና መከራ ልክ ሁሉንም እናስወግድ ካልን የሚተርፈን አንዳች ነገር የለምና ሀገር ባዶዋን ትቀራለች፡፡ የተዋረደች ሀገር ከፍ እንድትል ማስወገድ ያለብን ነገር የመኖሩን ያህል መለወጥ ያለብንም ብዙ ነገር አለ፡፡ ውኃውን ሁሉ ማፍሰስ የለብንም፤ አንዳንዱን ወደ ወይን ጠጅነት እንዲቀየር ማድረግም ከሰሞኑ ጥምቀት ልንወርሳቸው ከሚገቡን ቁም ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

በዚህ ቀን አንድ ታላቅ ሰው እናስታውሳለን፤ መጥምቁ ዮሐንስ፡፡ እውነተኛ፤ ቆራጥ፣ፊት አይቶ የማያደላ፣ ሰው እንዲለወጥ እንጂ እንዲጠፋ የማይፈልግ፣ ለድሆች ጥብቅና የሚቆም ሰው ነው፤ ዮሐንስ፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዮሐንስ ከመምጣቱ በፊት ብዙ ሰዎች ቀድመው መጥተው ነበር፡፡ ዮሐንስ በዚያ በረሐ ሦስት ነገሮችን ያደርግ ነበር፡፡ የሚመጡ ሰዎች ሲጠይቁት የሚገባቸውን ይነግራቸዋል፡፡ ምንን መለወጥ እንዳለባቸው ይመክራቸዋል፡፡ ቀጥሎም ካልተለወጡ ምን እንደሚያጋጥማቸው ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ ከዚያም ዋና ተልዕኮው የሆነውን ማጥመቁን ይቀጥላል፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ በዋናው ተልዕኮው ላይ ሲያተኩር እንጂ ጊዜውን ከመጡት ሰዎች ጋር በመጨቃጨቅና እነርሱንም ለማሳመን በመጣጣር ሲያጠፋ አናየውም፡፡ለእርሱ ዋናው ጉዳይ ተልዕኮውን መፈጸሙ ነው፡፡ በዓላማው ላይ ያተኩራል እንጂ ሰዎች በሚፈጥሩለት አጀንዳ ውስጥ ገብቶ ዘይት እንደሚጨምቅ ግመል አታካች አዙሪት ውስጥ አይኳትንም፡፡ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን መጥተው ነበር፡፡

ቀራጮች ወይም ግብር ሰብሳቢዎችም መጥተው ነበር፡፡ ወታደሮችም መጥተው ነበር፡፡ ለሁሉም የሚገባቸውንና ማሻሻል ያለባቸውን ነገራቸው፡፡ ከዚያም ወደ ዋናው ተልዕኮ ገባ፡፡ የኛም የለውጥ ጉዞ መርሕ ይህ መሆን አለበት፡፡

ጉልበታችንን፣ ጊዜያችንን፣ ገንዘባችንን እና ልምድ እውቀታችንን በዋነኝነት ማዋል ያለብን ዋናው የለውጣችን ተልዕኮ ላይ ነው፡፡ በጎዳናችን ከሚያጋጥሙን አይለወጤዎች ጋር ሁሉ ስንከራከር፣ ስንጨቃጨቅ፣ መልስ ስንሰጥና እነርሱን እናሳምናለን ብለን ስንደክም አንውልም፡፡ እንዲለወጡ እንንገራቸው፤ መንገድ እናሳያቸው፤ ቅን ልብ ይዘን እንቅረባቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ያለውን ለራሳቸው እንተወው፡፡

ጎበዝ ሯጭ በመንገዱ ግራና ቀኝ ያሉ ተመልካቾች ለሚሰነዝሩበት ነገር ሁሉ መልስ አይሰጥም፡፡ ፈተናውም የሁሉም ኢትዮጵያ ልጆች እንቅፋት መሆኑን በመረዳት እጅ ለእጅ ተያይዘን በፍቅር እና በመደመር ልንሻገረው ይገባል፡፡ ጥምቀት የሽግግር ወቅትም ነው፡፡ ለዓለም ሳይገለጥ የቆየው ክርስቶስ ለዓለም የተገለጠበት ድንቅ በዓል ነው፡፡ ለዚህም ነው የመገለጥ ወይም የአስተርእዮ በዓል የሚባለው፡፡

ጥምቀት መገለጥ ቢሆንም ክርስቶስ ለሁሉም የተገለጠው ግን ከተጠመቀ ከዐርባ ሦስት ቀናት በኋላ ነው፡፡ ክርስቶስ በተወለደበትና ለዓለም በተገለጠበት ጊዜያት መካከል ብዙ ዘመን አልፏል፡፡ አንድ ነገር የሚጀመርበትና የሚገለጥበት ጊዜ ይለያያል፡፡

በዚህች ሀገር ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ትግሉ ከተጀመረ ቆይቷል፡፡ ለውጡ ሕጋዊና ተቋማዊ ሆኖ የተገለጠው ግን በቅርቡ ነው፡፡ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ለዓለም ከተገለጠ በኋላ ዐርባ የሽግግር ቀናት አልፈዋል፡፡ በነዚያ ዐርባ የሽግግር ቀናት ብዙ ፈተናዎች ነበሩ፡፡ ብዙ ጥያቄዎችም ነበሩ፡፡ ያለንበት ጊዜም እንደዚያው ነው፡፡ የጀመርነውን የለውጥ ሂደት ሁሉም እስኪረዳው፣ ሁሉንም እስኪነካ፣ በሁሉም ቤት እስኪገባ ድረስ ብዙ ፈተናዎች፣ ብዙ ጥያቄዎች ይኖራሉ፡፡ እርግጠኛ የምንሆነው ዋና ጉዳይ ግን ሁሉንም ፈተናዎቻችንን በድል የማለፋችን ነገር እርግጥ መሆኑን ነው፡፡

ጥምቀት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ልዩ በዓላችን ነው፡፡ ከከተራ ቀን ጀምረን ውኃ ባለበት ሜዳ ተሰብስበን እናከብረዋለን፡፡ ኢትዮጵያችን የሁላችንም መሆኗን የምናሳይበት በዓላችን ነው፡፡ «ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ...» ብለን የየባህላችንን

አልባሳት ለብሰን የምንወጣበት ደማቅ በዓላችን ነው፡፡ የሁላችንም ቋንቋ፣ የሁላችንም ዜማ በአንድ መስክ ላይ ኅብር ሆኖ የሚቀርብበት የመደመር በዓል ነው፡፡ እዚህ አማርኛ፣ እዚያ ትግርኛ፣ እዚያ ወላይትኛ፣ እዚያ ጉራግኛ፣ እዚያ አገውኛ፣ እዚያ ሲዳምኛ፣ እዚያ ሶማልኛ፣ እዚያ ኦሮምኛ፣ እዚያ ኩናምኛ፣ እዚያ አፋርኛ፣ እዚያ በርትኛ፣ እዚያ አኝዋክኛ ይዜማል፡፡ ሁሉም ያለውን ይዞ ይወጣል፡፡ አንዱ ወደ ሌላው ሄዶ ይጋራል፤ የራሱንም ያጋራል፡፡ መደመር ይሄ ነው፡፡

የጥምቀት በዓል ውበት ከመደመር ዕሴቱ የሚመነጭ ነው፡፡ «የነብርን ጅራት አይዙም፤ ከያዙም አይለቁም» እንደሚባለው የለውጥ ጉዟችንን ይዘናል፡፡ የለውጡ ፋና ይበልጥ እየተገለጠ በሄደ ቁጥር ችግሮቻችንም ይበልጥ እየቀነሱ ይሄዳሉ፡፡ በዋናው ተልዕኳችን ላይ አተኩረን ጋሬጣዎችንና ዕንቅፋቶችን ካለፍናቸው ከባሕር ወለል በታች የጀመርነውን ለውጥ ከከፍታ በላይ እንጨርሰዋለን። የምንጠብቀውም ሆነ የማንጠብቀው ችግር ከምንጓጓለት ግብ እንዳያስቀረን ትኩረታችንን በለውጥ ሂደታችን ላይ እናድርግ፡፡ ያንን ካደረግን በጥምቀት መስክ ላይ የምናያትን ኢትዮጵያ በሁሉም መስኮች ላይ እናያታለን፡፡

**ኢትዮጵያ፣ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፣**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# ለከተሞች ቀን ክብረ በዓል የተላለፈ መልእክት

**የካቲት 8/2011**

ከተሞቻችንን የሥልጣኔ ማዕከላት እንዲሆኑ የዘንድሮ የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በጅግጅጋ ከተማ ይከበራል፡፡ ከተሞች የደረሱበትን ደረጃ የሚመዝኑበት፣ ልምድ የሚለዋወጡበት፣ የላቀ ልማትና የሥራ ውጤት፣ የተሻለም አስተዳደር ያስመዘገቡ የሚመሰገኑበትና የሚሸለሙበት መድረክ ነው፡፡
የዘንድሮው በዓል በተለይም የኢትዮጵያዊነትን ቀለምና ውበት የምንዘክርበት፤ መደመር ለከተሞች ሰላምና ብልጽግና መሠረት መሆኑን የምናጠናክርበት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በሀገራችን በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት በብልሐትና በብቃት የሚያስተናግዱ፣ ለነዋሪያቸውም ሆነ ለአድሮ ሂያጅ ምቹ የሆኑ፣ የኅብረ ብሔራዊነታችን ማሳያና ከራስ አልፎ በሌሎች የሚወደዱ፣ ለሀገር ሰላምና ልማትም አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ከተሞችን ለመፍጠር መትጋት የክብረ በዓል ብቻ ሥራ አይደለም፡፡ እንድናስታውስና እርስ በእርሳችን እንድንማማር መድረክ ይከፈታል እንጂ፡፡ በመሆኑም ይህን በዓል ስናከብር የተሠራውን እያደነቅን፣ እየተማማርን፣ የቤት ሥራችንንም እየለየን የምንንደረደርበት ይሆናል፡፡

ባለፉት ጥቂት ወራት ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ካለቺው ለውጥ አንፃር ከተሞቻችን የመደመር መናኸሪያዎች፣ የትስስርና የአንድነታችን መገመጃዎች

እንዲሆኑ መሥራት ያለብን ወቅት ላይ እንገኛለን። በመደመር እሳቤ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የትም ሄዶ መሥራት፣ መኖር፣ መበልጸግና ከሌሎች የሀገሩ ልጆች ጋር እኩል መብት የመጋራት ሕገ መንግሥታዊ መብቱን መጠቀም እንዲችል ከተሞች የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት መዘጋጀት አለባቸው።

የከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ፣ በቂና ጥራት ያለው መሠረተ ልማትና አገልግሎት ለመስጠት አስተዳደርን ማቀላጠፍ፣ ሥራ አጥነትን መቀነስ፣ የመሬት አስተዳደርን ማሻሻል፣ አረንጓዴነትን ማስፋፋትና ቴክኖሎጂና ፈጠራን ተጠቅሞ መሠልጠን ዋና ተግባራቸው ነው። የለውጥ አቅጣጫችንም በሁሉም የአሠራር መዋቅሮች ይህንኑ ሕዝብ ተኮር የሆነ የአገልግሎትና የተቋማት ግንባታን ይሁነኝ ብሎ እስከ ታች ድረስ ለማዳረስ፤ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅሙን በማደራጀት ተጨባጭ ተቋማዊ ማሻሻያዎች አድርጓል።

ይህም በአንድ ጀምበር ሳይሆን በሂደት በሁሉም ከተሞች የሚታይ ለውጥን እንደሚያመጣ አያጠራጥርም። ከዚህ አንጻር የከተማ ነዋሪዎች የሚያነሡዋቸው ፍትሐዊና ምክንያታዊ የመኖሪያ ቤት፣ የውኃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የትራንስፖርት፣ የመንገድ፣ የጤና፣ የፍሳሽና ቆሻሻ አወጋገድ ወዘተ ጥያቄዎችን ለመመለስ እነዚሁ የመንግሥት መዋቅሮች ተግተው ይሠራሉ።

የከተሞች ቀንን ስናከብር ሌላው ማሰብ ያለብን ስለ ከተሞቻችን የእርስ በእርስ ትብብር፣ መማማርና መረዳዳት ነው። ይህ ሲሆን አንዳችን ከአንዳችን ስኬትም ሆነ ስሕተት ትምህርት እየወሰድን ሀገራዊ ዕድገታችንን የበለጠ ለመደገፍ መንገድ እንከፍታለን።

የሀገራችን ለውጥ እየበሰለ፣ እየጎመራ፣ ሁሉም ዓይኑን ወደ እኛ እየጣለና “ምን እናግዛችሁ፣ እንዴትስ የዚህ ታሪካዊ ክሥተት አካል እንሁን?” የሚልበት ወርቃማ ጊዜ ላይ እንገኛለን። ወርቃማው ጊዜ ዋጋ እንዲኖረው የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ ሙዓለ ንዋይን ለመሳብ የማንተኛ፣ ለመማር የምንፈጥን፣ ለመተባበር የማንለግም፣ ለመለወጥ የምንጓጓ መሆንን ይጠይቃል። ሌሎች ከኛ ለመጠቀም ሲችሉ እኛ እራሳችንን እንዴት እንጥቀም የሚል አስተሳሰብን ሰንቀን መጓዝም የግድ ይለናል።

ኢትዮጵያውያንም በኢትዮጵያ ውስጥ እስካለን እኩል ተጠቅመን ለመበልጸግና ሀገር ለማልማት ኢትዮጵያዊ መተባበርን መገንዘብ፣ በመደመር መገናዘብን ይጠበቅብናል። አንድ አካላችን ታሞ ሙሉ ጤና ሆኖ ውሎ ማደር ይቻል ይሆናል። መክረም ግን አዳጋች ነው። የታመመ አካላችንን ማከም የምንችለው ደግሞ የተባበርን የተደመርን እንደሆነ ነው። ይህንኑ እሳቤ ይዘን ነገ ማየት ለምንፈልጋት የልጆቻችን ኢትዮጵያ፣ ዛሬ ተባብረን መሠረት መጣል አለብን፡፡ ለዚህ ደግሞ ከተሞቻችንን የኅብረት ዐውድማ ማድረግ ይጠበቅብናል። ከተሞች በዜጎችና በብሔሮች ስብጥር የኢትዮጵያ ናሙና ናቸው፡፡ ከተሞችን የኅብረት ዐውድማ ስናደርግ የምርት፤ የጉልበትና የአገልግሎት ግብይቱ ለሁሉም ትሩፋት ያመጣል፤ ከተሞችን የኅብረት አውድማ ስናደር የሁሉም ድምፅ ተሰምቶ ፍትሕና ርትዕ አካል ይነሣል፡፡ ከተሞችን የኅብረት ዐውድማ ስናደርግ ብዝኃነት ያላቸው ማንነቶች የተደመረ ጥበብ አፍልቀው ፈጠራ ይበልጥ ይመጥቃል፤ ይጠልቃል፡፡

የዘንድሮን የከተሞች ቀን ስናከብር ከተሞች የቁሳዊ ልማታቸው ደረጃ የት እንደደረሰ ከመፈተሽ ባሻገር፤ በከተሞች ውስጥ በቋሚነት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዜግነታቸው እንዲከበር፣ ፍላጎትና ጥቅማቸው እንዲጠበቅ፣ ፈጠራቸው እንዲያብብ የሚያስችል በመደመር መንፈስ ልምድና ሐሳብ የምንለዋወጥበት፤ ስኬትን የምናወድስበት፤ ከውድቀትም ትምህርት የምንወስድበት ሊሆን ይገባል፡፡ ከተሞቻችንን የሥልጣኔ ማዕከላት ለማድረግ ከነዋሪዎች፣ ከአልሚዎች እና ከመላው ኢትዮጵያውያን ቅን ልቦናና ተጨባጭ እንቅስቃሴ ይጠበቃል፡፡

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፣**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!"**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# ለ123ኛው የዐድዋ ድል መታሰቢያ በዓል የተላለፈ መልእክት

**የካቲት 23/2011**

በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በሙሉ ለመላው አፍሪካውያንና ለዓለም ነጻነት ወዳድ ሕዝቦች ሁሉ በየዓመቱ የካቲት 23 ቀን በሀገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ዝግጅቶች በታላቅ ድምቀት ለምናከብረው ለ123ኛው የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓል እንኳን በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን፡፡

ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን እናቶቻችን እና አባቶቻችን በወራሪው የጣልያን ጦር ላይ በዓድዋ የተቀዳጁት ታላቅ ወታደራዊ ድል፣ በኢትዮጵያ ምድር የኢትዮጵያ እንጂ የቅኝ ገዢ ሮማ ባንዲራ እንዳይውለበለብ ያደረገ ብቻ ሳይሆን፣ ፖለቲካዊ ነጻነታችንም ከዘመን ዘመን ታፍሮና ተከብሮ እንዲኖር ያስቻለ ደማቅ የታሪክ አሻራ ጭምር ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን በዓድዋ ላይ በደምና በአጥንት የከፈሉት መሥዕዋትነት የዛሬው እና የነገው ትውልድ በቅኝ ግዛት ቀንበር ትከሻው ጎብጦ፣ አንገቱን ደፍቶ እንዳይኖር አስችሎታል፡፡ የዓድዋው ድላችን ቀንተንም፣ ነቅተንም በዓለም ፊት ለመቆማችን አባቶቻችን ያቀዳጁን አክሊል ነው፡፡

ይህ ብቻም አይደለም፤ በወራሪውና በተስፋፊው የጣልያን ጦር ላይ ጀግኖቹ እናቶቻችንና አባቶቻችን የተቀዳጁት ድል ከራሳችን ነጻነት ባሻገር ለመላው አፍሪካ ብሎም በባርነት ቀንበር ይማቅቁ ለነበሩ መላ የዓለማችን ሕዝቦች ሁሉ ተስፋ የፈነጠቀ እና ወኔ ያሰነቀ ታሪካዊ ክሥተት ነው፡፡ ይህን በውል ለመረዳት

መቻል ትናንታችንን ዘክረን፣ ዛሬን መርምረን፣ ነጋችንን ለማቃናት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ የዓድዋው ድላችን ወደ ሌሎች ድርብ ድርብርብ ድሎች መሻገሪያችን፤ የድካም መርቻ ጉልበታችን፤ በዝለት ጊዜም መበርቻችን ነው፡፡ ለዚህም ከዓድዋ ድላችን ወዲህ በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ የተቀዳጀናቸው ስኬቶቻችን ሕያዋን ምስክሮች ናቸው፡፡

የዛሬው ትውልድም እንደ አባት እናቶቹ፣ እንደ አያት ቅድመ አያቶቹ ሁሉ የሚገጥሙትን ፈተናዎች እና የሚያደናቅፉትን ተግዳሮቶች በድል በመወጣት የአባቶቹና የእናቶቹ ልጅ መሆኑን በተግባር የሚያረጋግጥበት ታሪካዊ የዘመን አንጓ ላይ ቆሟል፡፡ ዓድዋ ከትግል እና ድል የሚሻገር የተጨቋኞች ረቂቅ ኃይል ነው፡፡ ዓድዋ መልከ ብዙ ትርጓሜና ሕይወታዊ አስተምህሮ በውስጡ አቅፎ የያዘ የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ፍልስፍና ነው፡፡ በፈተና ጊዜ፣ ህልውና አደጋ ላይ በወደቀ ጊዜ፣ የመደመር መንፈስና ንቅናቄ አንድን ሕዝብ ሊያደርስበት የሚችለውን የልዕልና ጫፍ ያየንበት ነው፡፡ ዓድዋ ኢትዮጵያውያን ከመሐልና ከዳር እንዲሁም ከምሥራቅ ጫፍ እስከ ምዕራብ ጫፍ፣ ከሰሜን ጫፍ እስከ እስከ ደቡብ ጫፍ አብረውና ተባብረው የማንነታቸውን ልክ ያሳዩበት የመሥዕዋዕትነታቸው ውጤት ነው፤ ዓድዋ እኛ ነን፡፡ አትንኩኝ ባይነት - ጸዳላችን፣ የሀገር ፍቅር ስሜት - ጥበባችን፣ ለአንድ ዓላማ መጽናት - ጥለታችን፣ ጀግንነትና ነጻነት ወዳድነት ደግሞ - የራስ ቁራችን ሆኖ የዋልንበት፤ እኛ ማለት ዓድዋ ነን፡፡ የሀገር መሪዎቻችን ሕዝብን የማስተባበር ችሎታ፣ የጦር ጄኔራሎቻችን የጦር አመራር ጥበብ፣ የዲፕሎማቶቻችን የዲፕሎማሲ ልቀት የታየበት የጥቁር ሕዝቦች የፀረ ኮሎኒያሊዝም ገድል ነው ዓድዋ፡፡

የዓድዋ ድል የሴት ኢትዮጵያውያን የዐርበኝነት ተጋድሎና የላቀ ሚና መገለጫ ነው፡፡ እኅቶቻችንና እናቶቻችን ከስንቅ ዝግጅት እስከ ጦር መሪነት፣ በግጥምና ዜማ ዐርበኞቹን ከማጀገን እስከ ቁስለኛ ተከባካቢነት፣ ከትጥቅ አቀባይነት እስከ ምርኮ ሰብሳቢነት፣ የተሰለፉበት ደማቅ ዐደባባይ ነው፤ ዓድዋ፡፡ የዓድዋን ድል የሚያከብር ሕዝብ የሴቶች ክብር የገባው መሆን አለበት፡፡

ዓድዋ መሪ እና ተመሪ፣ አስተዳዳሪ እና ተዳዳሪ ሲደማመጡ፣ ሲግባቡና ለአንዲት ሀገር ሲሠሩ የሚበግራቸው ነገር እንደማይኖር አስተምሮን ያለፈ

ታሪክ ነው፡፡ «የክብርህ መመኪያ፣ ደስታ እና ሕይወትህ የሆነችውን ውብ ሀገር ከወራሪ ትታደግ ዘንድ የምሥራቅ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን እና የደቡብ ሰው ፊትህን ወደ ዓድዋ አዙረህ ወረኢሉ ላይ ቆየኝ» ያለውን የመሪውን የዐፄ ምኒልክን ቀጠሮ አክብሮ፣ ለነፍስ ቀጠሮ በነፍስ የደረሰ ሳተና ሕዝብ፣ የድል አክሊል የተቀዳጀበት ታሪካዊ ቀን ነው፤ ዐድዋ፡፡

በዛሬው ዕለት የዘንድሮውን የድል በዓል ስናከብር እንደዚህ ዘመን ነዋሪና እንደ አዲስ ትውልድ፣ በድሉ ውስጥ የተካተተውን ሰምና ወርቅ፣ ምስጢርና ቅኔ በጥልቀት በመረዳት መሆን ይኖርበታል። በትክክል ታሪክን ለሚመረምር ትውልድ ዓድዋ ውስጥ፣ ህልውናን አጽንቶ የመኖር፤ ዐድዋ ውስጥ ዲፕሎማሲ፤ ዐድዋ ውስጥ ወታደራዊ ስትራቴጂ፤ ታላቅ ውስጣዊ የሕዝቦች ኅብረትና አንድነት፣ ጥበብ እና ተግባቦት፣ ፍቅር እና መስጠት፣ ክብር እና ጀግንነት መልቶና ሰፍቶ የነበረ መሆኑን እናያለን፡፡ አንድን ሀገራዊ ድል ለማስመዝገብ የሁሉንም አካላት ተሳትፎ የግድ እንደሚል እንማራለን፡፡

የሀገር መሪዎች፣ የጦር አበጋዞች፣ ቃፊሮች፣ ወታደሮች፣ ስንቅ አዘጋጆች፣ ሐኪሞች፣ አዝማሪዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ እንጨት ፈላጮች፣ ውኃ ቀጆዎች፣ የጥበበ እድ ባለሞያዎች፣ ታሪክ መዝጋቢዎች፣ ሌላው ቀርቶ ከብቶችና አጋሥሶች እንኳን ሳይቀሩ ለድሉ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ አድርገዋል፡፡ መደመር ማለት ይሄ ነው፡፡

በጦር መሣሪያ አቅም፣ በሀብት፣ በወታደራዊ አደረጃጀት እና በዘመናዊ የጦር ስልት በወቅቱ ታላቅ ደረጃ ደርሻለሁ ብሎ ያሰበውን የጣልያን ወራሪ ጦር ከዚያ በፊት ባልታየና በታሪክ ውስጥ ባልተስተዋለ ጀግንነት፣ ዐርበኞች እናቶቻችንና አባቶቻችን ድል የመቀዳጀታቸው እና የማሸነፋቸው ቁልፍ ምስጢር ውስጣዊ ልዩነታቸውን አቻችለው በኅብረትና በአንድነት ተደምረው፣ ለአንድ ሀገራዊ ግብ፣ በፍቅር መቆማቸው ነው፡፡ ብልህ ትውልድ ከዓድዋው የድል መሠዊያ ላይ ሊጭር የሚገባው ቁም ነገርም ይሄው ነው፡፡

የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን እንደ ትናንቶቹ ኢትዮጵያውያን በሕይወት መሥዋዕትነት ብቻ ሳይሆን እየኖርን በመሥራት፣ በደም የተቀበልናትን ሀገር

ነጻነቷን ጠብቀን ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ ጠንክረን መታገል ይገባናል፡፡ በልዩነት ተቆራቁሰን እርስ በርስ የምንጫረስና የምንጠፋፋ ሳይሆን የውዷቷ ሀገራችንን ችግሮች ለመቅረፍ እንድንችል በኅብረትና በአንድነት፣ በፍቅርና በይቅርታ ወደፊት መራመድ ይጠበቅብናል፡፡ መሪና ተመሪ በሁሉም ጉዳዮች ባይግባቡ እንኳን የሀገርን ነጻነት፣ አንድነት፣ እኩልነት፣ ፍትሕና ዴሞክራሲን በተመለከቱ ጉዳዮች ግን ተግባብተውና አንድ ሆነው ከራሳቸው አልፎ ለሌላው የሚተርፍ ድል ያስመዘግባሉ፤ ዓድዋ ያስተማረን ይኼንን ነው፡፡ ዓድዋ ያስተማረን ሌላም ነገር አለ፡፡ በደምና በአጥንት የተጠበቀው ነጻነት ከሥነ ልቡናና ከክብር ትሩፋትነት አልፎ ለኢኮኖሚ ጸጋነት እንዲተርፍ በደም ሳይሆን በላብ፤ በአጥንት ሳይሆን በጉልበት የምንከፍለው የመጪው ትውልድ ዕዳ እንዳለብን ዓድዋ ያስተምረናል፡፡ ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም ይላሉ ቀደምቶቻችን፡፡ የዓድዋ ድል ሀገራችንን የምናዘምንበትን ፍልስፍና የምናገኝበት፣ ሀገራችንን ወደ ከፍታ ለማድረስ የሚያስችለንን አቅም የምንሸምትበት፣ በየዘመናቱ እየመነዘርን እንደ ታዳሽ ኃይል የምንስፈነጠርበት ሕዝባዊ አቅም ነው፡፡ ዓድዋን ለኢትዮጵያውያን ምን ማለት እንደሆነ፣ እንኳን የድሉ ትሩፋት የደረሰን ኢትዮጵያውያን ቀርተን፣ ስንቅ ያጓጓዙት እንስሳት እንኳን ሳያውቁት አይቀሩም፡፡

ይህ የተጋድሎ ታሪካችን በዓለም ፊት ተገቢውን ቦታ እንዲይዝ፣ በነጻነት ፊት ብቻውን ተነጥሎ የቆመ አንድ የዛፍ ጭራሮ ሳይሆን በልምላሜ የተከበበ ጫካ እንዲሆን፣ በሳይንሳዊ ምርምርና በጥበባዊ ሥራችን ማረጋገጥና ማድመቅ ይኖርብናል፡፡ ነገረ ዓድዋን በጥበብ፣ በአካዳሚያዊ ፈለግ እና በማኅበረ ባህላዊ ዐውድ መመርመር፣ ማክበር እና ማጥናት ያስፈልገናል፡፡

ይህ የሀገራችን ዕምቅ ሀብት የሆነ ታሪካዊ ድል ተገቢውን ክብር እንዲያገኝ ግጥሞችን የገጠሙ፣ ድርሳናትን የሰነዱ፣ ተውኔቶችን የደረሱ፣ ዜማዎችን የቀመሩ፣ መጣጥፎችን የከተቡ፣ የመድረክ ዝግጅቶችን ያቀናበሩ፣ የእግር ጉዞዎችን ያዘጋጁ፣ በሀገር ቤትና በውጭ የሚገኙ፣ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ብዙ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ሁሉ ያለኝን ላቅ ያለ ክብርና ምስጋና በዚሁ አጋጣሚ አቀርባለሁ፡፡

ዓድዋ በውስን ፊልሞች፣ በጥቂት ድርሳናት፣ በጣት በሚቆጠሩ ዜማዎች፣ እፍኝ በማይሞሉ የታሪክ ምርምር ጽሑፎች፣ በእግር ጉዞ እና በመድረክ ትወና ብቻ ተዘርዝሮ እና ተዘክሮ የሚታለፍ አይደለም፤ በፍጹም፡፡ ያገባናል የምንል አካላት ሁሉ ከሥነ ጥበብ፣ ከእምነት፣ ከፍልስፍና፣ ከታሪክ፣ ከሴቶች ተሳትፎ፣ ከመሪነት ጥበብ፣ ከሀገራዊ አንድነት፣ ከውትድርና ሳይንስ፤ በኢኮኖሚ ራስን ከመቻል፤ ብሎም ከጥቁር ሕዝቦች የነጻነት እና የትግል ታሪክ ፋና ወጊነት ጋር በማስተሳሰር ዓለም አቀፋዊ ሥራ መሥራት ገና ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህም ምሁራንና የጥበብ ሰዎች ዓለም አቀፋዊ ደረጃ ያለው ሥራ እንዲሠሩ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡ መንግሥትም የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ያለውን ዝግጁነት ለማሳወቅ እወዳለሁ፡፡

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፣**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!"**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ፡፡**

# ከመጋቢት

# እስከ መጋቢት

፳፻፲፩

# ከመጋቢት
# እስከ መጋቢት

የኢፌዴሪ ጠ/ሚር
ክቡር ዐቢይ አሕመድ
ከመጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 24 ቀን 2011 ዓ.ም. ያደረጓቸው ንግግሮችና ያስተላለፏቸው መልእክቶች



ISBN 978-999-44-74-88-2

**ዋጋ 100 ብር**